## ዓምደ ሃይማኖት

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

ከሲራክ ገብረክርስቶስ

መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጣቸው ሀብታት (ስጦታዎች) መካከል እምነት አንደኛው ዘርፍ መኾኑ ባለፈው ጽሑፍ ተመልክቷል። ከመንፈስ ቅዱስ በተሰጣቸው የማመን ጸጋ ቅዱሳን እጅግ አስደናቂ ነገሮች ለማድረግ እንደሚችሉ በአርአያነት ሦስቱን ያህል ማስታወሳችን ይታወሳል ካለፈው ክታብ በመቀጠል የተቀሩትንም አንድ በአንድ ለአብነት እንጠቅሳቸዋለን። በቅዱስ መጽሐፍ መሪነት ይልቁንም በቅዱስ ወንጌል ጌታ በምሳሌ የተናገረውን ብናጤን እምነት እንደ ስንዴ ቅንጣት በገበሬ በተመሰሉት መምህራን ቤተክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ በልባቸው እጅ (በእደ ልቡናቸው) በማኖር በለም እርሻ በተመሰሉት ምዕመናን ልብ የሚዘሩት የጽድቅ ቅንጣት ነው። (ማቴ ፲፫:፳፫-፴፬)

አማኞች (ምዕመናን) በስንዴ ቅንጣት የተመሰለችውን እምነት (ሃይማኖት) በቅንነት ተቀበለው በሚሠሩት ትሩፋት በጸጋ ላይ ጸጋ እየተጨመረላቸው ከመጣኒነት ወደ ማዕከላዊነት ከዚያም ወደ ፍጹም አማኒነት ይደርሳሉ። እምነታቸው ከጥርጥር የነጻች ከግብዝነት የተለየች እንደሆነ መቶ በመቶ ፍጹም የሆነ የእምነት ጸጋን በመጎናጸፍ የፈቀዱትን ለማድረግ የማይሳናቸው ይኾናሉ። የእምነታቸው ስንዴነት ሳይለወጥ በአጠቃቀም ላይ በልዩ ልዩ ዘርፍ የእምነታቸው ውጤት ለነፍስ ሕይወት ምግብ በመኾን ያገለግላል። ባለሙያ ሴት የያዘችው ስንዴ አንድ ዓይነት ሆኖ ሳለ በተለያየ መልኩ እንጀራ፣ ዳቦ፣ ንፍሮ፣ ቆሎ፣ ቂጣ፣ አምባሻ፣ አጥሚትና ሌላም እንደ አነባበሮ፣ ገንፎ፣ ቅንጬና የመሳሰሉት የምግብ ዓይነቶችን መሥራት እንደምትገለገልበት፤ የእምነት ሀብት የተሰጣቸው ቅዱሳንም የእምነቱ መሠረት ወይም ይዘት ሳይለወጥ በተለያየ ተዋልጦ ገድል ሲጠቀሙበት ይገኛሉ። እንግዲህ ከላይ እንደተጠቀሰው የተሰጣቸውን የእምነት ሀብት ቅዱሳን እንዴት እንደተጠቀሙበት የማመን ጸጋ በሕይወታቸው እንዴት እንደሠራ እንደሚከተለው እናቀርባለን። አስተዋይ አእምሮን፣ ቅን ሕሊናን የምሥጢር ባለቤት ናዛዚ ከሣቲ መንፈስ ቅዱስ ይመጽውተን። አሜን።

## ፩. የሰማዕቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ እምነት፦

ከክርስቶስ ልደት በኋላ በሁለተኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ አካባቢ የነበረው የልዳው ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስ በ፸ ነገሥታት ፊት በፋርስ ባቢሎን ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖቱ ዓላውያኑን ሳይፈራ እስከ ደም ጠብታ ድረስ የመሰከረ ሰማዕት ነው። ብቻውን ከጣዖት አምላኪዎቹ ጋር የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነትና ቤዛነት ሲመሰክር ለ፯ ዓመታት ልዩ ልዩ ፀዋትወ መከራዎች ደርሰውበታል።

እሱ ግን ስለ ተቀደሰችው ሃይማኖት ተጋድሎ ሲያደርግ በሙሉ እምነትና ቆራጥነት ነበር። በራእየ ዮሐንስ ቆራጥ እምነት ያላቸው ልበ ሙሉ ክርስቲያኖች ምን ዓይነት ጸጋ እንደሚሰጣቸው ተገልጧል። ለምሳሌ " ወኩን መሃይምነ እስከ ለሞት፤ ወእሁበከ አክሊለ ሕይወት። " ይላል። (ራእይ ፪:፲) " እስከ ሞት ድረስም የታመንክ ሁን የሕይወት አክሊልንም እሰጥሃለሁ። " ማለት ነው። ቅዱስ ጊዮርጊስ በተሰጠው የእምነት ጸጋ ዓላውያን ነገሥታትን አሳፍሯል። እሱ ግን ነቢዩ ዳዊት እንደተናገረው "በነገሥታት ፊት ምስክርህን እናገራለሁ አላፍርምም።" (መዝ ፻፲፰:፵፮) ለማለት በቅቷል።

ቅዱስ ጊዮርጊስ በእምነቱ በልዳ ከሚኖሩ ቅዱሳን ይልቅ እንደ አጥቢያ ኮከብ ደምቆ በመገኘቱ የተሰጠው የእምነት ሀብት ከዕድሜው ወጣትነት አንጻር ሲታይ እጅግ የሚያስደንቅ ነበር። ከዚህም የተነሣ በቤተክርስቲያን ሊቃውንት "ሰአል ለነ ጊዮርጊስ ሰማዕተ ኢየሱስ ክርስቶስ ጊዮርጊስ ኮከበ ልዳ።" በማለት ሲወደስ ይኖራል። ትርጉሙም "የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ጊዮርጊስ ለምንልን። የልዳው ኮከብ ጊዮርጊስ ለምንልን።" ማለት ነው። (ሰዓታት ዘጊዮርጊስ) ቅዱስ ጊዮርጊስ በተሰጠው የእምነት ጸጋ የወንጌልን ብርሃን እንደ ኮከብ አንጸባርቆ በመገኘቱ በትንቢተ ዳንኤል ፲፪:፫ ከተነገረላቸው መንፈሳውያን ከዋክብት አንዱ እንደኾነ አስመስክሯል። ትንቢቱም እነሆ "ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ጸዳል፣ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።" የሚል እውነት ነው። ቅዱስ ጊዮርጊስ ኮከብ ዘልዳ (የልዳው ኮከብ) እየተባለ ለዘላለም በመንግሥተ ሰማይ ደምቆ አሸብርቆ የሚኖር ነው። ልዳ የቅዱስ ጊዮርጊስ እናት የትውልድ ቦታ (ሀገር) ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በዚሁ ሥፍራ ኤንያ የተባለውን በሽተኛ ፈውሶበታል በልዳ ብዙ ቅዱሳን ክርስቲያኖች ይኖሩበት ነበር (የሐዋ ሥራ ፱:፴፪-፴፭።) ቅዱስ ጊዮርጊስም በዚሁ ሥፍራ ስለተወለደ የልዳው ጊዮርጊስ ይባላል። "የሚገልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም።" (ማር ፲፮:፲፰።) ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ወደ ዓለም ሲልክ በተናገረው መሠረት ቅዱስ ጊዮርጊስም ከሐዋርያት ጀምሮ ተያይዞ ስለመጣው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖቱ ሲመሰክር በተሰጠው የእምነት ሀብት ይኸን የወንጌል ቃል በተግባር አሳይቷል። በገድለ ቅዱስ ጊዮርጊስ ምዕ ፬:፳፰-፴፩። ያለውን ብናጤን በቅዱስ ጊዮርጊስ ሰውነት የእምነት ጸጋ እንዴት እንደሠራ እንደሚከተለው ማየት እንችላለን በፋርስ ባቢሎን በዱድያኖስና በ፸ው ነገሥታት ፊት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቀርቦ እንዲህ አለ "ፈጣሪዬ ፈጣሪዬ እየኝ ለምን ተውከኝ።" ቀጥሎም ዱድያኖስን"የፍርድ ባለ ሥልጣን ሆይ አንተ ሰነፍ ነህ። አጽሎንም ደንጊያ



www.ethiopisnorthodox.org

ነው እነሆ በፈጣሪዬ በክርስቶስ ኃይል ተነስቼ ልትፈርድብኝ መጣሁ " ብሎ አሰምቶ ተናገረ። ከሀድያንም በአዩት ጊዜ ጊዮርጊስ ሆይ፤ እንዴት ከመከራው ሁሉ ምንም አላገኘኽም። ያዳነህስ ማነው አሉት። ቅዱስ ጊዮርጊስም ከሀዲዎችና ወንጀለኞች ሆይ! እናንተ በደነቆረችው ጆሮአችሁ የፈወሰኝን የፈጣሪዬን ስም ልትሰሙ የሚገባችሁ አይደለም። ያን ጊዜም ርኩሳን ነገሥታት ጽኑ ቁጣ ተቆጥተው በአራት ረጃጅም ካስማዎች እጁን እግሩን ስበው እንዲያስሩትና በጀርባው ጅራፍ፤ እንዲገርፉት አዘዙ። ጭፍሮችም ሥጋው እስኪበጣጠስና ጥቂት በጥቂት በምድር እስኪወድቅ ድረስ ደሙም እንደ ውሃ እስኪፈስ ድረስ ግርፋቱን ፈጸሙበት። ዳግመኛም ሰዎች ሊያጠፉት የማይቻላቸው ግንፋል አምጥተው በላዩ እንዲደፈሉበት መጣጣ ዲንም እንዲጨምሩበት አዘዙ፤ ሥጋው ሁሉ ተቃጠለ፤ እጅግ በጣም ደከመ ከዚህም በኋላ ንጉሡ ስምንት ወታደሮች እሥር ቤት እንዲወስዱትና አምስት ሽማግሌዎች እስከ ማግስቱ እንዲጠብቁት አዘዘ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መከራውን ፈጽሞ መንቀሳቀስ የማይቻለው መሆኑን ባየ ጊዜ ከሉዓላዊ ዙፋኑ ላይ ወርዶ ወዳጄ ጊዮርጊስ ሆይ! ከድካምህም ሁሉ በርታ፤ እኔም ካንተ ጋራ ነኝ ሲል አነጋገረው። ጻድቁም ተነሣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እጁን ዘርግቶ ሰውነቱን ሁሉ ዳሰሰው። ከሕማሙም ፈወሰው ከዚህ በኋላ ሰላምን ሰጥቶት በፍጹም ምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ። ቅዱስ ጊዮርጊስም ፀሐይ እስክትወጣ ድረስ መላ ሌሊቱን በእሥር ቤቱ ውስጥ ያመሰግን ነበር። ይጥብቁት የነበሩ ወታደሮች ግን ከመፈወሱ የተነሣ አደነቁ። ለንጉሡም ነገሩት።

ዱድያኖስም ይህን በሰማ ጊዜ በዓለሙ ሁሉ የክርስቲያንን ሥራይ መፍታት የሚችለው ዓዋቂ ባለ መድኃኒት በእናንተ ዘንድ እንዳለ ወደ እኔ ይምጣ እኔም መቶ ምዝምዝ ወርቅ ሁለት መቶ ምዝምዝ ብር ከዚህም ሌላ የተመኘውን ሁሉ እሰጠዋለሁ በመንግሥቴም ሁለተኛው ባለ መዓረግ ይሆናል የምትል ደብዳቤ ጽፎ ሰደደ። ዱድያኖስም ይህንን ደብዳቤ በየሀገሩ በሰደደ ጊዜ አትናስዮስ የሚባል ታላቅ የሥራይ መምህር መጣለት፤ ንጉሡንም ጌታዬ ሺህ ዓመት ያንግስህ፤ ይህን ጊዮርጊስ የተባለውን ሰው አዘዘው፤ በፊቴ የሚያደርገውን ያድርግ፤ የእርሱን መድኃኒት እኔ እፈታዋለሁ አለው። ንጉሡም በሰማ ጊዜ ደስ ብሎት ሥራዩን እስክትፈታ ድረስ ምን ማድረግ ትችላለህ ? አለው አስማተኛውም ንጉሥን ላም እንዲያመጡ እዘዝ አለው። አመጡለት በጆሮዋም ሹክ አለባት ተሰነጠቀች ሁለት ክፍልም ሆነች ። ዱድያኖስም ስቆ በእውነት አንተ የክርስቲያኖችን ሥራይ ለመፍታት ትችላለህ አለው። አስማተኛው አትናስዮስም የሚበልጥ እስከታይ ድረስ ጥቂት ታገሥ አለው፤ ሚዛን እንዲያመጡ እዘዝ አለው። ሚዛንም አምጥተው ግማሹን በአንድ ወገን ግማሹን በአንድ ወገን አድርገው ሁለቱን ክፍል መዘኑት፤ እርስ በርሳቸው ትክክል ሆኑ ንጉሡና ከርሱ ጋራ የነበሩት አደነቁ።

ንጉሡም ቅዱስ ጊዮርጊስን ወደ ፍርድ አደባባይ እንዲያመጡት አዘዘ፤ ቅዱስ ጊዮርጊስም ወደ ፍርድ አደባባይ በመጣ ጊዜ እኛ ይህንን ሰው ያንተን ሥራይ እንዲፈታ አስመጥተነዋልና አንተ ለራስህ ዕወቅ፤ ወይም አንተ የርሱን ሥራይ ትፈታው ይሆናል አለው። ኃያሉ ቅዱስ ጊዮርጊስም ንጉሡን አንተ ከሐዲ በክርስቶስ የተቀጠሩ ክርስቲያን ሥራይ ሊያደርጉ አይገባቸውም አለው። ከዚህም በኋላ ኃያሉ ቅዱስ ጊዮርጊስ አስማተኛውን፤ ልጄ ሆይ በል የምታደርገውን ፈጥነህ አድርግ የእግዚአብሔር ጸጋ በፊትህ መልቶብህ አያለሁና አለው።

አትናስዮስም ጽዋ አንስቶ በውስጡ ልዩ ልዩ ቅመማት ሞልቶ ሥራዩን ቀምሞ የርኩሳን አጋንንትን ስም ከደገመበት በኋላ እንዲጠጣው ለቅዱስ ጊዮርጊስ ሰጠው ቅዱስ ጊዮርጊስም ከአስማተኛው እጅ ጽዋውን ተቀብሎ በቅዱስ መስቀል ምልክት አማትቦ ጠጣው፤ ፈጽሞ ክፉ ነገር አላገኘውም።

አስማተኛው አትናስዮስም ቅዱስ ጊዮርጊስን እኔ አንደገና ሌላ መርዝ እቀምማለሁ፤ እርሱን ጠጥተህ ክፉ ነገር ካላገኘህ እኔ በዕፀ መስቀል ላይ በተሰቀለው በአምላክህ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ አለው፤ እንደገና ሌላ ጽዋ አንሥቶ መርዝ መልቶ ከቀደሙት የከፋ የሚበልጡ አጋንንት ስም እየጠራ ከደገመበት በኋላ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ሰጠው። ቅዱስ ጊዮርጊስም ፀመስቀል አማትቦ ጠጣው። ፈጽሞ ሕማም አላገኘውም፤ አትናስዮስም ከቅዱስ ጊዮርጊስ እግር በታች ወደቀና ሰገደለት። ነፍሴን ታድን ዘንድ የመንግሥተ ሰማያትም በር እንዲከፈትልኝ አንተ በምታመልከው በክርስቶስ የምትሰጥ ማዕተበ ጥምቀትን ትሰጠኝ ዘንድ ኃጥአንን ሁሉ ሊያድን ወደ ዓለም በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ አምልሐለሁ አለው። ቅዱስ ጊዮርጊስም እምነቱን ባየ ጊዜ ምድርን በእግሩ ረገጠ፤ ያን ጊዜም መዓዛው እጅግ የሚያስደንቅ የውኃ ምንጭ ፈለቀ። ቅዱስ ጊዮርጊስም በለሆሳስ ጸለየ። ያን ጊዜም ሐዋርያው ቶማስ መጣና አትናስዮስን አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠመቀው።

አትናስዮስ የኃጢአቱን ሥርየት አገኘ። ከዚህ በኋላ ሐዋርያው በንቡዕ ሰላምታ ሰጥቷቸው ከእነርሱ ተሠወረ ። የውኃው ምንጭም ወደ ነበረበት ተመለሰ። ንጉሡም ከርሱ ጋራ የነበሩ ሁሉ ይህንን ባዩ ጊዜ እጅግ ተደነቁ ። አትናስዮስም በንጉሡ ፊት እኔ ክርስቲያናዊ ነኝ፤ ከአገልጋዮቹ ቆጥሮኛልና፤ ድንቅ ሥራውንም ሠርቶልኛል። ቅዱስ ጊዮርጊስ አገልጋዩ የሆነለት እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። በአሥራ አንድ ሰዓት ወደ ወይኑ ቦታ መጥቻለሁ። ንጹሕ ምስክር በሚሆን በኃያሉ በቅዱስ ጊዮርጊስ አማላጅነትም ቸርነቱ እንድትደረግልኝ ተስፋ አደርጋለሁ አለ። ከሐድያን ነገሥታትም ተቆጥተው አትናስዮስን ከሀገር ውጭ አውጥተው በሰይፍ እንዲቆርጡት አዘዙ። እንዲሁ ጥር ኻያ ሦስት ቀን ቅዳሜ በስድስት ሰዓት ሰማዕትነቱን ፈጸመ። መላእክትም ነፍሱን ተቀብለው በፍጹም ክብር ወደ ተድላ ገነት አገቧት። ንጽሕት በረከቱ ከሁላችን ጋር ትሁን ለዘለዓለም አሜን።

እንግዲህ በማመን ጸጋ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ የተደረገለትን ድንቅ ሥራ ተመልክተናል። በእምነት ጸጋ ውሀ ከምድር ማፍለቅ ፣ የመርዝን ኃይል አልሜ ማድረግ ፣ ሞትን በጥብዓት መጋፈጥ፣ በአፀደ ነፍስ ካሉ ቅዱሳን ጋር መነጋገር መቻሉን ከሰማዕቱ ገድል ተረድተናል። ለቀደሙት አርድእት ጌታችን ስለ እምነታቸው የሰጣቸው ጸጋ ቀጣይ ሆኖ ሲሠራ እንደነበር በቅዱስ ጊዮርጊስ ተጋድሎ ሲረጋገጥ ማየት ተችሏል። ቅዱስ ጊዮርጊስ በተሰጠው የማመን ጸጋ እንደ ፸ አርድእት እባቡን (ደራጎንን)፣ ጊንጡን ለመርገጥ



www.ethiopisnorthodox.org

በጠላት ሁሉ ላይ ሥልጣን ማግኘት፣ የሚጎዳውም አንዳች ነገር ምንም እንዳይኖር የእምነት ባለጸጋ መሆንን ገንዘብ ለማድረግ በቅቷል። በተሰጠውም ጸጋ በክርስቶስ ፍቅር ከአሸናፊዎች በልጦ መገኘቱን እናስተውል። (ሉቃ ፲ : ፲፱። ሮሜ ፰ : ፴፯።)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ። ስለ ክርስቶስ በድካም በመንገላታትም፣ በችግርም፣ በስደትም፣ በጭንቀትም ደስ ይለኛል ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና። " ፊልጵ. ፬ : ፲፫። ፪ኛ ቆሮ. ፲፪ :፲።) እንዳለው ቅዱስ ጊዮርጊስም በተሰጠው የእምነት ጸጋ ለ፯ ዓመታት ያደረሱበትን ___ ሥቃያት በመታገስ በመከራው ሁሉ ኃያል ሆኖ ስለተገኘ ኃያሉ ጊዮርጊስ እየተባለ በቤተክርስቲያን ሲደነቅ ይኖራል። በረከቱ ጸሎቱ ይደርብን አሜን። የቅዱስ ጊዮርጊስ አምላክ በተዋሕዶ ሃይማኖታችን ያጽናን።

፭ኛ) <u>የሶርያው ቅዱስ ኤፍሬም፣</u>

ታላቅ የእምነት ጸጋ የተሰጠው ቅዱስ አባት ነበር። በሦስተኛው ምዕተ ዓመት በዘመነ ክርስትና የነበረ የ፯ቱን ዕለታት የእመቤታችንን የቅድስት ድንግል ማርያምን ምስጋና የሚናገር ውዳሴ ማርያም የተባለውን በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የደረሰ ሊቅ ነው። ቅዱስ ኤፍሬም መንፈሳዊ ትምህርቱን የቀጸለው ከሠለስቱ ምዕት አንዱ ከነበረው ከያዕቆብ ዘንጽቢን ነው። የትምህርት ቤት ጓደኛው ስምዖን ቅዱስ ኤፍሬም ሊጠይቀው ሲመጣ " ሰላም ለኪ እ እግዝእትየ ቅድስት ድንግል ። . . . እመቤቴ ቅድስት ድንግል ሆይ ሰላም ላንቺ ይሁን። " እያለ ሲያስተምር ሰማው። ወዲያው እያይዞ ስምዖን ይጠይቀዋል። ወንድሜ ' <u>እ እግዝእትየን'</u> ከማን አገኘኸው መምህራችን አልነገረን አለው። ኤፍሬምም መልሶ ነግሮናል አለው። ስምዖንም ግን መቼ ነገረን አልነገረንም እኮ አለው። በዚህን ጊዜ ቅዱስ ኤፍሬም በተሰጠው የእምነት ጸጋ ተሞልቶ ይመስክር አለው። ስምዖንም ኧረ ! አልነገረንም ይመስክር አለው። ይኸን ከተባባሉ በኋላ ተያይዘው ከያዕቆብ ዘንጽቢን መቃብር ይሄዳሉ። ወዲያው በተአምራት ያዕቆብ ዘንጽቢን ተነሥቶ አሥሩ ጣቶቹ እንደ ፋና እያበሩ "በሕይወትየ እብለኪ ሰላም ለኪ እ ቅድስት ድንግል ከመ ስምዖን ዘዓምድ ወድኅረ ሞትየሰ ኩሎሙ አዕፅምትየ ይብሉኪ ወይዌድሱኪ ሰላም ለኪ እ እግዝእትየ ቅድስት ድንግል ከመ ኤፍሬም ሶርያዊ" ብሎ መስክሮለታል። (ትርጓሜ ውዳሴ ማርያም) ትርጉሙም "በሕይወተ ሥጋ ሳለሁ እንደ ስምዖን ዘዓምድ ቅድስት ድንግል ሆይ ሰላም ላንቺ ይሁን እል ነበር ከሞትኩ በኋላ ግን አጥንቶቼ ሁሉ እንደ ሶርያዊው ኤፍሬም እመቤቴ ቅድስት ድንግል ሆይ ሰላምታ ላንቺ ይሁን እያሉ ያመሰግኑሻል ያወድሱሻል።" ማለት ነው።

ከዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን ነገር አለ። ይኸውም ቅዱስ ኤፍሬም በተሰጠው የማመን ሀብት መምህሩን ከመቃብር ቀስቅሶ ለማናገርና ስለ እምነቱም ትክክለኛነት እንዲመሰክር ማድረጉ ነው። በልበ ሐዋርያት በልበ ሊቃውንት ተሠውሮ የነበረውን ምሥጢር በእምነት ጸጋ ፈልፍሎ ማወቅ መቻልና በተአምራት ማስመስከር የሚቻለው እንደ ቅዱስ ኤፍሬም ያለ የበቃ ሰው በእውነት ንዑድ ክቡር ሊባል ይገባዋል። የቅዱሱ ሊቅ የኤፍሬም በረከቱ ረድኤቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን።

፮. <u>የጻድቁ አባታችን የተክለሃይማኖት እምነት</u>

ክቡር አባታችን ተክለሃይማኖት ሁሉን ትተው እንደ ሐዋርያት ወንጌልን ለማስተማር በምናኔ ከወጡ በኋላ በኢትዮጵያ ባሉ አውራጃዎች በመዘዋወር ሐዋርያዊ ግዳጃቸውን በመፈጸም ላይ ሳሉ ግብራቸው እንደ እንስሳ የሆኑ እግዚአብሔርን የማያውቁ ለጣዖት የሚሰግዱ ሰዎች ገጠሟቸው።

እነዚህንም ሰዎች ከብዙ ዘመን ጀምሮ በዛፍ ላይ ሆኖ ራሱን በመሰወር ሰይጣን አምላካችሁ ነኝ እያለ ሲያሰግዳቸው ይኖር ነበር። ቅዱስ ተክለሃይማኖት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ነገር በማስተማር ሰዎቹን በመገሰጽ ሲመክሩ የሀገሩ ሰዎች በጠላትነት ተነሥተው እንደ አንበሳ ሊውጡአቸው ወድደው ነበር። አባታችን ግን ልበ ሰፊ ነገር ኃላፊ በመኾን እያለዛዘቡ ማስተማራቸውን ቀጠሉ። ጣዖት አምላኪዎቹን በፈሊጥ ምን ታመልካላችሁ ብለው ተክለሃይማኖት ጠየቋቸው ሰዎቹም የምናመልከው የምንሰግድለት ታላቅ ዛፍ አለ አሉ።

አባታችን መልሰው በሰገዳችሁለት ጊዜ ምን ይመልስላችኋል አሏቸው። ሰዎቹም እኔ ፈጠርኋችሁ ፈጣሪያችሁ እኔ ነኝ ብሎ ከዛፉ ላይ ቃል ይናገረናል። ስለዚህ ነገር እኛም እንሰግድለታለን። የወደደውን እንሠዋለታለን አሉ። አባታችን ተክለሃይማኖትም እሰግድለት ዘንድ እኔንም ከናንተ ጋራ ውሰዱኝ አሏቸው ሰዎቹም እሺ ነገ እንወስድሃለን አሉ። ሲነጋ አባታችንን ለጣዖት የሚሰግዱ ስለመሰላቸው ከእነርሱ ጋራ ወሰዷቸው። ከዛፉ ዘንድ በደረሱ ጊዜ በላይዋ ያደረ ሰይጣን ጮኸ። እላንተ የዚች ሀገር ሰዎች ከእኔ ሥራ ልዩ የሚሆን ምን አመጣችሁብኝ በመካከላችሁ የሚሄድ ተክለሃይማኖት የተባለው ነው ለምን መጣብኝ እያለ ጮኸ። በዚህን ጊዜ ሰዎቹ አባታችን ፈጣሪያችን ጠልቶሃልና ከሩቅ አይቶ አንተን ወደ እኔ አታምጡብኝ አለ። ዘወትር እንደዚሁ ኃጢአት ያለበትን እያወቀ ወደሱ ሊመጣ አይወድም አንተም ዛሬ ቆይ ሂደን እስክንለምነው ድረስ፤ ከለመነው በኋላ ትመጣለህ አሉ።

ቅዱስ ተክለሃይማኖትም መልሰው የሚጠላው እኔን አይደለም ጌትነቱ በኔ ይገለጽ ዘንድ ልሰግድለት በመጣሁ ጊዜ ደስ ባለው ነበር እንጂ. እኔ ከሩቅ አገር መጥቻለሁና ነገር ግን ከናንተ የሚጠላው ሰው እንዳለ ፈልጉ አላቸው። ከዚህ በኋላ ወደዛፉ ቀረቡ። ይህ ከመካከላችሁ ያለ ከኔ ሥራ ልዩ የሚሆን ሰውን አታምጡብኝ አላልኳችሁምን እያለ ዳግመኛ ጮኸ። ያገሩም ሰዎች በሀገራችን በዚህ ስም የሚጠራ የለም። ተክለሃይማኖት እንተነህን ስምህ እንግዳ ነው ከሆን ጀምሮ እንደዚህ ያለ ስም አልሰማንም ፈጣሪያችን እንዳይቆጣን አትምጣ አሉ። ይህን ብለው ተክለሃይማኖትን ሦስት ምዕራፍ ያህል ጎዳና ሲቀር ትተዋቸው ሊሰግዱ ወደ ዛፉ ሄዱ።

አባታችን ተክልሃይማኖትም የተናቀ ሥራቸውን አይተው ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ መልሰው ወደ አምላክ (ፈጣሪ) አመለከቱ እንዲህ እያሉ ጸለዩ። "አቤቱ በፍጥረትህ ላይ የሚሠራውን የሰይጣንን ተንኮል ተመልከት ። ሥነ ፍጥረትክን ያጠፋ ዘንድ ይህን ተከራካሪያችንን ለምን አሰለጠንከው! ይህን ትዕቢተኛ ሰይጣን በእኔ እጅ ታዋርድ ዘንድ አቤቱ እለምንሃለሁ። በሥራህ ሁሉ ይረዳሃል



www.ethiopisnorthodox.org

ብለህ እንደነገርኸኝ ዛሬም ይረዳኝ ዘንድ ፈቃድህን የሚፈጽም ሚካኤልን ላክልኝ። ይህንም ሰይጣን ያስታቸው በነበረ ሕዝብ ሁሉ ፊት ጎፍረቱ እስኪገለጽ ድረስ ከዚች ከዛፍ እንዳይሄድ አድርገው። ይህችም ዛፍ ከሥሯ ተነቅላ ወደ እኔ ትምጣ። "የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል ሃይማኖት ቢኖራችሁ ይችን ዛፍ ከሥርሽ ተነቅለሽ ሂደሽ ከባሕር ተተከይ ትሏታላችሁ እንዳላችሁ ይደረግላችኋል። " (ሉቃ ፲፯:፭-፮) ብለህ እንደተናገርክ፤ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖቴም ምግባሬም አንተነህና ዛሬ በተሰበሰቡ ሰዎች ፊት የሥራዬን ጽናት የሃይማኖቴን ደግነት ግለጽ" በማለት ከጸለዩ በኋላ ፊታቸውን ወደ ዛፉ መለስ አድርገው ሰይጣን ባንቺ አድሮ እየተናገረ ሕዝቡን የሚያስትብሽ አንቺ ዛፍ እኔ በምሰግድለት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሻለሁ። ሰዎቹ ሁሉ የፈጣሪዬን ኃይል ያዩ ዘንድ ከሥርሽ ተነቅለሽ ወደ እኔ ነይ ብለው በቃላቅ ድምፅ አሰምተው ተናገሩ። የእምነት ጸጋ ያላቸው ስለኾኑ በተሰጣቸው የማመን ሀብት እንዳሉት ተደረገላቸው። ሰይጣኑ እየጮኸ ቅዱስ ሚካኤል ይዞት እየገረፈው ዛፊቱ ተነቅላ ተከትላ ከተክለሃይማኖት ኋላ ኋላ እየተወናጨፈች ትሄድ ጀመር በሥሯም መወናጨፍ እየተመቱ የሞቱም ሰዎች አሉ። ቁጥራቸውም ኻያ አራት ነው ዛፊቱ እየፈጠነች ተክለሃይማኖትን ስትከተል ሰይጣኑም ሚካኤልን ልቀቀኝ እያለ ሲጮኽ መልአኩም ተክለሃይማኖት ሳይቆም አለቅህም ሲል ይህ ሁሉ ድንቅ በጻድቁ ተክለሃይማኖት እምነት ተደረገ።

በመጨረሻም ሰይጣኑ እጅግ ተጨንቅሁ በምታመልከው በፈጣሪህ እለምንሃለሁ ቁምልኝ እያለ ጮኸ። አባታችንም ቆሙለት የምትከተላቸውንም ዛፍ ባለችበት ቁሚ አሏት ቀጥ ብላ ቆመች።አባታችን ተክለሃይማኖት ሰይጣኑን እኔ ፈጠርኳችሁ እያልክ ሰውን ለምን ታስታለህ አሉት ሰይጣንም እኔ ሐሰተኛ እንደሆንኩ ለሐሰትም ነቃ እኔ እንደሆንኩ አታውቅምን? በኔ ለሚያምነውም ሁሉ እንደለመድሁ ሐሰት እናገረዋለሁ አሁንም ተወኝ ልሂድ ወደዚች ሀገር ዳግመኛ እንዳልመለስ እለምንሃለሁ። አንተም ካለህበት ቦታ ፈጽሜ አልደርስም አለ።

ቅዱስ ተክለሃይማኖትም አንተ ቀድሞ እንዳሳትካቸው ዛሬም ጉስቁልናህን ያዩ ዘንድ የዚችን ሀገር ሰዎች እንዲህ በላቸው አሉት ቀድሞ እኔ በሐሰት አስቻችኋለሁና እንግዲህስ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስገዱ በላቸው አሉት። ሰይጣንም እሊህን ሦስቱን ስም መጥራት አይቻለኝም አለ። ክቡር ተክለሃይማኖትም የሦስቱን ስም መጥራት የማይቻልህ ከሆነ እናንተንም እኔንም ለፈጠረ ለሰማይና ለምድር ፈጣሪ ስገዱ ተገዙ በላቸው አሉት በዚህን ጊዜ ያ ሰይጣን እናንት የዚች ሀገር ሰዎች ቀድሞ እኔን በመሰላችሁኝ ጊዜ በሐሰት ሳስታችሁ ኖርኩ እንግዲህስ ሀገራችሁን ትቼላችሁ ሄድኩ ምድረ በዳ ይሁን ሰማይና ምድርን እኔንና እናንተን ለፈጠረ ስገዱ ተገዙ የኔን ሥራ የሚሠራ ግን ከኔ ጋራ በገሃነም ይኖራል። ይህን ብሎ ከዚህ ከሰው ወዴት እሸሻለሁ እያለ ሰይጣን አለቀሰ። ስንኳን ድል ላደርገው ልከራከረው የማይቻለኝ አርበኛ ተነስቶብኛልና።

ከዚህ በላይ እንደተገለጠው ቅዱስ ተክለሃይማኖት በተሰጣቸው የማመን ጸጋ (ሀብተ አሚን) እንደ ጣዖት ሆና ለሰይጣን ማደሪያ የኾነችውን ዛፍ ከሥሯ ሲነቅሉ በሰው ልብ ጣዖታዊ አምልኮን የተከለውንና ሲያስፋፋ የነበረውን ሰይጣን ከሥሩ ነቅለው ሊያባርሩት ችለዋል።

መንፈስ ቅዱስ ጥርጥርን ላስወገዱ አማኞች ከሚሰጣቸው ስጦታዎች እምነት አንዱ መኾኑንና ጥቅሙን በዚህ ተምሳሌት ሳንረዳ የቀረን አይመስለንም የተሰወረም ነገር ካለ የጻድቁ አምላክ በጸሎታቸው ይግለጽልን አሜን።

(ይቀጥላል)

# ምክንያት አናብዛ

በበጎ ግብገሮ ላይ ድግስ ተደግሶ
ነጭ የሠርግ ልብስ ለሁሉም ተዳርሶ
በደስታ በሐሴት በጥሩ ምስጋና
በሰፊው ቦታ ላይ በጽድቁ ጎዳና፤
ታዳሚ ሊያደርገን ጌታ ኑ ሲለን
መገናኘት ስንችል ጥሪን አክብረን፤
የዓለምን ስንክሳር ደስታን በመውደ
ለመባል እርጉማን ሲኦል ለመውረድ
መጓዙ ይቅርና በእነ ዴማስ ፋና
በማታዋጣዋ በዓለም ጎዳና፤
ኑ ዛሬ እንመለስ እንስማ ጥሪን
ምክንያት አናብዛ በቀኝ ለመሆን።

# ምልጃዋ የፀና

ለዓለም የተስፋ ምንጭ የድኅነት ማስገኛ
ለሕሙማን ሁሉ የሆነች መዳኛ፣
በመልአኩ ገብርኤል የተመሰገነች
ከሴቶች መካከል ልዩ የተባለች፤
ጌታን የወለደች በመንፈስ ቅዱስ
ክብሯን የገለፀው ዮሐንስ በፅንስ፤
የመንፈስ ሀብታትን ከአምላክ የታደለች
በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል ደግሞ የተባለች፤
እግዚአብሔር በፍቅሩ ሁሉን የሰጣት
ምንም ዓይነት እንከን የማይወጣላት፤
ሠርግ ቤት ተገኝታ አማላጅ የሆነች
በአደራ እናትነት ለዓለም የተሰጠች፤
ልዕልት ብፅዕት ናት ድንግል ማርያም
ምልጃዋ የፀና እስከ ዘለዓለም።

መኰንን አቦዬ
ምሥራቅ ወለጋ (ፊንጫአ)



www.ethiopisnorthodox.org

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

ከሲራክ ገብረክርስቶስ

መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጣቸው ሀብታት አንደኛው እምነት መኾኑ ተገልጿል። ለአብነት ያህል የማመን ጸጋ የተሰጣቸውን ጥቂት የእምነት ሰዎች መጥቀሳችን ይታወሳል። በይቀጥላል ካቆየነው በኋላ ለዛሬ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ወይም ቅዱሳን መካከል ጥቂቶቹን እናስታውሳለን። የማመን ጸጋ የተሰጣቸው ሰዎች በጸጋው ተጠቅመው ምን ዓይነት ኃይል እንደፈጸሙ በማስተዋል በእምነት ሰበብ የሚገኘው ጸጋ ምን ያህል ከፍተኛ ግምትና ከበሬታ ያለው መኾኑን በማጤን ግንዛቤ ልንወስድ ይገባናል። የእምነት ነቀዝ ወይም እምነትን እንዳይሠራ ሽባ የሚያደርገው የልብ ጥርጥረኛ መኾን ነው።

ከጥርጥር ፍርሃት ይወለዳል ። የሚፈራም ሰው እምነቱ ፍጹም አይደለም። ጎደሎ እምነት አለው ማለት ነው። በነቀዝ የተበላ የእህል ዓይነት መልኩ እንጂ ውስጡ የእህልነት ጣዕም የለውም ባዶ ነው። በዚሁ አንጻር ካየነው፣ አንድ ክርስቲያን በውጫዊ መልኩ አማኝ ሊመስል ይችላል። ምናልባት በውስጡ ጥርጥር ካለ እምነቱ ጎደሎ ይኾንበታል። ጎደሎ እምነት ያለው ሰው የማመን ጸጋ ከእርሱ የተቀነሰ ይሆናል። ስለዚህም እምነቱ ኃይል አይኖረውም የእህልነት ጣዕም እንደተለየው፣ በነቀዝ እንደተበላው ቅንጣት ወይም የእህል ዘር ይሆናል።

ቅዱስ ጴጥሮስ የሃይማኖት ሰው ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ በጽርሐ ጽዮን፣ በበዓለ ሃምሳ እስኪሰጠው ድረስና የእምነት ጸጋ ሙሉ በሙሉ እስከሚያድርበት ይወላውል፣ ይፈራ፣ ይደነግጥ እንደነበር መጽሐፍ ይመሰክራል። ለምሳሌ ከሌሊቱ በአራተኛው ሰዓት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕር ላይ ሲሄድ የተመለከተው ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ጌታ መኾኑን ካረጋገጠ በኋላ "ጌታ ሆይ አንተስ ከሆንክ በውኃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ" አለው ጌታችንም ና! ብሎ ፈቀደለት፣ ቅዱስ ጴጥሮስም ከታንኳይቱ ወርዶ ወደ ጌታ ለመቅረብ በባሕሩ ላይ እየተራመደ ጥቂት ከተጓዘ በኋላ፣ የነፋሱን ኃይል በማየቱ እሰጥም ይሆን ወይ የማለት ጥርጥር ሲያድርበት ፈራ፣ ደነገጠ ወዲያው ሲፈራ መስጠም ጀመረ። ጨርሶ ሰጥሞ እንዳይሞት ወደ እምነቱ ተመልሶ "ጌታ ሆይ አድነኝ" ብሎ ጮኸ ጌታችንም እጁን ዘርግቶ ያዘውና "አንተ እምነት የጎደለህ ስለምን ተጠራጠርህ? " አለው (ማቴ ፲፬:፳፰-፴፩)። የቅዱስ ጴጥሮስን እምነት ያጎደለው፣ የነፋሱን ግርማ በማየቱ እንዲፈራ እንዲደነግጥ ወደ ስጥመትም እንዲያመራ የገፋፋው፣ ለመንፈሳዊ ሕይወት፣ ለእምነት እንደ ነቀዝ የኾነው ጥርጥር ነበር።

ስለዚህ ጥርጥር የማመንን ጸጋ ከማራቁም በላይ ሰውን በማይጠቅም ፍርሃትና ድንጋጤ እንዲዋጥ ያደርገዋል። የእምነት ጸጋ በፍጹም እምነታቸው የተሰጣቸው ቅዱሳን ግን ምንም ነገር አያስደነግጣቸውም። በተሰጣቸውም የማመን ጸጋ ሁሉን ማሸነፍ ይችላሉ። ስለዚህ ሲመሰክር ቅዱስ ጳውሎስ "በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን" ብሏል (ሮሜ ፰:፴፯) ዳግመኛም ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ እንዲህ አለ "ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው" (፩ኛ ዮሐ ፭:፬) ከላይ እንደተገለጠው በማመን ጸጋ የተጠቀሙትን ሦስት የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን እንደሚከተለው እናቀርባለን። በጥሞና ለማስተዋል እንችል ዘንድ የቅዱሳን አምላክ በቅዱስ መንፈሱ ይግለጽልን አሜን።

፩) <u>ስለ ክቡር ዳዊት የእምነት ጸጋ</u> :- ዳዊት ከእሴይ በይሁዳ በቤተልሔም አገር የተወለደ ከወንድሞቹ ሁሉ ታናሽ የነበረና የአባቱን በጎች በመጠበቅ በእረኝነት የልጅነት ዘመኑን ያሳለፈ ሰው ነበር። በገና እየደረደረም ፈጣሪውን ያመሰግን ነበር። (፩ኛ ሳሙ ፲፮:፩-፲፫ ፣፩ኛ ሳሙ ፲፯:፲፫-፴፫) ከእርሱ ይልቅ በዕድሜ ብልጫ ካላቸው ወንድሞቹ መካከል ለንጉሥነት ታጭቶ የተቀባው በእግዚአብሔር ዘንድ የልቡ ቅንነትና እምልኮቱ ተመዝኖ ነው። ይኽንንም ሁኔታ ዳዊት በጸለየው ጸሎት እንዲህ ሲል ይገልጸዋል። "ንኡስ አነ እምአኀውየ ወወሬዛ በቤተ አቡየ። ወእርዒ አባግዐ አቡየ። እደውየ ይገብራ መሰንቆ ወአጻብእየ ያስተዋድዳ መዝሙረ መኑ ነገሮ ለእግዚእየ ውእቱ እግዚአብሔር ወውእቱ ሰምዐኒ ውእቱ ፈነወ መልአኮ ወአድኀነኒ ወነሥአኒ እምአባግዐ አቡየ ወቀብዐኒ ቅብዐ ቅዱስ።" ብሏል። (ከእግእዙ የዳዊት መዝሙር የመጨረሻው ክፍል)።

ትርጉሙም "ከወንድሞቼ እኔ ታናሽ ነኝ፣ በአባቴም ቤት ወጣት ነኝ፣ የአባቴን በጎች እጠብቅ ነበር፣ እጆቼ መሰንቆን ይሠራል፣ ጣቶቼም በገናውን አስማምተው ይመቷሉ፣ ይቃኛሉ። ለጌታዬ የነገረው ማነው? ማን ይነግረዋል! እሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው እርሱም ሰማኝ መልእክተኛውን ልኮ ያዳነኝ እሱ ነው። የአባቴን በጎች ከመጠበቅ ወስዶ ቅዱስ ቅብዓትን ቀባኝ (አነገሠኝ)" ማለት ነው። ዳዊት ተቀብቶም ሳለ እስኪነግሥ ድረስ ከሳኦል ቤተመንግሥት እየተመላለሰ የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር። በገናውን ከመደርደር ለፈጣሪው ከመዘመር አላቋረጠም። በቅብዓቱ አማካይነት በተሰጠው ሀብት ይበልጥ እምነቱ ተጠናክሮለት ስለነበር በዱር ሆኖ በጎቹን ሲጠብቅ ከአንበሳና ከድብ አፍ በጎቹን ያስጥላቸው ነበር።



www.ethiopisnorthodox.org

ይኽንንም ለንጉሥ ሳኦል ሲገልጥለት ዳዊት ራሱ መስክሯል ። ዳዊትም ሳኦልን አለው እኔ ባርያህ የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር፣ ከመንጋውም ጠቦት ይወስድ ነበር፣ በኋላውም እከተለውም እመታውም ነበር። ከአፉም አስጥለው ነበር፤ በተነሣብኝም ጊዜ ጉሮሮውን ይዤ እመታውና እገድለው ነበር ብሏል።(፩ኛ ሳሙ ፲፯:፴፬-፴፭)

ከዚህ ላይ የምናስተውለው ነገር ቢኖር በማመን ጸጋ የአራዊትን ኃይል ማድከም እንደተቻለና ፍርሃትና ድንጋጤ ቦታ እንደሌላቸው ነው፤ ከዚሁም በማያያዝ ዳዊት ፍልስጥኤማዊ ጎልያድን በእምነቱ ድል ማድረግ እንደሚችል ሙሉ እምነቱን በመተማመን ሲገልጽ ሳኦልን በትሕትና ቃል "እኔ ባርያህ አንበሳና ድብ መታሁ፤ ይህም ያልተገረዘው ፍልስጥኤማዊ የሕያውን አምላክ ጭፍሮች ተገዳድሮአልና ከእነርሱ እንዳንዱ ይሆናል። ከአንበሳና ከድብ እጅ ያስጣለኝ እግዚአብሔር ከዚህ ከፍልስጥኤማዊ እጅ ያስጥለኛል አለ።" ይኽ የእምነት ቃል ሊገኝ የቻለው ከተሰጠው የማመን ጸጋ የተነሣ እንደኾነ እናስተውል ሳኦል ዳዊትን የእምነቱን ፍጹምነት ካረጋገጠ በኋላ "ሂድ እግዚአ ብሔር ካንተ ጋር ይሆናል" አለው።

የእምነት ጸጋን የተሞላ ጀግናው ዳዊት ከባድ የሆነ የጦር ትጥቅ ሳይሻ፣ ከወንዝ የለቀማቸውን አምስት ድቡልቡል ደንጊያዎችን በኮሮጆው አኑሮ፣ በትርና ወንጭፍ ይዞ፣ በቁመትና በሥጋዊ ጡንቻ፣ በጦርመሣሪያም ድርጅት ገኖ ከሚታየው አረማዊ ጎልያድ ጋር ሊፋለም ቀረበ። ፍልስጥኤማዊው ጎልያድ ዳዊትን ትኩር ብሎ አየው። ቀይ ብላቴና መልኩም ያማረ ነበረና ናቀው። ቀጥሎም ዳዊትን "በትር ይዘህ የምትመጣብኝ እኔ ውሻ ነኝን?" ብሎ በጣዖታቱ ስም ዳዊትን ይረግመው ጀመር። በማያያዝም "እስቲ ወደ እኔ ና! ሥጋህንም ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት እሰጣለሁ" አለው። ዳዊት ግን በትዕግሥት ፉከራውን ካዳመጠ በኋላ በተሰጠው የእምነት ጸጋ ልበ ሙሉ ሆኖ በቆራጥነት መንፈስ የሚቀጥለውን ቃል ተናገረ። "አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ፤ እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርኸው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም፣ በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም፣ እመጣብሃለሁ። እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል፣ እመታህማለሁ። ራስህንም ከአንተ እነሣዋለሁ፤የፍልስጥኤማውያንን ም ሠራዊት ሬሶች ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት ዛሬ እሰጣለሁ። ይኸውም ምድር ሁሉ በእስራኤል ዘንድ አምላክ እንዳለ ታውቅ ዘንድ፣ ይህም ጉባኤ ሁሉ እግዚአብሔር በሰይፍና በጦር የሚያድን እንዳይደለ ያውቅ ዘንድ ነው። ሰልፉ ለእግዚአብሔር ነውና እናንተንም በእጃችን አሳልፎ ይሰጣል።"

ይኽን ካለ በኋላ ወደ ፍልስጥኤማዊው እየሮጠ ሄዶ፣ ከኮረጆው አንድ ደንጊያ ወስዶ፣ ወነጨፈበት፤ ግንባሩን መታው፣ ደንጋዩም በግንባሩ ተቀረቀረ፣ ጎልያድም በምድር ላይ በፊቱ ተደፋ። ዳዊት በሰይፍ ሳይሆን በወንጭፍ ባለሰይፉን ድል ሊመታ የቻለው በተሰጠው የማመን ጸጋ ነው። የጎልያድ ቁመና ከዳዊት ጋር ሲተያይ በዳዊት እጅ ድል ይመታል ማለት ለማያምን ተጠራጣሪ፣ ከቶ የማይታሰብ የማይደረግ ነው፤ ዳሩ ግን የማመን ጸጋ በተሰጣቸው ቅዱሳን ይኽ የሚቻል ከመጤፍ የማይቆጠር ሆኖ መታሰቡን ከዚህ ላይ ይገነዘቧል።

የጌት ሰው ፍልስጥኤማ ዊው ጎልያድ ቁመቱ ስድስት ክንድ ከስንዝር ሲሆን በራሱ ላይ የራስ ቁር ደፍቶ፣ አምስት ሺህ ሰቅል ናስ ጥሩር ለብሶ፣ በእግሮቹም ላይ የናስ ገምባሌ የነበረው፣ በትከሻውም የናስ ጭሬ ያለው፣ የጦሩም የቦ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ የነበረ፣ የጦሩም ሚዛን ስድስት መቶ ሰቅል ብረት የነበረ፣ በዚህ ሁሉ ትጥቅና ቁመና ለ፵ ቀናት በእስራኤል ላይ ግጠመኝ እያለ ሲያስፈራራ የከረመ ሰው ነበር። እምነታቸው የጎደለ ሲፈሩ ሲንቀጠቀጡ ተገኝተዋል። ይኽም ለጎልያድ የልብ ልብ ሰጥቶት ይዝናናባቸው ይፎክርባቸው ነበር። ዳሩ ግን የማመን ጸጋን በተቀዳጀ በትሑቱ ጀግና በዳዊት ወንጭፍ ጎልያድና ሠራዊቱ ድል ሊነሡ ችለዋል። (፩ኛ ሳሙ ፲፯:፩-፶፬)።

የእምነት ጀግኖች በጥቂት ሠራዊትና መሣሪያ በእግዚአብሔር ኃይል ሊያሸንፉ እንደሚችሉ ሲያረጋግጥ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ ብሏል። "ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም ኃያልም በኃይሉ ብዛት አያመልጥም ። ፈረስም ከንቱ ነው አያድንም፤ በኃይሉም ብዛት አያመልጥም እነሆ የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ሚፈሩት ናቸው ፣ በምሕረቱም ወደሚታመኑ።" (መዝ ፴፪:፲፮-፲፰)።

የእምነት ጸጋ ያላቸው ከሰይፍ ስለት ያመልጣሉ፣ ከድካማቸው ይበረታሉ፣ በጦርነት ኃይለኞች ይሆናሉ፣ የባዕድን ጭፍሮች ያባርራሉ። የእምነት ጸጋ ታላቅ ኃይል የሚሠራ ለያዙት ሁሉ ከፍተኛ ድልን የሚያቀዳጃቸው ነው። (ዕብ ፲፩:፴፬) ስለኾነም በጥርጥር ልቡናችን የፍርሃትና የመንቀጥቀጥ ደዌ እንዳያድርበት እምነትን ይዘን በሚሰጠን የማመን ጸጋ ለመጠበቅ ያብቃን። የዳዊት በረከት የቅዱሳን ሁሉ የእምነታቸው ረድኤት ይደርብን አሜን።

፲) <u>የነቢዩ ኤልያስ እምነት</u> :- ቴስብያዊው ኤልያስ በብሕትውና በድንግልናዊ ሕይወት የሚኖር፣ ለፈጣሪው አምልኮ ቀናተኛ፣ በሰው መካከል አድሎ ሳያደርግ ሁሉንም በትክክል የሚገሥጽ፤ መምህር ወመገሥጽ ዘኢያደሉ ለገጽ ነበር። የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ ከሚስቱ ከኤልዛቤል ጋር በመኾን፣ እግዚአብሔርን ትቶ በአል የተባለውን ጣዖት በማምለክ፣ ለእስራኤል ሕዝብ የስሕተት አብነት ሆኖ በመገኘቱ፣ ነቢዩ ኤልያስ በመንፈሳዊ ቅንዓት ተነሣሥቶ ተው! ጣዖት አታምልክ እያለ ይመክራቸው ይገሥጻቸው



www.ethiopisnorthodox.org

ነበር።ዳሩግን ንጉ ሡም ፣ሚስቱ ኤልዛቤል፣ሕዝበ እስራኤልም ጣዖት ማምለካቸውን ቀጠሉበት እንጂ ወደ እግዚአብሔር አምልኮት ሊመለሱ አልቻሉም ፤ ይልቁንም በቤተ መንግሥት እየተቀለቡ ሕዝቡን ወደ ጣዖት አምልኮት የሚቀሰቅሱ፣የእግዚአብሔርን ነቢያት ደም የሚያፈሱ፣ አራት መቶ ሃምሳ የበአል ነቢያት፣አራት መቶም የማምለኪያ ዐፀድ ነቢያት፣ በድምሩ ስምንት መቶ ሃምሳ ነቢያተ ሐሰት፣ ካህናተ ጣዖት ሠልጥነው ስለነበር፤ ኤልያስ መንፈሳዊ ቅንዓቱ እንደ እሳት ነደደ። በትምህርትና በተግሣጽ የማይመለሱ፣ የማይፈወሱ መሆናቸውን ከተረዳ በኋላ ኤልያስ በመንፈሳዊ ድፍረት፣ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀናተኛ ሆኖ በተሰጠው የማመን ጸጋ፣በንጉሡ ፊት ቆሞ ሰማይ ዝናብ ለዘር፣ ጠል ለመከር እንዳትሰጥ፤ምድርም ፍሬዋን እንዳታበቅል፣የተከሉባትን እንዳታጸድቅ እንዲህ ሲል አወገዘ፤ <u>"የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን! ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናም አይሆንም።"</u> (፩ኛ ነገሥ ፲፭:፩ ፣፲፰:፲፰) እንደቃሉ ውግዘት ለሦስት ዓመት ከመንፈቅ ድርቅ ሆነ። ጣዖት አምላኪዎች በራብ ይቆሉ ጀመር።

ከዚህ በኋላ ዳግመኛ በፈቃደ እግዚአብሔር፣ ኤልያስን ሊያስገድለው ሲያስፈልገው ከነበረው ንጉሥ ፊት ቀርቦ "የአንተንና የሚስትህ የኤልዛቤልን ካህናተ ጣዖታት በቀርሜሎስ ተራራ ሰብስብልኝ እስራኤል ሁሉ ይሰብሰቡ ከእግዚአብሔር ነቢያት እኔ ብቻዬን ቀርቻለሁ። መሥዋዕት እንሠዋና ከሰማይ እሳት ወርዶ መሥዋዕቱን የበላለትን ወገን አምላክ አምልኩ እንጂ እስከመቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ" ብሎ ተናገረ። በሐሳቡ ንጉሡ ተስማማ፣እንዳለው አደረገ። ፊት ካህናተ ጣዖቱ መሥዋዕት አቅርበው "በአል ሆይ ስማን!" ሲሉ ከጠዋት እስከ ሠርክ ሲጮኹ ዋሉ። ባዶ ጩኸት ብቻ ሆነ የሚመልስ አልነበረም። ቀጥሎ ተራው የኤልያስ ስለነበር ሕዝቡን ሰብስቦ ፈርሶ የነበረውን የእግዚአብሔርን መሠዊያ አበጀ። በመሠዊያው ዙሪያ ጉድጓድ ቆፈረ ። እንጨቱን ረበረበ። ወይፈኑን በብልት፣በብልት ቆረጠ። በእንጨቱም ላይ አኖረና አራት ጋን ውኃ ሙሉ በሚቃጠለው መሥዋዕትና በእንጨቱ ላይ አፍስሱ አለ። ደገሙ፤ ለሦስተኛም ጊዜ እንደፊተኛው አፍስሱ አለ። ውኃው በጉድጓዱ ሞላ፣መሥዋዕተ ሠርክ በሚቀርብበት ጊዜ ነቢዩ ኤልያስ ቀርቦ "አቤቱ የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ ሆይ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደሆንህ፣እኔም ባርያህ እንደሆንሁ፣ይህንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይገለጥ። አንተ አቤቱ አምላክ እንደሆንህ ልባቸውንም ደግሞ እንደመለስህ ይህ ሕዝብ ያውቅ ዘንድ ስማኝ" አለ። የእግዚአብሔርም እሳት ወደቀች መሥዋዕቱን፣ እንጨቱን ፣ ድንጋዮችንም ፣ አፈሩንም በላች በጉድጓዱም ውስጥ ያለውን ውኃ ላሰች።

ይኸ ውጤት ሊታይ የቻለው ኤልያስ በማመን ጸጋ፣ያለ ጥርጥር ባቀረበው የሃይማኖት ጸሎት ነበር፣ሕዝቡም ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ክብር ለመስጠት በቅቷል። ቀጥሎም ኤልያስ በእምነት ጸሎት አድርጎ ዕለቱን ዝናም አዝንሟል፤ ካህናተ ጣዖታቱንም አጥፍቷል። የእምነት ሀብት የተሰጠው በመኾኑ መንፈሳዊ ቅንዓቱ ድንቅ ሥራን ሊያሳይለት ችሏል። (፩ኛ ነገ. ፲፰:፲፱-፵፮)። ሐዋርያው ያዕቆብም ይኸንን ሁኔታ በመልእክቱ "ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ ፣ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ ፣ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም። ሁለተኛም ጸለየ ሰማዩም ዝናምን ሰጠ፣ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች።" በማለት ያጠቃልለዋል። (ያዕ. ፭:፲፯-፲፰)።

የእምነት ጸጋ ያላቸው እንደ ኤልያስ ያሉ ቅዱሳን፣ሕገ እግዚአብሔር ፈርሶ ሕገ አጋንንት ነገሠ በማለት፣በመንፈሳዊ ቅንዓት ፣ በመንፈስ ቅዱስ ይናደዳሉ። መንፈሳዊ ቅንዓታቸው አነሣሥቶ ፣ በተሰጣቸው የእምነት ጸጋ ፣ የእግዚአብሔር ክብር እንዲገለጥ ፣ ሰዎች ከስሕተት ተመልሰው ወደ እውነተኛው ሃይማኖት እንዲገቡ ተአምራት ይደረግላቸዋል። በማመን ጸጋ ተፈጥሮን መቆጣጠር እንደሚቻል፣ኤልያስ በእምነቱ ባሳየው ድርቅና ዝናም ማወቅ ይቻላል። ከሰማይ ምልክት በማሳየቱም ፣ እውነተኛው አምላክ ሊታወቅ ችሏል። ስለዚህ ለእኛም የቅዱሳኑ በረከት ተርፎን፣የምስጋናችን መሥዋዕት የሚያርግ፣የሃይማኖታችን ኃይል ሌሎችን ማርኮ ጣዖታውያንን የሚያሳፍር እንዲሆን የኤልያስ ጸሎት በረከት ይደርብን አሜን።

፯) <u>የሠለስቱ ደቂቅ እምነት</u> :- የእስራኤል ሕዝብ ጣዖት በማምለካቸው ፣ ኃጢአት በመሥራታቸው ምክንያት እግዚአብሔር በመቅሠፍት ጨንገር ሲገርፋቸው ከቆየ በኋላ፣ በእልከኝነት መንፈስ በኃጢአታቸው ስለቀጠሉ፣ለፋርስ ባቢሎን ሠራዊት አሳልፎ ሰጣቸው። በባዕድ አገር በምርኮ ሳሉ ብዙዎቹ ከአሕዛብ ጋር በጣዖት አምልኮና በአመጋገብ ሥርዓት አንድ ሆኑ።

ከተማረኩት መካከል "በኃጥኡ ዳፋ ጻድቁ ይዳፋ" እንዲሉ ደጋግ ሰዎችም የእምነት ጸጋ የነበራቸው ሠለስቱ ደቂቅን የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል። ሠለስቱ ደቂቅ ከነዳንኤል ጋር የተማረኩ ወጣቶች ናቸው። በምርኮ አገር ሳሉ ተመርጠው በባቢሎን ቤተ መንግሥት እንዲቀለቡና መልካቸው ያማረ ሆኖ ሲገኝ፣ለቤተ መንግሥት አገልግሎት እንዲታጩ በታዘዘው መሠረት ፣ እነዚህ ሦስት ወጣቶች ቁጥራቸው ከተቀላቢዎቹ መካከል ነበር። ሠለስቱ ደቂቅ አናንያ፣አዛርያ፣ ሚሳኤል የተባሉት ወጣቶች ግብረ ገብነት ከሃይማኖት ጋር አስተባብረው የያዙ ስለነበር የቤተ መንግሥት ግብር አልማረካቸውም። ሆዳችን ይምላ ደረታችን ይቅላ ብለው ሁሉን ላፌ አላሉም። የእምነት ጸጋ ያደረባቸው በመኾኑ የላመ፣ የጣመ ከመብላት ይልቅ፤በጥሬና በውኃ በጾም መኖርን መረጡ። ሥጋ ከሚበሉ፣ጠጅ ከሚጠጡ፣ለሆዳቸው ስሉ ከኾኑት ይልቅ፣በአሥር ቀን አመክሮ ጥሬ ቆርጥመው ውኃ የተጎነጩ የጾመኞቹ፣የሦስቱ ወጣቶች ፊት አምሮና ወፍሮ ሞገስ ያለው ሆኖ ተገኝቷል። (ዳን. ፩:፩-፲፯) የእምነታቸው ጥንካሬ እየጎለመሰ በመሄዱ ፈተናውም እየጠነከረባቸው መጣ። ምንም እንኳን በሙያቸውና በታማኝነታቸው የባቢሎን አውራጃ ገዢዎች ሆነው ቢሾሙም ለሹመትና ለሥልጣን ጓጉተው እምነታቸውን አላጎደሉም።

የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የወርቅ ጣዖት አቁሞ፣ሕዝቡን በዐዋጅ አሰብስቦ እንዲሰግዱለት በማዘዙ ምክንያት ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ



www.ethiopisnorthodox.org

ሲሰግድ፤ሦስቱ ወጣቶች ግን በእምነታቸው ጸንተው ያሉ በመኾናቸው ለጣዖት አልተንበረ ከኩም።ተከሰው፣ንጉሡ ፊት ቀርበው "ከእጄ የሚያስጥላችሁ ማን ነው" ብሎ ሊያስፈራራቸው ሞክሮ ነበር። እነርሱ ግን የማመን ሀብት ያደረባቸው፣እምነታቸው ፍጹም ስለነበረ የሚከተለውን ኃይለ ቃል በተቀደሰ ድፍረት ተናግረዋል። "ናቡከደነፆር ሆይ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም፣የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል። ከእጅህም ያድነናል ንጉሥ ሆይ! ዳሩ ግን ባያድነንም እንኳ አማልክትህን እንዳናመልክ፣ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ" አሉት። ንጉሡም በንዴት እሳቱን ከፊት ይልቅ ሰባት ዕጥፍ አድርገው እንዲያነዱትና ከነልብሳቸው ሦስቱን ወጣቶች አስረው በእቶኑ እንዲጥሏቸው አዘዘ። ጭፍሮች እንደታዘዙት አደረጉ፣ የተጣሉት ሳይቃጠሉ የጣሉዋቸው ሰዎች በወላፈኑ ተቃጥለው ሞቱ።

ሦስቱ ወጣቶች ግን በማመን ጸጋ ድነው መልአክ ወርዶ ፣ ሰንሰለታቸው ተፈትቶ፣ እግር ብረታቸው ተሰብሮ፣ከመልአኩ ጋር ሆነው በእሳቱ መካከል እየተመላለሱ ፈጣሪያቸውን አመስግነዋል። ይኽን ታምር በማየቱ ናቡከደነፆር ዐዋጁን በዐዋጅ መልሶታል። በግዛቶቹ ሁሉ ላሉት እንዲህ ሲል ማዘዣ በትኗል፣ አስተላልፏል። "መልአኩን የላከ ከአምላካቸውም በቀር ማንንም አምላክ እንዳያመልኩ፣ለእርሱም እንዳይሰግዱ ሰውነታቸውን አሳልፈው የሰጡትን፣ የንጉሡንም ቃል የተላለፉትን፣በእርሱ የታመኑትን ባሪያዎቹን ያዳነ፤የሲድራቅና የሚሳቅ የአብደናጎም አምላክ ይባረክ። እኔም እንደዚህ የሚያድን ሌላ አምላክ የለምና በሲድራቅና በሚሳቅ በአብደናጎም አምላክ ላይ የስድብን ነገር የሚናገር ወገንና ሕዝብ፣በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ይቆረጣሉ፣ቤቶቻቸውም የጉድፍ መጣያ ይደረጋሉ ብዬ አዝዣለሁ" የሚል ነበር (ዳን. ፫:፩-፳፱)

በእሳቱ ውስጥ ሳሉም ሦስቱ ወጣቶች የጸለዩት ጸሎት ያመሰገኑት ምስጋና በስማቸው ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ ተብሎ ከነቢያት ጸሎት ጋር ተቆጥሯል። ቤተክርስቲያናችን በዚሁ ጸሎት ትጠቀምበታለች። ከጸሎቱ ውስጥ "ይባርክዎ እሳት ወላህብ ለእግዚአብሔር ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም" የሚል ይገኛል። ትርጉሙም "እሳትና ሙቀት እግዚአብሔርን ያከብሩታል፣ያመሰግኑታል፤ለዘላለም እርሱ የተመሰገነ፤ከፍከፍ ያለ ነው እያሉ ያመሰግኑታል" ማለት ነው። በእምነት ጸጋ ሠለስቱ ደቂቅ የንጉሥ ዐዋጅ፣የእሳቱ ነበልባል ሊያስፈራቸው አልቻለም። በእምነት ጸጋ የእሳትን ኃይል አጥፍተዋል። (ዕብ ፲፩:፴፬) እኛም የፈተናን እሳት ለማጥፋት እንድንችል የእምነታቸው ጸጋ ይደርብን አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

# ባልንጀራዩ . . .

ከገጽ ፳፰ የዞረ

መፍትሔ የሚያሻውም ከሆነ እንደ ባለቤቱ አብሮ ይቸገራል። ይኸ ሲጠፋ ባልንጀርነትም አብሮ ይጠፋል። የጓደኛን የሥራ ውጤት በመኮረጅ እኔ ልታወቅበት እኔ ልሸለምበት ማለትም ምሥጢር ማባከን ነው። ይህ ችግር በተለይ በተመራማሪዎች፣ በደራሲዎች፣ በሠዓሊዎች በዲዛይን (ሞዴል) አውጭዎች፣ በተማሪዎች አካባቢ በተደጋጋሚ ይከሰታል ባልሠሩት ሥራ ለመመስገን መጣር ያስጸይፋል። በዚህም መንስዔ ፍቅር ይቀዘቅዛል ጓደኝነት ይቀራል። ሰዎችንም ራሳቸው እስኪያጠፉ ያደርሳቸዋል።

## ፲. በሃይማኖት መለያየት

:- ብዙ ሰዎች በሃይማኖት ከማይመስሉን ሰዎች ጋር ጓደኝነት መመሥረት እንችልምን? የሚል ጥያቄ አላቸው። ይሁን እንጂ እነዚያን ሰዎች መውደድ ቢቻልም ጓደኛ ማድረግ ግን የማይሞከር ነው። ጓደኛ አለማድረግ ማለት እነርሱን መጥላት ማለት አይደለም። አለመጥላታችንም የሚታወቀው ከእነርሱ ጋር በመዋል በማደራችን እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል።

በአንዲቷ የክርስትና እምነት አብረው ይጓዙ ከነበሩ ጓደኛሞች መካከል አያድርስና አንደኛቸው ሃይማኖታቸውን ቢተውና የማይመለሱ ከሆነ መለየት ያስፈልጋል። አንድ ሰው የግድ መናፍቅ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ስሙ ኦርቶዶክሳዊ ሆኖ ምግባረ ሃይማኖት የሌለው ከሆነ እርሱም ሃይማኖቱን የተወ ነውና የቅርብ ጓደኛ ሊያደርጉት አይገባም። ንዋየ ኅሩይ ቅዱስ ጳውሎስ "ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል" እንዳለው። (፩ቆሮ ፲፭:፴፫) እርሱም ከተጠራ በኋላ ቅዱስ እስጢፋኖስ ሲወገር ልብሳቸውን ይዞላቸው የነበሩትን ወጋሪዎች(አሳዳጆች) ጓደኞቹን ከእነዚህ ጋር ጓደኝነት አያስፈልግም ብሎ ትቷቸዋል። ደግሞም "ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ" ሲል አስተምሯል። (፪ቆሮ ፮:፲፬) የማያምኑ የተባሉ ከአንዲቷ ከተዋህዶ ሃይማኖት የተለዩ ሁሉ ናቸው እንጂ እምነት አለኝ ብሎ ለጣዖት የሚሰግደው ሁሉ ያምናል ማለት አይደለም።

ሰብአዊነትና ጓደኝነት ሁለት የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው። ማንኛውም ሰው በሰውነቱ አይጠላም። ስለማይጠላ ግን ጓደኛ ይሁን ማለት አይደለም። ብዙ ሰዎች ከእነልዩነታችን አንድ እንሁን የሚል ሐሳብ አላቸው። በሃይማናት ተለያይቶ ጓደኝነት የለም።

ከመናፍቃን ጋር ኅረቤት መሆን፣ አብሮ መሥራትና መማር ማለት ጓደኛ መሆን ማለት አይደለም። ጓደኛ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው። አምላካችን በጓደኛችን ላይ አድሮ ያስተምረናል፣ ይመክረናል፣ ይገስጸናል፣ ይመራናል። ስለዚህ ጓደኛ የእግዚአብሔርን ድምጽ የምንሰማበት መሰንቆ ነው ማለት እንችላለን። ይህን መልእክት የሚያመጣ ሰው ደግሞ በቀናችው በተዋህዶ ሃይማኖት የሚጓዝ የሆነ እንደሆነ ነው። ከዚያ ውጭ ያለ ሰው የእግዚአብሔርን ድምጽ እንኳን ለሌላው ሊያስተጋባ ለራሱም ያልሰማ በመሆኑ አይረባንም።እሳትና ጭድ፣ አህያና ጅብ፣ በግና ተኩላ እንዴት ባልንጀሮች ይሆናሉ?

ፈያታዊ ዘየማን ካመነ በኋላ የወንጀል ጓደኛውን ትቶት ወደ ገነት እንደተጓዘ እኛም፣ እንዲሁ የምናደርግበትን ኃይል እግዚአብሔር ይስጠን።

ማጠቃለያ :- እስካሁን ባልንጀራ ማለት ምን እንደሆነ እንዴት እንደሚመሠረትና እንዴት እንደሚፈርስ በመጠኑ ለማየት ሞክረናል። በዚህች አነስተኛ ጽሑፍ ራሳችንን እንመዝንና ማንነታችንን ፈልገን እናግኝ። ነገር ግን ጓደኝነት ማለት አለመፈተን ጎደኛም ማለት የማይሳሳት ማለት አይደለምና አንዱ ሲወድቅ ሌላው እያነሳው፤ሲደክም እያበረታው መጓዝ ያስፈልጋል። የጓደኝነት መሰናክሎች እንዳያደናቅፉን በማስተዋል እንኑር። በተሳሳተ ዓላማ ሰዎችን ጓደኛ ያደረግን ወይም የምናስብ ሁሉ ከክፉ ሐሳባችን እንመለስ። የተጣላን እንታረቅ፣ የተራራቅን ልዩነታችንን እናጥፋ። የፍቅር ባለቤት እግዚአብሔር ፍቅር ይስጠን አሜን።



www.ethiopisnorthodox.org

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

(የመፈወስ ሀብት) /ካለፈው የቀጠለ/

ሀብተ ፈውስ /የመፈወስ ጸጋ/ ከተሰጣቸው ቅዱሳን አባቶች መካከል ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ዮሐንስን በጥላቸው ማለትም በጽላሎተ ረድኤታቸው ማንኛውንም ዓይነት ደዌ ለማራቅ ፈውስ ይሰጡ እንደነበር ባለፈው ጽሑፍ መግለጻችን ይታወሳል። ከዚያው በመቀጠል የመፈወስ ጸጋ ከመንፈስ ቅዱስ የተሰጣቸው አበው ምስክርነት እንጠቅሳለን።

በመጀመሪያ ካለፈው የቀረውን ቅዱስ ጴጥሮስና ዮሐንስ እንዴት አድርገው በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ይፈውሱ እንደነበር በግብረ ሐዋርያት ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ የጻፈልንን በዋቤነት ጠቅሰን ልናስገነዝብ እንወዳለን።

በሐዋርያት ሥራ ምዕ. ፫ ከቁጥር ፩ እስከ ፲ በተመዘገበው ቃለ እግዚአብ ሔር ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ሐዋርያት በተሰጣቸው ሀብተ ፈውስ ከእናቱ ማኅፀን አንስቶ አንካሳ (ልምሻ) ሁኖ የተወለደውን ሰው እንደፈወሱት ይናገራል።

ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ በዘጠኝ ሰዓት ሊጸልዩ ወደ ምኩራብ ይገባሉ ከ፯ቱ ጊዜያት ዘጠኝ ሰዓት አንዱ ስለሆነ ለሰው አብነት የሚሆኑበትን ተገልጸው ይጸልዩ ስለነበር ለጸሎት ወደ ምኩራብ ወይም ቤተ መቅደስ ይሄዱ ነበር።

ለምን ወደ ምኩራብ ሄዱ? ጌታ በተሰቀለ ጊዜ አድሮባት የነበረ መንፈስ ቅዱስ በነጭ ርግብ አምሳል ተለይቶ ወጥቶ ሲሄድ ታይቶ አልነበረምን? የሚል ጠያቂ ቢኖር አዎን ይኸ ሁሉ ተደርጓል። ሐዋርያት ወደ ምኩራብ (ቤተ መቅደስ) መውጣታቸው ይህን ዘንግተው ምኩራብ አሪት ናት በማለት ሳይሆን ወንጌል ብለው ይጸልዩባት ስለነበር ነው።

ለጸሎት ሲሄዱ አርያ በምትባል በምኩራብ ደጅ ዕለት ዕለት እየተሸከሙ ወስደው ያኖሩት የነበር ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ልምሾ የሆነ አንድ በሽተኛ ሰው ወድቆ ምጽዋት ሲለምን ያገኙታል። በሽተኛው ባያቸው ጊዜ ምጽዋት ምጽዋት ብሎ ለመናቸው። "ተመየጥ መንገለነ" ይሉታል። ወደእኛ ተመልከት ሲሉት ፊቱን መልሶ ወርቅ ብር የያዙ መስሎት ዞሮ አየ። እነርሱ ግን ወደ እኛ ፊትህን አዙረህ ተመልከት ማለታቸው የምስጢር አነጋገር ነው። ወደእኛ ሃይማኖት ተመለስ ሲሉት ነው። "ወይቤሎ ጴጥሮስ ወርቅሰ ወብሩር አልብየ" ጴጥሮስም አውቆበት ወርቅና ብር የለኝም "ወእምዘ ብየሰ እሁበከ ናሁ በስመ ኢየሱስ ክርስቶስ ናዝራዊ ተንስእ ወሁር" አለው። ትርጉሙ ከያዝኩት እሰጥሃለሁ፤ እነሆ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነስና ተመላለስ። ማለት ነው። በቀኝ እጁም የበሽተኛውን እጅ ይዞ አስነሳው። ከሽባነቱ የተፈወሰው ሰውም እግሩ ጸንቶለት ወገቡ ቀንቶለት ጥግ መቋሚያ ሳይሻ ተነስቶ ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ዮሐንስን ተከተለ።

"ወቦአ ምኩራብ ወአእኰተ እግዚአብሔርሃ " ከምኩራብ ገብቶ ከዚህ ያደረሰከኝ፣ ከደዌዬ የፈወስከኝ ብሎ እግዚአብሔርን አመሰገነ። ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲሄድ ባዩት ጊዜ፤ አሪያ በምትባል ምኩራብ ደጅ ተቀምጦ ምጽዋት ሲለምን የነበረው ሰው እንደሆነ አውቀው ለርሱ ስለተደረገው ነገር አደነቁ። እንዲህ ያለ አስደናቂ ሥራ ሊሠራ የቻለውም ሀብተ ፈውስ በተሰጣቸው በቀና ሃይማኖት በበጎ ምግባር ፍፃሜን በሆኑ በሐዋርያት አማላጅነት፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑን ያስተውሏል። ሕዝቡም ሊያደንቁ የቻሉት ክቡር ዳዊት በትንቢት አስቀድሞ እንደተናገረው "መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ " /መዝ. ፷፯: ፴፭ / እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው። ባለው መሠረት የተፈጸመ ስለሆነ ነው። ዳግመኛም ነብዩ ኢሳይያስ ክርስቶስ ወደ ዓለም ከመጣ በኋላ ቤተክርስቲያን ስለሚኖራት ጸጋ ትንቢት ተናግሯል። /ኢሳ. ፴፭ :፭-፮/ በዚያን ጊዜም የእውሮች ዓይን ይገለጣል፤ የደንቆሮዎችም ጆሮ ከሲራክ ገብረክርስቶስ ይከፈታል። "በዚያን ጊዜ አንካሳ እንደ ሚዳቋ ይዘላል። የድዳ ምላስ ይዘምራል በምድረ በዳ ውሃ በበረሃም ፈሳሽ ይፈልቃል።" ተብሎ የተነገረው ይኸንኑ የሚያስረዳ ነው።

"በዚያን ጊዜም" ሲል ዘመኑ ዘመነ ሥጋዌ ነው። ጌታችን ሰውን ሁሉ ለማዳን ሥጋን ነፍስን ከድንግል ማርያም ነስቶ በተዋሕዶ ገንዘብ አድርጎ የተገለጸበት ጊዜ ዘመነ ሥጋዌ ወይም ዓመተ ምህረት ይባላል። ካረገም በኋላ ዘመኑ ዘመነ ወንጌል ወይም ዘመነ ሐዲስ ስለኾነ ከዘመነ ሥጋዌ ውጭ አይደለም።

ጌታችን ለሐዋርያትና ለተከታዮቻቸው የመንፈስ ቅዱስን ሀብት (ጸጋ) አድሏል፣ ናኝቷል። ቅዱሳኑም በተሰጣቸው ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ ተግባራትን አከናውነዋል። ከዚያ መካከል አንዱ የመፈወስ ሥራ ነው። በዚህ የመፈወስ አገልግሎት በሥጋ የታወሩት በተአምራት በነፍስ የታወሩት በትምህርት ተፈውሰዋል። ግዙፉን ብርሃን ረቂቁን ፀዳል አይተዋል። የሥጋቸው ጆሮዎች ከመስማት የተከለከሉ ህሙማን በተአምራት እንዲሰሙ ተደርገዋል። የነፍስ ጆሯቸው የደነቆረ በትምህርተ ወንጌል ተከፍቶላቸው ድህነተ ነፍስ አግኝተው ምሥጢር የሚሰሙ ሆነዋል። ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስተምር ታስተውል ዘንድ እዝነ ልቦናዋ (የልብ ጆሮዎቿ) የተከፈቱላት ልድያ የተባለች ሐር ሻጭ ለአብነት ልትጠቀስ ትችላለች። /ግብረ ሐዋር.፲፮:፲፬-፲፭/ በሥጋቸው ልምሾ (አንካሳ) የሆኑት በተአምራት እንደ ሚዳቋ ዘለዋል። በጥርጥርና በኃጢአት ሐንካሳነ ነፍስ የሆኑትም በትምህርት ድነው በፍኖተ ወንጌል በተዋሕዶ ምግባርና ሃይማኖት እንደ ልባቸው እየተራመዱ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያመሩ የሚገሰግሱ ሆነዋል። "የላሉትን እጆች የሰለሉትንም ጉልበቶች አቅኑ፤ ያነከሰውም እንዲፈወስ እንጂ እንዳይናጋ ለእግራችሁ ቅን መንገድ አድርጉ።" /ዕብ.፲፪ :፲፪-፲፫/

ጌታም በወንጌል "በጠበበው ደጅ ግቡ ወደ ጥፋት የሚወስደው

www.ethiopisnorthodox.org

ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነው ወደርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው። ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው" /ማቴ.፯:፲፫-፲፬/ ማለቱ በሰፊው ጎዳና በፈቃደ ሥጋ ሳይሆን ሕይወት የሚገኘው በቀጭኗ መንገድ በተዋህዶ መስመር በፈቃደ ነፍስ በምግባር በትሩፋት በሃይማኖት መሆኑን አስገንዝቧል። በዚህ መስመር ለመጓዝ እግረ ልቦናቸው ከልምሾነት ከአንካሳነት የረታላቸው የቀናላቸው እንደ ልባቸው ሊራመዱ ይችላሉ። ይህም ሊከናወን የሚቻለው የመንፈስቅዱስ ጸጋ ባደረባቸው የመፈወስ ጸጋ በተሰጣቸው ሐዋርያትና በጻድቃን በሰማዕታት ነው።

በበሽታ ምክንያት በሥጋቸው ድዳ የሆኑ በቅዱሳኑ ጸሎት በተሰጣቸው የመፈወስ ሥልጣን ሲድኑ በደስታ ይዘምራሉ ያመሰግናሉ። የነፍሳቸው አንደበት እግዚአብሔን ከማመስገን በደዌ ኃጢአት በጥርጥር በክህደት ድዳ የሆኑ ተፈውሰው በተመስጦ ያመሰግናሉ።

"በምድረ በዳ ውኃ በበረሃ ፈሳሽ ይፈልቃልና" ተብሎ በምሳሌያዊ አገላለጥ የተነገረው ትንቢት ሲተረጎም ከኃጢአት ከክህደት ከጣዖት አምልኮት የተነሣ የሰው ልቡና የሃይማኖት ልምላሜ የገድል የትሩፋት ጽጌ (አበባ) የጸጋ ፍሬ ሳያገኝ በዓመተ ፍዳ በዓመተ ኩነኔ ከኖረ በኋላ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በፈሳሽ ውሃ የተመሰለውን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ባደለ ጊዜ የሰው ልጅ ልቡና የመንፈስ ቅዱስ ገዳም ማደሪያ ሆኖ ልጅነትን ተጎናጽፎ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በዝቶ እንደሚሰጠው የሚናገር ሃይለ ቃል ነው። ለዚህም ምስክር እንዲሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጥቅሶችን እንዘግባለን።

ሀ) "ወዘጸማእኒ ለይምጻእ ወዘይፈቅድ ለይንሣእ ማየ ሕይወት በከንቱ። " /ራዕ ፳፪:፲፯/ "የተጠማ ይምጣ ለወደደም የሕይወት ውሃ እዲያው ይውሰድ" ማለት ነው። የሻም የወደደም ያለዋጋ ማየ ሕይወትን ይውሰድ የሻ የፈለገ በኔ ይመን ሳይጥር ሳይግር ልጅነትን ያግኝ ማለት ነው።

ለ) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቆሞ ማንም የተጠማ ቢኖር ወደኔ ይምጣና ይጠጣ። በኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ አሰምቶ ተናገረ። ይህን ግን በርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ቅዱስ ተናገረ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ስላልተሰቀለ መንፈስ ቅዱስ ገና አልወረደም ነበርና። /ዮሐ.፯:፴፯-፴፱/ ሁለተኛም "በምድረ በዳ ውኃ በበረሃም ፈሳሽ ይፈልቃልና" የተባለውን በሌላ መልኩ ስናየው መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳን አድሮ ጠበሎችን በበረሃ (በገዳማትና በአድባራት) እንዲፈልቁ በማድረግ ሕሙማንን ከተለያዩ ደዌያት የሚፈውሳቸው መሆኑን የሚያበስር ሲሆን ቅዱሳንም በጠበሉ እያጠመቁ እንደሚያድኑ የሚገልጥ ትንቢት ነው።

ለምሳሌ በኤልሳዕ ጸሎት የሶርያው ቢትወደድ ንዕማን በዮርዳኖስ ተጠምቆ ድኗል። በቤተሳይዳ በፈለቀች ጸበል መልአኩ እየወረደ ስለሚባርከው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ሲያርፍበት ፍልቅልቅ ብሎ ሲፈላ ቀድሞ ገብቶ የሚታጠብ ይፈወስ ነበር። ጌታችንም ይኸንኑ በተግባር ሲያሳይ ዕውር ሆኖ የተወለደውን በምራቁ ለውሶ ጭቃ ከቀባው በኋላ ይኸውም (እምነት) የምንለው ነው በሰሊሆም ውኃ በጸበል ማለት ነው እንዲጠመቅና እንዲፈወስ በማድረጉ ምንም ያዳነው ራሱ ክርስቶስ ቢሆንም ምክንያተ ድኂን የመዳኛ ምክንያት አድርጎ እምነቱንና ጸበሉን አክብሮታል። ወደ ጸበል መሄድ በእምነት መቀባባት የተፈቀደ እንጂ ሃይማኖትን የሚያቃውስ የባዕድ አምልኮ ሥርዓት አለመሆኑን ገልጾልናል። "ትንቢት ይቀድሞ ለነገር" እንደተባለው ስለ ጸበሎች መፍለቅ አስቀድሞ በነቢያት ሲነገር እንደነበር ከላይ የተጠቀሰው የነቢይ ቃል ያስረዳናል። (ነገ ካልዕ. ፭:፲-፲፱ ፤ዮሐ. ፭:፱ ፤ ዮሐ. ፱:፩-፲፪)

፪. <u>ቀዳሚ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ የመፈወስ ሀብት ነበረው</u> :- የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያንን፤ የምዕመናንን አንድነት እንዲመሩ በሕዝበ ክርስቲያን ውስጥ ከተመረጡት ዲያቆናት መካከል አንዱ ሊቀ ዲያቆናት ቅዱስ እስጢፋኖስ ነበር። (የሐ ሥራ. ፮:፩-፯) ቅዱስ እስጢፋኖስ ከተመረጠ በኋላ በአባቶች በሐዋርያት እጅ መጫን (በአንብሮተ እድ) ተባርኮ የዲቁናን ማዕረግ ተቀብሏል። ይኸውም ይህ መንፈሳዊ ሲመት ቤተ ክርስቲያንን ሊቀ አርድእት በመሆን የሚያገለግልበት ሲመተ ዲቁና ነው።

ቅዱስ እስጢፋኖስ የሐዋርያት ሲኖዶስ ላወጣው ቀኖና ሕገ ቤተ ክርስቲያን መስፈርቱን ያሟላ እውነተኛ ክርስቲያን ነበር። ይኸውም በመልካም ሥነ ምግባሩ በውስጥ በአፍአ የተመሰከረለት በሃይማኖቱ፤ በምግባሩ ያልተናወጠ፤ መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላበት እምነተ ጠንካራ ሰው ነበር ማለት ነው። የተመረጠላትን ቤተ ክርስቲያንን የማስተዳደር ተግባሩን በቅንነት ከማከናወን ጋር በተሰጠው የመፈወስ ጸጋና ኃይል ተመልቶ በሕዝብ መካከል ድንቅና ታላቅ ምልክት በማድረግ የክርስትናን እውነትነት የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት አስታውቋል አስመስክሯል። በግብረ ሐዋርያት ፮:፰ "ወእስጢፋኖስሰ ምሉዕ ጸጋ እግዚአብሔር ወኃይል ወይገብር ዓቢየ ተአምረ ወመንክረ በውስተ ሕዝብ" የሚል ኃይለ ቃል እናገኛለን። ትርጉሙም እስጢፋኖስ ግን ጸጋ እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ኃይል ያደረበት ሰው ነበር። በሕዝቡም ዘንድ ደጋግ ተአምራት ያደርግ ነበር። ቅዱስ እስጢፋኖስ ያደረጋቸውን ታላላቅ አስደናቂ ተአምራት ገድሉን በሚናገረ መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል። ከዚያም ውስጥ ለአብነት አንዱን እናቀርባለንና በማስተዋል ተመልከቱ።

ናየስ የሚባል አንድ መሠርይ (አስማተኛ ጠንቋይ) ነ በር። ይኸውም ሙሴን ይቃወሙ እንደነበሩት ኤያኒስና ኢያንበሬስ ተብለው እንደሚጠሩት የግብፅ አስማተኞች ወይም እንደ ሲሞን መሠርይ ያለ ሰው ነበር። (ጢሞ. ካልዕ. ፫:፰፤ የሐ. ሥራ. ፰:፱-፲፩)

ቅዱስ እስጢፋኖስ ዲዳ ደንቆሮ አግኝቶ በልቡናው ጸሎት ካደረገለት በኋላ እንዲፈወስ እፍ ቢለው ዲዳ የነበረው ተናገረ፤ ደንቆሮ የነበረው ሰማ። ሕዝቡም ይኽን ታምር ባዩ ጊዜ ተአምራትስ ይኽ ነው ብለው አድንቀዋል። ከጠንቋዩ ተለይተው የእስጢፋኖስን ሃይማኖት ለመቀበል ተመልሰዋል። ጠንቋዩ ናየስ ግን ሕዝቡ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ማዘንበላቸው አሳስቦት በሰይጣናዊ ተአምራት በአስማቱ ተቃውሞውን ቀጠለ። አንድ በሬ አስመጥቶ ሕዝቡ ሁሉ ሲያየው ወደ ጆሮው ተጠግቶ ሹክ ቢለው በሬው ከሁለት ተከፈለ።



www.ethiopisnorthodox.org

ሚዛን ቢያገቡት ተካክለ የሕዝቡም ልቡና ወደ ነፈሰበት የሚያዘነብል ገና ተጠራጣሪ በመኾኑ ታምራትስ የናዖስ ነው ብለው ተገልብጠው ወደ ጠንቋዩ አዘነበሉ። በዚህን ጊዜ ቅዱስ እስጢፋኖስ ወደ ክርስቶስ ጸሎት አድርሶ በሬውን በተሰጠው ጸጋ አስነስቶ ናዖስን ጠርተህ አምጣው አለው።

በቃል ሰብአዊ በሰው ልሳን በሰው ቋንቋ በሬው ናዖስን ጠርቶ አመጣው ይኸውም የበለዓም አህያ በሰው ቃል እንደገሰጸችው እንደዘለፈችው ያለ ተአምራት ነው (፪ኛ ጴጥ. ፪:፲፭-፲፮) ሕዝቡም እንደ ገበታ ውኃ፣ እንደ መስኖ ወደ እስጢፋኖስ ተቀልብሰው ተመልሰዋል። ይህ ናዖስ ሕዝቡን ሰብስቦ ይህ እስጢፋኖስ የተባለው ሰው ስሕተቴን ሳይገልጥብኝ አልቀረም ብሎ የዕገሌ ሀብቱ ይህ ነው የዕገሌም ሀብቱ ይኸ ነው እያለ ማዕርግ የሰጠ መስሎ አጋንንትን በምስሐብ ጠርቶ ወደ ላይ ይዛችሁኝ ውጡ አላቸው ይዘውት ሲወጡ ከምድር ከፍ ሲል አይቶ ቅዱስ እስጢፋኖስ ቢያማትብባቸው አጋንንት ጥለውት ሸሹ ወርዶ ተንቆጫቁጮ ሙቷል።

የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተሰጠው ሰው ሕሙማንን ከመፈወስ ጋር ሌላም ተአምራት ማድረግ መቻሉን በቅዱስ እስጢፋኖስ ድርጊት ማገናዘብ ይቻላል። ከዚህ ውስጥ ሀብተ ፈውስ የምንለው የዲዳውን መናገር የደንቆሮውን መስማት የመሳሰለው ፈውስ ነው። መንፈስ ቅዱስ የመፈወስን ሀብት ለሰው የሚያድለው ሰዎች ከደዌ ሥጋቸው ብቻ ተፈውሰው እንዲቀሩ ሳይሆን ከነፍሳቸው በሽታም ድነው ፍጹም ድኅነተ ነፍስ እንዲያገኙ ጭምር መኾኑን መገንዘብ ታላቅ ብልኅነት ነው።

፫. <u>ቅዱስ ፊልጶስ ከ፯ቱ ዲያቆናት አንዱ ሀብተ ፈውስ ነበረው</u> :- ቅዱስ ፊልጶስ በመልካም ከተመሰከረላቸው መንፈስ ቅዱስና ጥበብም ከሞላባቸው ከ፯ቱ ዲያቆናት አንዱ ነበር። እርሱም እንደ ቅዱስ እስጢፋኖስ የመፈወስ ሀብት (ጸጋ) ነበረው። ቅዱስ እስጢፋኖስ በሰማዕትነት ካረፈ በኋላ በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ስደት ሆነ። ከሐዋርያት በቀር ሁሉም ወደ ይሁዳ ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ።

ስደተኞቹ ክርስቲያኖች ፳ሺህ ማኅበረ እስጢፋኖስ በየሄዱበት ቃለ ወንጌልን በማሰማት የክርስትናን ሃይማኖት ያስፋፉ ነበር። በዚህን ጊዜ ቅዱስ ፊልጶስ ከኢየሩሳሌም ወደ ሰማርያ ወርዶ ወንጌልን ይሰብክላቸው ጀመር። ከትምህርቱ ጎን ተአምራት ፈውስ ያደርግ ነበር። ሕዝቡም በትምህርቱም በተአምራቱም እየተሳቡ በአንድ ልብ ክርስትናን ለማመን ችለዋል። ቅዱስ ፊልጶስ በተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ብዙ ሽባዎችን አንካሶችን ፈውሷል። ከዚህም የተነሣ በዚያች ከተማ የነበሩ ሰዎች ታላቅ መንፈሳዊ ደስታ አድርገዋል። ይኸም ሁኔታ በግብረ ሐዋርያት ፰:፯ ላይ "ወብዙኃን ፅውሳን ወሐንካሳን የሐይው።" (ብዙ ልምሾ የሆኑ አንካሶችም ይድኑ ነበር።) ተብሎ ተጽፏል።

ይኸ ፊልጶስ በ፴፬ ዓ.ም የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘቧም ሁሉ የሠለጠነውን የኢትዮጵያ ሰው ትንቢተ ኢሳይያስን ተርጉሞላት ተስፋ እንደደረሰ አካላዊ ቃል ወልድ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው እንደኾነ በመስቀል ድኅነተ ዓለምን እንደፈጸመ ሕማሙን፣ ሞቱን፣ ትንሣኤውን፣ ዕርገቱንና ዳግም ምጽአቱን ከመጻሕፍት እየጠቀሰ በማስረዳት አሳምኖ ያጠመቀ የሃይማኖት አባታችን ነው። (የሐ. ሥራ. ፰:፳፮-፵)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እንደሌሎቹ የእምነት ድርጅቶች በቢጽ ሐሳውያን ስብከት የተመሠረተች ሳትሆን በፊቃዱ ያለ ጥርጥር ወንጌልን አምና በሐዋርያት ሃይማኖት በተዋሕዶ ሥርዓት ጸንታ እስከ ዛሬ ተጠብቃ ያለች ሐዋርያዊት ጥንታዊት ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን መኾኗን ዐውቀን እንደ አሸን በየጊዜው በሚነሡ መናፍቃን ልጆቿ ሳንነዋወጽ በሃይማኖታችን ጸንተን ልንኖር ይገባናል። ለዚሁም አጽናኝ መንፈስ ጰራቅሊጦስ በቅዱሳኑ ጸሎት ይርዳን አሜን።

፬. <u>ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በተሰጠው የመፈወስ ጸጋ ብዙዎችን አድኖአል</u> :-

ሀ) ሐዋርያው ለትምህርተ ወንጌል ሲፋጠን ልስጥራን ከተባለች ከተማ ይደርሳል። ከተማይቱም በትንሹ እስያ በሊቃኦንያ አገር የነበረች ናት በዚች ከተማ እግሩ የሰለለ ከእናቱም ማኅፀን ጀምሮ አንካሳ የሆነ ከቶም ሄዶ የማያውቅ አንድ ሰው ተቀምጦ ያገኘዋል። ይህ ሰው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስተምር በተመስጦ ያዳምጥ ነበር ቅዱስ ጳውሎስ ሰውየው ለመዳን እምነት እንዳለው ተገንዝቦ ድምፁን ከፍ አድርጎ በልቡ ከጸለየለት በኋላ ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም አለው። ሽባውም ድኖ ፈውስ አግኝቶ በእግሩ ቀጥ ብሎ ወዲያ ወዲህ ይመላለስ ጀመር። በትምህርተ ወንጌል ጉባኤ የፈውስ ኃይል ተደርጎ እንደነበር ያስገነዝበናል። (የሐ. ሥራ. ፲፬:፰-፲)

ለ) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን በነበረበት ወቅት በተሰጠው የመፈወስ ጸጋ በአማላጅነቱ እግዚአብሔር በእጁ የሚያስገርም ተአምራት ያደርግለት ነበር። ልዩ ልዩ ዓይነት በሽታ የነበረባቸው ሕመምተኞች ሐዋርያው ከለበሰው ጨርቅ ወይም ልብስ ይወስዱላቸው ነበር። ልብሱ ወይም ጨርቁ ሲነካቸው ደዌያቸው ለቆዋቸው ይነሣሉ ተረፈ ደዌ ሳይኖርባቸው ፍጹም ፈውስን ያገኙ ነበር። (የሐዋ. ሥራ. ፲፱:፲፩-፲፪)

ሐ) ቅዱስ ጳውሎስ መላጥያ ከተባለች ደሴት በደኅና ከደረሰ በኋላ የደሴቲቱ አለቃ ፑፕልዮስ ቤት ለእንግዳ ብሎ ለሦስት ቀናት በፍቅር ያሳድረዋል። የፑፕልዮስም አባት በንዳድና በተቅማጥ ታሞ ተኝቶ ነበር።ቅዱስ ጳውሎስም ወደ እርሱ ገብቶ ጸለየለት እጁንም በላዩ ጭኖ ፈወሰው። ይህም በሆነ ጊዜ የቀሩት ደግሞ በደሴቲቱ ደዌ የነበረባቸው እየመጡ ተፈወሱ። በብዙ ክብር ቅዱስ ጳውሎስንና አብረውት የነበሩትን አከበሩዋቸው። ለጉዞ በተነሡም ጊዜ በመርከብ ላይ የሚያስፈልጋቸውን ነገር አኑረውላቸው በፍቅር ተሰናብተዋቸዋል። (የሐ. ሥራ. ፳፰:፯-፲) ይኸ ሁሉ የሚያሳየው ቅዱስ ጳውሎስ በተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ጸሎት አድርጎ እንደፈወሳቸው ነው።

፭. <u>ቅዱስ ጊዮርጊስ የመፈወስ ጸጋ እንደነበረው</u> :- ከገድለ ጊዮርጊስ ገጽ ፵፫ና፵፭ ተመዝግቦ እንደሚነበበው ያንዲት ድሀ አረማዊት ሴት ደንቆሮ ዕውር አንካሳ የነበረውን ልጇን እንዳዳነላት ይተርካል። ከዚህ ቀጥሎ ሙሉ ታሪኩን እንደሚከተለው ጽፈናልና በማስተዋል እንመልከት።

ቅዱስ ጊዮርጊስ በአረማዊቱ መበለት ቤት ታሥሮ ሳለ ሊቀመላእክት ቅዱስ ሚካኤል ከሰማይ



www.ethiopisnorthodox.org

ወርዶ ምግቡን አመጣለት ቅዱስ ጊዮርጊስ ካመጣለት ምግብ ከበላ በኋላ ሰማያዊውን ምግብ ከሴቲቱ መሶብ ላይ አደረገ መሶቡም ነጭ እንጀራ መላበት። ቤቷም ተባረከ፤ መልካሙን ሁሉ ነገር እንደ ንግሥታት ቤት ሞላ። ያች ሴትም ወደ ቤት ገብታ የቅዱስ ጊዮርጊስ ፊቱ እንደ ፀሐይ ሲያበራ በአየች ጊዜ ዳግመኛም እንጀራውንና በቤቷ የመላውን መልካሙን ነገር ሁሉ የአደገውንም እንጨት በአየች ጊዜ ፈራች፤ ደነገጠች፤ ከእግሩም በታች ወደቀች። በልቧም እኔስ የገሊላውያን አምላክ ሰው መስሎ ወደኔ ወደ ምስኪኒቱ ቤት ገብቷል፤ ድህነቴንም አይቶ ረዳኝ እላለሁ አለች፤ ከዚህ በኋላ ፈጥና ጌታዬ ራራልኝ ብላ ከእግሩ በታች ሰገደች፤ ቅዱስ ጊዮርጊስም መልሶ አንቺ ሴት ተነሽ፤ እኔ የርሱ ባርያ ነኝ እንጂ የገሊላውያን አምላክ አይደለሁም አላት። ሴቲቱም መልሳ የአምላክ ባርያ ከሆንክስ እኔ ባርያህም ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ የምነግርህን ስማኝ፤ ጌታዬ በፊትህ አንድ ነገር ልናገር አለችው። ኃያሉ ቅዱስ ጊዮርጊስም በይ ተናገሪ አላት ጌታዬ አራት ዓመት የሆነው ልጅ ዲዳ ደንቆሮ፤ ዕውር አንካሳ ነው ለጎረቤቶቼ እንኳ ላሳየው እፈራለሁ እኔ እሱን ፀንሼ አራት ወር ሆኖኝ አባቱ ሞተ። ከወለድኩት ጀምሮ ማንም እንዲያየው አላደረግሁም። አቤቱ ይቅርታ ታደርግልኝ እንደሆነስ ልጄን ፈውስልኝ፤ እኔ በአምላክህ አምናለሁ አለችው። ቅዱስ ጊዮርጊስም የእግዚአብሔር ቸርነት ዛሬ ይደረግልሽ፤ ሕፃኑን ወደዚህ አምጭው አላት ከዚህ በኋላ ሕፃኑን አምጥታ በቅዱስ ጊዮርጊስ አጠገብ አስቀመጠችው። ቅዱሱም ቸል አላለም፤ ፊቱንም ወደ ምሥራቅ መልሶ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ እንጂ ሕፃኑም በፊቱ ነበር፤ ጸሎቱንም ጨርሶም አሜን ባለ ጊዜ በሕፃኑ ዓይኖች ላይ አማተበ፤ በፊቱም እፍ አለበት። ፍም መስሎ እንደ ድንጋይ ተፈንቅሎ ከዓይኖቹ ላይ ወደቀ። ያን ጊዜም አየ። ሴቲቱም በጆሮው እንዲሰማ፣ እንደበቱም እንዲናገር፣ በእግሩም እንዲሄድ ቸርነትህ ፍጹም ትሁንለት አለችው። ቅዱስ ጊዮርጊስም በዚህ ጊዜ ያገኘው ጸጋ ይበቃዋል፤ እኔ ከአንቺ እርሱን እስከምሻበት ድረስ ጠብቂው እኔ በጠራሁት ጊዜ ይሰማል ይሄዳል ይናገራል። ቃሌን ይፈጽማል ያገለግለኛል አላት። ሴቲቱ ግን ቃል ልትመልስለት አልደፈረችም። የመላከ እግዚአብሔርን ፊት የመሰለ ፊቱን ታይ ነበርና። ቅዱስ ጊዮርጊስ ከእሥር ቤት ወጥቶ ባደባባይ በተገለጠ ጊዜ ሴቲቱ ለፊሊጥ ያደረገው ስላልገባት ሃይማኖቱን የተወ መስሏት ስታዝን ቃሏን ሰምቶ ስለ ሃይማኖቷ ጽናት ደስ አለው።

በፊቷም ፈገግ አለና ልጅሽን ከትከሻሽ አውርደሽ ከምድር አስቀምጭው አላት። ባስቀመጠችውም ጊዜ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሕፃኑን ጠርቶ ዓይንህን በከፈተልህ በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና በእግርህ ቁም ብዬሃለሁና ትዕዛዜን ፈጽም አለው፤ ያን ጊዜም እግሮቹ ረትተውለት ተነሣ ጆሮዎቹም ተከፈቱ፤ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስም መጥቶ እግሮቹን ሳመው። ቅዱስ ጊዮርጊስም በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሕፃኑን አንተ ሕፃን አንተን አዝዤሃለሁ፤ ሂድ ወደ አጵሎን ቤት ግባ የማያውቅ፣ የማያስተውል፣ ዕውር፣ ዲዳና ደንቆሮ አጵሎንን ፈጥነህ ና! የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ ጊዮርጊስ ይጠራሃል በለው አለው፤ያን ጊዜም ሕፃኑ ሄዶ ወደ ጣዖቱም ቤት ገብቶ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንደላከው ተናገረ። ያን ጊዜም በጣዖቱ ላይ ያደረው ሰይጣን ደነገጠ እንግዲህ ከዚህ ማስተዋል የሚኖርብን ነገር ቢኖር ቅዱስ ጊዮርጊስ በተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ሕፃኑን እንዳዳነው ነው።

፲. <u>ኢትዮጵያዊው ጻድቅ የኢቲሳው አቡነ ተክለሃይማኖት በተሰጣቸው የመፈወስ</u>

<u>ጸጋ ስለፈጸሙት አገልግሎት</u> :- በገድለ ተክለሃይማኖት ፻፲፱ና፻፳ የተጻፈውን እንዳለ መስደን ብንመለከት አባታችን በጸሎታቸው እንደተሰጣቸው የመፈወስ ጸጋ ማርያን የተባሉት ጠንቋዮች ማዳን ያልተቻላቸውን የዳሞት ንጉሥ (የወላይታ) መቶሎሚን እንደፈወሱት እናነባለን። ይህን ካለ በኋላ ክቡር አባታችን ተክለሃይማኖትን ወስዶ ከንጉሥ ዘንድ አገባው መቶሎሚም ክቡር አባታችን ተክለሃይማኖትን ባየው ጊዜ አንተ ሰው አድነኝ ቀፈረውድም እንደነገረኝ ኋላ እናደርጋለን አለ።

ክቡር አባታችን ተክለሃይማኖትም እስኪ ቀድሞ ማርያኖችህን አድኑኝ በላቸው። አንተን ማዳን ቢሳናቸው እኔ በፈጣሪዬ ስም አድንሃለሁ አለው። ንጉሡም ማርያንን እናንተ ለምን አታድኑኝም አላቸው። እኔ ስለእናንተ ዘወትር እጣላለሁና ብታድኑን አድኑኝ ባታድኑኝ እናንተን እገድላችኋለሁ አላቸው። ማርያንም ይህ ሰው መድኃኒት አድርጎብሃል እኛ በምን ማዳን ይቻለናል ያንዱ መድኃኒት ካንዱ መድኃኒት፣ ያንዱ ብልሃት ከሌላው ብልሃት ጋር አንድ አይደለምና። ነገር ግን አሁን እንግደለው አስናብተን ፍቀድልን አሉት ገብረ ዋህድም በምንም በምን ልትገድሉት አትችሉም ነገር ግን ንጉሡን አድኑኝ እንዳላችሁ አድኑት አላቸው። ማርያንም መድኃኒታችሁ ከመድኃኒታችን ልዩ ነውና ማዳን አይቻለንም አሉ። ክቡር አባታችን ተክለሃይማኖትም ይህስ ነገር ምክንያት ነው፤ ከሥራችሁ የተነሣ ፍጻሜአችሁ ይታወቃል አላቸው።

እኔ በፈጣሪዬ ስም አድነዋለሁ በእናንተም በእኔም መካከል ነገር እንወስን ንጉሥ እኔን እንደወጋ እናንተንም ይውጋችሁ መውጋት ባይቻለው ጡሩን በእጁ አጣብቆችሁ መከራ ብታጽኑበት እኔ አድነዋለሁ ባላድነው እኔን ይግደለኝ አላቸው። ንጉሡም ይህ ነገር የቀና ነው እንደዚህ ይሁን ነገር ግን ቀድሞ እኔን አድነኝ አለ። ክቡር አባታችን ተክለሃይማኖትም ይህን ታደርግ ዘንድ ማል አለው እንዲያደርግ ማለ ዳግመኛ ንጉሡ አንተም ለራስህ እወቅ ያላዳንከኝ እንደሆን እገድልሃለሁ የተናገርኩትን አላስቀርም አለው። ክቡር አባታችን ተክለሃይማኖትም ግደለኝ እኔ ለራሴ አላዝንም አለው።

ክቡር አባታችን ተክለሃይማኖት በስሙ በማስተምርበት በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከደዌህ ዳን ብሎ ዳሰሰው። ከደዌው ፈጥኖ ዳነ። ሁለቱም ጦሮች ከእጆቹ ተለይተው ወደቁ። የሰለለ ክንዱም ፈጽሞ ዳነ። አዕምሮውም ተመለሰለት። ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ቅዱስ አባታችን በተሰጣቸው የፈውስ ጸጋ ሕመምተኛውን ንጉሥ ባለ ጤና እንዳደረጉት ወይም እንደፈወሱት እናረጋግጣለን። በገድለ ተክለሃይማኖት ገጽ ፻፶፬:፲፬-፲፭ በአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ሳሉ ብዙ ሕሙማንን እንደፈወሱ ተጽፏል።

የተአምራቱም ነገር የትሩፋቱም ወሬ በአማራ አውራጃ ሁሉ ተሰማ ደዌያቸው ልዩ ልዩ የሆነውን ሕመምተኞች ሁሉ እያመጡ ከእግሩ በታች ያኖሯቸው ነበር። ክቡር አባታችንም እጁን በላያቸው እየጫነ ያድናቸው ነበር። የደብሩም መነኮሳት ሥራውን አይተው ያደንቁ ነበር። ያለማቋረጥ በማገልገሉና ድውያንን በመፈወሱ ሥራ ተአምራቱ በበዛባቸው ጊዜ ሥራውን እንደ ተርታ ነገር አደረጉት። የሆነውን ሁሉ ሆኖ ማድነቃቸውን ተውት። አንዱም ለሌላው ልቡ የተቀረቀረበትን ሐሳብ ቢነግረው ያም ደግሞ ከተክለሃይማኖት ዘንድ ሂድ ያዘንክበትን እሱ ይጨርስልሃል ይፈጽምልሃል ይለዋል። ሄዶ ይነግረዋል እሱም የወደዱትን ያደርግላቸዋል። ያዘነውን ያጽናናዋል፣ ድውዩንም ይፈውሳል፤ አሥራ አምስት ድውያን በአንዲት ቀን ይፈወሱ ነበር።ለአብነት ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ ድኅረተ ጻድቃን የመፈወስ ጸጋ የተሰጣቸውን የጥቂቶቹን ተግባር ገልጸናል። እነርሱን የመሳሰሉ በቁጥር የበዙ ቅዱሳን በርካታ ናቸው መንፈስ ቅዱስ ለሰው እንደ ሃይማኖቱ ጽናት እንደ አዕምሮው ስፋት ከሚሰጣቸው ልዩ ልዩ ጸጋዎች መካከል ሀብተ ፈውስ አንዱ መሆኑን በተገለጹት ማስረጃዎች የተወሱ ስለሆነ ግንዛቤ ወስደን የእግዚአብሔርን ስጦታ ልናደንቅ ይገባናል።

ቅዱሳንም በእምነታቸውና በሥነ ምግባራቸው ማግርና ጽናት ለዚህ ጸጋ መታደላቸውን አውቀን ማክበር በጸሎታቸው መታመን የክርስቲያንነታችን መታወቂያ መሆኑን ልንዘነጋ አይገባንም ቸሩ መድኃኒዓለም የቅዱሳን ጸሎት ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ ይፈውሰን ድኅነተ ሥጋ ድኅነተ ነፍስ ይመጽውተን። አሜን

<u>ወስብሐት ለእግዚአብሔር</u>



www.ethiopisnorthodox.org

www.ethiopisnorthodox.org

www.ethiopisnorthodox.org

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

( ከሚራክ ገብረ ክርስቶስ)

መንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ሥላሴ ሦስተኛው አካል መኾኑን ከዚህ ቀደም ስለ መንፈስ ቅዱስ በተሰጠው የሃይማኖት ትምህርት መግለጻችን ይታወሳል ። ጠቅለል ባለ መልኩ በዚህ ርዕስ ሥር የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት በመጠኑም ቢሆን መመልከት ይኖርብናል ።

መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና እንደ ወልድ የራሱ የኾነ ልዩ አካል አለው ። የቅዱሳት መጻሕፍትን ምስክርነት መሠረት በማድረግ ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ከጥንት ጀምሮ ቤተክርስቲያን ስትመሰክር ኖራለች ። ዛሬም ቢሆን ይኸንኑ ከመመስከር ወደኋላ አትልም ።

ከሊቃውንት መካከል አቡሊዲስ ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ሲገልጽ " መንፈስ ቅዱስኒ በአካሉ ወበገጹ ወበመልክኡ ፍጹም ውእቱ " ብሏል ። መንፈስ ቅዱስ የራሱ የኾነ አካል ገጽ መልክ እንዳለው የሚያስረዳ ገጽ ንባብ ነው ።

የመንፈስ ቅዱስ አካሉ የአብንና የወልድን ይመስላል ። መንፈስ ቅዱስ አብና ወልድን በመልክ የሚመስላቸው በባሕርይ የሚስተካከላቸው ነው ።

በሕልውናው ግን በአብና በወልድ የሚኖር ከአብና ከወልድም ተነጥሎ ለብቻው የማይሠራ የባሕርይ አምላክ ነው። ስለኾነም በሕልውና በባሕርይ ከአብና ከወልድ ጋር አንድ ነው ይገናዘባል ።

አረጋዊ መንፈሳዊም የሥላሴን ሕልውና ሲገልጽ በሕልውና መገናዘባቸውን ሲያስረዳ " ከመ ኢይትፈለጡ እምነፍስ ንባብ ወእስትንፋስ ወሕይወት ዚአሃ ከማሁ ኢይትፈለጡ እምአብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" ብሏል ።
ትርጉሙም ፣ከነፍስ ንግግሯና እስትንፋስ እንደማይለይ እንደዚሁ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ አይነጠሉም " ማለት ነው ። ስለኾነም መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ እስትንፋስ በመሆኑ በአብና በወልድ ሕልዋን ሆኖ ይኖራል እንጂ ከአብና ከወልድ ተነጥሎ የኖረበት የሚኖርበት ጊዜና ሁኔታ የለውም ።

መንፈስ ቅዱስ የተለየ አካል የተለየ ስም የተለየ ግብር አለው በተለየ አካሉ ተፈናዊ ( ተላኪ ) በተለየ ስሙ መንፈስ ቅዱስ በተለየ ግብሩ ሠራጺ ይባላል በባሕርዩም ሕያው ማሕየዊ ( አዳኝ ) ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት ይገልጻል። ለምሳሌ በግብረ ሐዋርያት ምዕ. ፲፫ ፡ ፪ ላይ "ወይቤሎሙ መንፈስ ቅዱስ ፍልጥዎሙ ሊተ ለበርናባስ ወለሳውል ለግብር ዘፈቀድክዎሙ አነ " ይላል ።

መንፈስ ቅዱስ ሳውልንና በርናባስን እኔ እነርሱን ለመረጥኩለት ሥራ ለዩልኝ አላቸው ማለት ነው ።

ይኸ አባባል አካል ላለው የሚነገር እንጂ አካልነት ለሌለው ብትን ነገር ዝርው ኃይል ግዑዝ ሕይወት የለሽ ነገር የሚነገር አይደለም ። መንፈስ ቅዱስ እንደ ግዑዝ ፍጥረታት አካል የለሽ ብትን የማይታይ የመንፈስ ክምችት ወይም እንደ ኤሌክትሪክና የመሳሰሉት ነገሮች የሚቆጠር ፈጣን ኃይል ( Active force ) አይደለም አይባልም ።

መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና እንደ ወልድ የተለየ አካል ያለው ሕያው ባሕርይ አዳኝ ጌታ ነው ።

አካል የሌለው ሕይወት አልባ ኃይል ብቻ ቢኾን ኖሮ የመምረጥ ለሥራ የመለየት የማዘዝና የመሳሰሉት ጠባዮች እንዳሉት ባልተነገረለት ነበር ። ከዚህ በላይ ከዚህም ባሻገር መንፈስ ቅዱስ ሁሉን የሚያውቅ የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚገልጽ መኾኑን ሲናገር "ለእኛም እግዚአብሔር በመንፈሱ ገለጠልን ፤ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ባሕርዩን ይግልጣልና በሰው ልቦና ያለውን የሚያውቅ ሰው ማነው ፣ በእሱ ያለችው ነፍሱ ናት እንጂ ፣ እንዲሁም ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር የእግዚአብሔርን አሳብ የሚያውቅ የለም" ፩ኛ ቆሮ ፪ ፡ ፲ - ፲፩ ብሏል ።

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ቢኾንም ምሉዕ በኩለሄ ነው በቦታ አይወሰንም በሁሉ ቦታ አለ ይኖራል ። መዝ ፩፻፴፰ ፡ ፯ - ፲

## ስለ መንፈስ ቅዱስ ጸጋ ወይም ሀብት

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ቢሆንም ቤተክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ልዩ ልዩ ጸጋን ሲያድላት በጸጋው ሲኅብኛት ኖሯል ።

የመንፈስ ቅዱስ አካሉ አንድ ቢሆንም ለቤተክርስቲያን ልጆች ለማኅበረ ምዕመናን እርሱ መንፈስ ቅዱስ በወደደው በፈቀደው መንገድ ሀብቱን ያሳድራል ፤ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ያድላል ።

በዚህ ጽሑፍ ለጊዜው የምንመለከተው በቀዳማዊ ቆሮንቶስ ምዕ ፲፪ የተጠቀሰውን ስለ መንፈስ ቅዱስና ስለስጦታዎቹ የተነገረውን ብቻ ይሆናል ።

የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ማለት መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን የሚሰጠው ስጦታ በምዕመናን ላይ የሚያሳድረው ሀብት ማለት ነው ።

ጸጋ የሚለው ቃል ጸገወ ፣ ሰጠ ካለው ግዕዛዊ ግስ የወጣ ዘር ነው ትርጉሙ በአጭሩ ሀብት መልካም ስጦታ ፣ ስርየት ፣



www.ethiopisnorthodox.org

ይቶርታ ፣ የቸርነት ሥራ አለዋጋ የሚሰጥና የሚደረግ ማለት ነው ።

ለዚሁም ምስክር በመጠኑ "በጸጋ ዘነሣእክሙ በጸጋ ሀቡ ወእመ አኮሰ ጸጋ ኢይከውኒ ጸጋ" ያለውን ጥቅስ ያስረዳል ማቴ ፲ : ፰ ሮሜ ፲፩ . ፮ ፣በልግስና የተቀበላችሁትን በልግስና ስጡ ። ያለዚያስ ጸጋሃ ጸጋ አይባልም፣ ስለዚህ ጸጋ ማለት እግዚአብሔር በርኅራኄው በነጻ ዋጋ ሳይጠይቅ በለጋስነቱ ለፍጥረቱ የሚሰጠው ሀብት ሁሉ ነው መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ ጋር በህልውና አንድ ስለኾነ እግዚአብሔር እንደ መሆኑ ጸጋን ይሰጣል ።

መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያንና ለልጆቿ ( ለህዋሳቷ ለአባላቷ ) እንደ አስፈላጊነቱ በለጋስነቱ ጸጋውን ያድላል ለእያንዳንዱ ምዕመን እንደ ሃይማኖቱ ጽናት እንደ አዕምሮው ስፋት መንፈስ ቅዱስ ሀብቱን ይቸራል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን አባላት ጸጋውን እያካፈለ እንደሚገባ ማደሉን ፲ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ስለ መንፈስ ቅዱስና ስጦታው ለይተው እንዲያውቁና የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው በመልእክቱ በ ፩ኛ ቆሮ ፲፪ በዝርዝር ገልጸላቸዋል::

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቃለሉትን ፍሬ ነገሮች በክፍል በክፍል ለአጠናን እንድሚቀና ሲመደቡ እንደሚከተለው ይዘረዘራሉ::

ሀ) ስለ መንፈስ ቅዱስ በአጠቃላይ እንዲገነዘቡ ።
፩ኛ ቆሮ ፲፪ : ፩ - ፫

ለ) ከመንፈስ ቅዱስ ስለሚገኘው ሀብት ።
፲፪ : ፬ - ፲፩

ሐ) ስለቤተክርስቲያንና ሕዋሳቷ (አባሎቿ) ፲፪ : ፲፪ - ፳፯

መ) ስለቤተክርስቲያን ማዕረግ::
፲፪ : ፳፰ - ፴

ሠ) ስለ ፍቅርና ትሕትና ።
፲፪ : ፴፩

በ ፩ኛ ቆሮ ፲፪: ፩ ላይ የአማርኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላይ ንባቡ 'ስለመንፈሳዊ ነገርም ወንድሞች ሆይ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ'' ይላል በግዕዙ ግን ''ወበእንተ ዘመንፈስ ቅዱስ ኢንፈቅድ አኃዊነ ትኩኑ አብዳነ'' በማለት ያነበዋል ። ቃል በቃል ፍቹ በሊቃውንት ጉባዔ በተዘጋጀው ሐዲስ ኪዳን'' ወንድሞቻችን ስለ መንፈስ ቅዱስ በምታስቡትም ዐላዋቆች ልትሆኑ አንወድም እንድታውቁ እንጂ'' ተብሎ ተተርጉሞአል ።

የመንፈሳዊ ነገር ምንጩ መገኛው መንፈስ ቅዱስ በመኾኑ ፍሬውን ከማወቅ በቅድሚያ ግንዱን መገንዘብ ይሻላል ። በግንድ የተመሰለው መንፈስ ቅዱስን ማወቅ ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን ወይም የሚገኘውን መንፈሳዊ ነገር ከማወቅ ይቀድማልም ይበልጣልም ስለሆነም የግዕዙን ንባብ ለትንታኔያችን ተጠቅመንበታል::

በዚህ ምዕራፍ ሐዋርያው ሊያስገነዝበን የፈለገው የቆሮንቶስ ምዕመናን በጥምቀት በሚሮን (በእንብሮተ ዕድ) ዳግመኛ በመንፈሳዊ ልደት ተወልደው መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸው ሳለ አላደረብንም በማለታቸው ይኸን ጥርጥራቸውን እንዲተው ሊያሳውቃቸው ወዶ ይጽፍላቸዋል ። አላደረብንም ብለው ለጥርጥር የበቁቱም ገቢረ ተአምራት ወመንክራት (ተአምራት የመሥራት ድንቅ ነገር የማድረግ) ስላልተሰጣቸው ነው ። የቆሮንቶስ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ቢያድርብን ኑሮማ እንደሌሎች ድንቅ ድንቅ ተአምራትን እናደርግ አልነበረምን ይኸ የኾነው እኮ መንፈስ ቅዱስ ባያድርብን ነው ብለው ተሳስቱ ። ይኸን ስሕተታቸውን ለማረም ቅዱስ ጳውሎስ ማረጋገጫ ይሰጣቸዋል ። በ ቁ ፪ ላይ ሐዋርያው የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን በሃይማኖት የልጅነት ሀብት ሳይሰጣቸው በፊት በአረማዊነት ሳሉ ጣዖት የሚያመልኩ ጣዖት የሚቀርጹ ለአምልኮተ ጣዖት አስተዋጽኦ በማውጣት እንደነበሩ ያስታውሳቸዋል ። በቁጥር ፫ ላይ ክርስቶስን በማመን መንፈስ ቅዱስ ካደረባቸው በኋላ ግን የቀድሞ የአረማዊነት ግብራቸውን እርግፍ አድርገው ትተው የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት (ጌትነት ) ተገንዝበው እርሱን ፍጡር ከሚሉ ቢጽ ሐሳውያን ተለይተው ክርስቲያን መኾናቸው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መኾኑን እንዲያስተውሉ ያስገነዝባቸዋል ። ስለዚም መንፈስ ቅዱስ አላደረብንም ማለታቸውን ይተው ከተአምራት ድንቅ ሥራ የበለጠ ክርስቶስን ለማመን በቅተዋል ። የክርስቶስን ጌትነት ዐውቆ እርሱን ማምለክ መንፈስ ቅዱስ ባያድርባቸው ኑሮ የማይሞከር ነበር ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸዋልና ጥርጥራቸውን ይተው ፲ መንፈስ ቅዱስ የማደሩ ምልክት ክርስቶስ በተዋሕዶ ሰውነቱ ከመለኮቱ መለኮቱ ከሰውነቱ ሳይለይ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ስለኾነ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በጌትነት አንድ ነውና ይኸን የቀና ሃይማኖት ክርስቶስ በተዋሕዶ ከብሮ የባሕርይ አምላክ መኾኑን የገለጸላቸው መንፈስ ቅዱስ ነው ቢያድርባቸው እንዲህ አድርገው ለማመን በቁ ፣ ስለሆነም ተአምራት የማድረግ ጸጋ አልተሰጠንም ብለው መንፈስ ቅዱስ አላደረብንም አይበሉ ዛሬም እኮ የብዙ ክርስቲያኖች ችግር ይኸው ነው ። ተአምራት ማድረግን ፣ ምልክትን ከሃይማኖት አስበልጠው ያያሉ ምልክቶችና ተአምራት ሲፈልጉ በሃይማኖት መሠረትነት የተሰጣቸውን ክርስቲያን የመሆን ጸጋ ይኸውም የሥላሴ የጸጋ ልጆች መባልን እንደቀላል ነገር ይቆጥሩታል ። ስለዚህም የሐዋርያው መልእክት ዛሬም ላለነው በእንዲህ ዓይነቱ ጥርጥር አላዋቂነት እንዳንያዝ ያስገነዝበናል ። የቆሮንቶስ ምዕመናን ስሕተታቸው ከላይ የተጠቀሰው ብቻ አልነበረም ። ሌላም ስህተት ነበራቸው'' ይኸውም የመንፈስ ቅዱስ አካሉ እንደ ሀብቱ ( ጸጋው ) ብዛት እንደዚያው ብዙ ነው ይሉ ነበር'' ይኸ ታላቅ ስህተት መኾኑን ሐዋርያው ይገልጽላቸዋል በቁ ፬ ላይ'' ወመክፈልታተ ሱታፌ ሀብት ህልው እንዘ አሐዱ መንፈስ'' ይላል ። '' መንፈስ ቅዱስ አንድ ሲሆን የሀብት እድል እድል አለ ወይም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ የማድረግ ሀብት ዕድል ዕድል አለ ይላል በአማርኛውም የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው ።''' ይላል



www.ethiopisnorthodox.org

## ዓምደ ሃይማኖት

የመንፈስ ቅዱስ ሀብት ፣ ጸጋ ስጦታዎቹ በርካታ ናቸው ። ለእያንዳንዱ እንደ እድል እንደ እድሉ መንፈስ ቅዱስ ያከፋፍላል ጸጋውን እየመጠነ እንደ አስፈላጊነቱ ለምዕመናን የሚያድለው መንፈስ ቅዱስ አካሉ ብዙ ነው ማለት ስህተት ነው ብዙ መንፈስ ቅዱሶች የሉም ። የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች ግን ብዙዎች ናቸው ። ልዩ ልዩ ጸጋዎች ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ቢኖሩም በስጦታዎቹ ልክ የመንፈስ ቅዱስ አካሉ ብዙ ነው ወይም ብዙ መንፈስ ቅዱሶች አሉ ማለት ታላቅ ስህተት ነው ። ይኸን ዐውቀው ከስህተታቸው እንዲታረሙ ሐዋርያው ይመክራቸዋል ። ዛሬስ እንዴት ነው ብዙ መንፈስ ቅዱሶች ያሉ ይመስል አንዳንድ ስጦታ ያለን ክርስቲያኖች በተሰጡን ስጦታዎች ልክ መንፈስ ቅዱስ አካሉ የሚሸንሽን ይመስል የቤተክርስቲያንን አንድነት በአንድ መንፈስ አጋኝነት ፣ የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ በመፈጸም በመጠበቅ ፈንታ ስንለያይ እንገኛለን ። በዚህ ድርጊታችን ወደ ክርስቲያንነት እንዳይገቡ ለኢጥሙቃን ለአሕዛብ በር ዘግተናል ። በዚህ ግብራችን እንዳንወቀስ እኛም በአንዲት ቤተክርስቲያን እድሮ ጸጋውን የሚያድለው እውነተኛውን የቀናውን የተዋሕዶ ሃይማኖት የገለጸው መንፈስ ቅዱስ አንድ መኾኑን አውቀን በመቀናናትም በሥጋዊ ስሜትም ተነሳቁረን ከመለያየት እንጠበቅ ፣ ወደ ቤተክርስቲያን ለሚመጡ እንቅፋት እንሁን የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎቹ ብዙ ቢኾኑም ያንን ሁሉ ጸጋ ያደለ የቸረ መንፈስ ቅዱስ አካሉ አንድ መኾኑን አውቀን ሁላችንም በየተሰጠን ጸጋ በአንድ ሃይማኖት ጸንተን በአንድ መንፈስ ተመርተን አንድነታችንን እናጽና ያደረብንን መንፈስ ቅዱስ በጥላቻ እየተለያየን በጥርጥራችን በግብዝ ነታችን አናሳዝነው ።

በቁጥር ፬ ላይ" <u>ወመክፈልታተ ምግባር ሀለው እንዘ አሐዱ እግዚአብሔር ዘይገብር ኩሉ ውስተኩሉ" ። ይላል"</u> <u>በኹሉ ስፍራ ኹሉን የሚሠራ እግዚአብሔር አንድ ቢኾን የሥራ እድል እድል አለው</u> "ይላል ። በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ንባቡ በቁጥር ፭ እና ፮ ላይ " <u>አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው። ጌታም አንድ ነው ። አሠራርም ልዩ ልዩ ነው ፣ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው"</u> ይላል ። አገልግሎትም ወይም አሠራር የሚለው ተመሳሳይ ነው ። ለአጠይቆ ሠለስቱ አካላት <u>መንፈስ አንድ ነው ። ጌታ አንድ ነው እግዚአብሔር አንድ ነው ቢል</u> ጸጋን በማደል መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በህልውና ፣ በጌትነት አንድ መኾኑን የሚያመለክት ስለኾነ ምሥጢረ ሥላሴን ያስገነዝበናል ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታው በሁለት ክፍል ሊመደብ ይችላል አንዱ <u>መክፈልታተ ሱታፌ ሀብት</u> ሲኾን ሁለተኛው <u>መክፈልታተ ምግባር ነው ።</u>

በቁጥር ፬ ላይ ስለ መክፈልታተ ሱታፌ ሀብት ሲገልጽ በቁጥር ፭ ላይ ደግሞ ስለ መክፈልታተ ምግባር ያሳያል ። አንዱ መንፈስ ቅዱስ ለምዕመናን የሚያድለው ጸጋው በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ተመድቦ ለቤተክርስቲያን ሲሰጥ ይኖራል ። የሀብት እድል (መክፈልታተ ሱታፌ ሀብት ) የሥራ ዕድል መክፈልታተ ምግባር ) ተብሏል ። ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችን ለምዕመናን ሀብቱን የሚያድል ለምግባር ለትሩፋት እንዲነቃቁ ገድል የመሥራት ኃይል ይኸውም የሥራን ዕድል የሚሰጣቸው የሚመራቸው ኃይል የሚሆናቸው መንፈስ ቅዱስ በተለየ አካሉ አንድ ሲሆን ከአብና ከክርስቶስ ጋር በህልውና ስለሚገናዘብ በጌትነት በሥልጣን አንድ ነው ። ስለኾነም መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ኃይል ምንጭ ሆኖ ቤተክርስቲያንን ሲያጽናናት ሲያበረታታት ሲያረጋጋት ሲመራት ይኖራል ።

ሐዋርያው መንፈስ ቅዱስ አካሉ አንድ ሲኾን ለቤተክርስቲያን አባላት ለምዕመናን ጸጋውን በክፍል በክፍል እያደረገ እንዴት እንደሰጠና የጸጋ ዓይነቶቹ ምንና ምን እንደኾኑ ለቆሮንቶስ ምዕመናን ከቁጥር ፯ እስከ ፲፩ ድረስ በሰፊው ይገልጽላቸዋል ።

በቁጥር ፯ እና ፲፩ ላይ " እስመ ለለአሐዱ ዘዘዚአሁ ጸጋሁ በመንፈስ ቅዱስ ወበኵሉ በበመክፈልቱ እንዘ እግዚእ ይረድእ ወለለአሐዱ ይሁቦ ግህደ በከመ ይድልዎ ወይበቁዖ " ይላል ። ትርጉሙም እነሆ ያንዱም ያንዱም መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ልዩ ነውና ለሁሉም ጌታ እያገዘ በየእድል በየእድሉ ይሰጠዋልና ።

መንፈስ ቅዱስ በአካሉ አንድ መኾኑን ሀብቱ (ጸጋው) ግን ብዙ መሆኑን ሐዋርያው ካስረዳ በኋላ ለምዕመናን እንደ የዕድላቸው መንፈስ ቅዱስ ባወቀ ለጥቅማቸው የሚሰጣቸው ጸጋ ግን አንድ ዓይነት አለመሆኑን እንዲያውቁ በመጠኑ የመንፈስ ቅዱስን ሀብታት (የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች ) ይዘረዝርላቸዋል ። <u>መንፈስ ቅዱስ ጸጋውን ለምዕመናን የሚያድለው ለምዕመናኑ እንደፍላጎታቸው ሳይሆን እሱ መንፈስ ቅዱስ ባወቀው ጥበብ ለእያንዳንዳቸው እንደሚጠቅማቸው እንደአስፈላጊነቱ ለጥቅማቸው ይሰጣቸዋል ። ለአንድ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ሀብት የሚሰጠው እንደ ሃይማኖቱ ጽናት እንደ አዕምሮው ስፋት ነውና የሚገባውን የሚጠቅመውን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ባደለው ጊዜ ተመስገን ብሎ መቀበል እንጂ ያልተሰጠውን ጸጋ መሻት ፣የተሰጠውን ጸጋ ማኮሰስ እንደ ኢምንት ቀላል አድርጎ መቁጠር ወይም በሌሎች ጸጋ መቅናት መመቅኘት የተሰጠውን ጸጋ ከማጣት ስለሚያደርሰው ይጠንቀቅ።</u> የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ያልተሰጣቸውን ጸጋ በመሻት ይልቁንም በቋንቋ ( በልሳን ) የመናገርን ነገር አብልጠው አግነው በመገኘታቸው እነርሱ እንደፈለጉት ሀብት መንፈስ ቅዱስ ሊታደላቸው የማይቻል መሆኑን ይገልጽላቸዋል። መንፈስ ቅዱስ ራሱ ለማን ምን ዓይነት ጸጋ መስጠት እንዳለበት ያውቃል ስጦታው በታደለ ጊዜ አሜን ብሎ መቀበል እንጂ -ታእምራት ድንቅ ምልክት ለምን አላደርግም ፣ በቋንቋ ለምን ሳልናገር ቀረሁ ብሎ ያልተሰጠውን ሀብት መፈለግ ጤናማ ሕይወት አለመ ኾኑን በቆሮንቶስ ያሉት ምዕመናን እንዲገነዘቡ ሐዋርያው አሳስቧቸዋል ። መስክሮላቸዋል ።

www.ethiopisnorthodox.org

## ዓምደ ሃይማኖት

እኛስ የዘመኑ ክርስቲያኖች ያልተሰጠንን ጸጋ በመሻት፣ በሌሎች ጸጋ እንቀና ይሆንል በአንዱ የጸጋ ስጦታ ሌላውን እናስበልጥ ይሆንል የተሰጠንን ጸጋ ባለማወቅ መንፈስ ቅዱስ ሀብተ ሃይማኖትን ሀብተ ልደትን አድሎን በክርስቶስ ክርስቲያን ተሰኝተን ሳለ ገቢረ ተአምራት ወመንክራት ሌላም ሌላም ሀብት ( ጸጋ ) ስላልተሰጠን እናማርር ይሆንል እንጠንቀቅ፤ እነዚያ ያልተሰጣቸውን በመሻታቸው እንደተገሰጹ እኛም እንደነሱ እንዳናት ያልተሰጠንን ጸጋ እንፈልግ ። በሌሎች ጸጋ አንቅና ። በተሰጠን ጸጋ ጸንተን እንኑር ። መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን ጸጋ ካለም በተሰጠን ጸጋ እያመሰገንን ቤተክርስቲያንን እናገልግል እንጂ በተሰጠን ሀብት እንኩራራ ። አዳምና ሔዋን ከገነት ሊወጡ የልጅነት ጸጋ ሊያጡ የቻሉት ያልተሰጣቸውን ጸጋ በመፈለግ መኾኑን እናስተውል ። አበው ሲተርቱም የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች ይባላል ። የሌላውን ስንሻ የራሳችንን እንዳናስወስድ እናስብበትና እንመክር እንገሰጽ እንጂ እንሳሳት ።

ከቁጥር ፰ እስከ ፲፪ ለምዕመናን መንፈስ ቅዱስ የሰጣቸውን የጸጋ ዓይነቶች በዝርዝር ያስረዳል እነርሱም እንደሚከተሉት ተዘርዝረዋል ።

ሀ)ጥበብን የመናገር ሀብት፤
ለ)ዕውቀትን የመናገር ስጦታ፤
ሐ)የእምነት ወይም የማመን ሀብት
መ)ድውይ የመፈወስ ሀብት (ሀብተ ፈውስ) ።
ሠ)ኃይን የማውጣት ሀብት ፤
ረ)የረድኤት ስጦታ( የመርዳት በዚያውም ኃይል የማድረግ )
ሰ)ሀብተ ትንቢት ( መጻያትን የማወቅ ሀብት )
ሸ)ትርጓሜ የማወቅ ሀብት ፤
ቀ)ቋንቋ የማወቅ ሀብት ፤

በዝርዝር የሰፈሩትን የጸጋ ዓይነቶች እንደሚከተለው እናብራራለን ። የጸጋ ዓይነቶች ሙሉ በሙሉ መተንተን በዚህች አነስተኛ ጽሑፍ ባይቻልም አጠቃላይ ይዘቱን ለማወቅና በጥቂቱም ቢሆን ለመገንዘብ ማብራራቱ ይጠቅማልና በማስተዋል እናጢነው መንፈስ ቅዱስም ለሁላችንም ምሥጢሩን ይግለጽልን ። አሜን ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።
(ይቀጥላል)

## የምክር ስንቅ

ወዳጄ ክርስቲያን ሆይ መንፈሳዊ ሕይወትህ አደጋ እንዳይገጥመው ራስህን መግዛት አትተው በዘመኑ የሥልጣኔ ጥበብ ሰው በቴክኒዎሎጂ ዕውቀቱ በጥቂትም ቢሆን አፍአዊ ነገሮችን መቆጣጠር ችሏል። እጅግ ውስብስብ የሆነውን ሰብአዊ ተፈጥሮውን ግን ለመግራት ገና አልቻለም ። በዕውቀት በኩል በባይንሳዊ ጉዞው የትየለሌ ደርሷል ። መንፈሳዊነቱ ፣ የግብረ ገብነቱና የሞራሉ ሁኔታ ግን እያደር የቁልቁለት መንገዱን ብቻ ሆኗል። እኛ ራሱንና ሌላውን ወገኑን በማታለል በመሆኑ ሕይወቱ በማብዛት ፤ ደስታው በማጭበርበር ላይ የተመሠረተ ሆኗል። በሚቀራረቡ የትዳር ጓደኞች መካከል እንኳን የሚታየው አለመግባባት ፤ የባልና ሚስት ፍቺ መናር ከዚሁ የመንፈሳዊነት ማሽቆልቆል ፣ ከሞራል ውድቀት የተነሣ በተፈጠረ ሰበብ ነው። ዓለማችን በሥጋዊ መንገድ የሰለጠነች በትመስል በመንፈሳዊ ሕይወቷ ግን ከእንስሳት በታች በመኾን እጅጉን ወደኋላ ቀርታለች። ሮሜ ፩ ፣ ፳፪ -፴፪ አንተ ሆይ የዚህ ውጤቱ አደገኛ መኾኑን ተገንዝበኸው ታውቃለህን ? ወንድሜ ምዕመን ሆይ ኑሮ ዋዛ አይምሰልህ !! ሰው ሆነህ መፈጠርህ ከዚያም በላይ ክርስቲያን የመኾንን ፀጋ መቀመስህ ለከንቱ አይሁን ። ጸጋህ እንዳይገፈፍ ሰው ነህን ለቱድቢና ሕይወት ራስህን አስገዛ ፤ እንስሳዊ ፈቃድም ሠልጥኖ መሪ እንደሌለው መርከብ በምኞት ባሕር ላይ ተንሳፋፊ አትሁን ። ወይም ፍሬን እንደሌለው መኪና ጭልጥ ብለህ በሥጋዊ ምኞትህ ጎዳና አትሽምጥጥ ፤ አትከንፍ ። በተሰጠህ ሕሊና በወንጌል ምክር ራስህን የምትመራ የምትቆጣጠር ሁን ። እንዲህ የኾንክ እንደኾነ ሕይወትህ የተወደደ ለመንግሥተ ሰማይ የበቃ ይሆናል ።

በሰውነትህ ውስጥ ክፉ ምኞቶችና መጥፎ አስተሳሰቦች ሊኖሩ ይችላሉ ። እነዚህ ክስተቶች ሕይወትህን ፍሬ አልባ የሚያደርጉ አረሞች ስለኾኑ በፍጥነት በንስሐ ሊወገዱ ይገባል ። ችላ ብለኸ ግን የገዛ ምኞትህ መሰናክል ሆኖ ልጓም እንደሌለው ፈረስ ከሞት አዘቅት ላይ ገልብጦ ይጥልሃል ።

ክፉ ምኞት የሰይጣን መግቢያ በር ነው ። ይኸንን የሞት በር በንስሐ ካልዘጋኸው በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ካልቆለፍከው ከጥፋት መዳን አትችልም ። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የፈተናውን ምንጭ ይነግርሃል ። መድኃኒቱንም ሳይጠቁምህ አላለፈ አያውቅም ። ጥቂት የክፋት እርሾ በሊጥ የተመሰለ ክርስቲያናዊ ግብረተሰብን በመከራ ይሰውጠዋልና፤ ኑሮውን ይመረረ የጎመዘዘ ያደርገዋል ። ከክፉ እርሾ ተጠበቅ ። ምኞትህን ተቆጣጠር ወደ ፈተና ደጅ ገብተህ መውጫው እንዳይጠብህ ለሥጋዊ ፍላጎትህ ገደብ አብጅለት ። ወዳጄ ሆይ ! የሞት ጎዳና ክፉ ምኞት ከምን መንጭቶ ከምን እንደሚያደርስ ቅዱስ ያዕቆብ ይመክርሃል ስማው "እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች ።" ያዕ. ፩ ፡ ፲፬ - ፲፭

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.ethiopisnorthodox.org

## ዓምደ ሃይማኖት

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

ካለፈው የቀጠለ

በኢትዮጵያ የፋሲል መንግሥት ሲደላደል በእጨጌ በትረ ጊዮርጊስ መሪነት ከካቶሊካዊው አልፎንሱ ሜንዴዝ ጋር ለመከራከር የተዋሕዶ ሊቃውንት ፈቃድ ጠየቁ ፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ በጎንደር ጉባኤ ተደረገ የተዋሕዶዎቹ አፈጉባኤ እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ነበሩ። አልፎንሱ ሜንዴዝም ከወገኖቹ ጋር ሁኖ ለክርክር ቀረቡ ጥያቄውን የጀመረው ራሱ አልፎንሱ ሜንዴዝ ነው። የመጀመሪያው ጥያቄ እንዲህ የሚል ነበር።

<u>ጥያቄ</u> አልፎንሱ ሜንዴዝ የአብ የባሕርይ ልጅ ሞተ የሚለው ገጸ ንባብ ከምን ይገኛል ?

<u>መልስ</u> እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ፣ ጠላቶቹ ስንሆን እግዚአብሔር በልጁ ሞት አዳነን ይልብሀል (ጳውሎስ ሮሜ ፭ ፡ ፲ ) መልሱ ትክክለኛ ስለሆነ አላከራከረም ።

<u>ጥያቄ</u> አልፎንሱ ሜንዴዝ ፣ የእግዚአብሔር ፊቱ ወዴት ነው ?

<u>መልስ</u> እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ በዚህ ጊዜ መብራት አስበርተው በጉባኤው መካከል አድርገው የዚህ መብራት ፊቱ ወዴት ነው ብለው ጠየቁት ይባላል እርሱ ግን መልስ አልሰጠም። መልሱን ራሳቸው መለሱ፣ የዚህ መብራት ገፅ በዚህ በኩል ብቻ ነው እንደማይባል እግዚአብሔርም በዓለም ሁሉ ምሉዕ ነው አሉት ። ይልቁንም የእግዚአብሔር ፊት በክፉ አድራጊዎች ዘንድ ነው መዝ ፴፫ ፡ ፲፮ የሚለውን የዳዊት መዝሙር በመጥቀስ አልፎንሱ በጓደኞቻቸው ላይ ያደረሰው ግፍ እናዶአቸው ስለነበር ፊቱን በጥፊ አሉት ይባላል ። በዚህ ጊዜ የጎንደር ሊቅ

*"ረከብናሁ ለበትር ዘያደክማ ለሮሜ ጽሩብ በንባብ ወቅሩጸ በትርጓሜ"*

ብሎ ደስታውን በቅኔ ገለጠ ይባላል።

(የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአባ ጎርጎርዮስ ገፅ ፷፪ ና ፷፫ )

መንፈስ ቅዱስ እፍና ጥበብ የሆናቸው መምህራን በሰይጣን ትምህርት ልባቸው ባነቃው ጥርጥር የመጽሐፍትን ቃል የሚጠመዝዙ ቢጽ ሐሳውያንን ምላሽ ያሳጧቸዋል ትምህርት ብቻውን አይጠቅምም መንፈስ ቅዱስ የጥበብን ቃል ሲሰጥ በማንኛውም ጉባኤ የሃይማኖት ጠበቃ አፍሮ የማይመለስ የወንጌል ምስክር ለመሆን ይበቃል።

<u>፭ኛ. የአስተዳደር ፈሊጥ</u> ሕልምና ራዕይ የመተርጎም ጥበብ ይህ ጥበብ ከተሰጣቸው ሰዎች መካከል ከቀደሙ አበው ዮሴፍ ወልደ ያዕቆብን ከኋላ ሰዎች ከአበይት .ነቢያት አንዱ የነበረውን ዳንኤልን መጥቀስ ይቻላል። ሁለቱም በዘመናት ቢለያዩም ተመሳሳይ ጠባይና ማስተዋል ይንጸባረቅባቸዋል ። ሁለቱም እግዚአብሔርን በመፍራት ከሕጉ እንዳይዛነፉ ከአምልኮቱ እንዳይወጡ በማንኛውም አካባቢና ሁኔታ ከልብ የሚያመልኩ አማኞች እንደነበሩ ስለ ሁለቱም የሚናገረውን የሕይወት ታሪክ ዜና ገድል በማጥናት ማወቅ ይቻላል።

ሀ) <u>ዮሴፍ ወልደ ያዕቆብ</u> እስራኤል ተብሎ ለተጠራው ለያዕቆብ አሥራ አንደኛ ለራሔል የበኩር ልጅ ነው። (ዘፍ ፴ ፡ ፳፪ - ፳፬ ) ከጠባዩ መልካምነትና ከዝናው ከፈጸመውም ትልቅ ሥራ የተነሳ ከያዕቆብ ልጆች ሁሉ የተከበረ ሆነ በተለይ አባቱ ይወደው ነበር። ሕልሞችን ስለአለመና ስለ ሌላም ነገር ማለት በአባቱ ዘንድ ይበልጥ በመፈቀሩ ወንድሞቹ ጠልተው ተመቅኝተው ሸጡት ። (ዘፍጥ ፴፯) በግብጽ ባርያ ሆኖ ሳለ በጲጥፋራ ቤት ለአስተዳዳሪነት ተሾመ ። የጲጥፋራ ሚስት በሐሰት ስለከሰሰችው ያለ ወንጀሉ በግዞት ታሰረ። እዚያም ሞገስን አግኝቶ የአስተዳደር ፈሊጥ አዋቂ ጥበበኛ ሰው መሆኑ በግብጽ ስለተገለጸ ከግዞት ቤት አለቃ (ከወህኒ ቤት አዛዥ) በታች ኀላፊ ሆነ። (ዘፍ ፴፱)

ሕልሞችን የመተርጎም ጥበብ ስለተሰጠውና እርሱ እንደፈታው ሆኖ በመገኘቱ በዚህ ችሎታው ፈርዖን ከእስር ፈታው። በግብጽ ምድር ሁሉ ላይ አለቃ አስተዳዳሪ አድርጎ ሾመው ። (ዘፍ ፵) በተሰጠው የማስተዳደር ፈሊጥ በጥበብ እየተጠቀመ ለሰባት ዓመት እህልን እያሰባሰበ በረሀብ ዘመን ብዙ ሰዎችን የገዛ ቤተሰቡን ጭምር ከሞት አዳነ። (ዘፍጥ ፵፩፡ ፵፭ ፣ ፵፯ ፡፲፫ -፳፯ )

ለ) <u>ነቢዩ ዳንኤል</u> በይሁዳ አገር ከንጉሣዊ ወይም ከመሳፍንት ወገን የተወለደ ነው። በናቡከደነጾር ዘመን በምርኮ በ፮፻፭ ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ባቢሎን ተወስዶ በዚያ ሳለ ስሙ ብልጣሶር ተባለ ። የከለዳውያንንም ትምህርትና ቋንቋ ተማረ (ዳን ፩ ፡ ፩- ፯) ዳንኤል እግዚአብሔርን አልረሳምና እንዳይረክስ በልቡ አሰበ እንዳሰበውም የላመ የጣመ ሳይቀምስ ጥሬ በመቆርጠም ፣ ውሃ በመጠጣት ፣ በጾም ፤በጸሎት ፤ከአሕዛባዊ አኗኗር ልዩ መሆኑን አሳወቀ። እንዳሰበውም ሆነለት። (ዳን ፩ ፡ ፰ -፲፯ ) ተምሮም በባቢሎን ተሾመ (ዳን ፩ ፡ ፲፯ - ፳፩ ) ዳንኤል እስከ ፭፻፴፯ ከክርስቶስ ልደት በፊት ናቡከደነጾርን ፤ ብልጣሶርን ፤ ዳርዮስንና ቂሮስንም በማስተማር ሕልምን በመፍቷት ጽሑፍንም በመተረጎም አገለገለ። በአስተዳደር ችሎታውና በተሰጠው ልዩ ሕልምና ራዕይ የመተርጎም ጥበቡ የተደነቀ ነበር።

ለእግዚአብሔርም ሕዝብ እየጸለየ ብዙ ራዕይ ለማየት በቅቷል።

ዳንኤል ጣዖት ባለማምለኩ በአንበሳ ጉድጓድ ተጣለ። እግዚአብሔር ግን አዳነው። ዳንኤል በመልካም አካሄዱ በመንፈሳዊነቱ የታወቀ ነበር (ሕዝ ፲፬



www.ethiopisnorthodox.org

: ፲፬ - ፳ ) የነቢዩ ዳንኤል መንፈሳዊ ጥበብ ሕልም የመተርጎምና የተሰወረውን ምሥጢር ፈልፍሎ በእግዚአብሔር ፀጋ በመታገዝ የማግኘት ስጦታው አስደናቂ ነበር። በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ፪ : ፩ - ፵፱ ያለውን ክፍል ብንመለከት የዳንኤልን ታላቅነት መረዳት እንችላለን ንጉሡ ናቡከደነጾር ሕልም አይቶ ሕልሙ ጠፋበት የጠፋውን ሕልምና ትርጉሙን ጭምር እንዲያስታውቁት በጊዜው በነበረው ዓለማዊና ስይማናዊ ጥበብ ሰልጥነው አለን አለን ይሉ የነበሩትን ቢጠይቃቸው ሕልሙን ካልነገርከን አሉት ። ሕልሙ ጠፍቶኛል ፈጠራ ነግራችሁ እንዳታታልሉኝ በልቤ ይወጣል ይወርዳል ። ከነገራችሁኝ ትሾማላችሁ ትሸለማላችሁ የማትነግሩኝ ከሆነ ግን ከምድረ ገጽ አጠፋችኋለሁ አላቸው።

ሳይቻላቸው ቀረ እንዲሰየፉ ትዕዛዝ ተላለፈ ። ነቢዩ ዳንኤል መንፈሳዊ ቢሆንም ለጊዜው ቁጥሩ ከጠቢባን ነበርና አዛዡን ቀን እንዲሰጠው ጠየቀ። ወደ እግዚአብሔር አመልክቶ ንጉሥ ያየው ሕልም ከነትርጓሜው ተገለጠለት በወርቅ ከተመሰለው የባቢሎን መንግሥት ቀጥሎ በብር የተመሰለው የፋርስ መንግሥት እንደሚመጣ ከእርሱም ቀጥሎ በናስ የተመሰለው የግሪክ መንግሥት ፤ ከዚያም በኋላ በመብራት የተመሰለው የሮም መንግሥት በመጨረሻም የሮም መንግሥት ተከፋፍሎ እኩሉ እንደ ሸክላ ደካማ እኩሉም እንደ ብረት የጸና እንደሚሆን ከነገረው በኋላ በሮም መንግሥት ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ሚሠለጥን ለወደፊት የሚሆነውን እየተረጎመ ገለጠለት ። ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት የተባለውም ክርስቶስ ያለ ዘርአ ብእሲ (ያለ ወንድ ዘር) በማኅፀነ ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ በምዕመናን ላይ መንፈሳዊ ግዛቱን እንደሚያስፋፋ የሚገልጥ እንደሆነ ማስተዋል ይገባል።

ነቢዩ ዳንኤል በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እየተቃኘ የተሰወረውን ሕልም ከነትርጉሙ በመግለጽ በአስተዳደርም ፤ በትክክል በመምራት በማስተማር የኖረ ሰው ነበር። ከላይ የጠቀስናቸው የሁለቱ ቅዱሳን ሕይወት በአስተዳደርና በሕልም ትርጉም ጥበብ የተመሩ ሰዎች ወይም ጥበብ መንፈሳዊ የተሰጣቸው እንደነበሩ ያስገነዝበናል።

፲ኛ ) የሃይማኖትን ነገር ምሥጢረ ሥላሴን ምሥጢረ ሥጋዌን አምልቶ አስፍቶ የማወቅና የመናገር ጥበብ።

ምሥጢረ ሥላሴ የታወቀው ጎልቶ ይፋ የሆነው ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ሰው በሆነ ጊዜ በዘመነ ሥጋዌ እንደሆነ የታወቀ ነው ። ምሥጢረ ሥላሴን በምሥጢረ ሥጋዌ ተገልጾ እንዳየን ምሥጢረ ሥጋዌንም ያለ ምሥጢረ ሥላሴ መረዳት ያስቸግራል። በምሥጢረ ሥላሴም ፣ በምሥጢረ ሥጋዌም ፤ ተዋሕዶ መሠረትና ጉልላት ናት። ስለዚህም ከሊቃውንት ቃል ብንመለከት "ሥላሴ በተዋሕዶ ወተዋሕዶ በሥላሴ ይሤለሱ በአካላት ወይትወሐዱ በመለኮት እስመ ተዋሕዶ እኤተታ ለምንታዌ " የሚሉ ሐረጎችን በስፋት እናገኛለን። በምሥጢረ ሥላሴ የአካላት ሦስትነት በመለኮት አንድነት ተዋሕዶው ይገለጣል። በምሥጢረ ሥጋዌም የምሥጢረ ሥላሴ ተዋሕዶ እንደተጠበቀ ሆኖ የቃልና የሥጋ (የመለኮትና የትስብእት) ተዋሕዶ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ እንደሆነ በተዋሕዶ ምንታዌ (መንታነት) እንደጠፋ የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ለቃል በተዋሕዶ እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል።

ተዋሕዶ በምሥጢረ ሥላሴ ሲነገር የትድመ ዓለም ተዋሕዶ ሲሆን በምሥጢረ ሥጋዌ ግን የድህረ ዓለም ተዋሕዶ ይባላል።

ይህ የሃይማኖት ምሥጢር ጥበብ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ካልታወቀ መረዳት አይቻልም። የሃይማኖትን ምሥጢር አከናውኖ ለመናገርም ሆነ ለማወቅ የመንፈስ ቅዱስ ሀብት ያስፈልጋል። ከዚህ በፊት ከገለጥናቸው ጥበባት ሁሉ የሥላሴን አንድነት ሦስትነት ምሥጢረ ተዋሕዶን (ምሥጢረ ሥጋዌን) የመናገርና የማወቅ ጥበብ ይበልጣል። ሰማይ ከምድር እንደሚበልጥ ፤ እንደሚልቅ ፍጡራንን ከማወቅ ራሱ ባለቤቱ እግዚአብሔርን በሦስትነቱ በአንድነቱ ማወቅ ይበልጣል። ምሳሌ እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ ዓለሙን ያዳነበት ጥበቡ እንደሚበልጠው ዓይነት ማለት ነው። ከቅዱስ ጳውሎስ ቃል ለመረጃነት የሚከተለውን ኀይለ ቃል እናስተወል።

ጥበበ ንነግሮሙ ለጠቢባን ወአኮ ጥበበ ዝ ዓለም ወኢጥበብ መላእክተ ዝንቱ ዓለም ዘሀለዎሙ ይሥዐሩ ዘንነግሮሙ ዘእንበለ ጥበበ እግዚእብሔር ዘንነግር ዘኅቡዕ ወከቡት። (፩ኛ ቆሮ ፪ : ፮ - ፯) ትርጉሙ ጠቢባን ነን ለሚሉ ሰዎች ጥበብን እንነግራቸዋለን ። ያልፉ ዘንድ ያላቸው የዚህ ዓለም ነገሥታት ፈላስፎች የሚያውቁትን ጥበብ እንነግራቸውም። ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገኘውን ጥበብ እንነግራቸዋለን እንጂ ። ጥበብም ያልኹት ኅቡዕ (ስውር ምሥጢር) ከቡት (የተሸሸገ ያልተገለጠ) የሚኾን ሥጋዌ ነው ይላል።

በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር ፰ ዘኢየአምርዎ መላእክተ ዝዓለም ወሶበሰኬ አእመሩ እምኢሰቀልዎ ለእግዚእ ስብሐተ (ያዕ ፪ : ፩ ፤ ሉቃ ፳፫ : ፴፬ ፤ መዝ ፳፫ : ፰-፱) ትርጉሙ ለእኛ መክበሪያ እንደኾነ የዚህ ዓለም ነገሥታት ፈላስፎች አንድም አይሁድ መናፍቃን አጋንንት የማያውቁት ባያውቁት ነው እንጂ አውቀውትስ ቢሆን የክብር ባለቤት እሱን ባልሰቀሉትም ነበር። ማለት ነው። ባለበገናውም ሲያደንቅ እኔስ መስሎኝ ድኀ ተራቁቶ ባየው፤ ለካስ ጌታ ኖሯል የተሰቀለው ብሏል።

በ፩ኛ ቆሮ ምዕ ፲፪ : ፰ ላይ የተነገረው ኀይለ ቃል በውስጡ ብዙ ነገሮችን እንደያዘ ቢታወቅም በተለይ የሃይማኖትን ምሥጢር በሚመለከት የተነገረ ነው። ጥበብን የመናገር ሀብት የሚሰጠው ሰው አለ። ጥበብ የተባለው የሃይማኖት ምሥጢር ነው። ይኸውም አንድነትን ሦስትነትን (ምሥጢረ ሥላሴን) የማወቅ ሀብት ነው። መንፈስ ቅዱስ ሀብት አድርጎ ነገረ መለኮትን የማወቅ ጥበብ ለሰጠው ሰው በዚህ ሀብት ተጠቅሞ ሌሎችንም ከኑፋቄ ይጠብቅበታል።

በቤተክርስታያን ታሪክ የዚህ ዓይነት ሀብት ከተሰጣቸው የቤተክርስቲያን ጠበብት መካከል ስለ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ (እምቂሳርያ) የሚተረክ አለ።

የምሥጢረ ሥላሴ ነገር ረቅቶ ይኖር ነበር ይባላል። ግብር ገብቶ ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም ያመለክታል እመቤታችንም አማልዳ ዮሐንስ ወንጌላዊን ሂደህ አስረዳው ብላው ሄዶ አስረድቶታል።



www.ethiopisnorthodox.org

መንፈስ ቅዱስ በእመቤታችን እማላጅነት ፤ በዮሐንስ ወንጌላዊ ትምህርት ጥበቡን ስለገለጸለተ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምሥጢረ ሥላሴን አምልቶ አስፍቶ የሚናገር ሁኗል። በዚህም ጸጋው ነባቤ መለኮት የሚል ትጽል ተሰጥቶታል። የመለኮትን ነገር የሚናገር የሚያስተምር ማለት ነው።

ወንጌላዊ ቅዱስ ዮሐንስ ቀዳሚሁ ቃል (በመጀመሪያ ቃል ነበረ) በማለት ምሥጢረ ሥላሴን አምልቶ አስፍቶ ቢናገር ታእጎሎስ እንደተባለ ጎርጎርዮስም ነባቤ መለኮት ተብሏል። በአራት ዘዳግም ምዕ ፴፬ ፡ ፱ ላይ በሚነበበው ቃለ እግዚአብሔር ሙሴ በኢያሱ ወልደ ነዌ ላይ በአንብሮተ እድ (እጆቹን በመጫን) ስለባረከው የጥበብን መንፈስ እንደተሞላ ይነግረናል። በዚሁ አንጻር የሙሴ እመቤት የጌታችን የመድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም በምልጃዋ ከዚህ የበለጠ እንደምታስደርግ ልንጠራጠር አይገባም።

በሐዋርያት ትምህርት ፣ በሐዋርያት እጅ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ሲታደል እንደነበር ግብረ ሐዋርያት ይዘረዝርልናል። ለምሳሌ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ በሰማርያ ተገኝተው ጸሎት ከአደረጉ በኋላ በአንብሮተ እድ (እጃቸውን በመጫን ) በመባረክ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን አሳድረዋል።(የሐዋ ፰፡ ፲፬ - ፲፯ ) ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ በሃይማኖተ አበው ምዕ ፩፻፳ ክፍል ፬ ቁጥር ፮ ና ክፍል ፯ ቁ ፲፩ ላይ ያስተላለፈውን ቃለ ግዝት ተመልክተን በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ጥበብ ተገልጸላቸው ያስተላለፉልንን የሃይማኖት ምሥጢር ጠብቀን ከልዩ ልዩ መናፍቃንና አረማውያን አስተሳሰብ እንጠበቅ እንጠንቀቅ።

የቅዱስ ጎርጎርዮስ ቃለ ግዝት

ሀ) እመቦ ዘይቤ ከመ ዘተወልደ እምድንግል ኢኮነ ቃለ እግዚአብሔር ውጉዘ ለይኩን።

ትርጉም ከድንግል የተወለደው የእግዚአብሔር ቃል አይደለም የሚል ቢኖር ውጉዝ ይሁን።

ለ) እመቦ ዘኢይሰግድ ለዘተሰቅለ ውጉዘ ለይኩን ወይትጌለቁ ምስለ ሰቃልያን እምላክ።

ትርጉም ለተሰቀለው የማይሰግድ ቢኖር ውጉዝ ይሁን እምላክን ከሰቀሉ ከአይሁድም ጋር የተቆጠረ ይሁን።

ከቅዱስ ጳውሎስ ቃለ ግዝት

ወዘሰ ኢያፈቅሮ ለእግዚእነ ውጉዘ ለይኩን እምተስፋ እግዚአብሔር በምጽአቱ ለእግዚእነ (፩ኛ ቆሮ ፲፮ ቁ ፳፪)

ትርጉም " ጌታችንን የማይወደውስ እግዚአብሔር ከሚሰጠው ተስፋ የተለየ ይሁን። "

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

# ርትዕት ሃይማኖቶሙ ለቅዱሳን አበዊነ

ስማዕታት በተነሡ በዘጠኝ መቶ ሶስት ዓመት የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አባታችን አባ ዘካርያስ ወደ እንጾኪያው ሊቀ ጳጳሳት ወደ አባ ዮሐንስ ጽፎ ከላከው መልእክት እኛስ ዛሬ በጌታችን በፈጣሪያችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ያለ መለያየት ያለመከፋፈል እንደ አንድ አፍ ሆነን እናምናለን ።

እንዲሁም በጥበብ በዕውቀት ጸንተን የሚታየውንና የማይታየውን ፍጥረቱን ሁሉ በፈጠረው ሁሉን በሚገዛ በአንድ አምላክ በአብ ተቀዳሚና ተከታይ በሌለው በልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትን በሚያድል በጌታችን በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን። ሥላሴ በአንድ ክብር ፣ በአንድ መለኮት ፣በአንድ ባሕርይ ፣ ፈጽሞ ባለመለያየት አንድ የሚሆኑ ንጹሐን ባሕርይ ሶስት አካላት ናቸው። ፍጥረትን በመፍጠር በከሃሊነት አንድ አምላክ ሲሆኑ የሶስቱ አካላት ገጸት ጌትነት አንድ ነው። ሥልጣናቸውም አንድ ነው ፤ እገዛዛቸውም አንድ ነው ፤ ክብራቸው አንዲት ናት መንግሥታቸውም አንድ ነው። እነዚህም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው ።

መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወልድ ጋር አንድ መሆንንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱም እንደ እኔ ያለ በአካል ልዩ የሆነ ጰራቅሊጦስን ይልክላችሁ ዘንድ እኔ አባቴን እለምነዋለሁ ብሎ በተናገረበት በወንጌል ለእኛ ገልጦልናል። እንኪያስ ለመንፈስ ቅዱስ ክብርና ምስጋና የማያቀርቡ እነዚህ መቅዶንዮስና አብሳልዲስ አሁን ይፈሩ ። እንደእኔ ያለ ሌላ ማለት የአካልነት ሶስትነትን ያስረዳል። አካላዊ ቃልም ጰራቅሊጦስ እሰድላቸኋለሁ ቃልነትም ከእኔ ገንዘብ አድርጎ ይነግራችኋል ማለቱ በዚህ ለመለኮት ያለውን አንድነት ያስተምረናል ። ይህም ቃል ለመለኮት አንድ የሚሆኑ ሥሉስ ቅዱስን የሚቃወሙ የአርዮስና የሰባልዮስ ወገኖች የሚሆኑ መናፍቃንን ይዘልፋቸዋል ።

እኛ ግን እናምናቸዋለን ፤ አንዲት ምስጋናን እናመሰግናቸዋለን ፤ በአንድ መለኮት ባለመለያየት እናመልካቸዋለን ፤ አንዲት ስግደት እንሰግድላቸዋለን። ሦስቱን አካላት በማመበላላጥ የሚከፋፍሏቸው ከዚህ በቀር ሌላ አምላክን የሚያመልኩ የሚታመኑ ግን በማህበራችን ተወግዘው የተለዩ የተጠሉ ናቸው። (ሃይማኖተ አበው ዘዘካርያስ ምዕ ፲፰ ክፍል ፩ ቁጥር ፳፬ ፳፯ ገጽ ፩፻፶፬ )



www.ethiopisnorthodox.org

ዓምደ ሃይማኖት

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

(ካለፈው የቀጠለ)

ከሲራክ ገብረክርስቶስ

ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ "ጥበብን የመናገር ሀብት" እንደሆነ ባለፈው ጽሑፍ ተረድተናል። ከዚህ ቀጥሎ ከመንፈስ ቅዱስ ሀብታት ሌላውን ክፍል እንመለከታለን ። ይኸውም በ፩ኛ ቆሮ ምዕ ፲፪ ቁ ፰ ላይ " ወቦ ለዘይሁቦ ቃለ አእምሮ በመንፈስ ቅዱስ " (በመንፈስ ቅዱስም የዕውቀት ቃልን የሚሰጠው አለው) ያለውን ኃይለ ቃል ይሆናል ።

፲፬.ለ) <u>ዕውቀትን የመናገር ስጦታ</u>:- መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጣቸው ስጦታዎች መካከል አንዱ ዕውቀት ነው ። በዓለም ላይ ብዙ ዓይነት ዕውቀት ይኖራል በጠቅላላ ዕውቀቶችን ሁሉ በሁለት ክፍል መመደብ ይቻላል ።

፩ኛ. ሥጋዊ ዕውቀት

፪ኛ. መንፈሳዊ ዕውቀት

፲፬.፩ኛ) <u>ሥጋዊ ዕውቀት</u>:- ለሰው ሁሉ በተፈጥሮ የተሰጠ በምርምር የሚስፋፋ የሚያድግ ነው ። ሃይማኖት ባላቸውና በሌላቸው መካከል ልዩነት ሳይኖር ሰው ሁሉ በተፈጥሮው ሥጋዊ ዕውቀት ይኖረዋል ። በትምህርት ሊስፋፋ የሚችል ዕውቀት በሰው ተፈጥሮ ውስጥ በባሕርዩ ያለ ስለሆነ ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር ከእንስሳት በላይ ሆኖ ኑሮውን አሻሽሎ መኖር የቻለው በተፈጥሮ ዕውቀቱ ላይ ትምህርት በማከል ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻለው በመሔድ ነው ።

እንዲህ ዓይነቱ ዓለማዊ ዕውቀት በመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ ፍጥረታዊ ዕውቀት ወይም ሥጋዊ አእምሮ ይባላል ። ይኸም የማወቅ ችሎታ ለሰው በጥንተ ተፈጥሮ ከፈጣሪ የተሰጠው ሀብት በመኾኑ በሚገባ ከተጠቀመበት በሥነ ፍጥረት ምርምር በአእምሮ ጠባዩ (በተፈጥሮ ዕውቀቱ) መሰላልነት የፈጣሪውን ህላዌ (መኖር) አውቆ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር መሳብ ይችላል ። በሚገባ ካልተጠቀመበት ግን በከንቱ ፍልስፍና ባዝኖ ሃይማኖተ አልባ በመሆን ማንኛውንም ክፉ ነገር በመሥራት ለራሱና ለመሰሎቹ ፍጡራን ጠንቅ ከመሆን አይመለስም ።

ስለዚህ ሥጋዊ ዕውቀት መስፋፋት መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ትንቢታዊ ቃል አለ ፤ ታላቁ ነቢይ ዳንኤል በትንቢቱ ስለ ዓለማዊ ዕውቀት መስፋፋትና ስለ ዘመናዊ ምርምር ትንቢት ተናግሮዋል ። ትንቢቱም እነሆ " .. ሰዎች ይመራመራሉ ዕውቀትም ይበዛል" ። (ዳን. ፲፪ ÷ ፩)

ተፈጥሮን በመመራመር የእግዚአብሔርን መኖርና በባሕርዩም ኃያል ዘለዓለማዊ አምላክ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ። ይኸውም በአእምሮ ጠባይዕ (በተፈጥሮ ዕውቀት) በመጠቀም ነው ። በሚገባ ካልተጠቀሙበት ሰውን ወደ ክህደት የድንቁርና አዘቅት ይጥላል ። በዚህም ሳቢያ የሰው ጠባዩ ሥነ ምግባሩ ከአውሬ የከፋ ይሆናል ። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል " እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፤ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና ። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና ፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመለኩት የሚያመካኙት አጡ ። ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ ። የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ ። (ሮሜ. ፩ ÷ ፲፱ - ፳፩) እንደ እነዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ፍጥረታዊ ሰዎች ይላቸዋል ። ከመንፈሳዊ ዕውቀት የራቁ በመንፈስ ቅዱስ ያልተቃኙ እንደ ተፈጠሩ ያሉ ሥጋውያን ስለሆኑ ነው ። ዕውቀታቸውም ፍጥረታዊ ስለሆነ መንፈሳዊው ነገር አይጥማቸውም ፤ አመለካከታቸው አስተሳሰባቸው ሁሉ ቁሳዊ (ማቴሪያል) ብቻ ነው ። ጥልቅ የሆነውን የሃይማኖት ነገር ለእነርሱ የተሰወረ በመሆኑ ሲሰናከሉበት ይኖራሉ ። ይኸን በማስመልከት ሐዋርያው መንፈሳውያንና ሥጋውያንን በማነጻጸር ይገልጸዋል ። ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም ። በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም ። መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም ። እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው ? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን ይላል ። (፩ኛ ቆሮ. ፪ ÷ ፲፬ - ፲፮) ።

በፍጥረታዊ ዕውቀት ተመርተው ከተሳሳቱት ሰዎች መካከል ሰዱቃውያን ይገኙበታል ። ሰዱቃውያን በዓለማዊ አስተሳሰባቸው በመመራት ትንሣኤ ሙታንን ጽድቅና ኩነኔ የመላእክትና የነፍስን መኖር በመካድ ምድራዊ አመለካከት ብቻ ይዘው ከመንፈሳዊ ዕውቀት ርቀው እንደነበሩ ፤ የእነርሱን መንገድ የሚከተሉ ሥጋውያን ተፈላሳፊዎችም ብዙዎች ናቸው ። እንደ እነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች አንድ ዘመን ራሳቸውን የዕውቀት ሰዎች ነን ብለው (ግኖስቲሲዝም) በሚል ዘይቤ አያሌ ኑፋቄዎችን በማስፋፋት ለቤተክርስቲያን ጠንቅ ሆነው እንደነበር በቤተክርስቲያን ታሪክ ተጽፏል ።

እንደእነዚህ ያሉትን ሰዱቃውያንና ግኖስቲኮች ቃለ እግዚአብሔር እንዲህ ይላቸዋል ። " መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ" (ማቴ. ፳፪ ÷ ፳፱) እንዲህ ያለውን የማይጠቅም ፍጥረታዊ ዕውቀት ክርስቲያኖች እንደ ቁምነገር ሊቆጥሩት አይገባም ። የእግዚአብሔር ሰዎች ከዓለማዊ ዕውቀት በላቀ መንፈሳዊ አእምሮ ተመርተው በክርስቲያናዊ ኑሮ መኖር ይገባቸዋል ። ቅዱስ ጳውሎስ በጢሞቴዎስ በኩል ለክርስቲያን ሁሉ ያስተላለፈው መልእክት ሊጤን የሚገባው ነው ።



www.ethiopisnorthodox.org

"ጢሞቴዎስ ሆይ በውሸት ዕውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ ፣ ይህ ዕውቀት አለን ብለው አንዳንዶች ስለ እምነት ስተዋልና ጸጋ ካንተ ጋራ ይሁን ። " ይላል ። (፩ኛ ጢሞ. ፮ ÷ ፳ - ፳፩)

፲፩.፪ኛ <u>መንፈሳዊ ዕውቀት</u> :-ይህ ዓይነቱ ዕውቀት የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነው እግዚአብሔር ሁሉን የሚያውቅ ነው ። የባሕርይ ዕውቀቱን በጸጋ ለሰዎች ያድላል ። የእግዚአብሔር ሰው መዝሙረኛው ዳዊት " አሕዛብንስ የሚገስጸው <u>ለሰውም ዕውቀትን የሚያስተምረው እርሱ አይዘልፍምን</u> ? የሰዎች አሳብ ከንቱ እንደሆነ እግዚአብሔር ያውቃል ።" (መዝ. ፺፫÷፲-፲፩) ይላል ። የዕውቀት ባለቤት ሁሉን የሚያውቅ ዕውቀትንም በጸጋው ለሰዎች የሚለግስ አምላክ እግዚአብሔር መሆኑን ያመለክተናል ።

እግዚአብሔር መንፈሳዊ ዕውቀትን የሚያድል ዕውቀትን የሚገልጥ የዕውቀት ባለቤት መሆኑን በብሉይ በሐዲስ አውቀነዋል ። ለምሳሌ ሙሴ ዕውቀትን ከእግዚአብሔር በሃይማኖት ቢለምን መንገዱን አሳየው ። (ዘፀ. ፴፫÷ ፲፪-፳፫ ፣ መዝ. ፻፪ ÷ ፯) ዳንኤልና ጓደኞቹ ሦስቱ ወጣቶች ውሃ ጠጥተው ጥሬ ቆርጥመው እግዚአብሔርን በጾም በጸሎት ቢጠይቁት ከሌሎች የተሻለ ማስተዋልና ዕውቀት ተሰጣቸው ። (ዳን. ፩÷ ፲፯) በሐዲስ ኪዳንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ወዳጆቹ ልዩ የኾነ መንፈሳዊ ዕውቀት እንደሰጣቸው ሲገልጥ " ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ ፣ ከአባቴ (በህልውና) የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና" (ዮሐ. ፲፭÷ ፲፭) ብሏል ።

መንፈሳዊ ዕውቀት ልዩ ልዩ ዘርፍ ይኖረዋል ፤ ከዕውቀቶች ሁሉ ብልጫ ያለው ዕውቀት ግን የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት በሃይማኖት ተረድቶ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በክብር በባሕርይ አንድ አድርጎ የሚያምኑበት የነገረ ሃይማኖት ዕውቀት ነው ። ብቻውን ለዕውቀትነቱ ተብሎ የሚያውቁት ዓይነት የቲዎሎጂ ዕውቀት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ በትምህርት የተረዱትን ዕውቀት በሃይማኖት የሚያውቁት ዕውቅት ነው ። ይኸውም ግብር ግብተው የሚረዱት ነው ። ይህ ዓይነቱ ዕውቀት ዘላለማዊ ሕይወትን ያስጣል ። ስለዚህም ጌታችን እንዲህ አለ " እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት ። " (ዮሐ. ፲፯ ÷፫)

በሥጋ ተገልጦ የሚታየው ኢየሱስ ክርስቶስ ከላኪው ከአብ ጋር እርሱም እንደ አብ እውነተኛ አምላክ መሆኑን የሚገልጥ ንባብ ነው ። ወልድን (ኢየሱስ ክርስቶስን) ከባሕርይ አባቱ ከአብ ነጥሎ የሚመለከት ቃል አይደለም ። ቀደም ብሎ " እኔና አብ አንድ ነን ።" (ዮሐ. ፲ ÷፴) " እኔን ያየ አብን አይቷል ። " (ዮሐ. ፲፬ ÷ ፱) ሲል ባስተማረው መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ አብን በመልክ የሚመስለው በባሕርይ የሚተካከለው እውነተኛ አምላክ መሆኑን የሚያስረዳ አነጋገር ነው " እውተኛ አምላክ ብቻ " የሚለው ሐረግ አብን ከፍጡራን ሊለየው የተነገረ ቃል እንጂ ከባሕርይ ልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ወይም ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ለይቶ ለመናገር ሲባል የተገለጠ ቃል አይደለም።

ስለዚህ በ ሃ ይ ማ ኖ ት የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ማወቅ የዘላለም ሕይወት እንደሆነ ለመረዳት ችለናል ። እግዚአብሔርን ከማወቅ የበለጠ ዕውቀት ሊኖር ስለማይችል ፣ እርሱን ለማወቅ የሚያስችል መንፈሳዊ ዕውቀት ከሁሉም የላቀ ሆኖ ይገኛል ። በትንቢት ቀደም ብለን እንዳመለከትነው ስለ ሥጋዊ ዕውቀትና ምርምር መስፋፋት የተነገረውን በማገናዘብ ስለ መንፈሳዊ ዕውቀትም መስፋፋት የተነገረውን ብ ና ን ጻ ጽ ር እግዚአብሔር ሁለቱንም ዓይነት የዕውቀት መስኮች ለሁሉም ክፍት እንዳደረገውና ማንም ሰው በፈቀደው ጎዳና መመላለስ የሚችል እንዲሆን ነጻነት እንደሰጠው እናያለን ብልጫ ያለውን ለዘላለማዊ ሕይወት የሚያበቃውን ሰው በነጻነቱ መርጦ የሚሻለውን መከተሉ የራሱ ፈንታና ምርጫ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል ።

በምድር ያለ ሰው ሁሉ ስንኳን አሕዛብ ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተባሉ እሥራኤል ሳይቀሩ በአምልኮተ ጣዖት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቀው በአለማወቅ ጨለማ ተጋርደው የመንፈሳዊ ብርሃን ብልጭታው ዕውቀቱ ተሰውሮባቸው በነበረበት ወቅት በዓመተ ፍዳ በዓመተ ኩነኔ ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ በዓመተ ምሕረት ይኸውም በክርስቶስ ሰው ሆኖ መገለጥ በዘመነ ሐዲስ መንፈሳዊ ዕውቀት ለሰው ሁሉ ለሕዝብም ለአሕዛብም እንደሚዳረስ በትንቢቱ አመልክቷል ። ይኸውም ትንቢታዊ ቃል ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ ለዓለም በተሰበከው የወንጌል ቃል ፍጻሜውን አግኝቷል ።

ኢሳይያስ " ውኃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለችና ። " (ኢሳ.፲፩÷፱) በማለት የተናገረው ትንቢት ጌታ ሐዋርያትን " ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው " (ማቴ. ፳፰ ÷ ፲፱ ፣ ማር ፲፮÷ ፲፭) ብሎ ባዘዘ ጊዜ በሐዋርያት አገልግሎት ተፈጽሟል ።

ቅዱሱ ጳውሎስም አሕዛብን ወደ ወንጌል ሃይማኖት ሲያገባ የመንፈሳዊ ዕውቀት ዘመን መድረሱን የድንቁርና የጣዖት አምልኮት ዘመን ማለፉን በማብሰር " እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል " (የሐዋ. ፲፯ ÷ ፴) በማለት ያስተምር ነበር ።

በተጨማሪም ክርስቶስን በቅንሣኤውም የተገለጠውን ኃይል ማወቅ ከሁሉ እንደሚበልጥበት ዕውቀቱንም በይበልጥ ለማግኘት የሚያደርጋቸውን ተ ጋ ድ ሎ ዎ ች ሐዋርያው አብራርቷል ። (ፊልጵ.፫÷፱ - ፲፩) በቆላስይስ ክታቡም " ልባቸው እንዲጸናና በፍቅርም ተባብረው በማስተዋል ወደሚገኝበት ወደ መረዳት (ማወቅ) ባለጠግነት ሁሉ እንዲደርሱ የ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ም ምሥጢር እርሱንም ክርስቶስን እንዲያውቁ እጋደላለሁ ፤ የተሰወረ የጥበብና የዕውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና" በማለት ለምዕመናን ክርስቶስን ለማስተዋወቅ ትግል እንደሚያደርግ አስታውቋል ። መንፈሳዊ ዕውቀት ደረጃ አለው ። ዕውቀቱ በቦታና በጊዜ በደረጃ



www.ethiopisnorthodox.org

ይለያያል ። ይኽንን ሲያስረዳ ንዋይ ኅሩይ ጳውሎስ " ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል ከዕውቀት ከፍለን እናውቃለንና ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል ። ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር ፤ እንደ ልጅም አስብ ነበር ፤ እንደ ልጅም እቆጠር ነበር ፤ ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ ። ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን ። ዛሬስ ከዕውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ አውቃለሁ " (፩ኛ ቆሮ.፲፫ ÷ ፱ - ፲፪ ) ብሏል ።

ከሕፃንነት ዕውቀት በጎልማሳነት ሳሉ የሚያውቁት ዕውቀት ብልጫ እንዳለው የታወቀ ነው ። እንዲሁም በወጣኒነት ሳሉ ከሚያውቁት ዕውቀት በፍጹምነት የሚያውቁት ይበልጣል ። በዚህ ዓለም ሳሉ ከሚያውቁት ዕውቀት በዓለመ ነፍስ የሚያውቁት ይበልጣል ። በገነት ሳሉ ማለትም ፡ በፀጸደ ነፍስ ከሚያውቁት ዕውቀት ከትንሣኤ በኋላ በመንግሥተ ሰማያት የሚያውቁት እጅግ በጣም ይበልጣል ። ይህንንም ሊቃውንት በምሳሌያዊ መግለጫ እንደሚከተለው አነጻጽረውታል ።

ቅዱሳን በዚህ ዓለም ሳሉ የሚያውቁት ዕውቀት ሕፃናት እስከ ፯ ዓመት እንደሚያውቁት ዕውቀት ነው ። ከበቁ በኋላ ግን የሚያውቁት ዕውቀት እስከ ሃያ ዓመት እንደሚያውቁት ዕውቀት ነው ። ከሞቱ በኋላ የሚያውቁት እስከ ፴ ዓመት እንደሚያውቁት ፤ ዕውቀት ከትንሣኤ በኋላ የሚያውቁት ዕውቀት ከ ፴ ዓመት በላይ እንደሚያውቁት ዕውቀት ነው በማለት አብራርተውታል ።

መንፈሳዊ ዕውቀት ከሥጋዊ ዕውቀት ብልጫ እንዳለው መንፈሳዊ ዕውቀት በጊዜና በቦታ በደረጃ እንደሚለያይ ከዚህ በላይ በተሰጠው ሐተታ ከሞላጎደል መረዳት ይቻላል ። ስለ መንፈሳዊ ዕውቀት ጥቅምና ምንነት ማር ይስሐቅ እንደሚከተለው ይገልጣል ።

ጥያቄ:- አዋቂ ነው ተብሎ መመስገን ለማን ይገባዋል ?

ምላሽ የዚህችን ዓለም ፍጻሜዋን (ኃላፊነቷን) በእውነት ለሚያውቅ ለኃጢአቱ ወሰን ድምበር ለሚሰጥ ነው ማለት በቃኝ ለሚል ነው ። ምን ዕውቀት ነው ?

ምን ማስተዋል ነው ? ኃጢአትን በቃኝ ከማለት ዓለምን ከመናቅ የሚበልጥ ዕውቀት ምን ዕውቀት ነው ይኸውም ጥበብ መንፈሳዊ ፍልስፍና አምላካዊ ነው ። ኃጢአት ሳይኖርበት በሞት በምናኔ ከዚህ ዓለም አኗኗር ይለይ ዘንድ በሐልዮ ኃጢአት (በሐሳብ በሚፈጸም ኃጢአት) ያደፈ አንድ አካል ሳይኖረው ሰውነቱን ከጸጋ የለያት ኃጢአት ሳይኖርበት አንድም ኃጢአት ደስ ከማሰኘቷ የተነሣ ሰውነቱን ወደ ኃጢአት የሳባት ሐልዮ ኃጢአት ሳይኖርበት ፤ (ማር ይስሐቅ ፪ አንቀጽ ፬ገጽ ፸፯ ) ዳግመኛም በአእምሮ ጠባይዕና (በተፈጥሮ ዕውቀትና) በመንፈሳዊ ዕውቀት መካከል ያለውን ልዩነት ማር ይስሐቅ በምዕ ፩በ ፳፯ኛ አንቀጽ እንደሚከተለው ይገልጣል ። የአእምሮ ጠባይዕን የአእምሮን መንፈሳዊን ማለት የአእምሮን ሁለትነት ይናገራል ። ዕውቀት ከሁለት ወገን ነው ፤ ከሁለት ይከፈላል ። ከሃይማኖት የሚቀድም ዕውቀት አለ ፤ አእምሮ ጠባይዕ ነው ። ከሃይማኖት የሚገኝ አእምሮ አለ ፤ አእምሮ መንፈሳዊ ነው ። ከሃይማኖት የሚቀድም ዕውቀት አእምሮ ጠባይዕ ነው ፤ ከሃይማኖት ሰሚዕ የሚገኝ ዕውቀት መንፈሳዊ አእምሮ ነው ። አእምሮ ጠባይዕ በጎውን ከክፉ ለይቶ የሚያውቅ ነው ። የነፍስ ዕውቀት ይባላል ። ባሕርያችን ሳይማር ክፉውን ከበጎ ለይቶ በአእምሮ ጠባይዕ ያውቃል ። የእግዚአብሔር ቸርነት በነፍስ በትምህርት የሚሰፋ አእምሮ መንፈሳዊን አሳደረ ። ከአእምሮ መንፈሳዊና ከአእምሮ ጠባይዓዊ አንዱ የሌለው ግን ባለ አእምሮ አይባልም ። የነባቢት ነፍስ የባሕርይ ዕውቀት ሥራ ዘወትር በነፍስ የምታድር ፤ ነፍስን የምትቃኝ ክፉና በጎን ለይቶ ማወቅ ነው ፤ አንድም የአእምሮ ጠባይዕ ሥራ የነፍስ ገንዘብ ናት ፤ ይኸውም በጎውን ከክፉ ለይቶ ማወቅ ነው ለዕውቀት የሚስማማ ሥራ የማይሠሩ ሰዎች ከነባቢ ነፍስ ማዕርግ የወጡ ናቸው ማለት ባለ አእምሮ አይባሉም ።

ለአእምሮ ጠባይዕ የሚስማማ ሥራ የሠሩ ሰዎች ግን ባለ አእምሮ ይባላሉ ፤ እንድም አእምሮ ጠባይዕን ቢይዙ አእምሮ መንፈሳዊ ይሰጣል ። በአእምሮ ጠባይ ላይ አእምሮ መንፈሳዊን ክብር ይሁናቸው ብሎ ለነቢያት የሰጠ የእግዚአብሔር ቸርነቱን ባሕርዩን መለወጥ አያገኘውም ። በጎውን ከክፉ ለይቶ የሚያውቅ የአእምሮ ጠባይዕን ሥራ የተውን ሰዎች ግን ነቢይ ሰው ክቡር ሲሆን ክቡር የሚሆንበትን አላወቀም ብሎ ይዘልፋቸዋል ። (መዝ. ፵፰ ÷ ፲፪) የነባቢት ነፍስ ክብሯ ዕውቀት ነው በጎውን ከክፉ መለየት ነው ። ለአእምሮ ጠባይዕ የሚስማማ ሥራ ያልሠሩትን ግን በጎውን ከክፉ ለይተው በማያውቁ በእንስሳ ሊመስላቸው ይገባል ። በአእምሮ ጠባይዕ ሕገ እግዚአብሔርን እንጠብቅ ዘንድ ገንዘብ እናደርግ ዘንድ ይገባናል ከሃይማኖት አስቀድማ የምትገኝ የባሕርይ ዕውቀት ይህች ናት ። ክብር ይግባውና ወደ ፈጣሪ የምንደርስባት ዕውቀት ይህች ናት በአእምሮ ጠባይዕ በጎውን ከክፉ ለይተን ዐውቀን እናምን ዘንድ ይቻለናል ብሏል ።

ይቀጥላል ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ።

## መልክዐ ዜና

ዋኖስ አሳታሚ ድርጅት አዲሱን ዓመት ምክንያት በማድረግ የወንጌላዊው ማርቆስን ሥዕል ከ፲፱፻፺ ዓ.ም የቀን መቁጠሪያ ጋር ድንቅ የሆነ ፖስት ካርድ አሳትሞ በቅርብ ቀን በገበያ ላይ የሚያውል መሆኑን በአክብሮት ይገልጻል።

## ሥነ ግጥም

የክረምቱ ሰዓት ተክቶ በጋውን
ሰውን ለመመገብ ደርሷልና ፈጥኖ
ነፋሱም ይነፍሳል ደመናውን ገፍቶ
ፍርሃት የሌለበት ገበሬው ሲሠራ
አምላክን ለምኖ በተስፋ ሲዘራ
እስቲ እናስበው ስንበላ እንጀራ ።
ምርቱ የታፈሰው እህል በያይነቱ
ሮማን ትርንጎው ፍሬው አታክልቱ
የገበሬ ትጋት ነውና ውጤቱ
ሰዎች አትሰንፉ ተማሩ በውነቱ ።
ይህ ጊዜ ያልፍና የክረምቱ ወራት
ማሩ ጋሩ ተረስቶ የገበሬው ልፋት
ንብረቱ ተሟልቶ ሲሆን እሸት በሸት
ቢገርመው ሰነፍን ከአፈር ጋር መጫወት
ሀብታም ሰው ያደርጋል ሥራ ሥሩ በውነት





www.ethiopisnorthodox.org

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

## ጋኔን የማውጣት ሀብት

ከሲራክ ገብረክርስቶስ

ከዚህ ቀደም ባለው ከታባችን ርኩሳን መናፍስት በሰዎች ላይ ሲያድሩ ስለሚያስከትሉት ጉዳትና በጥንተ ተፈጥሮም ርኩስ መንፈስ በሰው ላይ ስላስከተለው አደጋ፤ መደረግ ስላለበትም ጥንቃቄና መንፈሳዊ ተጋድሎ፤ የመጽሐፍ ቅዱስን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ መግለጻችን ይታወሳል። ከዚያው በማያያዝ በዚህ ጽሑፍ ተከታዩን እናቀርባለን። እንደተለመደው አንባብያን በአትኩሮት ከጸሎት ጋር እንድታጣጥሙት እንጋብዛችኋለን። ለዚሁም ማስጀመርና ማስፈጸም የሚቻለው ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግል እናቱ ጸሎት አማላጅነት፣ በቅዱስ መንፈሱ ይርዳን አሜን።

ሐ) <u>ርኩስ መንፈስ በጻድቁ ኢዮብ ላይ ስለፈጸመው ደባ</u>፡- በዘመነ አበው ከነበሩት ደጋግ መንፈሳውያን አባቶች መካከል አንዱ ኢዮብ እንደሆነ ይታወቃል። በዚያን ዘመን የነበሩት ቅዱሳን አባቶች በሕገ ልቡና በመመራት፣ ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔር በማምለክ፣ ትዕዛዙን በማክበር ይገዙለት ነበር። ጻድቁ ኢዮብም በሕገ ልቡና ጸንቶ ፈጣሪውን እግዚአብሔርን በንጹሕ አምልኮ በማምለክ፣ በሥነ ምግባር በማጌጥ ይገዛለት እንደነበር፤ ዜና ሕይወቱን የሚገልጸው፣ በስሙ የሚታወቀው፣ ከሟኘቱ ብሉያት አንድ ተብሎ የሚቆጠረው መጽሐፈ ኢዮብ ይመሰክርለታል።

ይህ ደግ ሰው ዖፅ በሚባል አገር ሲኖር በሀብቱ መደርጀት፣ በብልጽግናው ብዛት በዘመኑ ከነበሩት የምሥራቅ ሰዎች ታላቅና የከበረ በመሆኑ እንደ ንጉሥ ይታይ ነበር። አኗኗሩም አንድ ወንድ በአንድ ሴት በሚለው ሕጋዊ ጋብቻ ተወስኖ፣ ሰባት ወንዶች ሦስት ሴቶች ልጆች አፍርቶ፣ በሥርዓት በማሳደግ አርአያና ምሳሌ በመሆን ነበር። በመጽሐፈ ኢዮብ ም. ፩:፩ ላይ "ዖፅ በሚባል አገር ስሙ ኢዮብ የተባለ አንድ ሰው ነበር፤ ያም ሰው ፍጹምና ቅን፣ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፣ ከክፋትም የራቀ ነበረ" ሲል በጋብቻ ሕግ የሚኖረውን ኢዮብ በዓለም ሳለ በመንፈሳዊ ብቃቱ የከበረ ጻድቅ ሰው እንደነበር ይገልጸዋል። ከዚህ በላይ የሚያስገርመው አስደናቂ ሥራው ደግሞ፤ ልጆቹን በሥርዓት አሳድጎ ለቁም ነገር ማብቃቱ ሳያንሰው፤ በተጨማሪ ምናልባት በሐሳባቸው እግዚአብሔርን ተጠራጥረው እንዳ ያስቀይሙብትና እነርሱም እንዳይጎዱ፤ ዕለት፣ ዕለት በእያንዳንዳቸው ስም፣ በቁጥራቸው ልክ፣ መሥዋዕት እያቀረበ በጸሎት የሚያስብላቸው፣ በፍጹም አባታዊ ፍቅሩ የሚጠነቀቅላቸው ሆኖ መገኘቱ ነው። ስለዚህም ተግባሩ በኢዮብ ም.፩:፭ ላይ ሲገልጽ እንዲህ ይላል "የግብዣውም ቀኖች ባለፉ ጊዜ ኢዮብ ምናልባት ልጆቼ በድለው እግዚአብሔርንም በልባቸው ሰድበው ይሆናል ብሎ ይልክና ይቀድሳቸው ነበር። ኢዮብም ማልዶ ተነሣ እንደ ቁጥራቸውም ሁሉ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ። እንዲሁ ኢዮብ ሁልጊዜ ያደርግ ነበር"።

ኢዮብ በሥጋዊ አኗኗሩና መንፈሳዊ ሕይወቱ ፍጹምና የበቃ ሰው ሁኖ ሲኖር፤ የበጎ ሥራ ጠላት በግብሩ ጸላኤ ሠናያት የተሰኘ ሰይጣን በተቃውሞ ተነሣበት። ቅዱሳን መላእክት በጸጋ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ልጅነት ስላለ በቅድስና ኑሮ ፈቃደ እግዚአብሔርን በማክበር ስለሚኖሩ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም የሚችሉበት ሞገስ የባለሟልነት ጸጋ አላቸው። ስለ ሰዎች ልጆች መልካም ኑሮና አጠባበቅ ወደ እግዚአብሔር የምልጃ ጸሎት ለማቅረብ በፊቱ ይቆማሉ። እነርሱ ቅዱሳን ስለኾኑ ሐሳባቸው ሁሉ ቅድስና ነው። ስለሰዎች ጥቅም ያስባሉ እንጂ ቅንዓትና ምቀኝነት እንደ በጎ ጠላት ሰይጣን የለባቸውም። ከዚህ የተነሣ ከዕለታት አንድ ቀን እንደልማዳቸው ለሰዎች ልጆች ምሕረትን ሊለምኑ፣ ሊያማልዱ በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ሳለ፤ የሰዎች ባላጋራ ምቀኛው ሰይጣን ደግሞ በመካከላቸው መጣ። የሰይጣን አመጣጥ ለክስ፣ ለደባና ለተንኮል ነው። የሰው ልጆች በሥጋና በነፍስ ጉዳት እንዲደርስባቸው ከማሰብና የክፋት መረቡን ከመዘርጋት የሚቆጠብበትና የሚያርፍበት ጊዜ የለውም። ምንም እንኳን የሰይጣን አመጣጥ የታወቀ ያው ለተንኮል ቢሆንም፤ እግዚአብሔር ከወዴት መጣህ? ብሎ ጠይቆታል። እግዚአብሔር የማያውቀው ነገር ኑሮ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ ሐሳቡን እንዲገልጽ ነጻነቱን ሊገፍ ስላልፈቀደ ነው።

ልዑል አምላክ ለሰውና ለመላእክት ከሰጣቸው ልዩ ስጦታ አንዱና የመጀመሪያው ነጻነት ነው። ነጻ ፈቃድ፣ ነጻ ምርጫ ለሁሉም ፍጡራን ስላላቸው የወደዱትን መምረጥ፣ የፈቀዱትን መከተል ይችላሉ። በዚህ ነጻነታቸው ገደብ የለባቸውም። ምርጫቸው በጎ ከኾነ መልካም ውጤት ይጠብቃቸዋል። የሚከተሉት ጎዳና፣ የመረጡት ፈለግ ግን ክፉ ከኾነ እንደ ምርጫቸው ክፉ ነገር ይገጥማቸዋል። በዚህ ምክንያት ከሰዎች ወገንም ሆነ ከመላእክት፣ ክፉዎችም ሆኑ ደጋግ፣ ምርጫቸውን የመከተል ነጻነት አልተወሰደባቸውም። ያው በጥንተ ተፈጥሮ የተሰጣቸው ነጻ ፈቃድ ሲሠራ ይኖራል። በዚህ ምክንያት ነበር ነጻነቱን ተገፈፍሁ ብሎ ሰበብ እንዳያደርግ፤ ፈጣሪ የመጣበትን ጉዳይ አውቆ ሳለ እንዳላወቀ ሆኖ ሰይጣንን የጠየቀው! ሰይጣንም ሲመልስ "ምድርን ሁሉ ዞርሁአት፣ በእርሷም ተመላለስሁ አለ።" እግዚአብሔርም ዳግመኛ መልሶ "በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፤ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፣ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም አለው።" እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ የኢዮብን ደግነት፣ ብቃትና ባለሟልነት



www.ethiopisnorthodox.org

የገለጸው፤ ምቀኛው ሰይጣን ለክስ እንደመጣ ስለሚያውቅ ሊያሳፍረው፣ ከንቱነቱን ሊያጠይቀው ወዶ ነው።

ተንኮለኛው ሰይጣንም ደባውን ከልቡ አፍት አውጥቶ "በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራ በከንቱ ነውን? እርሱንም፣ ቤቱንም፣ በዙሪያውም ያሉትን ሁሉ አላጠርህለትምን? የእጁን ሥራ ባርከህለታል፤ ከብቱም በምድር ላይ በዝቷል፤ ነገር ግን እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ዳብስ፣ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል" ብሎ ክሱን መሠረተ። እግዚአብሔርም የኢዮብን ደግነት፣ ጻድቅነት የተገነባው፤ በኀላፊ ንብረትና በኋላ በተገኙ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ልጆች ላይ ሳይሆን፤ በራሱ በእግዚአብሔር ጌትነትና ፍቅር ላይ መሆኑን ምቀኛው ሰይጣን ፈትኖ ይረዳ ዘንድ "እነሆ ለእርሱ ያለው ሁሉ በእጅህ ነው። ነገር ግን በእርሱ ላይ እጅህን አትዘርጋ አለው።" ሰይጣን ከእግዚአብሔር ፈቃድ አግኝቶ ጻድቁን ሊፈትነው ሄደ። ኢያሱ ሲራክ "የደረሰብህን መከራ ሁሉ በትዕግሥት ተቀበል። ወርቅን በእሳት እንዲፈትኑት፤ ጻድቅንም ሰውችግርን በሚያመጣ መከራ ይፈትኑታልና፤ ገንዘብ በተቸገርህበት ወራት መከራውን ታገሥ።" (ሲራክ. ፪:፬-፭) ብሎ እንደናገረው ሰይጣን በሚፈትነው ጊዜ ኢዮብ መከራውን እንዴት አድርጎ ያልፍ ይሆን? በውኑ ሰይጣን እንደተናገረው በፈተናው ወራት ኢዮብ ፈጣሪውን ይክድና ይሳደብ፣ ወይስ ያማርር ይሆን? ወይንስ ፈተናውን በትዕግሥት፣ እግዚአብሔርን በማመስገን፣ በአኮቴት፣ በጸጋ ይቀበለው ይሆን? ለሁሉም ውጤቱን ተከታትሎ በማጤን ፍርድ መስጠት ይሻላል።

ሰይጣን እንደተንኮሉና ጭካኔው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ቢያገኝ፤ አንድም ሰው በሕይወተ ሥጋ ወይም በሕይወተ ነፍስ ይኖራል ተብሎ አይጠረጠርም። ነገር ግን ሰውን ያለ አቅሙ እንዳይፈትን በጠላታችን በሰይጣን ሥልጣን ላይ ሁልጊዜም ገደብ የሚያደርግ አምላካችን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን። ይኸንኑ ሁኔታ ሲገልጽልን ታላቁ ሐዋርያ አባታችን ቅዱስ ጳውሎስ፤ ለቆሮንቶስ ምዕመን በጻፈው ክታቡ "ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው። ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።" ብሏል። (፩ቆሮ. ፲:፲፫)

እንግዲህ ጻድቁ ኢዮብ በፈተናው ወቅት ይኸው ዕድል ገጥሞት ይሆን? እስቲ ቀጣዩን የፈተና ታሪክ አንድ በአንድ ለመመልከት እንሞክር። ያ ክፉ ፈታኝ፣ የሰዎች ሁሉ ባላጋራ ሰይጣን፤ ኢዮብን ለመፈተን ፈቃድ ካገኘ በኋላ፤ በተከታታይ የፈተና አሽክላውን ዘርግቶ፤ ጻድቁን ከእግዚአብሔር መስመር ለማውጣት ጦሩን አንድ ባንድ ወረወረበት። የመጀመሪያው የፈተና ጾር የተሰነዘረው በኢዮብ ንብረትና አገልጋዮች ላይ ነበር። ቀጥሎ በታላቅ ወንድማቸው ቤት በደስታ ባሉ በኢዮብ ፲ሩም ልጆቹ ላይ ተቃጣ።

የኢዮብ አገልጋዮች በአምስት መቶ ጥማድ በሬ ሲያርሱ፤ አምስት መቶ እንስት አህዮች ዘር ተሸክመው በእርሻው መስክ ሳሉ፤ የሳባ ሰዎች አደጋ ጥለው ብላቴናችን በሰይፍ ካረዷቸው በኋላ አንድ ሳያስቀሩ ከብቶቹን ነድተው ሄዱ። ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢዮብ እረኞች ፯ሺህ በጎች አሰማርተው በመጠበቅ ላይ እያሉ፤ በድንገት እሳት ከሰማይ ወርዶ በጎቹን አቃጠለ፣ ጠባቆቹንም በላ። ይኸ መከራ ሳያልፍ ሌላ አስደንጋጭ አሰቃቂ ነገር ተፈጠረ። ይኸውም ከለዳውያን በሦስት ረድፍ ተከፍለው የኢዮብን ሦስት ሺህ ግመሎች ከነጠባቆቻቸው አደጋ ላይ በመጣል ብላቴኖቹን በሰይፍ ስለት ከገደሉ በኋላ ግመሎቹን ዘርፈው ተፈተለኩ፤ ዱካቸው ሊገኝ አልቻለም። ከዚህ ሥቃይና አስደንጋጭ መከራ በኋላ በእግዚአብሔር ጸጋ በፍጹምነት ያለ ሰው ካልኾነ የማይችለው ፈተና መጣ።

የኢዮብ ልጆች ከፍቅራቸው ብዛት የተነሣ ተራ በተራ እየተጠራሩ፣ እንደ ጽዋ ማኅበር እየዞሩ፣ በኅብረት ይመገቡ፣ ይጫወቱ ነበር። በዚህ በፈተና ቀን የግብዣው ጥሪ ተራው በታላቅ ወንድማቸው ቤት ስለነበር፤ ሁሉቸም ጥሪውን አክብረው በመገኘት በግብዣና በሰላም እየተጫዋወቱ ሳለ፤ አውሎ ነፋስ ከምድረ በዳ መጥቶ የቤቱን አራቱን ማዕዘን መታው። ግንቡ በብላቴናቹ ላይ ወደቀ። ለወሬ ነጋሪ ሳይተርፉ ሁሉም ሞቱ። የሕንፃው ፍራሽ የመቃብር ቤታቸው ሆነ፤ ቀባሪም አላስፈለጋቸውም። እነዚህ ሁሉ አደጋዎች የመጡት በሰይጣን ተንኮልና ደባ ነው። በአንድ ጀንበር፣ በአንድ ቀን፣ አራት አደጋ፣ በተከታታይ በኢዮብ ንብረትና ልጆች ላይ ደረሰ። መርዶውንም ከአደጋው የተረፉ፣ ሁኔታውን ያዩ አራት ሰዎች በተከታታይ ለኢዮብ ነገሩት። ኢዮብ በዚህ ከባድ ፈተና ምን ተሰምቶት እንዴት ሆኖ ይሆን?! በውነት ሲመረመር ለሥጋ ለባሽ እጅግ የሚዘገንን፣ የሚያስቅቅ፣ እምነትን የሚያነዋውጥ፣ ሕሊናንም የሚበጠብጥ ነው። ጻድቁ ኢዮብ መርዶውን አንድ በአንድ ከአዳመጠ በኋላ፤ ሰከን ባለና በተረጋጋ መንፈስ፣ እንደ አገሩ ባሕል፣ ለጊዜው ተነሥቶ መጎናጸፊያውን ቀደደ፤ ራሱንም ተላጨ። ይኸም ባሕል የሚያመለክተው ሀብቱን ተገፈፍሁ፣ ብልጽግናዬ ተወገደ፣ የራሴ ክብር የሆኑ ልጆቼ አለቁ ሲል ልብሱን ቀደደ፤ ራሱን ተላጨ። ከዚህስ በኋላ ምን አደረገ? ፈጣሪውን ክዶ፣ ተሳድቦ፣ ተበሳጭቶ የማይገባ ሥራ ሠርቶ ይሆን? አምልኮቱን፣ ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅርና ታዛዥነት አጉድሎ ይሆን? መቼም እንደሚታወቀው የሰይጣን ዓላማው ሰውን በፈተና አስጨንቆ፣ ከፈጣሪው አምልኮትና ጸጋ ለይቶ፣ ለሥጋና ለነፍስ ኵነኔ ለመዳረግ ነው። ኢዮብ ግን ለሰይጣን ፈተና እጁን አልሰጠም። ለጊዜው በሰይጣን ተንኮል መፈተኑ ባይቀርም ድል አልሆነም። ሰይጣን ተስፋ ሊያስቆርጠው ወደ ጻድቁ መጣ። ታጋሹ ኢዮብ ግን ሰይጣንን ራሱን ተስፋ አስቆረጠው። እንዴት አድርጎ፣ በምን ጥበብ ተስፋ አስቆረጠው ቢሉ፤ የሚከተለው የኢዮብ ሕይወት አርአያነት ያስረዳናል። መጎናጸፊያውን ከቀደደና ራሱን ከተላጨ በኋላ፤ ጻድቁ አባታችን፣ የትዕግሥት መምህራችን ኢዮብ የብፅዕና ሥራ ሠራ። በምድር ላይ ተደፍቶ፣ ግንባሩን መሬት አስነክቶ ለፈጣሪው በትዕግሥት ሰገደ። በሃይማኖቱ፣ በምግባሩ ጸንቶ ሰይጣንን አሳፈረው። በትዕግሥቱ ለበለበው፤ አቃጠለው፤ ከሰገደ በኋላም እንዲህ አለ፡ "ራቁቴን ከእናቴ ማኅፀን ወጥቻለሁ፣ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ፤ እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚአብሔርም ነሣ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን።" (ኢዮብ. ፩:፩-፳፪)

በዚህ ምግባሩ፣ በዚህም ሃይማኖቱ፤ ኢዮብ በእውነት ታጋሽ፣



www.ethiopisnorthodox.org

እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ፍጹም፣ የበቃና ቅን ጻድቅ ሰው መኾኑን አረጋገጠ። ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰይጣን የቀረበበትን የፈተና ወጥመድ ሰባብሮ በጣጥሶ ጣለው። ድል ለኢዮብ፣ ኀፍረት ለሰይጣን ሆነ። ይኽ ጥንተ ጠላት ተንኮለኛ እባብ ሰይጣን በዚህ ድል ቢነሣም፤ ዳግመኛ ሌላ ተንኮል፣ ሌላ የአሸክላ ገመድ መተብተብ ጀመረ። ጀምሮም አልቀረ እንደገና ጻድቁን ለመፈታተን ፈቃድ ለማግኘት፤ መላእክት የአምላክ ልጆች ስለ ሰዎች ድኅነት በአማላጅነት ተግባር በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ሳለ፤ ይኽ ተንኮለኛ ቀበሮ ብቅ አለ። እንደተለመደው እግዚአብሔርም "ከወዴት መጣህ " ሲል ጠየቀው። ሰይጣንም "በምድር ላይ ዞርሁ በእርስዋም ተመላለስሁ።" ብሎ መለሰ፤ እግዚአብሔርም ሰይጣንን "በውኑ ባሪያዩ ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፣ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፣ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም። በከንቱም አጠፋው ዘንድ አንተ በእርሱ ላይ ምንም ብታንቀሳቅሰኝ እስከአሁን ፍጹምነቱን ይዟል።" ሲል የኢዮብን ጻድቅነት፣ የሰይጣንን ሐሰት ገለጸ። ሰይጣን ግን ሌላ ተንኮል ይዞ ስለነበር፤ ላለመሸነፍ፣ ላለመረታት በጥንተ ክፋቱ ጸንቶ እንዲህ አለ። "ቁርበት ስለ ቁርበት ነው፤ ሰው ያለውን ሁሉ ስለ ሕይወቱ ይሰጣል። ነገር ግን እጅህን ዘርግተህ አጥንቱንና ሥጋውን ዳብስ፤ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል። "ቀጥሎ እውነተኛው አምላክ እግዚአብሔር የሰይጣንን ውሸት፣ የኢዮብን እውነተኛነትና ፍጹምነት ለማጠየቅ "ሕወቱን ተወው እንጂ እነሆ እርሱ በእጅህ ነው" አለው። የሰዎች ባላንጣ ተንኮለኛው ሰይጣንም፤ ወጥመዱን ይዞ ኢዮብን ለመፈተን ገሰገሰ። ጻድቁ ኢዮብ የሚመጣበትን ፈተና አላወቀም፤ በድንገት ፈታኙ ጠሩን ወረወረበት፣ ከእግሩ ጫማ ጀምሮ እስከ አናቱ ድረስ በክፉ ቁስል መታው። ኢዮብም ሥጋውን ይፍቅበት ዘንድ ገል ወሰደ፣ በአመድም ላይ ተቀመጠ። ሚስቱም እስከአሁን ፍጹምነትህን ይዘሃልን? እግዚአብሔርን ስደብና ሙት አለችው።

ሰይጣን ቀድሞ ሔዋንን ከአታለለ በኋላ፤ አዳምን በሚስቱ አማካይነት ድል እንዳደረገ ስለሚያውቅ ኢዮብን በቀጥታ ማሳት ቢያቅተው፤ በሚስቱ ተጠቅሞ ረቂቅ የፈተና ጦር ሰነዘረ። የሚገርመው ግን በዚህ ሁሉ ፈተና ጻድቁ አልተበገረም። ታጋሹ ኢዮብ የትዕግሥትን ጥሩር ለበሰ፣ የሃይማኖት ጋሻውን አነሣ፣ አካሉ ሚስቱ እንዳትነዳበት በማሰብ እንዲህ ሲል መከራት። "እንቺዩ! ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገርሽ። ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፣ ክፉ ነገርንስ አንቀበልምን?" አላት እንጂ ኢዮብ በሐሳቡም በንግግሩም አልበደለም። ሰጭ፣ ነሽ እግዚአብሔር መኾኑን ማወቅ ብቻ ሳይሆን፤ በፍጹም የሚያምንበት እንደኾነ አስመሰከረ። በበጎ ምግባሩ፣ በፍጹም ትዕግሥቱ የእግዚአብሔር ክብር፣ ምስጋና የተገለጸበት፤ የበቃ፣ የነቃ መኾኑ ታወቀ፤ ተረዳ። ሰይጣን ከተፈቀደለት በደዌ ሥጋ ሰውን የሚቆማምጥ፣ የሚያተላና የሚያከረፋ እንደኾነ በኢዮብ ላይ በፈጸመው ደባ ታውቋል። የኢዮብ ሰውነት በሰይጣን የፈተና እሳት እንደ ወርቅ ነጠረ። የተወለወለ ዋጋው ከከበሩ አዕናቁ ሁሉ ብልጫ ያለው መኾኑ ተገለጸ።

ስለዚህ ነበር ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ "እነሆ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደታገሠ ሰምታችኋል፣ ጌታም እንደፈጸመለት አይታችኋል፤ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና።" (ያዕ. ፭:፲፩) በማለት፤ የኢዮብን ትዕግሥትና ብፅዕና ለክርቲቲያኖች ሁሉ አብነት አድርጎ የገለጸው። ስንቶቻችን ይሆን እኛ በማናውቀው ጎዳና በሰይጣን ስንፈተን፤ እግዚአብሔርን በማመስገን፣ ለስሙ በመንበርከክ ክብር የምንሰጠው? ከብፁዕ ኢዮብ ልንማር ይገባናል። ጻድቁን ሰው አብነት በማድረግ ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት ይኖርብናል። ሀብት፣ ልጆች፣ ጤንነት ሊጎለን ይችላል። አግኝቶ ማጣት፣ ከብሮ መዋረድ፣ ተወዶ መጠላት ቢገጥመን፤ የፈታኙ ሲሳይ እንዳንሆን መለስ ብለን ኢዮብን መመልከት አለብን። በጣም የሚቀርቡን ዘመዶቻችንና የልብ ጓደኞቻችንም በሰይጣን ተታለው ባላወቁት ምሥጢር ቢፈትኑን፤ እንደ ኢዮብ በትዕግሥት ሁነን ልንመክራቸው፣ ልናስተምራቸው ይገባናል። የኢዮብን ታሪክ ስንመለከት ያደረገው ገድል ይኽን የመሰለ ነውና እንከተለው። (ኢዮብ. ፪:፩-፲፫)

ኢዮብ በጽኑ ደዌ ሥጋ ተይዞ ለ፯ ቀንና ሌሊት ራሱን ሳያውቅ ተሠቃየ፤ ጓደኞቹ መጥተው አለቀሱለት፤ ዳሩ ግን ከሕመሙ የሚጋራው ወይም ሥቃዩን የሚያቃልልለት አልተገኘም። ኢዮብ በጽኑ ሥቃይ ለበርካታ ዘመናት መከራን ተቀበለ። ከ፴ ዓመት በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በዮርዳኖስ ፈሳሽ ወንዝ፣ በጸበል ተጠምቆ ተፈወሰ። ሀብቱ፣ ጤንነቱ፣ ልጆቹ እጥፍ ሆነው ተሰጡት። ዕድሜ ጠግቦ፣ የልጅ ልጅ አይቶ፣ በፍጻሜ ዘመኑ በደስታ ከዓለም ተለይቶ የሞት እንቅልፍ ሸለብ አለ። ይኽውም እንቅልፍ እስከ ትንሣኤ ዘጉባኤ የሚቆይ ነው። ነፍሱ ግን በዐጸደ ገነት በተድላ በደስታ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር እያመሰገነች፤ እስከ ቁርጥ ፍርድ ቀን ድረስ አለች፣ ትኖራለች። (ኢዮብ፤ ፵፪:፩-፲፯) ሰንክ መስከ ፩ቀን)

ርኩስ መንፈስ በጻድቁ ላይ ያመጣውን ተንኮልና ደባ ተመልክተናል። ኢዮብም በትዕፍሥቱ የሰይጣንን ተንኮል እንዳከሸፈበት አይተናል። ሰይጣን እስከዚህ ድረስ ጤና፣ ሀብት፣ ሕይወት በማሳጣት የሚፈታተን ከኾነ፤ ከሸንገላው ለመዳን የኢዮብን መንገድ ከመከተል ሌላ አማራጭ መፍትሔ እንደሌለን አውቀን፤ የመጣውን ፈተና ሁሉ በትዕግሥት መቀበል ይኖርብናል።

ለዚሁም የትዕግሥት ባለቤት መድኃኔዓለም ክርስቶስ በድንግል እናቱ አማላጅነት ይርዳን አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ይቀጥላል

ተዋሕዶ
ሲደክመን ግረፈን ጥላ ከለላዩ
ተዋሕዶ ለኔ ጋሻ መከታዬ ።
አበርቺኝ በጸሎት በስግደት በጾም
ጋሻ ሁኚኝ አጥግቤ ልጆቼ እንዲጸኑልኝ።
ተዋሕዶ መጠጊያ ተዋሕዶ ቤቴ
የዘወትር ተስፋ መመኪያ ሕይወቴ
የማትሰለቸኝ እውነተኛ እናቴ

ከደመ/ማርያም ልደቱ
ምዕራብ ሸዋ ዞን
ባንቱ ደ/ጽ.ቅ.ሚ.ቤ.ተ.ክ



www.ethiopisnorthodox.org

## ዓምደ ሃይማኖት

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

## ጋኔን የማውጣት ሀብት

ሲራክ ገብረክርስቶስ

ባለፈው ጽሑፍ በጋኔን ማውጣትና በመፈወስ ሀብት መካከል ስላለው ልዩነትና አንድነት በንጽጽር አመልክተን ነበር። ቀጥሎም ስለ ጋኔን ስሞች በተለያዩ ልሳናት ትርጉማቸውና ከመጽሐፍ ቅዱስ ስላለው ምስክር መጥቀሳችን ይታወሳል። አሁንም ደግሞ በዚህ ክታብ ርኩሳን መናፍስት በሰዎች ላይ ሲያድሩ ምን ዓይነት ጉዳት እንደሚያደርሱ በዝርዝር እናስረዳለን። በማስከተልም በርኩሳን መናፍስት የተለከፉ ወይም የተጎዱ ሰዎች ሥቃያቸው ምን እንደሚመስል ከብሉይና ከሐዲስ ማስረጃ በመጥቀስ ይተነተናል። ከዚህ በኋላም ጋኔን የማውጣት ጸጋ ወይም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሀብት ያላቸው ሰዎች አጋንንትን እንዴት ያወጧቸው እንደነበር ይተረካል። ለሁሉም "ያለ እኔ ረድኤት ምንም ምን መሥራት አይቻላችሁም" ያለ አምላክ ምሥጢሩን ይግለጽልንና መጻፍ ማንበብና ማስተዋል እንችል ዘንድ ጸጋውን ያሳድርብን አሜን።

ሀ) <u>ርኩሳን መናፍስት በሰዎች ላይ ሲያድሩ ስለሚያስከትሉት ጉዳት</u> :- የበጎ ነገር ተቃዋሚ ሰይጣን ወይም ርኩስ መንፈስ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሰዎችን ከማሳሳትና ከመተናኮል የተቆጠቡበት ጊዜ አልነበረም፣ የለም ወደፊትም አይኖርም። በጥንተ ተፈጥሮ ሰውን በማሳሳት ከእግዚአብሔር ያጣላ በነፍስና በሥጋው ጉዳት ያደረሰበት ሰይጣን ነው። ሐሰቱን እውነት አስመስሎ ጨለማውን ብርሃን፣ መራራውን ጣፋጭ፣ ክህደቱን ሃይማኖት እያለ ሲያታልልና በማታለል ላይ ያለ ባላጋራና አሳች ቢኖር ሰይጣን ነው።

በተለያዩ ስሞች የሚታወቀው ርኩስ መንፈስ ወይም ሰይጣን ሰዎችን በመቆራኘት እየለከፈ በሥጋዊ ኑሮአቸው፣ በጤንነታቸውና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያደረሰው ጉዳት ከአዳም ጀምሮ እስከ ሳሬ ድረስ ሥፍር ቁጥር የለውም። ነገር ግን በአጠቃላይ ርኩስ መንፈስ በሰው ላይ ሲያድር ስለሚያስከትለው ጉዳት መግለጽ ብቻ ይበቃል። ሰይጣን ተንኮሉን ሰውሮ ለሰው አሳቢ በመምሰል ወይ እራሱ በምትሐት ተገልጾ ወይም ከሥነ ፍጥረት በአንዱ ላይ አድሮ ከእግዚአብሔር ፍቅርና አምልኮት ለመለየት ይመክራል። ምክሩን ከተቀበሉት ኃጢአትን በሥራ ለማስፈጸም ያተጋል፣ ያስቸኩላል፣ እንቅልፍ ያሳጣል። ምክሩን በሥራ ላይ ከተረጎሙ ወይም ከፈጸሙለት በኋላ ግን ሰውነትን በመቆራኘት በነፍስ በሥጋ ያሰቃያል። በኃጢአይ ላይ ኃጢአትን፣ በመከራ ላይ መከራን ይደርባል። ደዌ ሥጋ በማምጣትም በሰዎች ላይ የተለያዩ ሥቃዮችን ያደርሳል። በአካል፣ በአእምሮና በነፍስ ላይ የሚያመጣቸው በሽታዎችና አደጋዎች እጅግ ብዙዎች ናቸው።

ለምሳሌ ጥቂቶቹን ብንጠቅስ እጅና እግርን ሽባ ያደርጋል። በዚህም ልክፍቱ ሰዎች እንዳይሠሩ፣ እንዳይንቀሳቀሱ በማድረግ የሰው ሸክም ተጠዋሪ ያደርጋቸዋል። ዓይንን በመከለል ያሳውራል። ዓይነ ልቡናንም ይሸፍናል ያደነቁራል አእምሮ ያቃውሳል ብስጭትን አሳድሮ አንጎል እንዲሆኑ እንዲያብዱ ያደርጋል። ከዛፍ ላይ ተወርውረው፣ ከፎቅ ወድቀው፣ወይም ከገደል ተገፍትረው ከባሕር ጠልቀው ሰጥመው ሕይወታቸው እንዲያልፍ ያደርጋል። በገዛ እጃቸው ታንቀው ተንጠልጥለው እንዲሞቱ፤ ኮረንቲ እንዲጨብጡ፤ ከእሳት ላይ እንዲወድቁ፤ በየመቃብሩ በየበረሀው እንዲንከራተቱ <u>በማድረግ</u> ያሰቃያቸዋል። ሕይወታቸውን በመከራና በአሰቃቂ ሞት ያሳልፋል። ርኩስ መንፈስ ሁልጊዜ ሰውን እያሳሳተ ወደ እግዚአብሔር እየከሰሰ ይተናኮላል። ሰውነትን ይቆማምጣል፣ ያቆስላል፣ እንዲሸት እንዲተላ ያደርጋል። በአገኘበት ቦታ እየጣለ አረፋ ያስደፍቃል፣ ያሸናል፣ አንደበትን ድዳ ጆሮን ደንቆሮ ያደርጋል። ልብን ያደክማል፤ ሰውነትን እንደ እሳት እንደ በርበሬ በማቃጠል ሌሊትና ቀን እንቅልፍ ያሳጣል። ራሱን በመሰወር የሕክምናና የወጌሻ ጥበብ እንዳይደርስበት በማድረግ የበሽታውን ዓይነት ወይም ምልክት በመቀያየር ግራ ያጋባል።

የሰውን አእምሮ በመጠምዘዝ ኃጢአትን እንዲያዘወትር፤ እንዲሰክር፣ እንዲያመነዝር፣ እንዲሰርቅ፣ እንዲቀማ፣ እንዲዋሽ፣ እንዲያታልል፣ ሰቶ እንዲያስት፣ ተጠራጥሮ እንዲያጠራጥር፣ ክዶ እንዲያስክድ ወዘተ... ሌላም ሌላም ያደርጋል። ርኩስ መንፈስ በሰው ልጆች ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ይኸንና ይኸንን ሲመስል በአጠቃላይ ደዌ ሥጋ ደዌ ነፍስ በመኾን የሚያሰቃይ የነፍስ የሥጋ ባላንጣ ባላጋራ መኾኑን በመገንዘብ ከተንኮሉ ለመጠበቅ በሃይማኖትና በምግባር ጸንቶ በእግዚአብሔር ኃይል መዋጋት ይገባል። ርኩሳን መናፍስት በሰዎች ላይ ሲያድሩ በነፍስና በሥጋ ስለሚያስከትሉት ጉዳት በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ነው። ከዚህ ቀጥሎ ከብሉይና ከሐዲስ በመጥቀስ በአጋንንት የተለከፉ ሰዎች ምን ምን ዓይነት ሥቃይ እንደደረሰባቸው ይተረካል።

ለ. <u>በጥንተ ተፈጥሮ ርኩስ መንፈስ በሰው ላይ ስላደረሰው ጉዳት</u> :- ሰይጣን የመጀመሪያዎቹን ሰዎች በተንኮሉ አሳስቶ ከመከራ ላይ እንደጣላቸው



www.ethiopisnorthodox.org

ከመተንተናችን በፊት በቅድሚያ ስለ ሰይጣን ተፈጥሮና ተግባር በአጭሩ ማወቅ ይኖርብናል። ሰይጣን (ዲያብሎስ) ሐሰተኛና የሐሰት አባት ነው። ትዕቢተኛም ነው። ፈጣሪ ነኝ ብሎ በትዕቢቱና በሐሰቱ የተዋረደ መልአካዊ ተፈጥሮ ያለው ነው። ከመጀመሪያ ጀምሮ ነፍሰ ገዳይ እንደ ኾነ በሥራው ታውቋል። በቃየል አድሮ አቤልን ያስገደለ የሰውን ዘር በሙሉ እያጣላ የሚያፋጅ ቂምና በቀልን በልቡና አሳድሮ ጥላቻን የሚያስፋፋ ክፉ መንፈስ ነው። ከቅዱሳን መላእክት ጋር በሰማይ ገጥሞ ከነሠራዊቱ ድል የተመታ የወደቀ የተዋረደ የእጋንንት ሁሉ አለቃ ዓለምን ሁሉ ያሳተ የመጀመሪያው ከይሲ (እባብ ዘንዶ) ተብሎ በግብሩ በክፋቱ የሚጠራ ነው። (ዮሐ. ፰:፵፬፤ ፩ዮሐ. ፫:፲፪ና፲፭ ፤ራዕይ. ፲፪:፺፤ ኢሳ. ፲፬:፲፪-፳፤ ሕዝ. ፳፰:፲፪-፲፱) ሰይጣን መልአካዊ ተፈጥሮ ያለው ክፉ መንፈስና አሳች ባላጋራ መኾኑን የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ከሞላ ጎደል ከረጅሙ በአጭሩ ስለሚያስረዱን ሌላ ተጨማሪ ማብራሪያ ማከል አስፈላጊ አይሆንም። ምክንያቱም ይኸው ራሱ በአጭሩ የተጠቀሰው ግንዛቤ ስለሚሰጠን ነው። ከዚህ ቀጥለን በጥንተ ተፈጥሮ በአዳም አባታችንና በእና ታችን በሔዋን ላይ ሰይጣን ስላደረሰው ጉዳት እንመለከታለን።

የአንድነት የሦስትነት ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር "ሰውን በመል ካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" ብሎ በነፍስና በሥጋ የከበረ በማድረግ በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ከፀሐይ በታች ገዛ ንዳ ብሎ እንደሾመው ቅዱስ መጽሐፍ በሥነ ፍጥረት አንቀጹ ከዚሁ ጋር በማያያዝም ሰውን በፆታ ወንድና ሴት አድርጎ በጋብቻ ሕግ አንድለአንድ ባለው አዋጅ አንድ አካል አንድ አምሳል እንዲሆኑ ፈቅዶዋል፣ ደንግጓል። ሥጋቸውን ከምድር ማለትም ከ፬ቱ ባሕርያተ ሥጋ ነፍሳቸውን እም ኀበ አልቦ ( ካለመኖር ወደ መኖር) አምጥቶ ለባዊነት ነባቢነትና ሕያውነት ባሕ ርይ ያላት አድርጎ ከሦት ጠባያት ፈጥሮዋል። እንደ ሰማያውያን መላእ ክት በጸጋ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ በንፍሐት (እፍ በማለት) የልጅነት ጸጋን (ሀብተ ወልድናን) ስላሳደረባቸው የእግዚአብሔር ልጆ ች ለመኾን በቅተዋል። (ዘፍ. ፪:፩-፺) አዳም በተፈጠረ በ፴ ቀኑ ሔዋን

በተፈጠረች በ፹ ቋኗ ልጅነት ተሰጥ ቷቸው በኤደን ገነት እንዲኖሩ መላእክት አሳረጉዋቸው። በእግዚአ ብሔር ፈቃድና ትዕዛዝ ኑሮአቸው በትፍሥሕተ ገነት በተድላ በደስታ ሆነ። (ዘፍ. ፪:፰-፲፯፤ ኩፋ. ፬:፱)

የፈጣሪና የፍጡር መታወቂያ ድንበርና ሕግ፣ ሥርዓት ስላስፈለገ እግዚአብሔር የቃል ትዕዛዝ ለፈጠረው ሰው ሠራ፣ ደነገገ። የተፈቀደለትን እንዲበላ ያልተፈቀደ ለትን ከመመኘትም ቀጥፎ ከመብ ላትም ከሌብነትና ከአመፀኛነት እንዲጠበቅ ለዚህ ምልክት የምትሆን ዕፀ በለስ የተባለች ክፉና ደግ የምታስታውቅ ዛፍ አበቀለ። ሰው ዕፀ በለስን ባይበላ ደግነቱ ታዛዥነቱ ደፍሮ ቀጥፎ ቢበላ ግን ክፋቱ ሌብነቱና አመፁ የሚታወቅባት ዛፍ ሆና የጾም የትሕርምት የእግዚአብ ሔር ሕግ አምሳል ሆና ተፈጠረች። ትዕዛዙን ተላልፎ ቢበላት የሞት ሞት ይደርስበታል። በነፍስና በሥ ጋው ይቀጣል። ፍጹም ተዋርዶ ያገኘዋል። ይኽን ያወቀ ፈጣሪ ሰው በነጻነቱ እንዳይባልግ በፈጣሪው ሕግ ተወስኖ እንዲኖር "ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታ ለህና" በማለት ጥብቅ ትዕዛዝ አዘዘው። (ዘፍ. ፬:፲፮-፲፯፤ ኩፋ. ፬:፲፰)

አዳምና ሔዋን የፈጣሪያቸውን ትዕዛዝ ጠብቀው ለሰባት ዓመት በኤዶም ገነት በተድላ በደስታ ኖሩ። (ኩፋ. ፬:፲፬) ከዚህ በኋላ የሰው ባላንጣ፣ ተጻራሪ ዲያብሎስ በእባብ ተሰውሮ ለማሳሳት ወደ ገነት ገባ። የእባብን አንደበት አንደበቱ አድርጎ ሔዋንን አታለላት። ለራሱ ፈልጎ አልሆንለት ያለውን አምላክነት በቅጠል ታገኛላችሁ ብሎ አሳሳታት። ሔዋን በከይሲ (ዲያብሎስ) ምክር ተጠልፋ ወደቀች። አወዳደቋም ብቻዋን ሳይሆን የኑሮ ጓደኛዋን አዳምንም ጨምራ ጣለችው። (ዘፍ. ፫:፩-፰) ከዚህ በፊት ዕርቃንነት አይሰማቸው የነበሩ ባልና ሚስት፣ ጸጋቸው ስለተገፈፈ፤ ባዶነት ተሰማ ቸው። በሰይጣን ምክር ተሰናክለው ከክብራቸው ወደቁ፤ ራቁታቸውን ቀሩ። ዛሬም ቢሆን ሰው በኃጢአቱና በክህደቱ ጸጋው ተገፎ ራቁቱን እንደሚቀር ተጽፎዋል። "እነሆ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ

ነው።" የተባለው ስለዚህ ነው። (ራዕይ.፲፮:፲፭ በሰይጣን ተንኮል በክፉ ምክሩ አደጋ ላይ የወደቁት አዳምና ሔዋን በነፍስ በሥጋ የደረሰባቸው ችግርና መከራ የነፍስና የሥጋ በሽታ በራሳቸው ላይ ብቻ ተወስኖ አልቀረም። በእነርሱ ምክንያት የሰው ዘር ሁሉ ተቀጣበት። ለድኅነተ ዓለም ምክንያት አድርጎ ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ ከጠበቃት ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በስተቀር ሰው ሆኖ ጸጋ ያልጎደለው መርገም ያልወደቀበት፣ በሰይጣን ቀንበር ያልተያዘ አለ ለማለት አይቻልም። በሰይጣን አሳችነት ሰው ነጻነቱን አጣ፤ በነፍስ በሥጋ ከጸጋ ተራቆተ። ገዢ የነበረው ሰው የሰይጣንና የኃጢአት ባርያ ሆነ። ተረገመ፣ ጣር ጋር ወደአለባት ምድረ ፋይድ እንዲወርድ ከገነት ተባረረ። ኀፍረት ፍርሃት ድንጋጤ ጭንቀት ወደቀበት። እሾህና አሜከላ በቀለበት። ፍትወታት እኩያት ኃጣውእ ሰፈሩበት። በሥጋው ልዩ ልዩ ሕመም በነፍሱ ኃጢአት ሰለጠነበት። ከዚህ ሁሉ መከራ ላይ የወደቀው የጠላቱን የሰይጣንን ምክር በመስማቱ የፈጣሪውን ቃል ባለማክበሩ ነው። ዛሬም ቢሆን የሰው ልጅ በነጻነቱ ካላወቀበት በንስሐ ወደ ፈጣሪው ተመልሶ የሕይወት ምግብና መጠጥ የሆነ የአማኑኤልን ሥጋውን ደሙን ካል ተቀበለ በጥምቀተ ክርስትና ከአጋ ንንት ቁራኝነትና አገዛዝ ነጻካል ወጣ፣ አጋንንት እንደ ጥንግ እንደ ሩር ወይም እንደ ኳስ የሚጫወ ቱበት ከንቱ ፍጡር መኾኑን መጠራጠር አይገባውም። (ዘፍ. ፫:፲-፳፬፤ ሮሜ. ፭:፲፯፤ ኢሳ. ፩:፱፤ ዕብ. ፪:፲፮፤ ዘፍ. ፳፪:፲፰፤ ሉቃ. ፩:፳፰ቁ. ፴፩-፴፫)

ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት ሰይጣን ገና ከመጀመሪያው አንስቶ ሰውን ከመከራ ላይ በመጣል ጉዳት ማድረሱን ተመልክተናል። ለክርስ ቶስ ክብር ምስጋና ይግባውና ከሰማ ያት ወርዶ፣ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፣ ሰይጣን በተንኮሉ በእባብ ተሰውሮ ቢጎዳን እርሱ ግን በሥጋ ማርያም በባሕርይ ተዋሕዶ ክብሩን ሰውሮ አድኖናል። ይኽን የማዳን ሥራውን አሞንዮስና አውሳብዮስ የተባሉ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በመቅድመ ወንጌል ሲመሰክሩ "ወበከመ ኮነ እንከ ሰይጣን በጉሕሉት ተኃብኣ ውስተ ሥጋ ከይሲ ከማሁ ኮነ ድኅነትነ እማዕሠር



www.ethiopisnorthodox.org

በተሠውሮተ ቃለ እግዚአብሔር በዘመድነ" ብለዋል። ትርጉሙም "ሰይጣን በተንኮል በሥጋ ከይሲ (በእባብ ሥጋ) እንደተሠወረ እኛም ከፍዳ መዳናችን ቃለ እግዚአብሔር በባሕርያችን በመሠወሩ ሆነ" ማለት ነው። የሊቃውንቱም አነጋገር ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን ክታቡ "ወከመ ቢጸሙ ኮነ ሎሙ ከመ በሞቱ ይስዐሮ ለመልአከ ሞት ዘውእቱ ሰይጣን ወያዕርፎሙ ለኵሎሙ እለ በፍርኃተ ሞት ተኮነኑ በኵሉ መዋዕለ ሕይወቶሙ ወተቀንዩ ለግብርናት" (ዕብ. ፪:፲፬-፲፭) ያለውን የሚመስል የሚተረጉም ነው።

የአንድምታ ፍቹም "እንደሳቸው ኾነላቸው በሞቱ መልአከ ሞትን ያጠፋው ዘንድ ይኸውም ሰይጣን ነው ባለ ዘመና ቸው ኹሉ ለግብርናተ ዲያብሎስ ተገዝተው የነበሩትን ዕረፍተ ነፍስ ሰጥቶ ያሳርፋቸው ዘንድ" ይላል። ሁሉም በምሥጢር አንድ ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በተዋሕዶ የተገለጸበት ምክንያት ሰይጣን ሰውን ለማጥቃት እባብን ሁኖ በእባብ ተሰውሮ ነድፎ የገደለውን የሰውን ባሕርይ አካል ለማዳን ነው። በዚህም መለኮታዊ ጥበቡ በትሕትና ሰውን ሁኖ በመገለጹ ድኅነተ ዓለም ተደርጓል። ሰይጣንን ድል ካደረገልን በኋላ ጸጋውን በማደል በሰይጣናት ላይ ሥልጣን እንዲኖረን አድርጓል። በክርስቶስ በማመን ጸንተው በጾምና በጸሎት የሚተጉ ክርስቲያኖች ሰይጣንን ከነሠራዊቱ በክርስቶስ መስቀል በማማተብ ስሙን በመጥራት ድል ያደርጉታል።

የክርስቲያን ልጆች በዚህ ዓለም በሕይወተ ሥጋ ቆይታቸው መንፈሳዊ ትጥቅ መታጠቅ ይኖርባቸዋል። ይኸውም ትጥቅ ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ያሳያቸው የእግዚአብሔር የጦር ዕቃ ነው። ቅዱሳን ሁሉ በዚህ የጦር ዕቃ ተሸልመው በገድል በትሩፋት ጸንተው በመዋጋታቸው መንፈሳዊ ጠላቶቻቸውን የጨለማውን ሠራዊት ድል እያደረጉ የጽድቅ አክሊል እየተቀዳጁ ወደ ፈጣሪያቸው ሄደዋል። እኛም ችላ ሳንል ትጥቃችንን ማሳመር ይኖርብናል። ለመኾኑ ሐዋርያው ታጠቁ ያለን መንፈሳዊ የጦር መሣሪያ ምን ምን ይሆን? አውቀን ለመታጠቅ የተዘጋጀን እንሁን።

ሐዋርያው " <u>እንከሰ ጽንዑ በእግዚአብሔር ወበጽንዐ ኃይሉ ወልበሱ ወልታ እግዚአብሔር በዘትክሉ ተቃውሞቶ ለመናግንተ ሰይጣን"</u> (ኤፌ. ፮: ፲-፲፮ ) ይላል። በአማርኛው ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ "በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን እቃ ጦር ሁሉ ልበሱ" ተብሎ ተወስዷል (ተተርጉሟል)

ሰይጣን ከጥንት ጀመሮ ሰውን በመቃወም በክፋቱ ጸንቶ እንደሚዋጋ ታውቋል። ምንም እንኳን ሰይጣን በተፈጥሮ መልአካዊ ኃይል ያለው ቢሆንና እኛ ሰዎች ደግሞ በሥጋና በደም ያለን ደካሞች ብንሆንም፣ ሰይጣንን ለመቃወም ክርስቶስ በሰጠን መንፈሳዊ መሣሪያ በመጠቀም ድል ልናደርገው እንደምንችል በእግዚአብሔር ላይ እምነታችን የጸና ሊሆን ይገባዋል።

ሐዋርያው ለኤፌሶን ክርስቲያኖች የላከላቸው መልዕክት ለእኛም መኾኑን አውቀን ልንጠቀምበት ይገባናል። የሐዋርያው ምክር የሚያስገነዝበን በእግዚአብሔር በማመን መጽናት እንዳለብንና በከሃሊነቱ አጋዥነት ጸንተን ጠላታችንን መዋጋት እንዳለብን ነው። "ሰይጣን በተንኮሉ የሚያመጣባችሁን ጦር ድል መንሣት በሚቻላችሁ ገንዘብ አላባሽ ጋሻ ያዙ" ማለቱ ድል የምታደርጉበትን ሃይማኖት ያዙ ሲለን ነው። ምክንያቱም ያለ ሃየማኖት ጋሻነት ከሰይጣን የሚሰነዘርብንን የማሳት ጦር መመከት ስለማንችል ነው። እንግዲህ ከትጥቃችን መማከል አንደ ጋሻ ያለ መሣርያ ሃይማኖት ነው ማለት ነው። ይህ ሐዋርያ በሃይማኖት ጋሻነት መከላከል እንዲገባን መግለጹ ትግላችን ፍልሚያችን እንደ እኛ ሥጋዊ ደማዊ ከኾኑ ፍጡራን ጋር ሳይሆን በዓለሙ ሁሉ ተሰራጭተው በአራቱ መዓዘን ካሉ የጨለማውን ዓለም ከሚገዙ ከአጋንንት ጋር በመኾኑ ነው። ይኸንንም ሲያስገነዝብ "<u>እስመ ቀትልክሙ ኢኮነ ምስለ ዘሥጋ ወደም ዘእንበለ ምስለ መኳንንተ ጽልመት ወአጋንንት እኩያን እለ መትሐተ ሰማይ። ወበእንተዝ ንስኡ ወልታ እግዚአብሔር ከመ ትክሀሉ ተቃውሞታ ለዕለት ዕኪት ወኩኑ ድልዋነ በኵሉ ከመ ትጽንዑ"</u> ( ቁጥር ፲፪ ተመክለት) ብሎ ይገልጸዋል። ትርጉሙም "ሰልፋችሁ ከሥጋዊ ከደማዊ አርበኞች ጋር አይደለምና በአራቱ መዓዘን ካሉ ዓለመ ጽልመትን ከሚገዙ ከአጋንንት ጋር ነው እንጂ" ስለዚ ህም ዋልታ እግዚአብሔርን ያዙ። ማለት የእግዚአብሔርን ጋሻ ያዙ ሃይማኖትን ያዙ ዕለት እኪትን (ክፉ ቀንን) መቃወም ትቻላችሁ ዘንድ መቃወም እንዳይገኙ መኾን ቢገኙም እንዳይጎዱ መኾን ነው። ዕለተ እኪት (ክፉ ቀን) የተባለችው ኃጢአት የሚሠሩባት ቀን ናት። ዳግመኛም ዕለተ ሞት፣ ዕለተ ምጽአት ናት ድል ትነሡ ዘንድ በሥራው ኹሉ የተዘጋጃችሁ ኹኑ።" ማለት ነው። ቀጥሎም የትጥቁን ዓይነት ከቁጥር ፲፬ እስከ ፲፰ በማከታተል ይገልጸዋል። "ወገባችሁን በጽድቅ ዝናር (ቀበቶ) ታጠቁ "ይላል። ንጽሕናን በልቡናችሁ ይዛችሁ ኑ ማለቱ ነው። " <u>ወልበሱ ልብሰ ሐፂን ዘጽድቅ"</u> ይላል። "የጽድቅን ጥሩር ልበሱ ማለት ትዕግሥትን ያዙ። "ተሰኢነ ክሙ ኃይለ ወንጌል ዘበሰ ላም" ይላል። ኃይል የሚኾናችሁ ጫማን ተጫምታችሁ አለ። ምግባረ ወንጌልን ይዛችሁ ኑ ሲል ነው።

"<u>ወምስለዝ ኵሉ ንሥኡ ንዋየ ሐቅል ዘሃይማኖት በዘትክሉ እጥፍአተ ኵሉ አሕፃሁ ለእኩይ ርሱን"</u> ይላል። ይህም ይህ ነው ከዚህም ጋር የልዳ ጸብት ያዙ አለ አምኖ የሚጠመቁትን ጥምቀትን ያዙ። እንደ እሳት የሚነድ የሰይጣንን ፍላፃ ማጥፋት በሚቻላችሁ ገንዘብ ጥምቀትን ያዙ አለ። በአርበኛ አምሳል ተናገረ። የወዲያኛው ማለትም ጠላት ቀስቱን እያተባ እያጋለ መርዝ እየቀባ ይመጣል። የወዲህኛውም ማለት ተፋላሚው ጥበቡን እግዚአብሔር ገልጸለት ጆባውን ከውኃ ነክሮ ለጋሻው አልብሶ ይይዛል። ስለቱን ጋሻው ይፋታለታል፣ መርዙን ጆባው ይጠርግለታል። ግለቱን ውኃው ያቀዘቅዝለታል። እንደዚህም ኹሉ ከጥምቀት ባገኙት ኃይል ድል ይነሡታልና።

"<u>ወንሥኡ ጌራ መድኃኒት ላዕለ ርእስክሙ ወሰይፈ ዘመንፈስ ቅዱስ ንሥኡ በእደዊክሙ ዘውእቱ ቃለ እግዚአብሔር በኵሉ ጸሎት ወሰእለት እንዘ ትጼልዩ በኵሉ ጊዜ በመንፈስ ትግሁ ወተፀመዱ ለጸሎት ኩሎ ጊዜ በእንተ ኵሎሙ ቅዱሳን።</u> " ይላል (በራሳችሁም ቦርቦርቴ (ራስ ቁር) ድፉ አለ። ተስፋ ትንሣኤን ያዙ



www.ethiopisnorthodox.org

በእጃችሁም የመንፈስ ቅዱስን ሰይፍ ያዙ አለ። በቃላችሁ አቡነ ዘበሰማያት ድገሙ ይኸውም ወንጌል ነው። በሥጋዊ አርበኛ አምሳል ተናገረ፤ እስራኤል ከግብጽ ሲወጡ ይህን አድርገው ወጥተዋልና፤ጫማቻውን አድርገው፣ ኩፌታቸውን ደፍተው፣ ዝናራቸውን ታጥቀው በሎታቸውን ይዘው ወጥተዋል" (ዘፀ. ፲፪:፲፩) አንድም በመንፈሳውያን አርበኞች አምሳል ተናገረ፤ እንደ ቦርቦርቴ ቆብ፣ እንደ ጦር አንካሴ (በትረ መስቀል) እንደ ጥሩር መቋረፊያ፣ እንደ ዝናር የለፉ መታድ፤ እንደ ጫማ ነጠላ ጫማ፤ እንደ ጋሻ ተረንተር አድርገው ወጥተው ወርደው ረቂቃን ጠላቶቻቸው አጋንንትን ድል ይነሣሉና።

በምትጸልዩት ጸሎት በምትለምኑት ልመና ኹሉ አቡነ ዘበሰማያት ድገሙ። በጊዜያቱ ኹሉ አለ በ፯ቱ፣ በ፳፬ ጊዜያት ስትጸልዩ በልቡና ተግታችሁ ለጸሎት ኹል ጊዜ ጽሙዳን ኾናችሁ ኑሩ። በጸሎት የተጠመዳችሁ ሁኑ። ስለ ቅዱሳን ሁሉ ጸልዩ ( ስለ ክርስቲያናች ጸልዩ በጥምቀት ከኃጢአት በሃይማኖት ከክህደት በወንጌል ከአሪት ተለይተዋልና ምእመናንን ቅዱሳን አላቸው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የክርስቲያናችን መንፈሳዊ ትጥቅ ዘርዝሮ ካስረዳ በኋላ ጠላቶቻቸው ረቂቃን አጋንንትን እንዴት አድርገው ማሸነፍ እንዳለባቸው አመልክቷል።

እኛም ይኸን እግዚአብሔራዊ መንፈሳዊ ትጥቅ ልንለብሰው ይግባናል። እንደ ጋሻ ተዋሕዶ ሃይማኖትና የክርስትና ጥምቀት፣ እንደ ዝናር ንጽሕና፣ እንደ ራስ ቁር (ቦርቦርቴ) ተስፋ ትንሣኤ፣ እንደ ጥሩር ትዕግሥት፣ እንደ ጫማ ምግባረ ወንጌል (ፍቅር አንድነት) እንደ ሰይፍ አቡነ ዘበሰማያት፣ ቃለ እግዚአብሔር ወንጌል ትጥቃችን ሊኾኑ ይገባል።

በመንፈሳዊ ትጥቅ ተላብሰን፣ ተዘጋጅተን፤ እግዚሐብሔ ርን በማመን ጸንተን፣ በክርስቶስ ኃይል ሁሉን በሚያቸንፍ ከኃሊነቱ ተማምነን፣ ረቂቃን ጠሳቶቻችንን ድል አድርገን፣ የድል ባለቤቶች ሆነን አበው ጻድቃን ሰማዕታት የጽድቅ አክሊል ተሳታ ፊዎች እንድንሆን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በኃይለ መስቀሉ ይርዳ ን። እናቱ ድንግል ማርያምም በጸሎቷ የአጋንንትን ኃይል ታድ ክምልን። አሜን።

መስብሐት ለእግዚብሔር።

ይቀጥላል።



www.ethiopisnorthodox.org

## ዓምደ ሃይማኖት

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

## ጋኔን የማውጣት ሀብት

ከሊራክ ገብረክርስቶስ

ርኩስ መንፈስ በጻድቁ ኢዮብ ላይ ስላመጣው የፈተና ፃርና ታጋሹ ኢዮብም ፈተናውን ሁሉ በጸጋ ተቀብሎ ሰይጣንን በማሳፈሩ፤ ለመላው ክርስቲያን የትዕግሥት አብነት እንደሆነ ባለፈው ጽሑፍ የተከተበውን አይተናል። ከዚያው በመቀጠል ርኩሳን መናፍስት በሰው ልጆች ላይ ስለሚያደርሱት ጉዳት ከመጽሐፍ ቅዱስ ከብሉይና ከሐዲስ ያንዳንዶቹን ገጠመኝ ከዚህ ላይ ለመግለጽ እንወዳለን። አንባብያን በተለመደው መንፈሳዊ አትኩሮት በጥሞና እንድትከታተሉት ከማሳሰብ ጋራ ምሥጢሩን ለሁላችንም እንዲገልጽልን የትንሣኤው ባለቤት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን። በልጇ ስቅለት ስታዝን የነበረች በትንሣኤው ብርሃን የተጽናናች ወላዲተ አምላክ ጸመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም የመንፈስ ቅዱስ ሀብት የማይቱተዋል ጥበብ እንዲሰጠን በጸሎቷ ትርዳን አሜን።

### መ. መንፈስ ርኩስ በንጉሥ ሳኦል ላይ ስላደረሰው ጉዳት :-

ሳኦል የብንያማዊው የቂስ ልጅ ነው። የአባቱ አህዮች ቢጠፉ ለመፈለግ ሂዶ ያጣቸዋል። ከሳኦል ጋር ሊያፋልገው የሄደ ብላቴና የእግዚአብሔርን ሰው ባለ ራዕዩን ሳሙኤልን ብንጠይቀው አህዮቻችን ያሉበትን ሥፍራ ሊነግረ ይችላልና እንሂድ አለው። በዚህ ጊዜ ሳኦል እነሆ እንሄዳለን ነገር ግን ለእግዚአብሔር ሰው ምን እናመጣለታለን እንጀራ ከከረጢታችን አልቆብናልና እጅ መንሻም የለንምና ለእግዚአብሔር ሰው የምናመጣለት ምን አለን? አለው። ብላቴናውም ሲመልስለት እነሆ በእጄ የሰቅል ብር ሩብ አለኝ፤ (፫.፩ ግራም የሚመዝን ነው) እርሱንም መንገዳችንን እንዲነግረን ለእግዚአ ብሔር ሰው እሰጠዋለሁ አለው። (ቀድሞ ባለ ራዕይ የሚባለው በዛሬው አነጋገር ነቢይ እንደሚባል እናስተውል) ሰዎች ከእግዚአብሔር ምሥጢራዊ የኾነ አንድ ጉዳይ፣ ለመጠየቅ ሲፈልጉ ወደ ባለራእይ ይሄዳሉ። በዚህ ትውፊት ነበር ባለ ራእዩን ለመጠየቅ ያሰቡት።

ሳኦልም ብላቴናውን "የተናገር ኸው መልካም ነው፤ ና እንሂድ" አለውና የእግዚአብሔር ሰው ወዳለበት ከተማ ሄዱ፣ ዳገቱን ለመውጣት ተያይዘውት ሳለ፣ ውኃ ለመቅዳት የሚወጡ ቆንጃጆች (ልጃገረዶች) አዩ፤ ባለ ራእዩ የሚገኝበትን ቤት ጠየቋቸው። ቆንጃጆቱም በምን አኳኋን ሊያገኙት እንደሚችሉ በዝርዝር ነግረው መንገድ አሳይዋቸው። ሳኦልና ብላቴናውም እየተጓዙ ሳለ ሳሙኤል መጣ። ሳኦል ከመምጣቱ ከአንድ ቀን በፊት እግዚአብሔር ለሳሙኤል የገለጠለት ምሥጢር ነበር። "ነገ በዚህች ሰዓት ከብንያም አገር አንድ ሰው እሰድልሃለሁ ልቅሶአቸው ወደ እኔ የደረሰ ሕዝቤን ተመልክቻለሁና ለሕዝቤ ለእስራኤል አለቃ ይሆን ዘንድ ትቀባዋለህ። ከፍልስጥኤማውያን እጅ ሕዝቤን ያድናል" የሚል ትእዛዝ ደርሶት ነበር። እውነትም እንደተባለው ሆነ፤ ሳኦል በጉዞ ላይ ሳለ ገና ከሩቅ እግዚአብሔር ዳግመኛ ለሳሙኤል "ያ የነገርሁህ ሰው እነሆ፤ እርሱም በሕዝቤ ላይ ይሠለጥናል" አለው።

በዚህን ጊዜ ሳኦል በበሩ ወደ ሳሙኤል ቀርቦ ነበር። አላወቀውም ነበርና "የባለ ራእዩ ቤት ወዴት እንደሆነ እባክህ ንገረኝ" አለው፤ ሳሙኤልም መልሶ ሳኦልን "ባለ ራእዩ እኔ ነኝ፤ ዛሬም ከእኔ ጋር ትበላላችሁና በፊቴ ወዳለው ወደኮረብታው መስገጃ ውጡ፤ ነገም አሰናብትሃለሁ፣ በልብህም ያለውን ሁሉ እነግርሃለሁ፣ ከሦስት ቀንም በፊት የጠፉ አህዮችህ ተገኝተዋልና ልብህን አትጣልባቸው፤ የእስራኤል ምኞት ለማንነው? ለአንተና ለአባትህ ቤት አይደለምን?" አለው።

ሳኦልም መለሰ እንዲህም አለ "እኔ ከእስራኤል ነገዶች ከሚያንስ ወገን የሆንሁ ብንያማዊ አይደለሁምን? ወገኔስ ከብንያም ነገድ ወገኖች ሁሉ የሚያንስ አይደለምን? እንዲህስ ያለውን ነገር ለምን ነገርኸኝ?" አለው። ከዚህ የሐሳብ ልውውጥ በኋላ ሳኦልና ብላቴናውን ወስዶ ወደ አዳራሽ አገባቸው። በመርፈቂያውም ራስ አስቀመጣቸው። ወጥ ቤቱንም "ባንተ ዘንድ አኑረው ብዬ የሰጠሁህን ዕድል ፈንታ አምጣ" አለው፤ ወጥ ቤቱም ጭኑንና በእርሱ ላይ የነበረውን አምጥቶ በሳኦል ፊት አኖረው።

ሳሙኤልም "ሕዝቡን ከጠራሁ ጀምሮ እስከ ተወሰነው ጊዜ ድረስ ላንተ ተጠብቋልና እንሆ የተቀመጠልህን በፊትህ አኑረህ ብላው" አለ። በዚያን ቀን ሳኦል ከሳሙኤል ጋር በላ። ከኮረብታውም መስገጃ ወደ ከተማይቱ ወረዱ፤ ሳሙኤልም ለሳኦል በሰገነቱ ላይ መኝታ አዘጋጀለት እርሱም ተኛ። ማልደውም ተነሡ፣ በነጋም ጊዜ ሳሙኤል ሳኦልን ከሰገነቱ ጠርቶ "ተነሥና ላሰናብትህ" አለው። ሳኦልም ተነሣ እርሱና ሳሙኤልም ሁለቱ ወደሜዳ ወጡ እርሱም በከተማይቱ ዳር ሲወርዱ ሳሙኤል ሳኦልን "ብላቴናውን ወደ ፊታችን እንዲያልፍ እዘዘው አንተ ግን የእግዚአብሔርን ቃል እሰማህ ዘንድ በዚህ ቁም" አለው። ብላቴናውም አለፈ። ሳሙኤልም የዘይቱን ብርሌ ወስዶ በራሱ ላይ አፈሰሰው። ሳመውም፤ እንዲህም አለው "በርስቱ ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ እንዚአብሔር ቀብቶሃል። የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ትገዛ ለህ፤ በዙሪያውም ካሉ ጠላቶቻቸው እጅ ታድናቸዋለህ። ዛሬ ከእኔ በተለየህ ጊዜ በብንያም ዳርቻ በጼልጻህ አገር



www.ethiopisnorthodox.org

ባለው በራሔል መቃብር አጠገብ ሁለት ሰዎች ታገኛለህ፤ እነርሱም ልትሻቸው ሄደህ የነበርህላቸው አህዮች ተገኝተዋል፤ እነሆም አባትህ ስለ አህዮች ማሰብ ትቶ የልጁን ነገር እንዴት አደርጋለሁ እያለ ስለ እናንተ ይጨነቃል ይሉሃል።

ከዚያም ደግሞ ወደ ፊት ትሄዳለህ፣ ወደ ታቦር ወደ ትልቁ ዛፍ ትደርሳለህ፣ በዚያም ሦስት ሰዎች አንዱ ሦስት ፍየል ጠቦቶች፣ ሁለተኛው ሦስት ዳቦ፣ ሦስተኛውም የወይን ጠጅ አቁማዳ ይዘው ወደ እግዚአብሔር ወደ ቤቴል (ቤተእግዚአብሔር) ሲወጡ ያገኙሃል፤ ሰላምታም ይሰጡሃል፤ ሁለትም ዳቦ ይሰጡሃል፤ ከእጃቸውም ትቀበላለህ።

ከዚያም በኋላ የፍልስጥኤማውያን ጭፍራ ወዳለበት ወደ እግዚአብሔር ኮረብታ ትመጣለህ፤ ወደዚህም ወደ ከተማይቱ በደረስህ ጊዜ በገናና ከበሮ፣ እምቢልታና መሰንቆ ይዘው ትንቢት እየተናገሩ፤ ከኮረብታው መስገጃ የሚወርዱ የነቢያት ጉባዔ ያገኙሃል። የእግዚአብሔርም መንፈስ በኃይል ይወርድብሃል፣ ከእነርሱም ጋር ትንቢት ትናገራለህ፣ እንደሌላ ሰውም ሆነህ ትለወጣለህ እነዚህም ምልክቶች በደረሱህ ጊዜ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና እጅህ የምታገኘውን ሁሉ አድርግ ብሎ፤ ዝርዝር መመሪያ ከዚሁ ጋር አያይዞ ሰጠው። ምልክቶቹም አንድ በአንድ ተፈጸሙ። በእስራኤል ላይ ተቀብቶ ነገሠ። (ሳሙ. ቀዳ. ፱:፩-፳፯፣፲:፩-፲፫፣ቁ. ፳፭-፳፯)

ሳኦል በነገሠ ከወር በኋላ አሞናዊው ናዖስ በኢያቢስ ገለዓድ ሰፈረ። የኢያቢስም ሰዎች ሁሉ "ቃልኪዳን አድርግልን እኛም እንገዛልሃለን" አሉት። ናዖስ ግን በትዕቢት ልቡን እንደ ሻኛ አሳብጦ በትምክህትና በእብሪት "ቀኝ ዓይናችሁን ሁሉ በማውጣት ቃልኪዳን አደርግላችኋለሁ፤ በእስራ ኤልም ሁሉ ላይ ስድብ አደርጋለሁ" አላቸው። ይኸን ሁኔታ የኢያቢስ ሽማግሌዎች ዝም ብለው በቸልታ ሳያልፉት ለእብሪተኛው ናዖስ "ወደ እስራኤል አገር ሁሉ መልእክቶችን እንድንልክ ሰባት ቀን ቆይልን፤ ከዚያም በኋላ የሚያድነን ባይኖር ወደ አንተ እንመጣለን" አሉት። እንድተናገሩትም መልእክተኞች ላኩ።

በዚህ ነገር እስራኤላውያን ተጨንቀው ሲላቀሱ ሳኦል ሰማ። የእግዚአብሔር መንፈስም በሳኦል ላይ በኃይል ወረደ፤ ቁጣውም እጅግ ነደደ። ጥማዱንም በሬዎች ወስዶ ቆራረጣቸው፤ ወደ እስራኤልም ዳርቻ ሁሉ በመልእክተኞች እጅ ሰደደና "ሳኦልንና ሳሙኤልን ተከትሎ የማይወጣ ሁሉ፤ በበሬዎቹ እንዲሁ ይደረግ" አለ። ድንጋጤም በሕዝቡ ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደቀ፤ እንደ አንድ ሰውም ሆነው ወጡ። በቤዜቅም ቆጠራቸው፤ የእስራኤ ልም ልጆች ሦስት መቶ ሺህ፣ የይሁዳም ሰዎች ሠላሳ ሺህ ነበሩ። የመጡትንም መልእክተኞች፤ የኢያቢስ ገለዓድን ሰዎች ነገ ፀሐይ በተኮሰ ጊዜ ማዳን ይሆንላችኋል በሉአቸው አሉአቸው። መልእክተኞችም መጥተው ለኢያቢስ ሰዎች ነገሩ፤ ደስም አላቸው። የኢያቢስም ሰዎች ነገ እንወጣላችኋለን ደስ የሚያሰኛችሁንም አድርጉብን አሉ።

በነጋውም ሳኦል ሕዝቡን በሦስት ወገን አደረጋቸው። ወገግም ባለ ጊዜ ወደ ሰፈሩ መካከል ገቡ። ቀትርም እስኪሆን ድረስ አሞናውያንን መቱ። የቀሩትም ተበተኑ፤ ሁለቱም በአንድ ላይ ሆነው አልቀሩላቸውም። ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት ንጉሥ ሳኦል በነቢዩ ተቀብቶ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ካገኘ በኋላ፤ ሕዝቡን የሚታደግ እንደኾነ እናስተውላለን። (ሳሙ.ቀዳ: ፲፩:፩-፲፭) ወደ እግዚአብሔር አመልክትልን ስላሉት ሳሙኤል ሕዝቡንና ንጉሣቸውን ሳኦልን ጠርቶ "መልካሙንና ቅኑን መንገድ አስተምራችኋለሁ እንጂ፤ ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ። ብቻ እግዚአብሔርን ፍሩ፣ ያደረገላችሁንም ታላቅ ነገር አይታችኋልና በፍጹም ልባችሁ በእውነት አምልኩት፤ ነገር ግን ክፉ ብትሠሩ እናንተም ንጉሣችሁም ትጠፋላችሁ" አላቸው። (ሳሙ.ቀዳ. ፲፪:፲፱-፳፭)

ንጉሥ ሳኦል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ፣ በሳሙኤል የተነገረውን ቃል በራሱ ሐሳብ እየለወጠ በመተላለፉ እግዚአብሔር ተቀየመው። ለሳሙኤልም የሳኦልን ጥፋት ነገረው። "ሳኦል እኔን ከመከተል ተመልሶአልና፣ ትእዛዜ ንም አልፈጸመምና ስላነገሥሁት ተጸጸትሁ" አለ። (ሳሙ. ቀዳ. ፲፭:፲-፲፩) የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ሳኦል የተነገረውን በሰማ ጊዜ ነቢዩ ሳሙኤል እጅግ ተቆጣ። ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፤ በነጋውም ሳኦልን ለማግኘት ማለደ። በጌልገላም አገኘው።

ሳኦልም ምንም ኃጢአት እንዳልሠራ ሰው፤ ዓይኑን በጨው አጥቦ በመመጻደቅ፣ እንዲህ ይል ጀመር "አንተ ለእግዚአብሔር የተባረክህ ሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፈጽሜአለሁ" አለ። ሳሙኤል ግን መልሶ "ቆይ እግዚአብሔር ዛሬ ሌሊት የነገረኝን ልንገርህ" አለው። እርሱም ተናገር አለው። ሳሙኤልም አለ "በዓይንህ ምንም ታናሽ ብትሆን ለእስራኤል ነገዶች አለቃ አልሆንህምን? እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ንጉሥ ትሆን ዘንድ ቀባህ፤ እግዚአብሔርም ሄደህ ኃጢአተኞቹን አማሌቃውያንን ፈጽመህ አጥፋቸው። እስኪጠፉም ድረስ ውጋቸው ብሎ በመንገድ ላከህ። ለምርኮ ሳስተህ ለምን የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማህም? ለምንስ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረግህ?" ሳኦልም ሳሙኤልን "የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቻለሁ፤ እግዚአብሔርም በላከኝ መንገድ ሄጃለሁ፤ የአማሌቅን ንጉሥ አጋግን አምጥቻለሁ፤ አማሌቃውያንንም ፈጽሜ አጥፍቻለሁ፤ ሕዝቡ ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር በጌልገላ ይሠው ዘንድ ከእርሙ የተመረጡትን በጎችንና በሬዎችን ከምርኮው ወሰዱ" አለው።

ሳሙኤልም መልሶ "በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው፤ እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ መታዘዝ ከመሥዋዕትነት ፣ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል። ዓመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፣ እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደማምለክ ነው፤ የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳትሆን ናቀህ" አለው። ሳኦልም ሳሙኤልን "ሕዝቡን ስለፈራሁ፣ ቃላቸውንም ስለ ሰማሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝና የአንተን ቃል በመተላለፍ በድያለሁ። አሁንም እባክህ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ ለእግዚአብሔርም እሰግድ ዘንድ ከእኔ ጋር ተመለስ" አለው። ሳሙኤልም ሳኦልን "የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና፣ እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዳትሆን ንቆሃልና ከአንተ ጋር አልመለስም።" አለው። ሳሙኤልም





www.ethiopisnorthodox.org

ሊሄድ ዘወር ባለ ጊዜ፤ ሳኦል የልብሱን ጫፍ ያዘ፤ ተቀደደም። ሳሙኤልም "እግዚአብሔር የእስራኤልን መንግሥት ዛሬ ከአንተ ቀደዳት፤ ከአንተም ለሚሻል ለጎረቤትህ አሳልፎ ሰጣት፤ የእስራኤል ኃይል እንደ ሰው የሚጸጸት አይደለምና አይዋሽም፣ አይጸጸትም።" አለው። እርሱም "በድያለሁ አሁን ግን በሕዝቤ ሽማግሌዎች ፊትና በእስራኤል ፊት እባክህ አክብረኝ፤ ለአምላክህም ለእግዚአብሔር እሰግድ ዘንድ ከእኔ ጋር ተመለስ" አለው።

ንጉሥ ሳኦል የእግዚአብሔርን ቃል በተደጋጋሚ በመተላለፍ በራሱ ፈቃድ በመመራቱ፤ ንስሐውም ለታይታ፣ በሰው ዘንድ ለመከበር ከመፈለግ አንጻር እንጂ እውነተኛ ባለመኾኑ፤ ከእግዚአብሔር አንድነት፣ ከተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት ሊለይ ችሏል። ምንም እንኳን ሳሙኤል ለሳኦል ምሕረትን በመጠየቅ ቢያለቅስለት፤ የእግዚአብሔር መልስ ግን "በእስራኤል ላይ እንዳይነግሥ ለናቅሁት ለሳኦል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው?" ብሎ ከነገረው በኋላ፤ ከእሴይ ልጆች አንዱን እንዲቀባ ወደ ቤተልሔም ላከው። እንደ ትእዛዙም ሳሙኤል ዳዊትን ቀባው። (ሳሙ.ቀዳ. ፲፭:፩-፴፭፣ ፲፮:፩-፲፫)። በቅብዓ መንግሥት ምክንያት፤ አድሮበት የነበረው ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ከሳኦል የራቀው ባለመታዘዙ ነበር። በእርሱም ፈንታ በእሴይ ልጅ በብላቴናው በዳዊት ላይ መንፈስ ቅዱስ ማደሩ ተገልጧል። ይኸንንም ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚከተለው ይገልጸዋል። "የእግዚአብሔርም መንፈስ ከሳኦል ራቀ። ክፉ መንፈስም ከእግዚአብሔር ዘንድ አሠቃየው። የሳኦልም ባሪያዎች እነሆ ክፉ መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያሠቃይሃል፤ በገና መልካም አድርጎ የሚመታ ሰው ይሹ ዘንድ ጌታችን በፊቱ የሚቆሙትን ባሪያዎቹን ይዘዝ፤ ከእግዚአብሔርም ዘንድ ክፉ መንፈስ በሆነብህ ጊዜ በእጁ ሲመታ አንተ ደኅና ትሆናለህ አሉት" ይላል።

ሰው የሥጋውን ፍላጎትና የግል አስተሳሰቡን ተከትሎ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ሲወጣ፤ ወይም በሌላ አባባል እግዚአብሔር በቅዱሳን አማካይነት የነገረውን ትእዛዝ ከፊሉን በመፈጸም ሌላውን በማሻሻል ፍጹም ታዛዥነት የማያሳይ ሲሆን፤ አድሮበት የነበረው ረድኤትና ጸጋ ይወስድበታል። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመናቁ ይዋረዳል። የመቅሠፍት ደዌም ያገኘዋል፤ ሰይጣን ከእግዚአብሔር የራቀውን ሰው ተቆራኝቶ በሥጋ በነፍስ ለማሠቃየት ወደ ኋላ አይልም። ምንም እንኳን በመቅሠፍትም ቢሆን በሌላ ሰይጣን ሰውን ለመቆራኘት የማያርፍ መኾኑ ቢታወቅም፤ ከእግዚአብሔር ሳይፈቀድለት አንዳች ማድረግ አይችልም። ሰዎች በተደጋጋሚ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፍ በራሳቸው ፈቃድ ብቻ ሲመሩ እግዚአብሔር ይቀየማቸዋል። ጸጋውንም ከእነርሱ ይገፋል። ከሀብት ከረድኤት የተራቆቱ ይሆናሉ።

እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለማይሆን ዕጣ ፈንታቸው የርኩሳን መናፍስት መጫወቻ መኾን ነው። ሰይጣን ታላቁን ሰው ሳኦልን እንደ ኳስ ሊጫወትበት የቻለው ሰበብ ወይም መግቢያ ቀዳዳ አግኝቶ እንደኾነ ያስተውሏል። ዛሬም ማንኛውም ሰው በተሰጠው ጸጋ ተኩሮርቶ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመተላለፉ ለሰይጣን በር መክፈት የለበትም። የክርስቲያኖች ልቡና የሰይጣን ሸንገላ ወይም የፆር ማዕበል ወደ ውስጣቸው ገብቶ በዓለም ምኞትና ፈቃድ ባሕር ውስጥ እንዳያስጥማቸው ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባቸዋል። ልቡናቸውን መክፈት ያለባቸው ለእግዚአብሔር መንፈስና በቅዱሳን አድሮ ለሚመክራቸው ምክር፣ ለሚገሥጻቸው ተግሣጽ ብቻ ቢሆን ከሰይጣን አሽክላ ይድናሉ፣ ይጠበቃሉ።

ንጉሥ ሳኦል የተሰጠውን ጸጋ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ቢጠብቅና የፈጣሪውን መመሪያ ቢከተል ኑሮ ውድቀት፣ ውርደት ባላገኘው ነበር። ከእግዚአብሔር እጅ የወጣች ነፍስ የሰይጣናት መጫወቻ አሻንጉሊት ትሆናለች። ክፉ መንፈስ ሰውን የሚጻናወተው ያለ ምክንያት እንዳልኾነ ከንጉሥ ሳኦል አኗኗር ገጠመኝ ማጤን ወይም መገንዘብ ይቻላል። ሰይጣን ከተፈቀደለት ሰዎችን በማሠቃየት እንደሚያስጨንቃቸው የታወቀ ነው። በብሉይ ኪዳን በዘመነ ነገሥት የነበረውን ሳኦልን በቁጥጥሩ ውስጥ አድርጎ በየጊዜው እያስጨነቀ ያሠቃየው የነበረው ከላይ ስለተፈቀደለት ነበር። ምክንያቱ ግን ኃጢአተኛው ሰው ከእግዚአብሔር ፈቃድና መመሪያ ወጥቶ፤ እንደልቡ በምኞትና በራስ ፈቃድ፣ በግለኝነት የሥጋ ኑሮ ሲጋልብ የደረሰበት አደጋ ነው።

እግዚአብሔር ሰውን መርጦ ለሹመት የሚያበቃው ፈቃዱን እንዲፈጽምለት ነበር። እንደ ሳኦል በራሳቸው ፈቃድ የሚመሩ ገዢዎች እግዚአብሔርን በብዙ ነገር ሲያስቀይሙት ይታያሉ። ኃጢአታቸውን፣ ስሕተታቸውን በውሸት ቃላት በመሸፋፈን፤ እውነተኞች መስለው ቢታዩም ከእግዚአብሔር ቅጣት መሠወር ግን አይቻላቸውም። ምናልባት በኃጢአታቸው ሲቀሠፉ፣ ንስሐ በመግባት ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ሲገባቸው፣ እንደ ሳኦል በመመጻደቅ እውነተኞች መስለው ለመታየት የማያደርጉት የግብዝነት ድለላና ማጭበርበር አይኖርም።

እንግዲህ እኛም ክርስቲያኖች ነን የምንል በሰይጣን እንዳንለከፍ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንፈጽም። እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔር አገልጋዮች ካህናትን ኃጢአታችንን በመሠወር ለማታለል አንሞክር። ሲሆን ልቡና ግዝተን ፈቃደ እግዚአብሔርን እንፈጽም። ከሥጋ ድካም፣ ከዓለም መታለል፣ ከሰይጣንም ተንኮል የተነሣ ባሕርያችን ተዳክሞ ኃጢአት በመሥራት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ብንወጣ፤ ሳንደባብቅና ምክንያት ሳንፈጥር በሳሙኤል አንጻር ለቆመልን መምህረ ንስሐ (የነፍስ አባት) ለኾነው ለቄሱ ኃጢአታችንን ከመናዘዝና ቀኖና ከመቀበል ወደ ኋላ አንበል።

በሰዎች ዘንድ ለመከበር ብለን አንዋሽ፣ አናታል፣ ኃጢአታችንን ከልብ አምነን እንፀፀት። እንዲህ ከኾነ በንስሐ ከመቅሠፍትና ከአጋንንት ቁራኝነት እንድናለን። ተወስዶብን የነበረው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋም ይመለስልናል። በሰይጣናት ቁርኝት፣ በነፍስና በሥጋ ከመሠቃየት እንሰወራለን። ዳሩ ግን ብዙዎቻችን ጠባያችን እንደ ንጉሥ ሳኦል ያለ ነው። መመጻደቅና ውዳሴ ከንቱ መንግሥተ ሰማያት የሚያስገቡን ይመስለናል። እንደ ፈሪሳውያን ጽድቃችን ሁሉ በሰው ፊት ነው። መመጻደቅ ለፈሪሳውያንም አልበጃቸውም። ለክርስቲያኖችማ ትሕትናና ተአምኖ ኃጣውዕ እንጂ የሚጠቅማቸው ውዳሴ ከንቱ ምን ይረባቸዋል ተብሎ ይታሰባል። በእውነቱ ከፈሪሳውያን እርሾ፣ ከግብዝነት መጠበቅ አለብን። ሳኦል በሰይጣን ተለክፎ፤ ሲሠቃይ ከኖረ በኋላ አሟሟቱም የማያምር ሆኗል። ከእንዲህ ዓይነት አደጋ እንዳንደርስ፣ በሰይጣናትም እንዳንለከፍ፣ እግዚአብሔርን ፈርተን፣ ትእዛዙን አክብረን እንኑር። እንደ ሳኦል አንሳሳት። ብንሳሳትም ተመ



www.ethiopisnorthodox.org

ልሰን፤ በእውነት ንስሐ በመግባት ከአምላክ እንታረቅ። እንዲህ ካላደረግን የሰይጣናት መጫወቻ እንሆናለን።

መጀመሪያ አጋንንት ሰውን ኃጢአት ያሠሩታል፤ ቀጥሎ ከእግዚአብሔር ጸጋ ከመንፈስ ቅዱስ ረድኤት መራቁን ሲያዩ ይለከፉታል። ልዩ ልዩ ሥቃይ በማሳየት መፈጠሩን ያስጠሉታል። በመጨረሻም በከፉ እሟሟት ራሱን እንዲገድል በማድረግ ሕይወቱን ያሳልፉሉ። ከነዚህ ጨካኞች ባላጋራዎቻችን እጅ እንዳን ወድቅ ለእግዚአብሔር አምላካችን በቀና ሃይማኖት፣ በበጎ ምግባር እየተ ገዛን ፈቃዱን በመፈጸም እን ኑር።

ለዚሁም መድኃኔዓለም ክርስ ቶስ በድንግል እናቱ ጸሎትና ምልጃ፤ ከሰይጣናት ተንኮልና በኃጢአት ከመ ውደቅ ይሰውረን አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## መስክርለት

የብሉይ የሐዲሱን።
በተኩላ ተንጥቀህ የጠፋኸው
ከእውነተኛዋ እናትህ የኮበለልከው-
ዘመር ብለህ እስኪ ታኘው ፤
መርዝ ሲረጭብህ ተሐድሶ
ራትን በማር ለውሶ፤
እረ ጠይቅ ኀበዝ ፤
ነቃ በል አትፍዘዝ።
ባባቶችህ ተመካ እንጅ፣
አትሁን ፈሪ ተሳዳጅ።
ቃሉን ታጠቅ
እንድትመልስ ስትጠየቅ
መናፍቅ ሲያጣምም ቃሉን
መስክርለት የብሉይ የሐዲሱን።
በኑሉተር ተመርዟል፣
የሱን ጥሎ ሌላ ይዟል።
መስሎት የሚያድነው ፣
ቅዱሳንን የሚሰድበው፣
በሰይጣን ጠላት ቀስቅሶት ነው።
የተዋህዶ ጥበብ ስለሚበልጥ፣
ኀበዝ ልብህን እንዳትሰጥ።
የአደራ ልጅ ነህ ባለተስፋ፣
የዘለዓለም ሀብት አለህ የማይጠፋ።
እናት ቢሉ እመ ኩሉ፣
ድህነት አለ የመስቀሉ፣
ፈውስ ቢሉ የፀበሉ ።
የሚራዱን ቅዱሳን ፣
መላእክትም አሉልን።
እኛ በእውነት ታድለናል
አለኝታዎቻችንን ይዘናል፣
በተዋህዶ ደስ ይለናል።

ተድላ ፍሑም
ከቅ/ሚካኤል/ቤ/ክ
/Bostan/ USA.

## መተሳሰብ

የሰው ልጅ ሥርዓቱ
ክፉን ከደግ መለየቱ
ታሪክ አለው እንደ ወቅቱ
እንደ ሥራው እንደ ዓይነቱ
አንዱ አንዱን ሲረዳው
ደስታውን ሲሳተፍ ችግሩን ሲጋራው
ካደገቡ ሆኖ አለሁልህ ሲለው
አሰቦ እንዳይርበው ፍቅርን ሲመግበው
ምንኛ ደስ ይላል የሰው ልጅ አዕምሮው
ሀሳቡን በሙሉ ለበጎ ሲያውለው

ኃይሉ ፈጠነ
መ/ህ/ኪ/ም/ሰ/ት/ቤት

## ትንሽ ስንፍና . . .

. . . ከገጽ ፲፱ የዞረ

ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል። "ምስጉን ነው በከፉዎች ምክር ያልሄደ፣ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፣ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ።" እንዳለው ክቡር ዳዊት። የምንሄድበትን፣ የምንቆምበትንና የምንቀመጥበትን ካስተዋልን ከኃጢአት እንጠበቃ ለን።

ወደ ዝሙት ኃጢአት የሚያ ደርሱ ደረጃዎችን ከተመለ ከትን፤ በዝሙት ሕይወት የሚኖር ሰው ምን ዓይነት ቅጣት እንደሚደርስበት እና ያለን። በዝሙት ሕይወት ያለ ሰው የሞተ ነው። ሞቱም ሦስት ዓይነት ነው።

፩. የሥጋ ሞት :-በኖኅ ዘመን ሕዝቡ ሁሉ በውኃ የጠፉት በዝሙት ምክንያት ነው። (ዘፍ. ፮) እንዲሁም የሰዶምና ገሞራ ሕዝቦች የጠፉት፤ ከዝሙትም በከፋው ኃጢአት ምክንያት ነው። በዘመናችንም የብዙዎች መነጋገሪያ የሆነው ኤድስ የመጣው በዚሁ በዝሙት ምክንያት ነው።

፪. የሕይወት ሞት:- ዝሙት እውርነትን ያስከትላል። በዝሙት ሕይወት የሚኖር ሰው እግዚአብሔርን አያይም፤ አምላኩም በእርሱ ከንቱ ነው። ስድብንና ውርደትን ያስከትላል። (ምሳ. ፮:፴፪-፴፫) አላዋቂና ሰነፍ ያደርጋል፣ ሠራተኛው ሥራውን በሚገባ አያከናውንም፣ ተማሪው ትምህርቱን አይከታተልም። ሰላም ያሳጣል፣ ደሃ ያደርጋል፣ ከመንፈሳዊ ኅብረት፣ በጥቅሉም ከእግዚአብሔር ይለያል። ይህም ከሞት ሁሉ የከፋ ሞት ነው።

፫. የነፍስ ሞት :- "የፀነሰች ሴት ለመውለድ ስትቀርብ እንደምት ጨነቅና በምጥ እንደምትጮኽ አቤቱ በፊትህ እንዲሁ ይሆናል" (ኢሳ. ፳፮:፲፯) በምጽዓት ቀን ምድር ሙታኖቿን አትከድንም "ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ፣ ሬሳዎችም ይነሳሉ" (ኢሳ. ፳፮:፲፱) ያን ጊዜ ሁሉም ወደ ፍርድ ይቆማል። በዚህ የዝሙት ሕይወት የኖረ ሰውም በዚያን ጊዜ ይፈረድበታል፤ ሉሩ እምኔየ! ከመባል ይሰውረን።

እንግዲህ ምን እንላለን? በቤተ ክርስቲያን እየኖርን፣ እየዘመርን፣ እያመሰገንን ብንኖር እንኳን በውስጣችን ትንሽ ስንፍና ካለ፤ መልካሙን ሥራችንን ሁሉ ያጠፋዋልና በጾም በጸሎት፣ በንስሐና ራስን በመመርመር ወደ ኃጢአት መንገድ የሚወስዱንን ትናንሾቹን ክፍተቶች የኃጢአት መዳረሻዎችን አጥፍተን በንስሐ ኖረን በቸርነቱ የመንግሥቱ ወራሾች ያደርገን ዘንድ የእግዚአብሔር መልካም ፈቃዱ ይሁን። ድንግል ማርያም በአማላጅነቷ ትርዳን አሜን።

## ተቻቻሉ

ኑሩ አትለያዩ ኑሩ ተቻቻሉ
አንተ ትብስ አንቺ ዘወትር ተባባሉ
እግዚአብሔር ፍቅር ነው ይላልና ቃሉ
ዛሬ አትለያዩ ትላንት ተዋዳችሁ
እንደ ዓለም እንዳይሆን አደራ ፍቅራችሁ
አንዱ ሆድ ቢብሰው ቢጨልም ተከፋው
እንደኛው ወንድሙ እጁዘህ ይበለው
ቅራኔ እንዳይኖር ሠይጣንን ተዋጉት
ኑሩ ተቻቻሉ በፀሎት ድል አድርጉት
አንዱ ሥቶ ቢገኝ አንደኛው ያቃናው
በአንዱ ጥፋት ቢገኝ ሌላው ሰው ያቃናው
ጥልና ክርክር የሠይጣን ነውና
እንዳትለያዩ ጽኑ በፈተና
በሰላምና ፍቅር በተጠማች ምድር
ኑሩ ተቻቻሉ! ታገኙ ዘንድ ክብር

ኃ/ኢየሱስ(ኃጋሢ)
ደ/ፀ/አ/ተ/ሰ/ት/ቤት
ከወንጂ ገፈርሳ



www.ethiopisnorthodox.org

## ዓምደ ሃይማኖት

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

## ጋኔን የማውጣት ሀብት

ከሊራክ ገብረ ክርስቶስ

በብሉይ ኪዳን ሰይጣን ሰዎችን ሲቆራኝ፤ ስለሚያስከትለው መንፈሳዊና ሥጋዊ ጉዳት ባለፈው ጽሑፍ መግለጹን እናስታውሳለን። ዛሬ ደግሞ በመጠኑም ቢሆን በሐዲስ ኪዳን በሰዎች ላይ ርኩስ መንፈስ ያደረሰባቸውን ጉዳት እንገልጻለን። ለሁሉም የሰይጣንን ተንኮል አውቀን ከሸንገላውና ከሚዘረጋቸው ወጥመዶች እንድንድን መድኃኔዓለም ክርስቶስ በቸርነቱ ይርዳን። የቅድስት ድንግል ማርያም ልመናዋ በረከቷ ሁልጊዜም የሚጠብቀን ይሁን አሜን።

### ሠ) <u>ጨረቃ ስትታይ ጋኔን ስለሚያሰቃየው ወጣት</u> :-

ወንጌላዊው ማቴዎስ ከዘገበው፣ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የጌትነት ነገር ከምትናገረው ወንጌል በም. ፲፯:፲፬-፲፰) በተጻፈው ታምር ጨረቃ በወጣች ቁጥር፤ በርኩስ መንፈስ ክፉኛ ይሰቃይ ስለነበረው ወጣት (ብላቴና) ተጽፎ እናነባለን። መድኃኒታችን መለኮታዊ ክብሩን በደብረ ታቦር ከገለጸ በኋላ ከተራራ ይወርዳል፣ ከተራራው ግርጌ የነበሩት ደቀመዛሙርት ካንድ ወጣት ላይ ጋኔን ማውጣት ተስኗቸው ልቀቅ ውጣ ብቻ በማለት ሲደክሙ ያገኛቸዋል።

በርኩስ መንፈስ ልጁ የሚሰቃይበት ሰው ወደ ጌታችን ቀርቦ፣ ተንበርክኮ፣ ከሰገደ በኋላ፤ በትህትናና በሃይማኖት "ተሣሃል ሊተ ወልድየ" (ልጄን ማርልኝ) ብሎ ለመነው። በማስከተልም ሲማጸን፣ ሲማለል እንዲህ አለ "እስመ እኩይ ጋኔን አኃዝዎ ወበ አርዕስተ አውራኅ ይሣቅዮ ወመብዝኅቶሰ ያወድቆ ውስተ እሳት ወቦ አመ ያወድቆ ውስተ ማይ ወአምጻእክዎ ኀበ አርዳኢከ ወስዕኑ ፈውሶቶ።" አለው። ትርጉሙ "ቢስ ጋኔን (ክፉ መንፈስ) አድሮበታልና፣ ወር እያየ ጨረቃ ስትወጣ ይጥለዋልና ይልቁንም ብዙ ጊዜ ከእሳት ከውኃ ይጥለዋል። ያድኑልኛል ብዬ ወደ ደቀመዛሙርትህ አመጣሁት ማዳን ተሳናቸው" ማለት ነው። የሰውየውን ልመና ሰምቶ መድኃኒ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ጋኔኑን ባለማውጣታቸው ከገሰጻቸው በኋላ ዓዕ መንፈስ ርኩስ ርኩስ መንፈስ ውጣ ብሎ ገሰጸው። ጋኔኑ ልጅየውን ትቶ ወጣ፣ ለቆት ሄደ "ወሐይወ ወልዱ በይእቲ ሰዓት" ይላል። ልጁ በዚያች ሰዓት ዳነ ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰ።

ሰይጣን ተንኮለኛ ነው ሰውን በተለያየ መንገድ ይለክፋል። ጨረቃ ስትወጣ ስቃይ በማጸናት የሚፈታተንበትም ምክንያት ይኖራል። መምህራን ይህንን ሁኔታ በማስመልከት የሚሰጡት ሐተታ አላቸው፤ ጨረቃ ሙሉ ስትሆን ማለትም ምልዓተ ወርህ ሲሆን ደም ይመላል፣ ብርድ ብርድ ይላል፣ ደዌ ይቀሰቀሳልና ጨረቃ እንጂ ባታመልኩ ነው ለማለት ስረቀ ወርህ እያየ ይጥላቸዋል፣ ስቃይ ያበዛባቸዋል በማለት አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።

ሰይጣን ወጣቱን ተቆራኝቶ ቦታ ሳይመርጥ አንዴ ከውኃ፣ ሌላ ጊዜ ከእሳት በመጣል በየጊዜው ማሰቃየቱን ከጽሑፉ ተረድተናል። በህክምና ፈውስ የማይገኝለት ክፉ ደዌ ነው። ሰይጣን በመርፌና በክኒን አይለቅም። በሌላም ዓይነት የሥነ ልቦና ጠበብቶች ብልሃት ፍንክች የማይል ባላጋራ ነው። በተለይም ቢስ ጋኔን በሰው ካደረ ማስለቀቁ ይከብዳል።

ሐዋርያት አጋንንትን የሚያወጡበት ሥልጣን ተሰጥቷቸው ነበር። ቢስ ጋኔንን ግን ለማውጣት ባለመቻላቸው የልጅየው አባት ክርስቶስን መማጸን ግድ ሆነበት። ሐዋርያት በቶሎ ጋኔኑን ማውጣት እንደተሳናቸው መድኃኒታችንን ጠይቀውታል። ያገኙት መልስ "ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው፤ስለ ሃይማኖታችሁ ጉድለት ነው፤ እውነት እላችኋለሁ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት (ሃይማኖት) ቢኖራችሁ፤ ይህን ተራራ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም። ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጾም በቀር አይወጣም"" የሚል ነው። (ማቴ. ፲፯:፲፱-፳፩) ክርስቶስ የመረጣቸው፣ አጋንንትን እንዲያወጡ ሥልጣን የሰጣቸው ሐዋርያት እንኳን ቢስ ጋኔን ማውጣት ተስኗቸዋል። በፍጹም ሃይማኖት፣ በጾም በጸሎት ካልሆነ፤ ሰይጣን በዋዛ የሚለቅ አይደለም። ሰይጣን ስለሮጬኸ ለቀቀ ማለት አይደለም፤ ሰይጣንና ውሻ ምልልስ ናቸው። ቢወጣም ተመልሶ ይገባል። ይህ የሚሆነው ከሁለት አንዳቸው ጉድለት ሲገኝባቸው ነው። ወይ ሰይጣን ከሚያስለቅቀው (እንደ ሐዋርያት ካለው) የሃይማኖት ሕፀፅ ሲገኝ፤ ወይም ከታማሚውና ካስታማሚው የባዕድ አምልኮ ቅሪት ካለ፤ ሰይጣን ለቀቅሁ በማለት እየጮኸ ሲቀልድ ይኖራል እንጂ በዋዛ አይለቅም።

ርኩስ መንፈስም የሚያስደስተው፤ የሰው ልጆች በመንፈሳዊ ሕይወታቸውና በሥጋዊ ኑሯቸው ሲሰናከሉለትና ሲሰቃዩለት ነው። ስለዚህ ነበር ያን ወጣት ተቆራኝቶ ስቃይ ሲያሳየው የኖረው። ለመድኃኔ ዓለም ክብር ምስጋና ይግባውና በእምነትና በትህትና የቀረበለትን ጸሎት ተቀብሎ፤ በክኂሎቱ፣ በቸርነቱ ከሰይጣን ቁራኝነት ከመቅጽበት ነፃ በማድረግ ፈውሶታል።

ዛሬም የሚያምን ከተገናና በትህትና ወደ መስቀሉ፣ ወደ ጠበ



www.ethiopisnorthodox.org

ሉ፣ ከቀርበ፤ ጌታችን በሾመለት እውነተኛ ክህነ ጸሎትና ሥልጣነ ክህነት በመጠቀም፤ የማይፈወስበት ምክንያት አይኖርም። ሕመምተኛም አስታማሚም ጥንቃቄ ማድረግ ያለበት ቢኖር ቀደም ተከተሉን ከማወቅ ላይ ነው። የልጅየው አባት ለዚህ ጥሩ አብነት ይሆናል። መጀመሪያ ክርስቶስ ሥልጣን ወደሰጣቸው ካህናት (ሐዋርያት) ነው የሄደው፤ ቀጥሎ ከእነርሱ አቅም በላይ መሆኑን ካየ በኋላ ወደ ክርስቶስ ቀርቦ ልጁን እንዲያድንለት ለማድረግ በቅቷል። ይህን ዓይነት የትህትናን መስመር መከተል ለክርስቲያን ሁሉ ይገባል። ሊሳም ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄ ቢኖር ከእውነተኞቹ ሐዋርያት (ቀሳውስት) ዘንድ መሄድ የሚገባ መሆኑን ነው። እውነተኛውንና ሐሰተኛውን ለመለየት ወንጌልን መመሪያ፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን መርህ ማድረግ ይገባል። ጠንቋይ ሁሉ በስምንተኛው ሺህ መነኩሲ ነኝ፣ መናኝ ነኝ በማለት፤ ሰዎችን ወደ ባዕድ አምልኮ በመምራት፤ በሰዕና በምትሀት በመጠቀም፣አጋንንትን በማቆራኘት፤ ለብር ለተማ ደፋ ቀና የሚል መኖሩን በመገንዘብ አስታማሚዎችና ታማሚዎች ሊጠነቀቁ ይገባቸዋል።

በዛሬ ዘመን ሥራ ፈቱ ሁሉ በአንዳንድ ዋሻ ተሸጉጦ፤ የጅብ ጉበት፣ የቀበሮ ቅንድብ፣ የውሻ አጥንት፣ የእንቧይ ሥር፣ የብሳና ትጠል ወዘተ. . . . አምጡና ጋኔኑን ለማውጣት እጸልይበታለሁ በማለት የሚያታልል አለ።

ሌሎችም ደግሞ ጋኔን የማውጣት ሀብቱም ብቃቱም ሳይኖራቸው፤ ለራሳቸው መናፍቃን ሆነው ሳለ፤ እንደ ደቂቀ እስቴዋ በኢየሱስ ስም ልቀቅ ውጣ ብለው የሚቀባጥሩ ሞልተዋል። በዛር አንጋሾች ቤትና በመናፍቃን ዘንድ፤ ሰይጣኑ ሳይለቅ የለቀቀ መስሎ በማታለል፣ በምትሀት ሲጫወት ይገኛልና ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል።

ከሁሉ በፊት መድኃኒታችን በዚህ ክፉ ዘመን መጨረሻ ላይ ላለነው ሰዎች እንድንጠነቀቅ የነገረንን ትንቢታዊ መመሪያ ማስተዋል አለብን፤ ለዚህም መረጃ የሚሆነን ቃል እንደሚከተለው ተዘግቧል "ያን ጊዜ ክርስቶስ ከወዲህ አለ ከወዲያ የለም፣ ከወዲህ ወዲያ ይሄዳል፣ ከወዲያ አለ ከወዲህ የለም፣ ከወዲያ ወዲህ ይመጣል ቢሏችሁ በጅ አትበሉ። መሲሕ ክርስቶስን የሚያሳብሉ፤ በመሲሕ ክርስቶስ የሚያብሉ ሐሰተኞች መምህራን ይነግሉና፣ መምህራንን የሚያሳብሉ በመምህራን የሚያብሉ ሐሰተኞች መምህራን ይነግሉና፤ ሰውን ለማሳት በምትሀት ደጋግ ተአምራት ያደርጋሉ፤ አይቻላቸውም እንጂ ቢቻላቸውስ ምዕመናንንም ባሳቷቸው ነበር።" (ማቴ. ፳፬፥፳፫-፳፬) እንግዲህ እንዳንሳሳት የተፈወሰውን ልጅ አባት ፈለግ በመከተል ወደ እውነተኞች የቤተክርስቲያን አባቶች ወደ ሐዋርያቱ ተርበን፤ በቅዱሳን ጸሎት ለመፈወስ ወጣንያን ሁነው ለጊዜው በእምነት ጉድለት ምክንያት ሊፈውሱን ባይችሉም፤ በሃይማኖት ጸሎት በትህትና ወደ ክርስቶስ በመቅረብ መፈወስ እንደምንችል አውቀን፤ ከሐሰተኞች ነቢያትና ከሐሰተኞች መሲሐውያን መጠበቅ ይኖርብናል።

## ረ) ሌጌዎን ስላደረበት ሰው ስቃይ :-

ቁጡ የሆኑ የጋንንት ጭፍሮች ሌጌዎን የተባሉ፤ አድረው፣ ተቆራኝተው ያሳበዱት አንድ ሰው እንደነበር ቅዱስ ማርቆስ ይነግረናል። ይህ ሰው ሰንሰለት የሚበጣጥስ፣ እግር ብረቱን የሚሰባብር፣ በምንም በምንም ቢያስሩት የማይቻል ነበር። አስሮ የሚያስቀረው የሚያሸንፈው ሰው አልተገኘም።

ሁልጊዜ ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ላይ ሆኖ ይጮኻል፣ ሰውነቱንም በድንጋይ ይቀጠቅጣል፣ ይቧጭራል። ይህን ሰው እንዲህ የሚያሰቃዩት በማኅበር ሆነው ያደሩበት ከሺህ የማያንሱ ሌጌዎን የተባሉ የጋንንት ጭፍሮች ናቸው።

ዘመዶቹም ማሠርና ማሸነፍ ስላልቻሉ፤ አጋንንት ያሳበዱትን ሰው ተስፋ ቆርጠው፣ መቼም አይድን በማለት ትተውት ይኖሩ ነበር። በዚህ ስቃይ ላይ እንዳለ፣ ከእለታት በአንድ ቀን፣ መድኃኒታችን ይህ ሰው ወዳለበት ወደ ጌርጌሴኖን አገር መጣ። ከታንኳ እንደወጣ ርኩስ መንፈስ ከነጭፍሮቹ ያደረበት ሰው፤ ወዲያውኑ ከመቃብር ወጥቶ ጌታ ኢየሱስን በሩቅ ሲያየው ሮጦ ሰገደለት።

ሰውየው እራሱን አያውቅም፤ በላዩ ላይ ያደሩ የሌጌዎን ጭፍሮች ግን ከነ አለቃቸው ያውቁታል። የመጣው በሥጋ ተገልጾ የሚታየው፣ ሰዎችን ከርኩሳን መናፍስት ቁራኝነት ነፃ የሚያወጣ የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ መሆኑን አጋንንት ያውቃሉ። ስሙ ሲጠራ ይደነግጣሉ "እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ መልካም ታደርጋለህ" ካለ በኋላ ሐዋርያው "አጋንንትኒ የአምኑ ቦቱ ወይደነግጹ" "አጋንንት ያምኑበታል ይንቀጠቀጡማል" ብሏል (ያዕ. ፪፥፲፱)

አጋንንትን የሚያንቀጠቅጥ ኃይላቸውን የሚያደክም አምላክ በሥጋ በተገለጸ ጊዜ፤ ሰዎች ዓይነልቡናቸው በድንቁርና ሞራ ተሸፍኖ ባያምኑበትም እንኳ፤ የሌጌዎን ማኅበር ርኩሳን መናፍስት ሳይወዱ በግድ ሰግደውለታል። በአለቃቸው አማካይነት አሰምተው "የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ ካንተ ጋር ምን አለኝ እንዳታሰቃየኝ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ።" (ማር. ፭፥፩-፲፫) ሲሉ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ፣ ከአምላክ የተወለደ እውነተኛ የባሕርይ አምላክ መሆኑን በመንቀጥቀጥ መስክረውለታል። ጌታም "ስምህ ማነው ውጣ" ብሎ ሲገስጸው፤ የአጋንንቱ አለቃ በፍርሃትና በድንጋጤ እየጮኸ፤ ብዙዎች ነን፣ ስሜ ሌጌዎን ነው፣ ከሀገር ውጪ አትስደደን፣ ወደ እሪያዎች እንድንገባ ስደደን በማለት ከነ ጭፍሮቹ ለምነውታል። ወደ እሪያዎች እንዲገቡ በፈቀደላቸው ጊዜ፤ ሁለት ሺህ በሚያህሉ እሪያዎች ገብተው ሲያድሩባቸው፤ የእሪያው መንጋ ከአፋፍ ወደ ባሕር እየተጣደፉ ሰጥመው ቀርተዋል።

በሌጌዎን ሠራዊት ይሠቃይ የነበረው ሰው ግን ተቀምጦ ልብሱን ለብሶ፣ ልቡም ተመልሶ ፍጹም ጤነኛ ሆነ። በኋላም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገለትን ምሕረት፣ አ



www.ethiopisnorthodox.org

ሥር ከተማ በሚባል ሀገር እየተዘዋወረ ይሰብክ ጀመር። ያዩትና የሰሙት ሁሉ ተደነቁ።(ማር. ፭:፲፬-፳)

ሰይጣን ብቻውንም ሆነ ከጓደኞቹ ከሌሎች ርኩሳን መናፍስት ጋር በመኾን የሰውን ልጆች ያሠቃያል። ሌጌዎን የተሰኙ ጨካኞችና ቁጡዎች የአጋንንት ጭፍሮች፤ በሰው ላይ ሲያድሩ እንደሚያሳብዱና ሌሊትና ቀን፣ ያለ ዕረፍት በመቃብርና በተራራ ልብ.ነሥተው፣ ዕርቃን አድርገው በማስጮኽ እንደሚያሠቃዩ፤ በሰውየው ላይ በፈጸሙት የጭካኔ ድርጊት መረዳት ይቻላል። አጋንንት የተቆራኙት ሰው ጉልበታም ይሆናል። ብርታቱ ሰንሰለት ከመበጠስ፣ እግር ብረት ከመሰበር፣ ራሱን በደጊያ ከመቀጥቀጥ ያደርሰዋል። ይኽ ሁሉ ሲኾን ሕመምተኛው ሕሊናውን አያውቅም፤በሱ ላይ የፈቀዳቸውን የተንኮል ሥራ የሚያከናውኑት ርኩሳን መናፍስቱ ናቸው። ከእነርሱ ነጻ የሚያወጣን፤ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፣ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በሰዎች መካከል እንደ ሰው የተመላለሰው፤ የእግዚአብሔር ልጅ ቤዛ ዓለም ክርስቶስ ነው። ይኽን ዐውቀን፣ በመስቀሉ ታሽተን፣ በቅብዐ ቅዱሱ፣ በወንጌሉ፣ በጸበሉ በመጠቀም እንዳን።

ጠንቋዮች፣ ጋኔን ሳቢ ወይም የመናፍቃን ሠራዊት የሚፈ ውሱን መስሉን፤ ይባስ የርኩሳን መናፍስት መጫወቻ ከመኾን እንጠበቅ። ሰይጣን በሰው ላይ ሲሠለጥን ብረት ያስቆረጥማል፣ በእሳት ውስጥ ያስጨፍራል፣ ያለማቋረጥ ሌሊትና ቀን ያስጮኻል፣ ያስጓራል፣ ጨርቅ ያስጥላል፣ ያሳብዳል፣ ከአገር አገር ያንከራትታል።መድኃኔዓለም ክርስቶስ በአጋንንት ከመለከፍ ይጠብቀን፤ አጋንንት ያደሩባቸውንም ሰዎች በቅዱሳን ጸሎት፣ በመስቀሉ፣ በጠበሉ፣ በቅዱስ ስሙ፣ በቸርነቱ፤ ያድንልን፣ ይፈውስልን አሜን።

## ለ) ርኩስ መንፈስ በተንኮሉ ጎባጣ አድርጎ ስላደከማት ሴት :-

በሉቃስ ወንጌል ፲፫:፲-፲፫ በሚነበበው ክፍል፤ ለ፲፰ ዓመታት ሰይጣን አድሮ ጎባጣ በማድረግ ስላሠቃያት ሴት ተጽፎዋል። ጌታችን በአንድ ምኩራብ፤ ቅዳሜ ወንጌልን ሲያስተምራቸው፤ ፲፰ ዓመት ሙሉ ሰይጣን በተንኮሉ ተብትቦ ጎባጣ ያደረጋትን ሴት ተመለከተ። ይህችን ምስኪን ሴት አይቶ አዘነላት።

ክርስቶስ መፍቀሬ ሰብእ (ሰውን የሚወድ) አምላክ፣ ስለ ሰዎች ድኅነት ሰው የሆነ ጌታ በመኾኑ በምሕረቱ ጎበኛት። "ወርእያ እግዚእ ኢየሱስ ወመሐራ ወጸውዓ ወይቤላ እ ብእሲቶ ተፈታሕኪ እምደዌኪ።" ይላል። ትርጉሙ "ጌታም አያት አዘነላት ጠርቶ አንቺ ሴት ከደዌሽ ተፈውሰሻል አላት።" ማለት ነው። ቀጥሎም "ወአንበረ እዴሁ ላዕሌሃ ወረትዓት ሶቤሃ ወአእኮተቶ ለእግዚአብሔር።" ይላል። "እጁን በላይዋ ጫነባት። ፈጥና ቀናች እግዚአብሔርንም አመሰገነች። ከደዌዬ የፈወሰኸኝ ከዚህ ያደረሰኸኝ ብላ " ማለት ነው። ይህችን ሴት ሰይጣን እንደ ተቋጠረ አቅማዳ አድርጓት ነበር። ክርስቶስ ግን በቃሉ ከሠይጣን ሰንሰለት ፈታት። ጎባጣ አድርጎ ለዘመናት እያደከመ ሰይጣን ተጫውቶባት ነበር። ክርስቶስ ግን እጁን ጭና ቀጥ ብላ እንድትቆም፣ እንድትራመድ አደረጋት። ሰንበት የዕረፍት ቀን መኾኗን በሥራው ገልጾ አሳየ።

አህዮቻቸውንና በሬዎቻቸውን ፈትተው ወደ ገለባ፣ ወደ ውኃ የሚወስዱ ሥጋውያን ግን፤ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረች የተፈጥሮ ዘመዳቸው ያች ሴት በሰንበት ቀን በመፈወሷ፤ የ፯ኛ ቀን አክባሪዎች አይሁድ፤ ክርስቶስን ሰንበት ሻሪ ብለው የተቃውሞ ድምፃቸውን አሰሙ። ዳሩ ግን በመጽሐፍም፣ በሕሊና ዳኝነትም ስለተረቱ በክርስቶስ ላይ እንከን ማግኘት አልቻሉም።

ፍጹም ዕረፍት የሚሰጠን ክርስቶስ ነው። ከታሠርንበት የኃጢአት ሰንሰለትም ሆነ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነጻ ያወጣናል። ክርስቶስ ስለእኛ ድኅነት ብሎ በፈጸመው ሥራ ሁሉ እኛ ከሰይጣን ቁራኝነት ድነናል። ጠንቋዮችና አስማተኞች ከዛር፣ ከቆሌ። ከጠቋር ከቦረንትቻና ከመሳሰሉት ርኩሳን መናፍስት ልቡሳን ሥጋ አጋንንት ሊያድኑን አይችሉም። ራሳቸውም የሰይጣን ፈረሶች የዛር በቅሎዎች ናቸው።

ነጻ አውጭውን ክርስቶስን በማመን ከሰይጣንና ከጠንቋዮች ከመሳሰሉት ሁሉ ነጻ እንውጣ። ከሙታን ተለይቶ ትንሣኤውን ያሳየን ክርስቶስ ሰይጣንን አሥሮ፣ አዳምን ከእነ ልጆቹ ነጻ አውጥቶ ሰላምንና ደስታን ስለሰጠን ክብር ምስጋና ይድረሰው። የክርስቶስ ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## በትንሣኤው ደስ ይበለን

ዜና ሕማማቱን ሰማን በሐዘን፣
አሁን በትንሣኤው ደስ ደስ ይበለን፤
ባንድ ቀን አፍርሱት ይህንን መቅደሱን፤
እኔ አነሳዋለሁ በሦስተኛው ቀን።

ብሎ ነበርና በአምላካዊ ቃሉ፣
ምሳሌው ነውና መቅደሱ ለአካሉ።
ፃርብ ዕለት ተሰቅሎ ለሕሙማን እንዲሆን ሕይወት፣
ቃሉ ሳትዛነፍ ሳትቀር ወደኋላችን፤
መግነዙን ፍቱልኝ ረዳት ጥሩልኝ፣
መቃብር ክፈቱ ድንጋዩን አንሱልኝ፣
እንደሩቱ ብእሲ ይኽን ሁሉ ሳይል፤
ብርሃን ተጎናጽፎ ከሙታን መኻል፣
በገዛ ሥልጣኑ ተነሣ በኃይል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ሲነሳ ፣
ዓቀብተ መቃብር ወደቁ እንደሬሳ፣
ለቅዱሳት አንስት ለሐዋርያት፣
ትንሣኤውን ገለጸ ቆሞ በሕይወት።

አርባ ቀን ቆይቶ ሕጉን አስተምሮ፣
ሥጋዊ መከራን እንዳይፈሩ መክሮ።
የሥልጣን ባለቤት የምስጋና ጌታ፣
አስማየ አረገ ሉዐላዊ በታ።

ጲራቅሊጦስንም በጽርሐ ጽዮን፣
ባርድዕቱ ላከ ባሥረኛው ቀን።
አሉድ በሆነች ሰዓት ካንድ ቤት እንዳሉ፣
እስኪያደንቅ ድረስ ሌላው ሕዝብ ሁሉ።
ድምፁን እያሰማ በንፋስ አውሎ፣
እንደ እሳት ላንቃ ተከፍሎ ተከፍሎ።
ሀብተ ፀጋ ሆኖ ለየእንዳንዳቸው፣
እንደ ጠጅ ብርሌ ተሞላባቸው።

መንፈስ ቅዱስንም እንደተቀበሉ፣
በቋንቋ በጥበብ በኃይል ተሞሉ።
ወንጌል መንግሥቱን ሲያስተምሩበት፣
ከአላውያኑ ብዙ ነገሥታት፣
እሳቱን ሰይፉን ጅራፉን ሳይፈሩ፣
ክብሩን ጌትነቱን ዞረው አስተማሩ።

ከአለቃ ተገኝ ታምሩ



www.ethiopisnorthodox.org

## ዓምደ ሃይማኖት

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

## ጋኔን የማውጣት ሀብት

ከሲራክ ገ/ክርስቶስ

ርኩሳን መናፍስት በሰው ላይ ሲያድሩ በሥጋና በነፍስ ላይ ስለሚያስከትሉት አደጋና ጉዳት፤ ከብሉይና ከሐዲስ መረጃ በማቅረብ እስካሁን ማዝገማችን ይታወቃል። ከእነዚህ ረቂቃን ጠላቶቻችን ለመዳን እንድን ችል እግዚአብሔር በቸርነቱ የሰጠን ጸጋ አለ። ልበ አምላክ ተብሎ የሚታወቀው ክቡር ዳዊት፤ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ስለሚሰጠው ጸጋ፤ በትንቢቱ የጠቀሰውን ዞር ብለን ማስታወስ ይኖርብናል። ትንቢታዊ ቃሉም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተነሣ በ፵ቀን፣ ባረገ በ፲ቀን፤ ጳንጠቆስጤ ተብሎ በሚታወቀው በበዓለ ሃ፣ ይኸውም የአሪቱ በዓለ ሰዊት በሚከበርበት ዕለት እሁድ፣ በጠዋቱ በ፫ሰዓት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በጽርሐ ጽዮን ቤተሰብ ላይ በወረደ ጊዜ ፍጻሜውን አግኝቷል። (የሐዋ. ፩:፲፭፣ ፪:፩-፬) የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በተከፋፈሉ የእሳት ላንቃዎች ለሐዋርያት የላከላቸው፤ በክብር ያረገው በአብ ቀኝ (ረና) በክብር ትክክል ሆኖ ያለው፤ የጸጋ ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን የዳዊት ቃል ያረጋግጥልናል።

> ሕያዋኖት ሕሊሙኑ ዘጥተዋል፣ ሕቁዋል ማሐቱ ሐደደሕም፤ ዘዚፀ መታሕልም ፕመደነቀም ኖሕብኀም።

ከዚያ በፊት ጌታችን ለሐዋርያትና ለአርድዕት፤ አጋንንትን የሚያወጡበት ሥልጣን እንደሰጣቸው ይታወቃል። ጋኔን ከማውጣት ሀብት ጋር፤ ሌሎችንም የጸጋ ስጦታዎች አድሏቸዋል። (ሉቃ. ፱:፩-፮፣፲፯፲፯-፳) ይሁን እንጂ ፍጹም የመንፈስ ቅዱስን ሀብት ለቤተ ክርስቲያን በምልአት አብዝቶ፣ አስፍቶ የሰጠው ካረገ በኋላ እንደሆነ፤ የዳዊትን ትንቢታዊ ቃል ከሐዲስ ኪዳን ጋር በማዛመድ መገንዘብ ይቻላል። ከእነዚህ ልዩ ልዩ ስጦታዎች አንዱ ጋኔን የማውጣት ሀብት (ጸጋ) እንደሆነ እናስተውል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሳትን ከሲዖል ማርኮ ወደ ገነት እንደሚያስገባ፣ ከዕርገት በኋላም ጸጋውን ለምዕመናን እንደሚያጎናጽፍ ነቢዩ ሲናገር "ዓረገ ውስተ አርያም ፄዊወከ ፄዋ ወወሀብከ ጸጋከ ለእጓለ እመሕያው" (መዝ. ፷፯:፲፰) ብሏል። ትርጉሙም በነጠላው "ወደላይ አረግህ፣ ምርኮም ማረክህ፣ ስጦታ ህንም (ጸጋህን) ለሰዎች ሰጠህ" ማለት ሲሆን በአንድምታው ሲብራራ ግን "ነፍሳትን ማርከህ በተነሣህ በ፵ ቀን አረግህ፣ ባረግህ በ፲ቀን በተነሣህ በ፶ቀን መንፈስ ቅዱስን ለሐዋርያት ሰጠህ" ተብሎ ይተረጎማል። የዚህን ትንቢታዊ ቃል ፍጻሜውን፤ ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን (ምዕመን) በጻፈው ክታብ ገልጾታል። (ኤፌ. ፬:፰)

ከላይ እንደተገለጸው ከመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች አንዱ፤ ጋኔን የማውጣት ሀብት ነው። ሀብቱ (ጸጋው) የተሰጣቸው፤ ነፍስና ሥጋን ተቆራኝተው የሚያስጨንቁ ክፉዎች መናፍስትን ማራቅ፣ ማስወገድ ይችላሉ። ስለሆነም ለአብነት የአንዳንድ ቅዱሳንን ሕይወት በመግለጽ እንደሚከተለው ስለምናቀርብ፤ አንባቢያን በጸሎትና በእንክሮ እንድትከታተሉት አደራ እንላለን። ለዚህም ተግባር እራሱ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ በጸጋው ይቀስቅሳችሁ፣ ይቀስቅሰን አሜን።

### ፩. ልበ አምላክ ዳዊት በበገና ክፉ መንፈስን ስለማራቁ :-

ንጉሡ ሳኦል ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ፤ ረድኤተ እግዚአ ብሔር ተለይቶት፣ መንፈሰ ረድኤት ርቆት በክፉ መንፈስ ይሰቃይ እንደነበር በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ተጽፎ ይገኛል። በኃጢአቱ ምክንያት አድሮበት የነበረው ቅዱስ መንፈስ ተለየው። ክፉ መንፈስ ይኸውም የሰዎች ባላንጣ መንፈስ ሰይጣን አደረበት፤ ስቃዩን የተመለከቱ አገልጋዮቹ መፍትሔ ይፈልጉለት ጀመር። መፍትሔው ወደ ጋኔን ሳቢ ወይም ወደ ጠንቋዮች ያም ባይሆን፤ ወደ ሞራ ገላጮች ወይም ወደ መናፍስት ጠሪዎች መሄድ አልነበረም። አንዳንድ ሞኛሞኞች በየዋህነት እንደሚታለሉት፤ ዛርና ውቃቢ መለማመንም አልነበረም። መፍትሔው የእግዚአብሔርን ሰው የተቀባውን፣ ሰባት ሀብታት ያደሩበትን፣ ባለ በገናውን ልበ አምላክ ዳዊትን ሳኦል አስጠርቶ፤ መንፈስ ርኩስ ሊያሰቃየው በመጣ ቁጥር፤ በገናውን ደርድሮ በጸሎት፣ በዝማሬ እንዲያርቅለት ማድረግ ነበር።

አገልጋዮቹ የመከሩትን ምክር ንጉሥ ሳኦል ተቀበለ። እነዚያኑ አገልጋዮቹን መልካም አድርጎ በገና የሚደረድር ሰው እንዲያመጡለት ጠየቃቸው። ከብላቴኖቹ መካከል አንዱ መልሶ እነሆ መልካም አድርጎ በገና የሚመታ የቤተልሔማዊውን የእሴይን ልጅ አይቻለሁ፣ እርሱም ጽኑ ኃያል ነው። በነገርም ብልህ፣ መልኩም ያማረ ነው፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነው በማለት አበሠረው። ሳኦልም ወደ ዳዊት አባት ወደ እሴይ መልእክተኞች ልኮ፤ ከበጎች ጋር ያለውን ልጅህን ዳዊትን ላክልኝ አለ። የዳዊት አባት እሴይም መልእክቱ እንደ ደረሰው፤ እንጀራና የወይን ጠጅ፣ አቁማዳ የተጫነ አህያ፣ የፍየልም ጠቦት ወስዶ በልጁ በዳዊት እጅ ወደ ሳኦል ላከ።

ዳዊትም ወደ ሳኦል [illegible]



www.ethiopisnorthodox.org

ትንቢት ፳ኛ) ሀብተ መዊዕ ናቸው። (ቆሮ. ቀዳ ፲፪:፲-፴፩)

## ፲. ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በጥላው ጋኔን ስለማውጣቱ ፡-

ጌታ ለሐዋርያት ሥልጣን በሰጠበት ቀን፤ ለቅዱስ ጴጥሮስም ጋኔን የማስለቀቅ ሥልጣን እንደሰጠው የታወቀ ነው። ይህንንም ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ በምዕራፍ ፲ ከቁጥር ፩-፰ ባለው ጽሑፉ አረጋግጦልናል። በተለይም ቁጥር ፰ን ብንመለከት "ድውዮችን ፈውሱ፣ ሙታንን አስነሡ፣ ለምጻሞችን አንጹ፣ አጋንንትን አውጡ" የሚል አምላካዊ ቃል ስላለ፤ በግልጽ አጋንንትን የማስወጣት ሥልጣን ለሐዋርያት ሁሉ መስጠቱን እንረዳለን።

ምንም እንኳን ሥልጣን ቢኖራቸውም፤ የመንፈስ ቅዱስን ሙሉ ሀብት (ጸጋ) በጽርሐ ጽዮን እስኪቀበሉ ድረስ፤ ሙሉ በሙሉ የመጡላቸውን፣ በአጋንንት የተለከፉትን ሕመምተኞች፤ በሥልጣናቸው ብቻ ማዳን ይሳናቸው እንደነበር ቅዱስ ወንጌል ይመሰክራል። ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ታቦር ምሥጢረ መለኮቱን ሲገልጽ፤ ወደ ተራራው ያልወጡት፣ ከተራራው ግርጌ የነበሩት ሐዋርያት፤ በርኩስ መንፈስ ይሰቃይ የነበረውን ወጣት ማዳን እቅቷቸው እንደነበር ቅዱስ ማቴዎስ ጽፏል። ጌታችን ከተራራው እንደ ወረደ፤ ሁኔታውን የብላቴናው አባት ተንበርክኮ እየሰገደ "ጌታ ሆይ ልጄን ማርልኝ በጨረቃ እየተነሣበት ክፉኛ ይሠቃያልና፤ ብዙ ጊዜ በእሳት፣ ብዙ ጊዜም በውኃ ይወድቃልና ወደ ደቀ መዛሙርትህም አመጣሁት ሊፈውሱትም አቃታቸው።" (ማቴ. ፲፯:፲፬-፲፯) ብሎ በመግለጹ ሐዋርያት ጋኔን ማስለቀቅ እንደተሳናቸው ታውቋል።

እርግጥ ነው ሐዋርያትም ሆኑ ሰባው አርድእት ጋኔን እንዳወጡ በወንጌል የተጻፈው ምስክርነት የታመነ ነው። እንደ ምሳሌ ብንጠቅስ፤ ሰባው አርድእት በደስታ ተመልሰው "ጌታ ሆይ አጋንንት እንኳ በስምህ ተገዝተውልናል" (ሉቃ. ፲:፲፯) ባሉት ቃል ማረጋገጥ ይቻላል። በተጨማሪም ሐዋርያት ሥልጣኑን ከተቀበሉ በኋላ፤ አጋንንት ያደረባቸውን ሕመምተኞችና ሌላም በሽታ ያለባቸውን ቅብዓ ዘይት (ቅብዓ ቅዱስ) ቀብተው እየጸለዩ እንዳዳኗቸው ቅዱስ ማርቆስ ይመሰክራል። (ማር. ፮:፲፫) ዛሬውንም ቢሆን ከቤተ ሥርዓት ቤተክርስቲያን ወይም ከቤተ ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን በአንዱ በምሥጢረ ቀንዲል፤ ለሕሙማን ቀሳውስት ጸሎት አድርገው አጋንንትን እንዲያስለቅቁ በሽተኞችን እንዲፈውሱ ሥርዓት አለ። ይኸውም በቅዱስ ያዕቆብ ክታብ "ወእመቦ ዘይደዊ እምኔክሙ ለይጸውዕ ቀሳውስተ እለ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወይጸልዩ ላዕሌሁ ወይቀብዕዎ ቅብዐ ጸሎት በስሙ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወጸሎተ ሃይማኖት የሐይዎ ለድውይ ወያነሥኦ እግዚአብሔር ወእመኒ ቦቱ ኃጢአት ይትኃደግ ሎቱ" (ያዕ. ፭:፲፬-፲፭) ተብሎ በመነገሩ ታውቋል።

የዚህም ትርጓሜ እንደሚከተለው ነው "ከእናንተ ወገን የታመመ ሰው ቢኖር፤ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ፣ በምዕመናን ላይ የተሾሙ ቀሳውስትን ጠርቶ ይጸልዩለት፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምነው መጽሐፈ ቀንዲል በዘይት ደግመው ይቀቡት፤ አምነው የሚጸልዩት ጸሎት

> የቅዱስ ጳውሎስ የልብሱ ዘርፍ፣ የመጠም ጠሚያውም ቅዳጅ ድውይ ይፈውስ ነበር።

ድውዩን ያድነዋልና፣ እግዚአብሔርም ያስነሳዋልና፣ ኃጢአትም ቢኖርበት ይሰረይለታል" ማለት ነው። ቅብዓ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስ አምሳል ነው፤ ወይም ጸሎቱ ቅሉ ዘይት (ቅብዕ) ተብሏል። ምነው ቢሉ ለሰው የሚቀባ ራሱ ሳይቀምስ፣ እጁ ሳይነካ እንዳይቀር፤ ለሰውም የሚጸልይ እራሱን ሳይጠቅም አይቀርምና። በጋኔንም የተለከፈ ይሁን በሌላ በሽታ የተያዘ ሊፈወስ የሚችለው፤ ማለትም ደዌው የሚርቅለት፣ ጋኔኑ የሚተወው በቅድሚያ ኃጢአቱ ሲሰረይ ነው። ኃጢአት ሳይሰረይ ደዌ አይርቅምና፤ አጋንንትም በሰው ለማደር ምክንያት የሚያደርጉት ኃጢአትን ነው። ምንም እንኳ ከሐዋርያት ጀምሮ ለቀሳውስት ሁሉ ቅብዐ ዘይት ቀብተው ጋኔን ማስለቀቅ፣ ሕሙም መፈወስ የተሰጠ መሆኑ ቢታወቅም፤ ከላይ እንደገለጽነው የተሰጣቸው ሥልጣን በፍጹም እምነትና ምግባር ካልጸናና ጋኔን የማውጣት ሀብት ከሌለ፤ መፈወስም ሆነ አጋንንትን ማስለቀቅ በዋዛ የሚቻል አይደለም።

ሐዋርያት ጋኔን ማውጣት ቢሳናቸው፤ ሥልጣን ሰጪውን ጌታ በቆይታ ብቻቸውን ቀርበው "ይቤልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ በእንተ ምንት ንሕነ ስዕነ አውፅኦቶ" "እኛ ማስወጣት ለምን ተሳነን" አሉት። (ማቴ. ፲፯:፲፰) ከዚህ በኋላ ጌታችን የሚከተለውን ቃል ነግሮ፤ ጉድለታቸው በምን ሊሞላ እንደሚችል መከራቸው፣ አስተማራቸው። ቃሉም "ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ በእንተ ሕፀተ ሃይማኖትክሙ፤ አማን እብለክሙ እመ ብክሙ ሃይማኖት መጠነ ኅጠተ ሰናፔ ወትብልዎ ለዝ ደብር ፍልስ እምዝየ ኀበ ክህ ወይፈልስ ወአልቦ ዘይስአነክሙ" (ማቴ. ፲፯:፲፱) የሚል ነበር።

ትርጉሙ "ጋኔን ማስወጣት የተሳናችሁ ስለ ሃይማኖታችሁ ማነስ ነው ወይም ሃይማኖት ባይኖራችሁ ነው፤ እንደ ሰናፍጭ ያህል ሃይማኖት ቢኖራችሁ ማለት ሰናፍጭ ፍጽምት እንደሆነች ነቅ እንደሌላት ፍጹም ሃይማኖት ቢኖራችሁ፣ ይህን ተራራ ከዚህ ተነስተህ ወዲያ ሂድ ብትሉት ይደረግላችኋል፤ ችግራችሁ የሚቀር እንደሌለ፣ የሚሳናችሁ እንደሌለ በእውነት እነግራችኋለሁ" ማለት ነው። ቀጥሎም በማያያዝ በቁጥር ፳፩ "ወዝንቱ ዘመድ ኢይወጽዕ ዘእንበለ በጾም ወበጸሎት" "ይህ አብሮ አደግ ጋኔን ካልጸሙ ካልጸለዩ አይወጣም ወይም ይህ አይነት ግን ከጸሎትና ከጾም በቀር አይወጣም"አላቸው።

እንግዲህ ጋኔን የማውጣት ሥልጣን የተሰጣቸው ሐዋርያት፤ ከትንሣኤና ከዕርገት በፊት ሃይማኖታቸውን በጾም በጸሎት ገና ፍጹም ስላላደረጉትና መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ከብልየት ስላልታደሱ፤ አንዳንድ ጉድለት እንደሚታይባቸው ግልጽ ነው። ከዕርገት በኋላ ግን፤ በተለይም በጽርሐ ጽዮን መንፈስ ቅዱስ ካደረባ

> ሐዋርያት ጋኔን ማውጣት ለምን ተሳናቸው?

ቸውና ኃይልን ከተቀዳጁ በኋላ የሚሳናቸው ምንም ነገር እንደሌለ የሐዋርያትን ሥራና ገድላቸውን በመመልከት ለማረጋገጥ ይቻላል። በግብረ ሐዋርያት ፭:፲፪-፲፮ ያለውን ብንመለከት፤ ሐዋርያት በጥላቸው ይፈውሱ፣ አጋንንትን ያወጡ እንደነበር መረዳት እንችላለን። በተለይም ቁጥር ፲፮ን ብቻ ብናጤን እውነትነቱ ማለትም ማስረጃው ጎልቶ ይገኛል።

"ደግሞም በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካሉትም ከተማ ድውያንንና በርኩሳን መናፍስት የተሰቃዩትን እያመጡ ብዙ ሰዎች ይሰበሰቡ ነበር፤ ሁሉም ይፈ



www.ethiopisnorthodox.org

ወሱ ነበር" ይላል። ሳይፈወስ የሚመለስ አንድም ሰው አልነበረም። ርኩሳን መናፍስት ለቀው ይሄዳሉ፤ አይመለሱም፣ አይሸሩጡም። ምክንያቱም ሐዋርያት ከብቃታቸው የተነሣ የተሰጣቸው ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፤ ከአካላቸው ተርፎ በጥላቸውም እንደሚ ይሰራ ነበር። በቁጥር ፲፭ላይ ግልጽ አድርጎ እንደጻፈው "ቅዱስ ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላውም ቢሆን ከእነርሱ አንዱን ይጋርድ ዘንድ፤ ማለትም በሽተኞችንና በአጋንንት የሚሰቃዩትን ይጋርድ ዘንድ፤ ድውያንን ወደ አደባባይ አውጥተው በአልጋና በወስከ ያኖሯቸው ነበር" ተብሏል። የቅዱስ ጴጥሮስ ጥላ ሲያርፍባቸው ሕሙማን ይፈወሱ፣ በአጋንንት የተለከፉትም ከስቃያቸው ያርፉ ነበር። ፈውሱ ለሁሉም ይደርስባቸዋል፤ አጋንንቱ እየተዝዘቱ እንደ ጢስ ተነው ወጥተው ይጠፋሉ። ፈውሱ ፍጹም ስለሆነ መመላለስ፣ ደጅ መጥናት የለም። ቅዱስ ጴጥሮስ በፍጹም ሃይማኖቱ በተሰጠው ሥልጣንና ጋኔን የማውጣት ሀብት፤ አጋንንትን ያስወጣቸው እንደነበር ከዚህ በላይ በተነገረው መግንዘብ ማስተዋል እለብን።

ቅዱስ ጴጥሮስ በተሰጠው የመፈወስና ጋኔን የማውጣት ጸጋ ሲፈውስ፣ አጋንንትን ሲያወጣ እንደ ኖረ ማረጋገጥ ችለናል። በቅዱሳን አድሮ ከአጋንንት ቁራኝነት፣ ከደዌ ሥጋ፣ ከደዌ ነፍስ የሚፈውስን አምላክ እንዴት ድንቅ ነው! ከነቢዩ ከዳዊት ጋር እንዲህ በማለት እናመስግን፣ እፁብ ድንቅ እንበል። "መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ" እግዚአብሔር በወዳጆቹ አድሮ በሚሰራው ተአምራት፣ በሚመሰገነው ምስጋና እፁብ ድንቅ ተብሎ ይመሰገናል። (መዝ. ፷፯፡፴፭)

## ፫. ቅዱስ ጳውሎስ በልብሱ በቁራጭ ጋኔን ስለማውጣቱ ፦

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በደማስቆ ጎዳና ክርስቶስ በተአምራት ከማረከው በኋላ፤ ቤተ ክርስቲያንን ከማሳደድ ተቆጠበ። የጌታችንን ትእዛዝ ተቀብሎ ለ፫ቀናት በተደም አከፈለ። የሚያጠምቅ፣ የሚናዝዝ፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የሚያሳድርበት ካህን (የክርስቶስ ደቀመዝሙር) ሐናንያ የተባለው ተላከለት። በሐናንያ እጅ የታወሩት ዓይኖቹ በርተውለት፣ በክርስቶስ አምኖ፣ ኃጢአቱን ተናዞ፣ ለክርስትና በሚያ በቃ ማየገቦ ተጠመቀ፤ ክርስቲያን ሆነ። በጥምቀት ባገኘው ጸጋ፣ በፍጹም እምነቱና በእውነተኛ ንስሐው፣ ተጋድሎና ትሩፋቱ ከፍጹምነት ማዕረግ ደረሰ። የአኅዛብ ሁሉ ፓትርያርክ፣ ሐዋርያ፣ አባት፣ መምህር ለመሆን በቃ። በማዕረጉም ከሐዋርያት የማይተናነስ ፍጹም ጸጋ ያለው ሰው ሆነ። ከተሰጡት የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች አንዱ አጋንንትን በልብሱ ቁራጭ ማውጣት፣ ሕሙማንን መፈወስ ነበር። (የሐዋ ፱፡፩-፲፰፤ ገላ. ፩፡፲-፲፯ ፪ቆሮ. ፲፩፡፳፱-፴፫)

በግብረ ሐዋርያት ም. ፲፱፡፲፩-፲፪ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ፤ ቅዱስ ጳውሎስ በልብሱ ቁራጭ ከሕመምተኞች አጋንንትን ያስወጣ እንደነበር ጽፎልናል። በግዕዝና በአማርኛ ኃይለ ቃሉ እንደሚከተለው ስለተጻፈ በማስተዋል እንመልከት። "ወቢየ ኃይሉ ይገብር እግዚአብሔር በእደዊሁ ለጳውሎስ ወይወስዱ እምጽንፈ ልብሱ ወሰበኑ መትሮሙ ወያነብሩ ዲበ ድውያን ወየሐይው ወአጋንንት እኩያን ይወፅኡ።" ይላል። ትርጉሙ "እግዚአብሔር በጳውሎስ ቃል፣ በጳውሎስ ሥልጣን ደጋግ ተአምራትን ያደርግ ነበር። ከልብሱ ዘርፍ፣ ከመጠምጠሚያው እየቀደዱ ወስደው በድውያን ላይ ይጥሉት ነበር። ድውያኑም ይድኑ ነበር። አጋንንትም እየወጡ ይሄዱ ነበር።" ማለት ነው።

አጋንንት የማውጣት ሀብት የተሰጠው ቅዱስ ጳውሎስ፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ በቃሉና በእጁ ብቻ ሳይሆን፤ በሰበኑና በልብሱ ዘርፍ አጋንንትን እስወጥቶ ይሰዳቸው እንደነበርና ሕሙማንን እንዳዳነ ካወቅን፤ ከአጋንንት ቁራኝነት ለመዳን ቅዱሳኑን መጥኛ ብለን ደጅ መጥናት እንዳለብን እንገንዘብ።

ከዚህ ላይ በምትሐት ለማታለል መናፍቃን ሳይቀሩ፤ አጋንንትን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናወጣለን ብለው ሊመጹ ይቀብን ይችሉ ይሆናል። ሰይጣናት ስለ ጮኹ ወጥተዋል፣ ለቀዋል ማለት አይደለም፤ ርኩሳን መናፍስት ለማታለል ተቃጠልን፣ ወጣን ብለው ሳይለቁ [illegible]ሉ። በዚህ መታለልም፣ [illegible] የለብንም ዘመናችንን ማስተዋል ይገባናል። ስንኳን ከቤተ ክርስቲያን የተለዩ ትዕቢተኞቹ መናፍቃን ይቅሩና፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቃትና ጋኔን የማውጣት ሀብት ከሌለ፤ ልቀቅ፣ ልቀቅ በማለት በኃይልና በስድብ አጋንንትን ማስወጣት አይቻልም። ከዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን ነገር ቢኖር፤ የዕበለ ሥራዎችን በጥንቃቄ በመመዘን፤ ጸጋው የተሰጣቸው እውነተኞች ካህናት ምዕመናንን እንዲያጠምቁ፣ እንዲባርኩ ቢደረግ ይመረጣል። ማንም አታላይ ውስጥ ውስጡን በአስማትና በጥንቆላ እየተጠቀመ ጻድቅ ነኝ በቅዱሳን እያለ እንዳያታልለን እንጠንቀቅ። [illegible] በጀናው ጊዜ በፍጹም ዘመን [illegible] በዘመነ ሐዋርያት [illegible]

በክርስትና ሽፋን ጋኔን እናወጣለን የሚሉ አታላዮች ተነሥተው እንደነበር እንወቅ።

በሐዋርያት ሥራ ም. ፲፱፡፲፫-፲፯ ያለውን ብንመለከት የአይሁዳዊው የሊቀ ካህናት አስቄዋ ልጆች፤ ጋኔን እናወጣለን በማለት እንደተጋለጡ እንረዳለን። ርኩስ መንፈስ እንኳን ታዝቦዋቸው። "ወተሠጥዎሙ ውእቱ ጋኔን እኩይ ወይቤሎሙ በኢየሱስኒ እአምን ወለጳውሎስኒ እአምሮ አንትሙ እንከ መኑ አንትሙ" (ቁ. ፲፭) በማለት ገምሶ፣ ገምሶ ለቋቸዋል። ይኸም ቃል ወደ አማርኛ ሲመለስ "ያ ቢስ ጋኔንም መለሰላቸው። በኢየሱስ አምናለሁ፣ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ እናንተ እነማን ናችሁ? እናንተ ከእኔ ልዩ ናችሁን?" ማለት ነው። ከዚህ በኋላ "ወእብደ ላዕሌሆሙ ውእቱ ዘጋኔን እኩይ ወተየሎሙ ወሞያሙ ወአቁሰሎሙ ወፈትእሎሙ ወሰደዶሙ እምውእቱ ቤት ወተሰምዐ ዝ ነገር በኀበ ኵሎሙ አይሁድ ወአረሚ እለ ይነብሩ ኤፌሶን ወፈርሁ ኵሎሙ ወአዕበዩ ስመ እግዚእነ ኢየሱስ" ይላል። (ቁ. ፲፮-፲፯) ተመልከት። ትርጉሙ "ክፉውም መንፈስ (ጋኔን) ያለበት ሰው፤ ዘለለባቸው (ተንሣባቸው)፣ ተበራታባቸው፣ ድል አደረጋቸው፤ ገምሶ፣ አቆስሎ፣ ከቤት አስወጥቶ ሰደዳቸው፤ ይህም ነገር በኤፌሶን በሚኖሩ በአይሁድና በአረሚ ዘንድ ደርሶ ተሰማ፤ በሁሉም ፍርሃት አደረባቸው፤ የጌታችንን የኢየሱስን ስም አከበሩ።" ማለት ነው።

የጌታችንን የመድኃኒታችንን [illegible] ክርስቶስ ስም [illegible]

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

### ለመሆኑ የዓረገው እሱ ማነው?

የዓረገው እርሱ በክብቶች ግርግም የተወለደው፣
በዮርዳኖስ ወንዝ በእደ ዮሐንስ የተጠመቀው፣
ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ዞሮ ያስተማረው፣
በዕለተ ዐርብ የተሰቀለው፣
የሞተው የተቀበረው፣
በሦስተኛው ቀን የተነሣው፣
ዳግመኛ ለፍርድ የሚመጣው፣
ጌታችን አምላካችን የሆነው፣
መድኃኒዓለም ክርስቶስ ነው።
ከተማሪ አስፋው ገዐኖሬ
ከአ/ተ/ሃ/ሰ/ት/ቤት ዱራሚ



www.ethiopisnorthodox.org

ይህ ዓምድ፣ ምዕመናን የተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት ወይም ቀኖናዋን፤ በተከታታይ የሚማሩበት፤ እንዲሁም የመናፍቃንን ማንነትና የሚያስተምሩትን ትምህርት ስህተት የሚረዱበት ነው።

# መ ን ፈ ስ ቅ ዱ ስ

## ጋኔን የማውጣት ሀብት

አጋንንትን የማውጣት ጸጋ ስለተሰጣቸው ቅዱሳን ለዓይነት ያህል ባለፈው እትም ላይ በቀረበው ጽሑፍ እንደገለጽነው በአሁኑ ጽሑፍ ተከታታዩን ለመዘገብ ተነስተናል። ያለፈውን ጽሑፍ ብናስታውስ ክቡር ዳዊት በገና ሲደረ ድር ክፉ መንፈስ ከሳኦል ላይ ይርቅለት እንደነበር፤ ቅዱስ ጴጥሮስ በጥላው በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ሰይጣናትን እንዳባረራቸውና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በልብሱ ዘርፍ ላይ ባደረው የመንፈስ ቅዱስ ሀብት አጋንንትን እንዳራቃቸው ተመልክተናል። የምሥጢራት ባለቤት እውቀትን የሚያድል ልዑል እግዚአ ብሔር በቸርነቱ ይግለጽልንና ከዘመነ ሐዋርያት በኋላም በቅዱሳን ሕይወት የመን ፈስ ቅዱስ ኃይል ይሠራ እንደነበር የቤተክርስቲያንን ታሪክ ገድለ ቅዱሳንን ዋቢ በማድረግ ጋኔን የማውጣት ሀብት ስለተሰጣቸው አበው (አባቶች) ለመግለጽ እንሞክራለን። መድኃኔዓለም ክርስቶስ በቅዱስ መንፈሱ ይርዳን የቅዱሳን እመቤት የወላዲተ አምላክ የድንግል ማርያም ጸሎቷ በረከቷ አይለየን አሚን።

### ፩. ሚልኪ ቁልዝማዊ በደብዳቤ ጋኔን ስለማስወጣቱ:-

በምናኔ ኑሮ በምንኩስና ሕይወት ገዳም አቅንቶ ይህ ቅዱስ አባት ሚል ኪ ቁልዝማዊ ይኖር እንደነበር ስንክ ሳር የተባለው የቤተክርስቲያን የታሪክ መጽ ሐፍ ይገልጽልናል። አባ ሚልኪ አጋንንትን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የማስወጣት ጸጋ ነበረው። ከሩቅ አገር ሰዎች ወደ እርሱ መጥተው በአጋንንት ስለተለከፉት ወገኖቻቸው ሲነግሩት በእቱን ለቆ ላለመውጣት በደብዳቤ "የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ሚልኪ ቁልዝማዊ በፈጣሪዬ ስም ከበሽተኛው ለቀህ ውጣ ብሎሃል " ብሎ ይጽፍና ይሰጣል። ሰዎች ያንን ደብዳቤ ይዘው ከአገራቸው ሲደርሱ በበሽተ ኞች ላይ ያነባሉ። አጋንንቱም "የሚልኪ ቁልዝማዊ አምላክ አነደደን የአባ ሚልኪ ጸሎቱ ድል አደረገን" በማለት ለቀው ይሄዳሉ። በሽተኞች ተረፈ ደዌ ሳይኖር ባቸው ፈጽመው ይድናሉ። አጋንንቱም እየተመላለሱ አያስቸግሯቸውም።

ለመሆኑ አባ ሚልኪ ማን ይሆን? ዕድገቱና አኗኗሩስ እንዴት ነበር? ለዚ ህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የደረሰው መንፈሳዊ ኑሮው ምን ቢሆን ነበር? የሚሉ ና የመሳሰሉት ጥያቄዎች በህሊናችን ሊውጠነጠኑ ይችላሉ። ከላይ በጠቀስነው መ ጽሐፍ የዚህ ቅዱስ አባት ሕይወት ምን ይመስል እንደነበር በአጭሩ የተተረከ ስለሆነ ለግንዛቤ ሙሉ ታሪኩን ከዚህ ላይ ብናሰፍረው መልካም መስሎ ይታየናል።

አባ ሚልኪ ተጋድሎውን ፈጽሞ ያረፈው መስከረም ፩ቀን ነው። ዕረፍቱ በዚህ ቀን ይታሰባል። በቤተክርስቲያናችን በዕረፍታቸው ቀን የቅዱሳን ገድል እንደሚነበብ የታወቀ ነው። ስለዚህም የዚህ ቅዱስ ጻድቅ ዕረፍትም በዕለቱ ስንክ ሳሩ ይነበባል፣ ይታሰባል። ታሪኩን እንዳለ በሚከተለው ዓይነት እንወስደዋለን። "በዚህች ዕለት ፍጹም ጻድቅ የነበረው አባ ሚልኪ ያረፈበት ነው። የዚህ ጻድቅ ወላጆቹ ከቁልዝምና ከአውራጃዋ በሀብት የበለጸጉ ለድሆችና ጦም አዳሮች ምጽ ዋት የሚሰጡ ታላላቆች ነበሩ። እግዚአብሔርን እጅግ አድርገው ያፈቅሩት ይገዙ ለት ነበር፤ ልጅ ግን አልነበራቸውም።

ከዕለታት በአንድ ቀን ሕፃናት በእጃቸው የተጻፈ ሰሌዳ ይዘው ጽሑፉን በማንበብ "ወላጆቻችንን እናስባቸዋለን በሕይወተ ሥጋ ሳሉ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን ስላስተማሩን አቤቱ ጌታ ሆይ ነፍሶቻቸውን ከጻድቃን ከሰማዕታት ነፍሳት ጋር አሳርፍ" ሲሉ የአባ ሚልኪ አባት ሰማ። እንዲህ ሲሉ ከሕፃናት አፍ በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ። "ልጆች የሌሉኝ እኔ ወዮታ አለብኝ በሞትኩ ጊዜ ማን ያስበኛል " ብሎ ከሚስቱ ጋር በጽኑ ምሕላ በጾም በጸሎት በምጽዋት ወደ እግዚአብሔር ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ አመለከቱ። እግዚአብሔርም ልመናቸውን ሰምቶ በአንድ ጊዜ መንታ ልጆች ወንድና ሴት ሰጣቸው። በልጆቹም መወለድ እጅግ አድርገው ፈጽመው ተደሰቱ ጊዜያቸው ሲደርስ ክርስትና አስነሷቸው።

ወንዱን ሚልኪ ሴቷን ሰፍና ብለው ስም አወጡላቸው። ሰፍና ማለትም ትርጉሙ ርግብ ማለት ነው። በመልካም አስተዳደግ አሳደጓቸው። ልጁ ፭ዓመት ሲሆነው አባቱ ወደ መምህር ወሰደው። የሐዲሳትና የብሉያትን ንባብና ትርጓሜ አጠና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በምልአት አደረበት። ከሕፃናት ጋር አይጫወትም አይቀልድም፤ አይስቅም ነበር ነገር ግን በመዓ ልትም በሌሊትም መጽሐፍትን ያነባል ይመለ ከታል። ትምህርት በቀጸለ ፲፪ ዓመት ሲሞላው ልጃቸውን ጠርተው ሚስት የምትሆንህን እንጭልህ አሉት ይኸውም የስም መጠሪያ ለማግኘት ነው እርሱ ግን ከልቡ ፈቃደኛ አልነበረም። እነር ሱን ላለማስከፋት በአፉ በፈሊጥ አነጋገር እሺ በቃላችሁ ያዘዛችሁኝን ሁሉ እፈጽማለሁ አላቸው። በነፍሱ ግን ከዓለም መለየትን ይፈቅድ ነበር።

ከዚህ በኋላ አባ ሚልኪ አባቱን አባቴ ሆይ ከእኔ ጋራ አብረው ከተማሩት የምሳ ግብዣ ላደ ርግ እፈቅድ ነበር አለው አባቱም አንድ ሺ ዲና ር ወርቅ ለሚወደው የምሳ ዝግጅት እንዲሆነው ሰጠው አሽከሮቹንና ሎላልቱን በሚፈልገው ሁሉ እንዲላ ላኩት አዘዘለት ከዚህ በኋላ አባ ሚልኪ ሎሌዎቹን አሽከሮቹን መቶ ዲናር ወርቅ ውሰዱ ብሎ በዚህ ምሳ አዘጋጁልኝ እኔ ደግሞ ጓደኞቼን ለመጥራት እሄዳለሁ አላቸው። የነገራ ቸውን ሰምተው አሽከሮቹ ተመለሱ እርሱ ግን ብቻውን ቀደም ብሎ በፈረስ ሄደ። እራቁት እንዳለ ለድሆችና ለጦም አዳሮች ወርቁን ሁሉ መጸወተ። ፈረሱንም ለአንድ ድሃ ሰጠው። ከለበሰው ልብስ በስተቀር ምንም ምን ሳያስቀር መጸወተ የመመ ለሻው ጊዜ ስለዘገየ ሎሌዎቹ ፈልገው አጡት አላገኙትም። እያለቀሱ ለአባቱና ለእናቱ ነገሯቸው እጅግ መሪር ልቅሶ አለቀሱ፤ እኅቱም ወንድሟን በማጣቷ በለቅሶ ብዛት ዓይኖቿ ታወሩ ከኀዘኗም ጽናት የተነሳ አረፈች።

ይህ ሚልኪ ግን ጡር ወደምትባል ገዳም ሄደ፤ ይህችውም ገዳም የእናቱ ወንድም ማር አውጊን የሚኖርባት ነበረች ይህ አውጊን ጻድቅ (ደግ) ሰው ነበር ብዙ ምግባር ትሩፋት ይሠራል። የተመረጡ ፫፻ መነኮሳት በእርሱ አበምኔትነት ይተዳደራሉ።

ሚልኪ ገዳም እንደደረሰ ዝቅ ብሎ እጅ በመንሣት ከማር አውጊን እግር ላይ ተደፋ። አባቴ በአንተ መንፈሳዊ አባትነት ጥላ ሥር እንድኖር ልብሰ ምንኩስና እንድታለብሰኝ እንድታ መነኩሰኝ እፈቅዳለሁ ብሎ ተማፀነ። አበምኔቱ አባ አውጊንም መልሶ ከወዴት ነው የመጣኸው ብሎ በገዳሙ ሥርዓት የአመክሮ ጥያቄ ጠየቀው እርሱም ሲመልስ የመጣው ከቁዝም እንደሆነና የቤተሰቡን ሁኔታ ሁሉ ነገረው።በዚህ ጊዜ አባ አውጊን ደስ ተሰኝቶ ማመን ኮሱን አመነኩሰሃለሁ ነገር ግን በቅድሚያ ለሦስት ዓመታት የምንኩስናን ቀንበር ለመሸከም መቻልህንና አለመቻልህን እራስህን ፈትን ብሎ ያመክሮ ጊዜ ሰጠው። ሦስቱ የአመክሮ ዓመታት እንደተፈጸሙ ልብሰ ምንኩስና አልብሶ ሥርዓቱን ፈጽሞ አመነኮ ሰው። አባ ሚልኪ ቁልዝማዊ በፋርስ (በፔርሺያ) አገር ሁሉ ዝናው እስኪሰማ ድረስ ትጋትን ተጋድሎን አበዛ ከመነኮሰ ሦስት ዓመት ሲሆነው እግዚአብሔር የመፈወስ ጸጋንና አጋንንትን በቃሉ



www.ethiopisnorthodox.org

# እ ና ጸ ጋ ው

ከሲራክ ገብረክርስቶስ

የማስወጣት ስጦታ አደለው።

አባ ሚልኪ ቁልዝማዊ ከዕለታት በአንድ ቀን ዳዊት እየደገመና እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲሄድ፤ በውስጡ የበለስ ዛፎች(ተክሎች) ካሉበት ታላቅ ጉድጓድ አጠገብ ደረሰ። በዚያም ብዙ እረኞች ተሰብስበው ሲያለቅሱ አገኛቸው አባ ሚልኪም ምን ያስለቅሳችኋል አላቸው እነርሱም መልሰው የአገረ ገዢው ልጅ የበለስ ፍሬ እየቀጠፈ ሲበላ፤ ታላቅ ዘንዶ መጣና ውጦት ወደ ጉድጓድ ገባ አሉት። እረኞቹ ይህንን አሳዛኝ ዜና እያረዱት ሳለ የልጅየው አባት ከአገሬው ሰዎች ጋር ሆኖ ልብሱን ቀዶ ፊቱን እየጸፋ እያለቀሰ መጣ አባ ሚልኪንም ከዚያ ቆሞ ስላየው "አባቴ እባክህን የልጄን ነገር" ብሎ በጸሎቱ እንዲረዳው ተማጸነ።

አባ ሚልኪም "ልጄ ሆይ! አትፍራ በእግዚአብሔር ተማመን ድንቅ ሥራውን ታያለህ " አለው። ከዚህ በኋላ ቅዱሱ መነኩሴ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ እጆቹን ወደላይ ዘርግቶ ለረጅም ጊዜ በተመስጦ ጸለየ። ጸሎቱንም ከፈጸመ በኋላ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ዘንዶውን ጠራው። ዘን ዶው እየተሳበ ገስግሶ መጣ ሕፃኑን እንዲተፋው አዘዘው። ሕፃኑን ከአፉ ተፍቶ ባወጣው ጊዜ ምንም ምን ደዌ ሳይኖርበት በሕይወት በጤና ድኖ ወጣ። በዘንዶው ውስጥ ያደረው ሰይ ጣን ግን ድምፁን አሰምቶ "ሚልኪ ቁልዝማዊ አንተ የሌለህበት ወዴት ልድረስ" ብሎ ጮኸ እንደ ጢስ ተኖ እንደ ትቢያ በኖ ወጥቶ ጠፋ።

በአባ ሚልኪ ቁልዝማዊ ጸሎት በተሰጠው አጋንንትን የማው ጣት ጸጋ ልጅየው እንደዳነለት አገረ ገዢው ባየ ጊዜ ለቅዱሱ ወርቅና ብር እንካ ብሎ ሊሰጠው አወጣ አባ ሚልኪ ግን አይሆንም ብሎ ሳይቀበለው ቀረ። በዚ ህም ተግባሩ ጌታ ለሐዋርያት በቅ ዱስ ወንጌል ". . . አጋንንተ አውፅኡ፤ በከንቱ ዘንሣእክሙ በከንቱ ሀቡ፤ በጸጋ ዘንሣእክሙ በጸጋ ሀቡ ኢታጥ ርዩ ለክሙ ወርቀ ወብሩረ፤ ወኢ ፀ ሪቀ ውስተ ቅናውቲክሙ" (ማቴ. ፲:፰) ብሎ ያዘዘ ውን ትዕዛዝ ፈጸመ ". . . አጋንንትን አውጡ ያለዋጋ የተቀበላ ችሁትን ያለ ዋጋ ስጡ፤ በልግስና የተቀበላችሁትን በልግስና ስጡ በመቀነ ታችሁም ወርቅ ብር መሐለቅም አት ያዙ ማለት ነው።

አባ ሚልኪ ቁልዝማዊ በዚህ ገድል ትሩፋቱ አባቶቹን ሐዋርያትን መስሏል። ለምሳሌ ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ጳውሎስን መጥቀስ ይቻላል።

ሀ) "ወይቤሎ ጴጥሮስ ወርቅሰ ወብሩር አልብየ፤ ወእምዘብየሰ እሁበከ፤ ናሁ በስሙ ለኢየ ሱስ ክርስቶስ ናዝራዊ ተንሥእ ወሑር . . . ጴጥሮስም ወርቅና ብር የለኝም፤ ያለኝንስ ልስጥህ፤ እነሆ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥተህ ሂድ አለው" (የሐዋ. ፫:፮) ያለውንና

ለ) "ተአምኑ ከመ ኢተሰቆቁ ንዋየክሙ ኢወርቀ ወኢብሩረ ወኢአልባስ ኢነሣእኩ ወኢእምነ አሐዱሂ እምኔክሙ . . . ገንዘባችሁን እንዳልፈለግሁ ታውቃላችሁ፤ ወርቅም ቢሆን ብርም ቢሆን ልብስም ቢሆን ከእናንተ ካንዱ ስንኳ አልተቀበልኩም" (የሐዋ. ፳:፴፫) የሚለውን መመልከት መገንዘብ እንችላለን።

አባ ሚልኪ እውነተኛ ባሕታዊ ዓለምን የናቀ ከፍቅረ ንዋይ የራቀ መናኝ ነበር። መናኝ ማለት የዓለምን ክብር፣ ሹመት፣ ሽልማት፣ ወርቅና ብር እንደ መርገም ጨርቅ እንደ ጉድፍ ቆጥሮ የናቀ በዓለም ምኞት ያልተጠላለፈ የእግዚአብሔር ሰው ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሕይወት በዚህ ቅዱስ አባት ሥራ ተንጸባርቋል። መናኝ ለመሆን የሚሻ ወይም መናኝ ነኝ የሚል ሁሉ ከውዳሴ ከንቱና ከፍቅረ ንዋይ የራቀ ራሱን ከዓለም ፍትወት የጠበቀ መሆን አለበት። ከዚህ ውጭ መኖር ግን የግያዝና የአስቆሮቱ ይሁዳ ጠባይ ስለሆነ እነዚያ እንዳልተጠቀሙ ይኸም አይጠቀምም። (፪ነገሥ. ካ. ፭:፳-፳፯፤ ማቴ. ፳፮:፲፬-፲፮፤ ፳፯:፫-፭)

ከሐተታው ወደ ታሪኩ እንመለስና የልጅየውን አባት አባ ሚልኪ ቁልዝማዊ "ልጅ በረከት ለማግኘት ከፈለግህ ገዳሙን አንጽ" አለው፤ አገረ ገዢውም ደስ ተሰኝቶ ለ፫፻መቶ (ለሦስት መቶ) መነኮሳት የሚሆን መኖሪያ በዓት አነጸ፣ የገዳሙን ቅጥርም በብረት አጥር ዙሪያውን አሳጠረ። ቤተክርስቲያን ሲያንጹ ሠራተኞቹ ለብዙ ሰዎች ጉልበት የማትነሳ ታላቅ ድንጋይ አገኙ ለቤተክርስቲያን የመዓዘን ድንጋይ እንድትሆን ወደላይ ለማውጣት ለ፫፻ ሰዎች ጉልበት እንኳ የማትቻል መሆኗን ገመቱ በዚህ ጊዜ አባ ሚልኪ ጸሎት አደረገ። በተአምራት ማንም ሰው ሳያነሳት ከቤተክርስቲያን ላይ ከሚፈለገው ሥፍራ ታንጻ ተገኘች። በዚያች ገዳም የተመረጡ ፭፻ መነኮሳት ገድል ትሩፋት በመሥራት ይኖሩ ነበር።

አበ ምኔቱ አባ ሚልኪ ቁልዝማዊ ነው። በየሀገሩ በየመንደሩ የቅዱሱ ሰው ገድል ትሩፋት ገቢረ ተአምራቱ የተሰጠው አጋንንትን የማውጣት ሕሙንን የመፈወስ ጸጋው ታወቀ ተረዳ። በዚህ ምክንያት ልዩ ልዩ በሽታ ያደረባቸውና በአጋንንት ልክፍት ቁራኝነት የሚሰቃዩ ሁሉ እየመጡ በጸሎቱ ይፈወሱ ነበር። አጋንንትም ለቀው ይሄዳሉ። ተሸርጠው አይቀሩም በጸድቁ ጸሎት በፋርስና በሮምያ በሌሎችም አካባቢዎች ያሉ ሰዎች ተጠብቀው ይኖሩ ነበ ር። አባ ሚልኪ ቁልዝማዊ በዓት አጽንቶ በገዳም ተወስኖ በገድል በትሩፋት እግዚአ ብሔርንና ሰውን ሲያስደስት በማየቱ ሰይጣን ከነወገኖቹ የባለጋራነት ቅንዓት ቀና ሰይጣን ለተንኮል የማያርፍ ነውና በሮሙ ንጉሥ ሴት ልጅ ላይ አድሮ አሳበዳት። በላይዋም ላይ ሲለ ፈልፍ ከሚልኪ ቁልዝማዊ ጸሎት በቀር እኔን የሚያስወጣኝ የለም ልጅቷንም አለቃትም እያለ ይቀባጥር ይወሻክት ጀመር።

በዚህን ጊዜ ንጉሡ ከወታደሮቹ መካከል ፬፻ (አራት መቶ) ጭፍሮችን መርጦ አባ ሚልኪ ከሚገኝበት ገዳም ሄደው እንዲያመጡት አዘዛቸው። ምናልባት ይዘውት ሳይመጡ ቢቀሩ አንገት አንገታቸውን በሰይፍ እንደሚስቆርጣቸው በማስጠንቀቅ ላካቸው። አባ ሚልኪ ያለበት ገዳም ከሮም የዓመት ጎዳና ያህል የሚርቅ ነው። ሰዎችን እያጠያየቁ እነዚያ ጭፍሮች አባ ሚልኪ ካለበት በዓት ደረሱ። ተገቢውን ለመንፈሳዊ አባት የሚቀርበውን የአክብሮት ስግደት ካቀረቡ በኋላ የተላኩበትን ጉዳይ ነገሩት ቅዱሱም ጥያቄያቸውን ከሰማ በኋላ "እኔ እጅግ ሸምግያለሁ ሮምያ ሩቅ ናት መሄድ አይቻለኝም" አላቸው። ጭፍ ሮቹም መልሰው ከእኛ ጋር የማትሄድ ከሆነ ንጉሥ የሞት መርዶ ነግሮናል በሰይፍ አስ መትሮ አንገት አንገታችንን አስመትቶ ይፈጀናል አሉት። ቅዱሱ መነኩሴም ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ በጣም አዘነ።

ከዚህ ቀጥሎ "ልጆቼ እናንተ መንገዳችሁን ሂዱ ከዚያ እንደደረሳችሁ እኔና እናንተ በሮሚያ ኬላ (ደጅ) እንገናኛለን" አላቸው። ቃሉን ሰምተው ሄዱ አንድ ዓመት ከተጓዙ በኋላ ሮሚያ ደጅ መድረሳቸውን አባ ሚልኪ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ወደ እግዚአብሔር



www.ethiopisnorthodox.org

ጸሎት አቀረበ ጸሎቱን የሰማ አምላክ መንፈስ ቅዱስ አንስቶ በቅጽበት እንደ ዓይን ጥቅሻ ከሮሚያ ደጅ ከኬላው አደረሰው መልእክተኞቹም ጭፍሮች ቅዱሱን በሮሚያ ደጅ ባገኙት ጊዜ እጅግ ደስ አላቸው፤ ለንጉሡም መጥቷል ተቀበለው አሉት ንጉሡም በጣም ደስ ብሎት በክብር ወጥቶ ተቀበለው ከቤተ መንግሥቱ አዳራሽ አስገብቶ በከበረ ወንበር ላይ አስቀመጠው ስለ ልጁ ሕመም ሁኔታ ነገረው ቅዱሱም አምጧት ብሎ አዘዘ ባመጧት ጊዜ ጋኔኑ ከመሬት ላይ ጣላት አረፋ አስደፈቃት ፈጽሞ እንደ ሬሳ በድን አደረጋት ይህንንም ያዩ ሰዎች ሁሉ ሞተች ብለው እስኪጠራጠሩ ድረስ ትንፋሿን አሳጣት ያን ጊዜ አባ ሚልኪ በሥርዓተ ጸሎት ተነስቶ ለብዙ ሰዓቶች ረጅም ጊዜ ጸለየ ከዚህ በኋላ የተጸለየበትን ውኃ (ማየ ጸሎት) ወይም በተለመ ደው አነጋገር ፀበሉን ፊቷ ላይ ረጨ፣ ቅብዓ ቅዱስም ቀባት ሰይጣኑን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አውግዞ ለቋት እንዲወጣ አዘዘው ሰይጣኑም በምትሐቱ ፊቱ ጨለማ በሚመስል ሰው አምሳል ወጣ። ቅዱሱም ሰይጣኑን በተሰጠው የጸሎት ኃይል በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ይዞ በቤት ውስጥ ዘግቶ ከዚያ እንዳይወጣ በመስቀል ምልክት አማትቦ አሰረው አጋዘው።

ንጉሡም ይህን ቷአምር ባየ ጊዜ ከጳድቁ ጫማ ላይ ወድቆ እጅ ነሳው ለገዳሙ መተዳደሪያ ይሁንህ ብሎ ብዙ ገንዘብ አመጣለት ጳድቁ ግን አይሆንም ብሎ ሳይቀበል ቀረ ንጉሡም አባ ሚልኪን አባቴ ሆይ ከእኔ ጋራ ኑር ገዳሙንም እኔ እንጽልሃለሁ አለው ቅዱሱም መልሶ መነኮሳት ልጆቼን ትቼ ከዚህ መኖር አይቻለኝም አለው። አባ ሚልኪ ቁልዝማዊ ለጥቂት ጊዜያት በሮሚ ሕመምተኞቻቸውን እየፈ ወሰ አጋንንትን እያወጣ ኖረ ከዚህ በኋላ ወደ ገዳሙ ከንጉሡ ተሰናብቶ ለመ ሄድ ቢነሳ ከደጅ የወደቁ የድንጋይ ገንዳዎች አየ ንጉሡም ከሠራዊቱ ጋር እየሸኘው ሳለ አባ ሚልኪ ለገዳም መገልገያ የድንጋይ ገንዳዎች ያገለግሉኝ ነበር አለው። ንጉሡም የሚወስድልህ ካገኘህ ለእኔ ምንም አይጠቅመኝም ስጥ ቹሃለሁ አለው። ቅዱሱም ከፈቀድክልኝስ የሚወስድልኝን ፈጣሪዬ ያዝልኛል ብሎ ሰይጣኑን ከታሰረበት ፈትቶ ገንዳዎችን በራሱ ላይ አሸክሞ ጌታ ሆይ እንሆ አባቱን፣ ቢገጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ የሚጎዳችሁም ምንም የለም ብለህ በሰጠኸን ሥልጣን በስምህ አ ጋንንትን እንዲገዙልን ስላደረግህ አመሰግናለሁ እያለ ይነዳው ጀመር። (ሉቃ. ፲:፲፱)

ብርቱ ብርቱ የሆኑ አሥራሁለት ወንዶች መሸከም የማይችሉትን ገንዳ አሸክሞ ከገዳሙ ደረሰ ገንዳዎችን ከገዳሙ እንዲያኖር ሰይጣኑን ካዘዘ በኋላ ዳግመኛ እንዳይፈታተነው በተሰጠው አጋንንትን የማውጣት የመገዘት ጸጋ፣ መንፈስ ቅዱስ ሀብት ተቆጣጥሮ በትምእርተ መስቀል አማትቦ ከጉድጓድ ውስጥ እንዳይወጣ በግዝት አሰረው ከዚያ በኋላ ሰይጣን ሊፈታተነው አልቻለም።

አባ ሚልኪ ከመነኮሰ ፵፩ ዓመት እንደሞላው ከሰማይ ቃል መጣለት ቃሉም አባ ሚልኪ ዕድሜህ አልቋል የ፫ቀናት ብቻ ዕድሜ ቀርቶሃል ወደ ዘለዓለም ዕረፍት ወደ ዘለዓለም ደስታ ትሄዳለህ የሚል ነበር።

ይህን ከሰማ በኋላ አባ ሚልኪ መንፈሳዊ ልጆቹን መነኮሳትን ጠርቶ የተነገረውን ቃል ከገለጸላቸው በኋላ "ለእግዚአብሔር ተገዙ ከሰይጣን ማሳት ከሽንገላው እራቁ ተጠበቁ አላቸው። በ፫ኛውም ቀን ወደ እርሱ አበው መነኮሳት መጡ እነዚህም መነኮሳት ካረፉ ብዙ ዘመናት ይሆናቸዋል። አመጣጣቸው በሥጋ ሳይሆን በአካለ ነፍስ ወይም በመንፈስ ነበር። እነዚህም አበው መነኮሳት የተባሉት አባ እንጦንስ፣ አባ መቃርስ፣ አባ መቃርዮስ፣ አባ ሲኖዳ፣ አባ ብስ ይና፣ አባ ጳኩሚስ ተገልጸው እንዲህ አሉት "ወንድማችን ከእኛ ዘንድ በመን ግሥተ ሰማያት በደስታ ከእኛ ጋር ለመኖርና" አሉት ይህን እያሉት ነፍሱ ከሥጋው ተለየች። መላእክት በምስጋና እየዘመሩ አሳረጓት እንዲህ እያሉ "ዘፃመወ በዓለም የሐዩ ለዘሉፉ ትርጉሙ (በዓለም ሳለ በገድል በትሩፋት የደከመ ለዘላለም ይድናል) ማለት ነው። (መዝ. ፵፰:፱) እንዲህ እያሉ ነፍሱን ደስታ ካለባት የመን ግሥተሰማያት አረቦን (መያዣ) በኾነች በገነት አኖሯት።

አባ ሚልኪ ቁልዝማዊ በእንዲህ ዓይነት ክብር ካረፈ በኋላ ሥጋውን ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳትና ካህናት እንደ ሥርዓቱ ገንዘው በቤተክርስቲየን በተወ ሰነለት ሥፍራ ቀበሩት። በመቃብሩም ላይ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ተአምራትና መንክራት (ድንቆች) ታዩ ተደረጉ። ጸሎቱ በረከቱ በወዳጆቹ በክርስቲያን ልጆች ላይ ለዘላለም አድሮ ይኑር አሜን።

አባ ሚልኪ ቁልዝማዊ አጋንንትን የማስወጣት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ቢኖ ረውም በዚህ ስጦታው ተኩራርቶ በውዳሴ ከንቱ አልተጠለፈም። በፍቅረ ንዋይ ፍላጻም አልተነደፈም። ገድል ትሩፋት ከመሥራት ወደ ኋላ አላለም በምንም ነገር አልተመጻደቀም። በገዳማዊ ሕይወት ጸንቶ በተስፋ መንግሥተ ሰማያት ተበራቶ ስሙ በሰማያዊ መዝገብ እንዲጻፍ አደረገ። በዚህም መንፈሳዊ ገድሉ የጌታን ቃል ተረጎመ።

ቅዱስ ሉቃስ በጻፈው ወንጌል ፲:፲፯-፳ ያለውን ቃል ከዚህ ላይ ልናስታ ውስ ይገባናል። ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው ጌቶ ሆይ አጋንንትስ እንኳ በስምህ ተገዝተውልናል ቢሉት "መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ" ብሎ ጌታችን የተናገረውን ማጤን ይገባል። አባ ሚልኪ ተግባራዊ ያደረገው ይህንን ኃይለ ቃል ነበር። በምድር ሳለን አጋንንትን የማውጣት ጸጋ ተሰጥቶን ለብዙ ዘመን ኖረን በኋላ "እናንተ አመፀኞች አላውቃችሁም" (ማቴ. ፯:፳፪-፳፫) ተብለን ለዘላለም በኩነኔ ከመኖር፤ ጋኔንን የማውጣት ሀብቱ ቀርቶብን በትህትና ለእግዚአብሔር በመገዛት ፈቃዱን ፈጽመን በመንግሥተ ሰማያት ስማችን ተጽፎ ዘላለማዊ ሕይወትን መቀዳጀት እንደሚበልጥብን ልናውቅ ልናስብ ይገባናል። ጋኔን የማውጣት ሀብት የተሰጠን ብንኖርም ሰዎች ስላሞገሱን ስላከበሩን ከሌሎች የላቅን መስሎን ሰይጣን በት ዕቢት እንዳይጥለን እንጠንቀቅ። በራሳችን ብቃትና ትሩፋት ያስወጣነው እየመ ሰለን እንመጻደቅ እራሳችን ተሳስተን ሌሎችን ከማሳሳት እንጠበቅ።

ሰይጣን በጸሎት በጾም በፍጹም ሃይማ ኖት በሥላሴ ስም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በተሰጣቸው ሰዎች ለቆ ሊሄድ ይችላል፡ እግዚ አብሔር በእኛ አድሮ አጋንንትን በማውጣቱ ልንደሰት እንችላለን ደስታችን ግን ከመጠን አልፎ የመንግሥተ ሰማያት ኑሮን እንዳያዘና ጋንና ከክርስቲያናዊ ሕይወት እንዳያወጣን ሁል ጊዜ ክብር ለእግዚአብሔር በመስጠት በትህትና እንኑር። እንዲህ ከሆነ ሰይጣንን ከሌሎች ላይ ብቻ ሳይ ሆን ከእኛም ልናርቀው ድል ልናደርገው እንችላለን።

ሰይጣንን ለማስለቀቅ የራሳችንን ጡንቻ እንጠቀም ለጊዜው አጋንንት ለማታለል ተሸር ጠው ለመቅረት እንዲመቻቸው ተቃጠልን ለቀ ቅን አባ እገሌ መናኝ እገሌ ወዘተ አቃጠለኝ ድል አደረገኝ በማለት ሊወሻክቱ ይችላሉ። በዚ ያን ጊዜ እናስተውል። የእግዚአብሔርን ክብር እንግለጽ የቅዱሳንን ምልጃ የድንግልን አማላጅነት የመላእክትን ተራዳኢነት በማሳ ወቃችንና ደካሞች መሆናችንን በትህትና ለሚያ ንን ወገኖች መግለጽ አለብን ይህን ከፈጸምን ሰይጣንን ድል ለማድረግ እንችላለን። በትዕቢ ትና በት ምክህት በወዳሴ ከንቱና በፍቅረ ንዋይ ተታል ለን ስንመጻደቅ ብንኖር ግን ለእግዚአብሔር ክብር ስላልሰጠን "እናንተ ርጉማን ከእኔ ሂዱ" የሚል አስፈሪ ቃል ሰምተን ከአጋንንት ጋር በጨለማ ጉድጓድ በገሃነም ተጥለን እንኖ ራለን (ማቴ. ፳፭:፵፩ና፵፮)

ይህ የዘላለም ቅጣት እንዳይደርስ ብን በሁሉ ነገር እራሳችንን ዝቅ ዝቅ እናድርግ፤ እግዚአብሔር በጸጋው ከፍ ከፍ ያደርገናል። (ሉቃ. ፲፬:፲፩) ወዳጆች ሆይ በሕይወታችን ምግባር ትሩፋት ቢኖረንም አጋንንትንም የማስወጣት ጸጋ ቢሰጠንም ሰጪውን በማመስገን በፊቱ በተሰበረ መንፈስ እንመላለስ። ከዚህ ላይ አንድ ልናስበው ወይም ልናምነው የሚገ ባን ቃል አለ። ይኸውም "የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው። የተሰ በረውንና የተዋረ ደውን ልብ እግዚአ ብሔር አይንቅም። ትሑት ልብ የሥጋ ሕይወት ነው። ቅንዓት ግን አጥን ትን ያነቅዛል። እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል እግዚአ ብሔር ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት መንፈሱም ወደ ተሰበረ በቃሌም ወደ ሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከ ታለሁ" የሚለ ውን ምእዳን ወይም ምክር ተግ ሳጽ ልብ እናድርግ።(መዝ. ፶:፲፯፤ምሳ. ፲፬:፴፤ ኢሳ. ፷፯:፱) የቅዱስ ሚልኪ ቁልዝማዊ አም ላክ ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግል እናቱ ጸሎት ማስተ ዋልን ሰጥቶ ከሰይጣን ሽንገላ ይጠብቀን ያድነን አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።



www.ethiopisnorthodox.org

ይህ ዓምድ፣ ምዕመናን የተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት ወይም ቀኖናዋን፤ በተከታታይ የሚማሩበት፤ እንዲሁም የመናፍቃንን ማንነትና የሚያስተምሩትን ትምህርት ስህተት የሚረዱበት ነው።

# መንፈስ ቅዱስና ጸጋው

## ጋኔን የማውጣት ሀብት

ከሲራክ ገብረክርስቶ

### ፳. ቅዱስ ሳዊሮስ ዘገብሉን ጋኔን ያወጣ ነበር:-

ቅዱስ ሳዊሮስ ዘገብሉን፤ እንደ ሚልኪ ቁልዝማዊ በክርታስ ላይ ጽፎ አጋንንትን ያስወጣቸው ነበር። "ሳዊሮስ ዘገብሉን የናዝራዊ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ! አንተ ርኩስ መንፈስ ውጣ ብሉሃል " በማለት በክርስታስ ጽፎ ይልካል። ክታብ፣ ጦማር ጽፎ ወደ ሩቅ አገር ለወዳጆቹና ለደቀመዛሙርት እንደመላክ ማለት ነው። ደብዳቤው ተልኮ በጋኔን ቁራኝነት ከታመሙት ሕሙማን ዘንድ ደርሶ ሲነበብ የሳዊሮስ ዘገብሉን ጸሎቱ አነደደን፣ የሳዊሮስ ዘገብሉን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈረደብን፣ ወጣን፣ ለቀቅን እያሉ፣ እየለፈለፉ አጋንንቱ በሽተኞቹን ለቀው ይወጣሉ። ሕሙማኑም ወዲያውኑ ፈውስ ያገኛሉ። ከዚያ ወዲያ ፍጹም ጤነኞች ሆነው ይኖሩ ነበር።

ለመሆኑ ጋኔን የማውጣት ሀብት (ጸጋ) የተሰጠው ቅዱስ ሳዊሮስ ዘገብሉን አኗኗሩ ምን ይመስል ነበር? መንፈሳዊ ሕይወቱን ከሕፃንነት ዕድሜው አንስቶ እስከ ጊዜ ዕረፍቱ በምን ዓይነት ትሩፋትና ገድል ጸጋ፣ ወይም የመንፈስ ቅዱስ ሀብት ይታኝ ነበር? በስንክሳር መጽሐፍ መስከረም ፲ቀን በሚነበበው ክፍል፤ የቅዱስ ሳዊሮስ ዜና ሕይወት ተዘግቧል። በቀጥታ ሙሉ ታሪኩን እንዳለ በመውሰድ፤ የቅዱሱን መንፈሳዊ ሕይወት እንዴት እንደነበር መግለጹን መርጠናል። የምሥጢር ባለቤት በቅዱሳኑ አድሮ ድንቅ ተአምራትን የሚሠራና የሚያሠራ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር፤ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ህሊናችንን አነሳስቶ የሚስተዋልን ጥበብ ይሰጠን ዘንድ፤ የቅዱስ ሳዊሮስ ጸሎትና ረድኤት የእመቤታችንም አማላጅነት አይለየን አሜን።

መስከረም ፲ቀን የገብላው ኤጲስ ቆጶስ የተቀደሰው አባት አባ ሳዊርያኖስ ያረፈበት ዕለት ነው።

የዚህ ቅዱስ አባቱ አብላርያኖስ ይባላል። በውጭ አገር የአቴናን ጥበብ ተማረ። ወ
ቂሳርያም ሄዶ ጥበባቸውን አጠና፣ ትምህርታቸውን ተማረ። ወደ ሮሜ ተመልሶ የቤተ
ርስቲያንን ትምህርት ተማረ። በጥቂት ዓመታት ውስጥ የብሉያትንና የሐዲሳትን ንባብ
ትርጓሜ አጠና። ከዚህ በኋላ ወላጆቹ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ዐረፉ፣ ቁጥር ስፍ
የሌላቸው ማለትም ብዙ ንብረት ትተውለት ሄዱ። እርሱም በቅዱስ ወንጌል እንደተጻ
ገንዘቡን ሁሉ ለክርስቶስ ለመስጠትና በዚያ ፈንታም መቶ እጥፍ ዋጋ ለማግኘት አሰበ
ወደደ። (ማቴ. ፲፱:፳፱) ከዚህ በኋላ የእንግዶች ማረፊያ (ማስተናገጃ መቀበያ) ቤት ሠራ
የተሠራውም ቤት ስደተኞችን፣ መንገደኞችን፣ ጦም አዳሪዎችንና ችግረኞችን የሚቀ
ልበት፣ የሚያስተናግድበት ሕንፃ ነበር። በግቢው ውስጥም ልዩ ልዩ የሚበሉ ፍሬ የ
ሰጡ አትክልት እንዲተከሉ አደረገ፤ ጠባቆችም ቀጥሮ ፍሬዎችን ለቅመው በእንግድነ
በሕንፃው ውስጥ ለሚያርፉት ሁሉ እንዲያድሉ መመሪያ ሰጣቸው። ሥፍራዎቹም ቅዱ
ሳዊሮስ ለድሆችና ለጦም አዳሪዎች ብሉ የከለላቸው፣ የሠራቸው ናቸው በማለት ለብ
ዘመናት በስሙ ሲጠሩ ኖረዋል።

የቅዱስ ሳዊሮስ የአባቱ ወንድም የነበረ አጎቱ፤ የዚያች አገር ገዢ ነበር። ሳዊሮ
ገንዘቡን ሁሉ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ ማዋሉን አልወደደለትም ነበር። በሮሜ ነግ
ለነበረው ለንጉሥ አኖሬዮስ አመልክቶ ሳዊሮስን እንዲህ ሲል ወነጀለው። "ንጉሥ ሆ
ሳዊሮስ ገንዘቡን ሁሉ ለክርስቶስ እሰጣለሁ እያለ በትኖ ጨረሰው። በወንጌል እንደተነ
ረው መቶ እጥፍ አድርጎ ክርስቶስ ይመልስልኛል እያለ ገንዘቡን ሁሉ ሰላባከነ እን
ማገኛ ስጠው" ብሉ ከሰሰው። አኖሬዎስ የተባለው ንጉሥ ግን ክርስቲያን እሱም የተ
ሕዶ አማኝ ስለነበር የቅዱሱ ገድል ደስ አሰኘው። ሥራው ሁሉ በንጉሥ ፊት ያማረ የተ
ወደደ ሆነ። በበጎ ሥራው ደስ ከመሰኘቱም በላይ ሳዊሮስን አፈቀረው፤ ከዚህም የተነ
ቅዱስ ሳዊሮስን አስጠርቶ ከቤተመንግሥቱ እንዳይለይበት በፍቅርና በትህትና አዘዘው
ቅዱስ ሳዊሮስም የንጉሡን የቀና ሃይማኖት ተመልክቶ እሺ ብሉ ታዘዘለት። ንጉሡ
ዘወትር ወደ ቤተክርስቲያን ለማስቀደስና ለጸሎት ሲሄድ ሳዊሮስ እንዳይለየው ያደር
ነበር። ምንም እንኳ በሮሜ የታወቀ ንጉሥ ቢሆንም፤ አኖሬዎስ በምሥጢር ፍጹ
መናኝ፣ ዓለምን የናቀ እራሱን በወንጌል ሃይማኖት የጠበቀ ነበር። ወደ ቤተክርስቲያ
ገብቶ፤ ሌሊቱን ሁሉ በትጋት ሲጸይል ያድራል። ይህ ጻድቅ ንጉሥ ከውዳሴ ከንቱ ር
ሥርዓተ ምንኩስናንም በስውር ይፈጽም ነበር። ከልብሰ መንግሥቱ ስር በርኖስ (ማቅ
ይለብሳል። በላይ ግን ክብር ያለው ልብሰ መንግሥት ይደርባል። እንዲህ በማድረግ
በምሥጢር የምንኩስናን ግብር ፈጻሚ ነበር። ስለዚህ ነው መንፈሳዊነት ስላለው መናኝ
ሳዊሮስም በፍቅር እንዳይለየው ያደረገው።

የዓለም ፍቅር የነገሰበት ሥጋዊና ዓለማዊ መሪ ቢሆን ኖሮ፤ ቅዱሱን ስንኳን ሊያ
ቀርበው እነ ዳኪዮስ፣ ኡልያኖስ እንዳደረጉት በሕይወተ ሥጋው ኑሮ በነፃነት ፈጣሪ
ውን እንዲያመልክ ባልፈቀደለት ነበር። በዚያን ዘመን ጻድቁ ንጉሥ አኖሬዎስ በነበረበት
ወቅት በሮሜ ሊቀ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ ዮናክንዲኖስ ነበር። ለወደፊት ሳዊሮስ ኤጲስ
ቆጶስ እንደሚሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሥጢር ተገልጾለት በዚህ ምክንያት እጅግ
አድርጎ ያፈቅረውና ያከብረው ነበር። ከፍቅሩም ብዛት የተነሳ፤ ሳዊሮስ ለጥቂት ጊዜ
እንኳን እንዲለየው ፈቃዱ አልነበረም። የዚህ ቅዱስ አባት የሳዊሮስ ዘገብሉን ዝናው
በቁስጥንጥንያ ነግሶ ከነበረው ከቴዎዶስዮስም ዘንድ ተሰማ፤ በሁሉም ዘንድ ተወዳጅና
የተከበረ ሆነ። ቅዱስ ሳዊሮስ በሰው ሁሉ ዘንድ መወደዱንና ክብሩም እንደበዛ ተመል
ክቶ፤ ውዳሴ ከንቱ እንዳይሆንበትና ሰማያዊ ክብር እንዳያጣ ፈራ። ከዚህም የተነሳ በሽ
ሉክታ፣ ማንም ሳያውቅ ተሰውሮ ከዚያች ሀገር ወደ ሌላ ለመሰደድና ለመመነን አሰበ።
ይህን ሲያስብ የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጾለት "ሳዊሮስ ክፍልህ ገብላ ናትና ወደ
ገብላ ገዳም ሄደህ በዚያ ኑር" በማለት አዘዘው። በመቀጠልም "በዚያም የገዳሙ አበም
ኔት ሆነህ ትኖራለህ የብዙዎች ነፍስ አባትም ትሆናለህ" አለው።

ቅዱሱም የምንኩስና ልብስ አስኬማ ካደረገ በኋላ፤ ቴዎድሮስ የተባለውን ረድ
አስከትሎ በሌሊት መንና ወደ ገብላ አመራ።

www.ethiopisnorthodox.org

በጉዞ ላይ ሳለ እግዚአብሔር ከፊቱ የምትሄድ የብርሃን መንኮራኩር ላከለት፤ ገዳመ ገብላ እስኪደርስ ትመራው ነበር።

በዚያች ገዳም ደግ (ጻድቅ) የሆነ አበምኔት ይኖር ነበር። የቅዱስ ሳዊሮስ መምጣት በራእይ ተገልጾለት ወደ እርሱ መጥቶ ተቀበለው። መንፈሳዊ ሰላምታም ሰጠው። ስለ እርሱም ራእይ እንደተገለጠለት ነገረው፣ ፈጽሞ አደነቀ። ዜናው በየሀገሩ ሁሉ ደረሰ። ከየሀገሩ ተወጣጥተው ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች ወደ እርሱ ዘንድ ተሰበሰቡ። ንጉሥ ቲዎዶስዮስም ከእርሱ ዘንድ ያሉትን ብዙዎች ሹማምንት፤ ለቅዱስ ሳዊሮስ አድባራትን (የመናንያንን ማረፊያዎች) እንፀሉት አላቸው። እንደ ታዘዙ አደረጉ። ቅዱስ ሳዊሮስም ብዙዎችን ነፍሳት የሚያረጋጋ፣ የሚያጽናና ሆነ፤ እግዚአብሔርም በእጁ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ታምራትንና ድንቆችን አደረገ። ከተደረጉትም ድንቆችና ምልክቶች መካከል። የገብላው አገረ ገዢ ሴት ልጅ፣ ሰይጣን ሰፍሮባት እንዴት እንደዳነች የሚተረከው ይገኝበታል።

በልጅቷ ላይ ያደረው ሰይጣን ወላጅ አባቷን፤ ሳዊሮስን ከዚህ ካባረርክልኝ እወጣለሁ እለቃታለሁ እያለ ይቀባጥር ይጮኽ ጀመር። የልጅቱም አባት ሰይጣን ያለውን ነገር ሰምቶ ከቅዱስ ሳዊሮስ ዘንድ ሄዶ ርኩስ መንፈስ የፎከረውን ቶከራ ነገረው። በጸሎቱም ልጁን እንዲያድንለት ተማፀነው። ቅዱስ ሳዊሮስም በብራና ላይ ከዚህ የሚከተለውን ቃል ጽፎ ለሰውየው ሰጠው። በደብዳቤው የተጻፈው ቃልም፤ "ክብር ምስጋና ይግባውና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አንተ ርኩስ መንፈስ ከእርሷ ወጥተህ እንድትሄድ እኔ ሳዊሮስ ዘገብሉን የክርስቶስ አገልጋይ አዝሃለሁ" የሚል ነበር።

አባትየውም ደብዳቤውን ወስዶ ወደ ልጅቱ ዘንድ ሄደ። ያን ጊዜ ደብዳቤው ደርሶ ሲነበብ፤ ሰይጣን ከእርሷ ተለይቶ ለቆ ወጣ። ከዚያ ወዲያ ፍጹም ጤነኛ ሆነች። አልተመለሰባትም።

ቅዱስ ሳዊሮስ ከጋኔን ማውጣት ጎን ሌላም ተአምራት ያደርግ ነበር፤ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ታሪካዊ መግለጫዎች በመመልከት የተሰጠውን ጸጋ መገንዘብ እንችላለን።

ወደ ቅዱስ ሳዊሮስ ከሳምራውያን ወገን የሚሆኑ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ ታላቅ የሕዝብ ጉባዔ ሆነ፣ ተደረገ። ወደ ቅዱስ ሳዊርያኖስ ገዳም ገብተው ለመዝረፍና በመነኮሳቱ ላይ አደጋ ለመጣል ያሴሩና ያድሙ ጀመር። በቅዱሱ ጸሎት እግዚአብሔር ሦስት መዓልትና ሌሊት ድቅድቅ ጨለማ አመጣባቸው። በእነዚህ ዕለታት ምንም ምን ማየት ተሳናቸው፣ ሊያዩ አልቻሉም። በብዙ ልቅሶና ዕንባ ቅዱስ ሳዊርያኖስን ማለዱት ለመኑት። እርሱም ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አድርጎ ጨለማውን አራቀላቸው። እነርሱም ፈጥነው ከዚያ ሥፍራ ሄዱ። ከዚህ የምንመለከተው አንድ ምሥጢር ይኖራል። ይኸውም አጋንንት ቅዱሳንን በቀጥታ ተገልጸው ማሸነፍ ሲሳናቸው፤ በተዘዋዋሪ መንገድ ለመዋጋት መምጣታቸውን ነው። ለዚህም ምስክሩ ሰይጣን በቀጥታ አዳምንና ሔዋንን ማሳት ባይሆንለት፤ በአርዌ ምድር ማለትም በእባብ ተሰውሮ ሊዋጋቸው መጣ።

አዳምን በውዳሴ ከንቱ ለጊዜው ጠልፎ መጣል ቢሳነው፤ ወደ እናታችን ሔዋን በመሄድ፣ ያለ ደረዋጃ ደረጃ በመስጠት በውዳሴ ከንቱ አሰናክሎ ጣላት። እርሷን ድል አድርጎ እጅ ካደረጋት በኋላ፤ በእርሷ አማካይነት አባታችን አዳምን አሳተው። ሁለቱንም በተዘዋዋሪ መንገድ ድል አደረጋቸው። ጸጋቸው ተገፈፈ እርቃናቸውን ቀሩ። (ዘፍ. ፫:፩-፲)

ዛሬም የአዳምን ልጆች በተለይም ቅዱሳንንና እውነተኞች ክርስቲያኖችን ለመጥመድ ዘዴ ይፈልጋል። ሌላ ቢያቅተው በሰዎች አድሮ መምጣት አይሳነውም። በምትሃቱም የብርሃን መልአክ መስሎ ያጠምዳል። ያም ባይሆን ክፉ ሰዎችን አነሳስቶ ቅዱሳኑን ይዋጋል።(፩ቆሮ. ፲፩:፲፫-፲፭፤ ፪ጢሞ. ፬:፲፬-፲፰) ምንም እንኳን ሰይጣን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ቅዱሳንን ለማጥቃት ቢዘምትም የእግዚአብሔር ሰዎች ጻድቃን መከራውን ሁሉ በትዕግሥት ከመቀበል ጋር፤ በሃይማኖታቸው ጽናት፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ድል ያደርጉታል። ይኸውም በቅዱሳን ገድል የተረጋገጠ፣ የተመሰከረም ነው።

ክቡር ዳዊት የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው፤ እግዚአብሔርም ከሁሉ ያድናቸዋል። እግዚአብሔርም አጥንቶቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል፤ ከእነርሱም አንድ አይሰበርም። (መዝ. ፴፫:፲፩-፳) ብሎ መዘመሩና ትንቢት መናገሩ፤ የቅዱሳንን ተጋድሎና ድል አድራጊነት የሚያረጋግጥልን ነው። ወደ ጥንተ ታሪኩ እንመለስና ስለ ቅዱስ ሳዊሮስ ገድና ተአምራት እናጢን።

ዳግመኛም በዚህ ቅዱስ አባት አበምኔትነት ስር ያሉ መነኮሳት ሁሉ ሲታመሙ ይጸልይላቸዋል፤ እነርሱም ፈጥነው ይፈወሱ ይድኑም ነበር። በመንፈሳዊ ምክርም ያረጋጋቸዋል፣ ያጽናናቸዋል። እግዚአብሔርን መፍራት ያስተምራቸዋል፤ ሁሉም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም፤ በሥራቸው የእግዚአብሔርን መልአክ እስኪመስሉ ድረስ ባለ ትሩፋት እንዲሆኑ አብቅቷቸዋል። በዚያች አገር (በገብላ) ኤጲስ ቆጶስነት ተሹሞ የሚኖር ፊላታኖስ የሚባል መንፈሳዊ አባት ነበር። ከእግዚአብሔር ዘንድ ራእይ ተገለጠለት ከእርሱ ቀጥሎ በገብላ ቅዱስ ሳዊሮስ ኤጲስ ቆጶስነት እንደሚሾም ተነገረ። እርሱም ወደ ሕዝበ ክርስቲያኑ ሁሉ ልኮ፤ ቅዱስ ሳዊሮስን ውሰዱና በእግዚአብሔር የተፈቀደለት ስለሆነ፤ መርጣችሁ በእናንተ ላይ ኤጲስ ቆጶስ እንዲሆን ይሾም አለ። ያን ጊዜም የጳጳሱን ቃል ሰምተው በመታዘዝ፤ በዘመኑ የነበሩት አርጤዎስና አኖሬዎስ የተባሉ ደጋግ ነገሥታት መኳንንቱን ጭምር በገብላ ሀገር ላይ ኤጲስ ቆጶስነት እንዲሾም፤ ቅዱስ ሳዊሮስን እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ መስካሪ ሆነው መረጡት። በቤተክርስቲያን ሕግ መሠረት ተሾመ፣ ኤጲስ ቆጶስ ሆነ።

ከተሾመበት ጊዜ አንስቶ ይህ ቅዱስ አባት፤ የክርስቶስን መንጋ ሕዝበ ክርስቲያኑን ለመጠበቅ ይችል ዘንድ ታላቅ መንፈሳዊ ተጋድሎ በማድረግ ይተጋ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ልኮ የቤተክርስቲያንን ቀሳውስትና አገልጋዮች ሁሉ ካስጠራቸው በኋላ "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች፣ ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፤ ደቀመዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሱ እኔ አውቃለሁ። ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በዕንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሰጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ። አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ከሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ። ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም፤ እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ። እንዲሁ እየደከማችሁ ድውዮችን ልትረዱና እርሱ ራሱ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው እንዳለ የጌታን የኢየሱስን ቃል ልታስቡ ይገባችሁ ዘንድ በሁሉ አሳየኋችሁ።" (የሐዋ. ፳:፳፫-፴፭) ብሎ የመጨረሻ የመሰነባበቻ ምክር እንደሰጣቸው ይታወሳል።

የቅዱስ ሳዊሮስ ተጋድሎም ይኸን የቅዱስ ጳውሎሳዊ ምዕዳን ያገናዘበ ተልእኮ ነበር። ቅዱሳን አባቶች፣ እንደ ሳዊሮስ ዘገብሉን ያሉት አበው ሐዋርያዊ ግዴታቸውን እንደጧፍ ተቃጥለው በማብራት፣ ለምዕመናን አብነት በመኾን አልፈዋል። ይህንን የቅዱሳንን ዜና በመከታተል መረዳት ይቻላል። ቅዱስ ሳዊሮስ በሚኖርበት አገር የሚኖር ሰው ሰቅሰጦስ የተባለ አንድ አይሁዳዊ ነበር። እሱም ምሁረ አሪት ስለነበር የሙሴን ሕግ ጠንቅቆ በማወቁ ይመካ ነበር። ከዚህ ትምክህት የተነሳ፤ ቅዱስ ሳዊሮስን ለመከራከር ተነሳ። ቅዱስ እስጢፋኖስን ቢጽ ሐሳውያን፤ ተስፋ ያልደረሰውን ደረሰ፣ ሥጋ

www.ethiopisnorthodox.org

ያልለበሰውን ሥጋን ተዋሕዶ መሲህ (ማስያስ) መጣ እያልክ የምታስተምረው ከምን አግኝተህ ነው በማለት የክርስቲያንን ትምህርት በማብጠልጠል ቢከራከሩትፃ አእምሮ ጠባይዕ የቀናለት፣ ጥበብ መንፈሳዊ የተሰጠው ሊቀ ዲያቆናት እስጢፋኖስፃ ምላሽ አሳጥቶ ሱባዔ ትውልድፃ የቴኖክን ሱባዔ ዕለት፣ የኤርምያስንና ሱባዔ ሰንበት፣ የዳንኤልን ጠቅሶ እንዳሳፈራቸው በሐዋ. ፯:፰-፲ ተጽፎ ይገኛል። (ግዕዝና አማርኛ የአንድምታ ትርጓሜ ተመልከቱ) በዚህ አንጻር አይሁዳዊው ትምክህተኛ ስቅስጦስም ለተቃውሞ ተነሳሳ። ቅዱስ ሳዊሮስን ተከራክሮ ለመርታት አልቻለም። በጊዜው ልቦናውን እንደ ድንጋይ አጽንቶ ክርክሩን ቀጠለ እንጂ። ከቅዱስ ሳዊሮስ የሚነገረውን ኃይለ ቃል ሊረዳ አልቻለም ነበር።

ይህ በዚህ እንዳለ እግዚአብሔር ለቅዱስ ሳዊሮስ በራእይ ተገልጾ "ወዳጄ ሳዊሮስ ለጊዜው አይሁዳዊው ባያምንም አትዘንፃ በክርስቶስ አምነው ካሉ ቅዱሳን፣ ብሩካን ምዕመናን ክርስቲያኖች እንደ አንዳቸው የሚሆንበት ጊዜ ሩቅ አይደለም ያምናል" አለው።

ከዕለታት በአንድ ቀን ተከራካሪው አይሁዳዊ ወደ ቤቱ ይገባል ተኝቶ ሳለ፣ ሌሊት በሕልሙ አስጨናቂ የሆነ የኩነኔ ሥፍራዎችን አየ። የእግዚአብሔር መልአክም በሕልሙ "ስቅስጦስ ሆይ እነሆ እይ፣ ተመልከት በክርስቶስ ያላመኑ ከሀዲዎች አይሁድ ዘመዶችህፃ የሚኖሩት በዚህ ዘላለማዊ ስቃይ ውስጥ ነው" አለው። ይህንን ምሥጢር ግን በማግስቱ ወደ ቅዱስ ሳዊሮስ ዘንድ ሄዶ፣ ከእግሩ በታች የጸጋ ሰጊድ በማቅረብ ወድቆ እንዲህ ሲል ተማፀነው። "ቅዱስ አባት ሆይ! የክርስቶስ አገልጋይ ሳዊርያኖስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ እንደሆነ፣ በእውነትም ከድንግል ማርያም ያለ አባት በድንግልና ተጸንሶ እንደተወለደ አምናለሁፃ ክርስቲያን እንድሆን እሻለሁና የክርስትና ጥምቀት እባክህ አጥምቀኝ" በማለት ለመነው።

ቅዱስ ሳዊሮስም በፍጹም ማመኑን አይቶፃ እሱንና ቤተሰቡን፣ በእርሱ ምክንያት የተመለሱትን የአገሩ ሰዎች ሁሉ የክርስትና ጥምቀት አጠመቃቸው። የተቀሩት አይሁድም መምህራቸው ክርስቲያን እንደሆነ በሰሙ ጊዜ በክርስቶስ ስም አምነው ተጠመቁፃ ክርስቲያን ሆኑ። ከሕፃንነታቸው ጊዜ አንስተው ክርስቶስን በማመን እንደኖሩት ክርስቲያኖች መሰሉ። በክርስትና ሃይማኖት ማለትም በተዋሕዶ ሃይማኖት ጸንተው ኖ

ይህም ተግባር ሌላው ለቅዱስ ሳዊሮስ የተሰጠው ጸጋ ነበር። የሚያስክድ፣ የሚያጠራ ሰይጣን ድል አድርጎ ያጠፋውን ሰውፃ ለክርስትና ማብቃትና እንዲድን ማድረግ ለቅዱ አባት የተሰጠው ተጋድሎና ጸጋ መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

ሰይጣን እንደ እባብ ያለ ወይም ሀሳዊ መሲህን የሚመስል ማደሪያ ባገኘ ጊዜ የክርስቲያንን ወገን ሁሉ ለማስካድ የማይፈነቅለው የተንኮል ድንጋይ፣ የማይቆፍረ የስድብ (የድፍረት) ጉድጓድ አይኖርም። ከሀዲዎችንና መናፍቃንን መሣሪያ በማድረ ቤተክርስቲያንን ይዋጋል። እግዚአብሔርን ይሳደባል ስሙንና የስሙን ማደሪያ ታቦቱን መስቀሉን ይነቅፋል፣ ስመ ሥላሴን ይሳደባል የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆኑ ምዕመናን ይቃወማል። የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ታቦት የሆኑ ማደሪያዎቹን ቅዱሳን ነቢያትን ሐዋርያትን በጠቅላላው ጻድቃን ሰማዕታትን ይሳደባል ይነቅፋል። ከሁሉ በላይም የአምላ ማደሪያ እናት የምትሆንፃ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት እመቤታችን ድንግል ማርያም ይሳደባል። ሰድቦ እንዲሳደቡ ሀሊናቸው ለማነሳሳት የክርስቲያኖችን ልቦና ይፈትናል በሰማይ የሚኖሩ ሰማያውያን መላእክትን ይነቅፋል ይሳደባል። ወዘተ እንግዲህ ይህ ተሳዳቢ ጋኔን ድል አድርገው፣ ከሌሎችም ላይ የክህደቱን መንፈስ የአውሬውን (የሀሳ መሲህን) መልእክተኞች አጋንንትንፃ በተሰጣቸው የሃይማኖት ጸጋ የሚያርቁ እንደ ቅዱስ ሳዊሮስ ያሉ ቅዱሳን በእውነት ብፁዐን ንዑዳን ክቡራን መባል ይገባቸዋል። (ራ ፲፫:፩-፲፣ ራእ. ፪:፲፪-፲፫)

ሌላው ቅዱስ ሳዊሮስ ያደረገው ተአምራት ለዝክረ ነገርና ለምስክርነ የሚከተለውን ታሪክ እናቀርባለን። በማስተዋል ለመመልከት ያብቃን አሜን።

ቅዱስ ሳዊሮስ ኒሞንጦስ ተብለው የሚጠሩ አስማተኞችን (ሰራየኞችን) መጠ ግብራቸውን ትተው ወደ ክርስቲያን ሃይማኖት እንዲገቡ ለመናቸው። እነርሱ ግ በሰራያቸው ስለታበዩ ምክሩን አልሰሙትም። እነዚህ አስማተኞች ተንኮላቸውን ይቀጥለ ጀመር። ሰው ወደ እነሱ ሲሄድፃ የበተነበት ማን እንደሆነ ሳያይ በመተት ሥራ አባራ ትቢያ እንዲበተንበት ያደርጋሉፃ ይህ ሁሉ የመተታቸው ውጤት ነበር። ቅዱስ ሳዊሮ እነዚህን አስማተኞች ወደ ተቀደሰችው የክርስትና ሃይማኖት እንዲያስገባቸው፣ ከክን ሥራቸው እንዲመልሳቸው ዕንባውን እያፈሰሰ በኀዘን፣ በጸሎት ጌታችን ኢየሱ ክርስቶስን ለመነው ማለደው። ጌታችንም ጸሎቱን ተቀብሎ በአስማተኞቹ ላይ ብቻ የመቅሰፍት ደዌ አዘዘባቸው። ክርስቲያኖችን ግን አልነካቸውም በሽታው የመጣው በአስማተኞች ላይ ብቻ ነበር። ከዚህ ቀደም በሙሴ ጸሎት በግብፅ አገር በፈርኦንና በግብፃውያን በአስማተኞችም ላይ ብቻ ቸነፈር እንደመጣባቸው አይነት ያለ ደዌ ነበር። ዕብራውያንን ለይቶ ሳይነካ ቸነፈሩ ያጠቃው ግብፃውያንን ብቻ ነበር። እንደዚያው አይነት የሆነ ተመሳሳይ መቅሰፍት በአስማተኞች ላይ ተደረገ። (ዘፀ. ፱:፰-፲፪)

ይህን ተአምራት ባዩ ጊዜፃ አስማተኞቹ የቅዱስ ሳዊሮስን አባታዊ ምክርና ትእዛዝ ባለመቀበላቸው የወረደባቸው መቅሰፍት መሆኑን ተገንዝበውፃ ንስሐ በመግባትና በማመንፃ በቅዱስ ሳዊሮስ እጅ ተጠምቀው ክርስቲያን ለመሆን በቁ።

ቅዱስ ሳዊሮስ የተሾመባት ያቺ ሀገር የተባረከች ሆነች። ምዕመናንም ፍቅርና ሰላምን አግኝተውፃ አንድ የክርስቶስ መንጋ ለመሆን በቁ። በቅዱስ ሳዊሮስ ገድልና ትሩፋት የሃይማኖት ጽናት የተበሳጨው ሰይጣንፃ በምትሀት ልብሱ በተቀደደበት ሽማግሌ ሰው ተመስሎ ተገልጾ ሲጮኽ ይሰማ ነበር። "ከአጥናፍ እስከ አጥናፈ ምድር በሁሉ ተጨነቅኹ፣ መከራዬን አየሁ ከግብፅ አገር ብሄድ ከዚያ በጸሎታቸው የሚያባርሩን መነኮሳት ሞልተውበታል። ወደ ሮሜ እንዳልሄድ ከዚያም ሊቀ ጳጳሱ ዮናክንዲኖስ አለ። ወደቁስጥንጥንያ እንዳልሸሽ ዮሐስን አፈወርቅ የተባለ ቅዱስ ሰው አለ። የኔ ድርሻ የቀረችኝ አገር ገብላ ናት ብዬ ተሰድጄ መጥቼ ነበርፃ አገሬን ሳዊሮስ ነጠቀኝ፣ ማርኮ ወሰደብኝ" እያለ ይጮኽ ነበር። የቅዱስ ሳዊሮስ ተአምራቱና አገልግሎቱ በዚህ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። በኤልሳ ጸሎት እስራኤል ተጠብቃ እንደኖረች በዘመኑ የክርስቲያን ነገሥታት ግዛታቸው ሕዝቦቻቸው ተጠብቀው ይኖሩ ነበር። (ነገ.ካል. ፮:፰-፳፫)

የፔርሽያ (የፋርስ) ሰዎች ጦርነት ለመግጠም ወደ አኖሬዎስና አርቃዴዎስ ደብዳቤ ላኩ። "ኑ ግጠሙን እንዋጋ" እያሉ ደጋግ የሚኾኑ እኒህ ነገሥታት ግን የፋርስ ሰዎች የላኩትን የማስፈራሪያ ደብዳቤ ወደ ቅዱስ ሳዊሮስ ላኩ። ደብዳቤው እንደደረሰው ይህ ቅዱስ አባት መልእክት ላከላቸው።

የላከላቸውም"ለክርስቶስ ያደርን የምናምን ክርስቲያኖች፣ መንግሥታችንምፃ የክርስቶስ የሆነ ሰልፍን፣ ጦርንና የጦር መሣሪያን አንሻውም አንፈቅደውም" በማለት ቀደም ያሉም ደጋግ ነገሥታት ያለ ሥጋዊ ጦር መሣሪያ በሃይማኖትና በተአምራት በጠላቶቻቸው ላይ የተቀዳጁትን ድል በማስታወስ የሚያሳስብ፣ የሚያስገነዝብ መልዕክት ነበር እውነትም እንዳለው ተደረገ። የአቢይ ጾም ከመድረሱ በፊት የፋርስ ጦረኞች ሊዋጉ መጡ ነገር ግን በተአምራት ድል ተነስተው አፍረው ተመለሱ። ይህም የድል

ወደ ገጽ ፴ ዞሯል



www.ethiopisnorthodox.org

፫. በማስተማር ሙያ ላይ ያሉ የቤተክርስቲያን ሰዎች በማ ሰባሰብ መመካከር ቢቻል፤

፬. ምዕመናኑ ይህንን ጉዳይ በየቦታው እንዲወያዩበት ሁሉም የቻለውን ጥረት ቢያደርግ።

፭. ይህንን እና ሌሎችንም አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ በሥራ ዓለም ካሉ የቤተክርስቲያን ልጆች ፈቃደኛ ከሆኑት ከ፭ -፲ በመቶ ያህል ከገንዘባቸው ተቆርጦ ለቤተክርስቲያን ገቢ የሚደረ ግበትን መንገድ ቤተክርስቲያን በማስተዳደር ላይ ያሉ አባቶች ከምዕመናን ጋር ቢመክሩበት።

በመጨረሻ ሁላችንም በአንድነት በመሆን የልጆቻችንን ትምህርት ቤት በማነጽ ህሊናችን ያርፍ ዘንድ እግዚአብሔር አምላክ ይርዳን።

ክፍለ ማርያም
ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት
አዲስ አበባ

## የጋራ የውውይት መድረክ ቢመቻች

በመለከት መጽሔት እንወያይበት አምድ ልጆቻችንን የት እናስተምር በሚል የቀረበውን ሳነብ ለዚህ ችግር መጋለጣችን በጣም አሳዘነኝ። ቤተክርስቲያን ዛሬ ብዙ ነገር አላት። የሃይማኖት አባቶች አሏት ዘመናዊ ትምህርት የተማሩም ልጆች አሏት የእኛ ተሰባስበን መወያየት አለመቻላችን ይህን ችግር አባብሶታል። ምናልባት የሚቻል ከሆነ ኃላፊነት ከሚሰማቸው አካላት ጋር በመነጋገር የቤተክርስቲያን አባቶች መምህራን በዘመናዊ ትምህርት የተማሩ የቤተክርስቲያን ልጆች ወላጆች እንዲሁም ልጆች በተገኙበት የጋራ የውይይት መድረክ ቢዘጋጅና ሁላችንም እግዚአብሔርን ለመለመን ብንነሳሳ መልካም ይመስለኛል። ተቀራርበን አለመነጋገራችን ምን ማድረግ እንደሚገባን ሁላችንንም ግራ አጋብቶናል። እንደዚህ ዓይነት ችግሮችን ለመፍታት የሚያመች መንገድ የተቀመጠ የለምና በተለይ ዛሬ ቤተክርስቲያን ዘመናዊ ትምህርት በተማሩ ልጆቿ አነሳሽነት ይህንን ችግር መፍታት ይገባታል።

ዛሬ በየቦታው ሁሉም ሰው ችግር እንዳለበት ስለሚያወራ እንዲህ ዓይነቱን 'መፍትሔ ለመፈለግ በተቻለ መጠን በብሩህ ተስፋ ብንወያይ መፍትሔው ይገኛል እላለሁ።

ተ.ከ
ከአ/አ

## ይህ መሠረታዊ ችግር መሆኑን ሁሉም ሰው ይረዳዋል ወይ?

የችግሩ መሠረታዊነት እያንዳንዱን እያሳሰበ ከመጣ አመ ታትን አስቆጥሯል የአንዱን አገር ዕድገትና ብልጽግና የሚወስነው በሕብረተሰቡ የተስተካከለ አቋምና የጠራ አመለካከት ቢሆን የዚህም ሕብረተሰብ ዋናው መሠረቱ ቤተሰብ ነው። አብዛኛው ቤተሰብ በአ ሁኑ ጊዜ ጥሩ መልክ የላቸውም። ሥነ ምግባር በጎደላቸው ወጣቶች ሳቢያ ጤናማ ሕይወት እንዳይኖር ተደርጎ ባለበት ሁኔታ ወደፊት የሀገራችንን ዕድገት ማሰብና ታሪካዊነቷን ጠብቃ እንድትኖር ያደረገችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የወደፊት ተረካቢዎች የሚያጋጥማቸውን ችግር ፈተና ሳስበው በጣም ይጨንቀኛል።

ባለፈው ባቀረባችሁት ጽሑፍ ላይ ችግሮቻችንን በምን መልኩ መፍታት እንዳለብን ማሰብ ለነገ የሚባል አይደለም። እኔን ግን እያሳሰበኝ ያለው ይህ ጉዳይ ነው። ነገር ግን አንዳንዶችን ስንመለከት የዚህ ዓይነት ችግርን እንደ ቀላላ ሲቆጥሩት እናያለን። ዛሬ ቤተክርስቲያን ይህንን መፈጸም እንዳትችል ያደረጋትም ከምዕመናን የሚጠበቀው አሥራ በኩራት መሰብሰብ ባለመቻሉ ነው። አምላካዊው የመጽሐ ቅዱስ ቃል የሚያዘውን ከአሥር አንድ የቤተክርስቲያን ድር በተገቢው መልኩ ሰጭና ተቀባይ የሚስተናገዱበት ሁኔ ማመቻቸት ተግባራዊነት የሚያሻው የጊዜው ወቅታዊ ጥያ ነው።

አ/አ

## ጋኔን የማውጣት ሀብት

ከገጽ ፮ የዞ

ተአምራት በኢሳይያስ ጸሎት ለንጉሥ ሕዝቅያስ የተደረገለት ይመስላል። (ኢሳ. ፴፯:፩-፴፰)

ንግሥት አውዶክስያ በቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳሳ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ አለ አግባብ ስደ ብታመጣበትና ግብረ አበር ለማድረግ፤ ቅዱስ ሳዊሮስ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ ግዝትህን አስተላልፍ ብትለ ተቃወማት እንጂ አልተቀበላትም። እንዲያውም ንግሥቲ ዘንድ ቀርቦ "በዮሐንስ አፈወርቅ ስደት መፍረድሽ ትክክ አይደለም። ጥፋት የለበትም" ብሎ ገሰጻት እንጂ ግብረ አበ አልሆነም። ተግሳጹንና ምክሩን ንግሥቲቱ ባትቀበለውም፤ ወደ ሀገረ ስብከቱ ከተመለሰ በኋላ ብዙ ድርሳናትና ተግሳጻ ጽፏል። ሃይማኖታቸው በቀና አብያተ ክርስቲያት እስካሁ ድረስ ድርሳኖቹና ተግሳጾቹ ይነበባሉ፤ ይተረጎማሉ። ምንም ጻድቅ ቢሆኑ ማርጀትና መሞት የማይቀር ርስት በመሆኑ ቅዱ ሳዊሮስም አጋንንትን በማውጣት ሀብቱ ምዕመናንን ሲረ ቆይቶ አረጀ። ዕድሜውም ፻ዓመት ሆነ። ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ "በተኩላና በእባብ ላይ ትጫማለህ፤ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ በእኔ ተማምኗልና አስጥለዋለሁ፤ ስሜንም አውቋልና እጋርደዋለሁ። ይጠራኛል እመልስለት ማለሁ። በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ፤ አድነዋለሁ፤ አከብረውማለሁ፤ ረጅምን ዕድሜ አጠግበዋለሁ፤ ማዳኔንም አሳየዋለሁ።" ያለው ቃለ ትንቢት የተፈጸመለት ታላቅ አባት ነበር። (መዝ. ፺:፲፫-፲፮)

ቅዱስ ሳዊሮስ መስከረም ፮ቀን ከቀኑ ፲ሰዓት ላይ ሲሆን የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጸለት "ከዚህ ዓለም ድካም ዕረፍት ወደምታገኝበት ዓለም ትሄዳለህ፤ ዕረፍትህም ዛሬ ነው ወደ ሚሻለው ዓለም ለመሄድ ተዘጋጅ" የሚል ቃል ነገረው። ይህን ቃል ከመልአኩ ከተረዳ በኋላ፤ ቅዱስ ሳዊሮስ ሕዝበ ክርስቲያኑን አስጠርቶ የእግዚአብሔርን ሕግና ፈቃድ ጠብቀው በቃናች ሃይማኖት ጸንተው እንዲኖሩ መከራቸው አዘዛቸው። ከዚህ በኋላ ወዲያው ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ በክብር አረፈ። ነፍሱንም በፈጣሪው እጅ አሳልፎ ሰጠ። ዕረፍቱም ዮሐንስ አፈወርቅ ባረፈ በሁለት ዓመት፤ ኢፒፋንዮስ የተባለው የቆጵሮሱ ኤጲስ ቆጶስ ባረፈ በዓመቱ ሆነ። ቅዱስ ሳዊሮስ ባረፈ ጊዜ ካህናትና ምዕመናን እንደሚገባው ንጹሕ ሥጋውን ገንዘው በዝማሬ በምስጋና በመቃብር ውስጥ አኖሩት፣ ቀበሩት።

ጸሎቱ በረከቱ ከወዳጆቹ ከምዕመናን ጋር ለዘላለም ይኑር አሜን።

www.ethiopisnorthodox.org